ዳግ ሂዋርድ ሚልሰ

# የማይታዩትን ጠላቶችህን እወቅ

... አሸንፋቸውም!

# የማይታዩትን ጠላቶችህን እወቅ…

## አሸንፋቸውም!

ዳግ ሂዋርድ ሚልስ

ትርጉም፡- ዳንኤል ነጋሳ

አርትዖት፡- ያሬድ ስለሺ

ካልተገለፀ በቀር፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

**የማይታየውን የአንተን ጠላቶችህን እወቅ...አሸንፋቸውም!**


ስለ ዳግ ሂዋርድ ሚልስ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ
በዚህ ኢሜይል ይጻፉ፡- evangelist@daghewardmills.org
ዌብሳይታቸውን ይጎብኙ፣ www.daghewardmills.org.
በፌስቡክ፣ Facebook: Dag Heward-Mills
በትዊተር፣ Twitter: @EvangelistDag



Copyright © 2011 Dag Heward-Mills



EBOOK ISBN: 978-1-64135-793-7

ላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል
ስልክ + 251912063821
መ.ሳ ቁጥር 15134
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ



ይህንን መጽሐፍ በሙሉም ሆነ በከፊል ያላሳታሚው ፈቃድ ማባዛት የተከለከለ ነው።

## ማውጫ


1. የማይታዩት የጠላቶችህ ዝርዝር ........................1
2. 10 የአጋንንቶች ተልዕኮ በአንተ ላይ ...................7
3. የማይታዩ ጠላቶች ልዩ ዒላማዎች ...................16
4. አምስቱ የእርሰኩሳን መናፍስት የተልዕኮ ግዛቶች21
5. የአጋንንት መኖር ምልክቶች ...........................26
6. አጋንንታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዴት ይመረመራል ..................................................38
7. አጋንንቶች እና ሀሳብ መስጠታቸው..................42
8. አጋንንታዊ ሥራዎች እና ሴራዎች...................48
9. አጋንንታዊ ማባበል ........................................56
10. አጋንንታዊ መግቢያ፤ አጋንንቶች ወደ አንተ መግባት ለምን ይፈልጋሉ ................................64
11. አጋንንታዊ ጭቆና፤ ምንድነው? .......................72
12. አጋንንታዊ ጭቆና፤ እንዴት ነጻ መሆን ትችላለህ ..................................................................77
13. በአጋንንት መያዝ.............................................82
14. አጋንንታዊ ጉስሚያ..........................................87
15. አጋንንታዊ ውህድ............................................91
16. የአጋንንት እና እንስሳ ዲቃላ ምሳሌዎች..........105
17. ልዕለ ሰዎች(የሰው ድብልቆች) እንዴት ተፈጠሩ .................................................................112
18. የግዙፎች(ኔፊሊም) ምሳሌዎች ........................138
19. የታዋቂ ሰዎች ምሳሌዎች(ሴሞች) ..................145

20. የአምባገነኖች እና ጉልበታሞች ምሳሌዎች (ጊቦራዊያን) ....................................................150
21. በከፊል ሰዎች ውስጥ ያለውን የዲያብሎስን ስራ መከልከል እንዴት ይቻላል...............................164
22. እንስሳ መሳይ አጋንንቶችን እንዴት ድል እንደምትነሳ....................................................170
23. አጋንንቶች ወዳንተ አካል ውስጥ እንዳይገቡ እንዴት ልታስቆማቸው ትችላለህ.....................183
24. በእግዚአብሔር የእቃ ጦር ደህንነትህን እንዴት ታጣናክራለህ? ...............................................196
25. በእግዚአብሔር የጦር እቃ ጥቃትን እንዴት ማገድ ትችላለህ.........................................................202
26. የዲያብሎስ መኖሪያ ከመሆን እንዴት እንጠበቅ ..............................................................223

# ምዕራፍ 1

# የማይታዩት የጠላቶችህ ዝርዝር

መጽሐፍ ቅዱስ ስለማይታዩት ጠላቶች ብዙ ዝርዝር ይሰጠናል።መጽሐፍ ቅዱስን ማመን እና እነዚህን ጠላቶቻችንን በእግራችን ሥር እስከምንረግጣቸው እያንዳንዳቸውን መዋጋት የእኛ ኃላፊነት ነው። የመንፈሳዊውን ዓለም እውነታን ማቃለል የለብህም። መንፈሳዊው ዓለም እውነተኛ ዓለም ነው። ይህ የሚታየው ዓለም ግን ጊዜያዊው ነው።በምድራዊ ኑሮህ የሚያጋጥሙህ እነዚህ የማይታዩ የጠላቶችህ ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ኢዩሱስ ክርስቶስ ብዙም ሳይቆይ ነበር ከዲያብሎስ ጋር የተገናኘው። በዚህ ምድር ላይ በነበረው አገልግሎቱ እና ሕይወቱ ውስጥ ከዲያብሎስ ጋር ሲገናኝ ነበር።

1. አለቆች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው።

**መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።**

**ኤፌሶን** 6፥12

2. ሥልጣናት የማይታዩ ጠላቶች ናቸው።

**መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።**

**ኤፌሶን** 6፥12

3. የጨለማው ዓለም ገዢዎች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው።

መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

ኤፌሶን 6፥12

4. በሰማያዊ ስፍራ ያሉ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት የማይታዩ ጠላቶች ናቸው።

መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

ኤፌሶን 6፥12

5. ርኩሳን መናፍስት የማይታዩ ጠላቶች ናቸው።

ሁሉንም መደነቅ ያዛቸው፥ እርስ በርሳቸውም፦ ይህ ቃል ምንድር ነው? በሥልጣንና በኃይል ርኩሳን መናፍስትን ያዝዛልና፥ ይወጡማል ብለው ተነጋገሩ።

ሉቃስ 4፥36

አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፥ እንዲያወጡአቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው።

ማቴዎስ 10፥1

6. ርኩሳን መናፍስት የማይታዩ ጠላቶች ናቸው።

ሕዝቡን ግን ከአስወጡ በኋላ ገብቶ እጅዋን ያዛት፥ ብላቴናይቱም ተነሣች።

ማርቆስ 9፥25

7. የወደቁ መላእክት የማይታዩ ጠላቶች ናቸው::

መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል።

ይሁዳ 1፥6

8. የዚህ ዓለም ገዦች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው::

ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር፤

1ቆሮንቶስ 2፥8

9. አጋንንቶች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው::

ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው።

ማርቆስ 6፥13አ.መ.ት)

10. ዙፋናት የማይታዩ ጠላቶች ናቸው

እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤

ቆላስይስ 1፥16

11. ጌትነት የማይታዩ ጠላቶች ናቸው::

እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤

ቆላስይስ 1፥16

12. መንፈሳዊ ዝንቦች እና በረሮዎች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው::

ከኢየሩሳሌም የወረዱ ጻፎችም፦ ብዔል ዜቡል አለበት፤ ደግሞ፦ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ብለው ተናገሩ።

እነርሱንም ወደ እርሱ ጠርቶ በምሳሌ አላቸው፦ ሰይጣን ሰይጣንን ሊያወጣው እንዴት ይችላል? መንግሥትም እርስ በርስዋ ከተለያየች ያች መንግሥት ልትቆም አትችልም፤

ማርቆስ 3፥22-24

13. የተጠሉ ወፎች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው::አንድ አንድ አጋንንቶች የተጠሉ ወፎች የሚል ስያሜ አላቸው::

በብርቱም ድምፅ፦ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤

ራእይ 18፥2

14. የጓጉንቸር መናፍስት የማይታዩ ጠላቶች ናቸው:: አንዳንድ አጋንንቶች ጓጉንቸር የሚል ስያሜ አላቸው::

ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጉንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኵሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤ ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፥ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ።

ራእይ 16፥13-14

15. መንፈሳዊ ጊንጦች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው:: አንዳንድ እርኩሳን መናፍስት ጊንጦች የሚል ስያሜ አላቸው::

እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም

ሉቃስ 10፥19

16. መንፈሳዊ ዘንዶዎች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው:: አንዳንድ እርኩሳን መናፍስት ጊንጦች የሚል ስያሜ አላቸው::

ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።

ራእይ 12፥9

17. መንፈሳዊ እባቦች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው::አንድ አንድ እርኩሳን መናፍስት እባብ የሚል ስያሜ አላቸው:: በእርግጥ እነዚህ በአይን የሚታዩ እባቦች ሳይሆኑ መንፈሳዊ እባቦች ናቸው::

እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተ ኋላዋ አፈሰሰ።

ራእይ 12፥15

18. መንፈሳዊ ፈረሶች እና ጋላቢዎቻቸው የማይታዩ ጣላቶች ናቸው::

አየሁም፥ እነሆም፥ ሐመር ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ነበረ። ሲኦልም ተከተለው፤ በሰይፍና በራብም በሞትም በምድርም አራዊት ይገድሉ ዘንድ ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው።

ራእይ 6፥8

19. መንፈሳዊ የባህር ጭራቆች የማይታዩ ጠላቶች ናቸው:: አንዳንድ ርኩሳን መናፍስት ልዋታን የሚል ስያሜ አላቸው:: ሌዋታን ባለ ብዙ ራስ ታዋቂ የባህር ግዙፍ እንስሳ/ጭራቅ/ፍጡር ነው::

የሌዋታንን ራሶች አደቀቅህ፤ ለምድረ በዳ ፍጥረታትም ምግብ አድርገህ የሰጠሃቸው።

መዝሙር 74፥14አመት)

20. ባለ ብዙ ራስ የባህር ፍጡራን በማይታዩ የጠላቶች ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ ናቸው::

**አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ።**

**ራእይ** 13፥1

21. **ከምድር በታች ያሉ ፍጡራን በማይታዩ የጠላቶች ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ ናቸው::**

**ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር።**

**ራእይ** 13፥11

# ምዕራፍ 2

# 10 የአጋንንቶች ተልዕኮ በአንተ ላይ

*ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና* **ተቃዋሚዎችም** *ብዙ ናቸው።*

1ኛ ቆሮንቶስ 16፥9

## ያለ ተቃውሞ የሚዘልቅ "ጥሪ" የለም

ማንኛውም ተልዕኮ ወይም ጥሪ ያለ ተቃውሞ አይዘልቅም:: እግዚአብሔር ቢጠራህ ዲያብሎስ ይቃወመሃል:: ሰይጣን ይዋጋሃል ምክንያቱም የሚኖረው ለዚህ ስለ ሆነ:: እያንዳንዱ ታላላቅ ጥሪ የሚዘልቀው ከታላቅ ተቃውሞ ጋር ነው::

*ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው።*

1ኛ ቆሮንቶስ 16፥9

ሙሴ እስራኤላውያንን ነጻ ለማውጣት ጥሪ ተቀብሎ ሲነሳ ፈርዖን በጽኑ ተቃውሞታል:: ፈርዖን የእግዚአብሔር ልጆችን እንደማይለቀው እንደ ሳይጣን ነው:: እርሱ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ሰዎችን እንደሚጠላው የዲያብሎስ ምሳሌ ነው:: ሙሴን ከዚህ ዓለም ለማጥፋት በተደረገው ሙከራ ውስጥ ሁሉም የእስራኤል ወንድ ሕፃናት እንዲሞቱ ተደርጓል::

ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ሁሉ ለማዳን በዚህ ምድር ሲወለድ ሄሮድስ አዳኙን ለማጥፋት የህፃናትን ግድያ አውጇል:: ይህን ዓለም የማዳን ታላቅ ጥሪ እና ተልዕኮ

የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ አጋጥሞታል።

የአንተም ጥሪ በተመሳሳይ ሁኔታ ተቃውሞ ያጋጥመዋል። ምዕራፍ አንድ ውስጥ የተጠቀሱት ፍጡራን ሁሉ ጥሪህን እንዳትፈጽም ሊያሳናክሉህ ተባብረው ይተጋሉ። ለእግዚአብሔር ለመስራት ስትወስን በህይወትህ እና በአገልግሎትህ ላይ የማይታዩት ጣላቶች ይቋቋሙሃል፣ ዕቅድህን ይገቱታል፣ ይከሱሃል፣ ያስፈራሩሃል፣ ይቃወሙሃል። የማትጸልይ እና መንፈሳዊ ካልሆንክ ይህን የማይታይ **ኃይለኛ** ውጊያ ተቋቁመህ መዝለቅ አትችልም። አጋንንቶች በእርግጥም አሉ። ክፉ ፍጥረቶች መኖራቸው እውነት ነው። አሁን ሰዓቱ በችርግጠኝነት ከማን ጋር እየተዋጋህ እንደሆነ ማወቅ ነው ብሎም መደምሰስ ነው።

# ፍጻሜህ የሚወሰነው ጠላቶችህን በኃይል በመደምሰስ ላይ ነው

ያለ እግዚአብሔር ኃይል ጥሪህን ልታሳካ አትችልም። የእግዚአብሔር ቃል ግልፅ ነው፤ የተሰጠህን ሁሉ የምትቀበለው በእግዚአብሔር ኃይል ነው። ብዙ የሚያስፈልገንን ነገሮች የምንቀበልበት መንገዱ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ባላጋራችንን ለመደምሰስ የሚያስፈልገን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ጠላት የኃይልን ቋንቋ በደንብ ይረዳል።

> **የመለኮቱ ኃይል፥** በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፥ …
>
> 2ጴጥሮስ 1፥3

# አስሩ የአጋንንት ተልዕኮዎች በአንተ ላይ

## 1. መቋቋም እና ተቃውሞ

**በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤**

1ኛ ጴጥሮስ 5፥8

ባላጋራህ ምንም ዓይነት አስፈላጊ ሰው የመሆንህን ሀሳብ ይቃወማል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመታዘዝ ስትሞክር የሚያጋጥሙህ ሁሉም ዓይነት ተቃውሞዎች የሚነሱት ከባላጋራህ ነው። አገልግሎቴን ከጀመርኩ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ተቃውሞዎች ከሁሉም አቅጣጫ አጋጥመውኛል። አንዳንድ ተቃውሞዎች ከዓለም ሲሆን ነገር ግን አንዳንዱ ደግሞ ከራሴው ቢሾፖች(ኤጲስ ቆጶሶች)" አንዳንዴ ከረዳቶቼ፤ አንዳንዴ ደግሞ ከቤተሰቦቼ ነበር። ከየትም ይሁን ከየት ታቃውሞዎችን አጋንንታዊ አድርገህ መለየት አለብህ።

**በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና።**

1ኛ ጴጥሮስ 5፥8

ባላጋራ ማለት ለማከናወን ያቀድከውን እንዳትፈጽም የሚቃወም፣ የሚዘጋ፣ የሚከለክል እና የሚያቆም ነው። ተቃውሞ፣ ክልከላ፣ ተግዳሮቶች፣ መዘግየቶች እና የመሳሰሉትን ቃላቶች ስታስብ ከአጋንንት መሆናቸውንም አስብ። በጥሪህ ውስጥ መዘግየቶች፣ ክልከላዎች እና መዘጋቶች ሲያጋጥሙህ የሳይጣን ሥራ ከጀርባው እንዳለ ኣስብ።

በአገልግሎት ውስጥ ብዙ ክልከላዎች የሚመነጩት ከአጋንንቶች ነው። ምንም እንኳን ነገሮች በውጪ በኩል ያማሩ ቢመስሉም እርኩሳን መናፍስቶች አሉበት። እርኩሳን መናፍስቶች የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ለመቃወም፣

ለመከልከል እና ለመዋጋት ይኖራሉ።

አገልጋዮችን የሚያጋጥሟቸው ችግሮች እና ተግዳሮቶች የሚጠነሰሱት በእርኩሳን መናፍስቶች ነው። የበለጠ መንፈሳዊ እየሆንክ በመምጣትህ ልክ የበለጠ የእርኩሳን መናፍስቶችን አሰራር እያወቅክ ትመጣለህ።

## 2. ተሰፋ ማስቆረጥ

**በልዑሉም ላይ ቃልን ይናገራል፥ የልዑልንም ቅዱሳን ይሰባብራል፥ ዘመናትንና ሕግን ይለውጥ ዘንድ ያስባል፤ እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ።**

**ዳንኤል** 7፥25

ሳይጣን አንተን ከሚቃወምበት ዕቅድ ውስጥ አንዱ ተስፋ ሊያሰቀርጥርህ ይነሳል። የሚያጋጥሙህ የመቆጣት፣ የመረበሽ እና የመበሳጨት ዓይነቶች የአጋንንቶች ሥራ ለመሆናቸው ምልክቶች ናቸው። አንዳንዴ መቆጣት እና መበሳጨት የሚመጡት ከውስጣዊ ሁነቶች ናቸው። አንድ ተራ ሥራ እየዘገየ በመሄድ ረጅም እና የማያስደስት ነገር ይሆናል። ይህ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመቋቋም እና ተስፋ ለማስቆረጥ ያለ ማቋረጥ የሚላኩ የአጋንንቶች መገለጫቸው ነው።

## 3. ሰዎችን መከልከል

**ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር።**

**ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ፦ አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።**

**ማቴዎስ** 16፥21-22

ከሰይጣን መደሰቻዎች አንዱ የእግዚአብሔርን ሥራ ሙሉ

በሙሉ ማስቀም ነው። የእግዚአብሔርን ሥራ እንዳይሰራ ተስፋ ከማስቆረጥ አልፎ የተወሰነ ሂዳቶችን ለመሄድ ችሏል። ሙሉ በሙሉ ለማስቆም ያቻለባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። የእግዚአብሔርን ሥራ ሙሉ በሙሉ ለማስቆም የሚደጋገሩትን ነገሮች ልብ በልና ተመልከት።

## 4. ሰዎችን መፈተን

**ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው። በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ነበረ፥ መላእክቱም አገለገሉት።**

**ማርቆስ** 1፥12-13

ለጌታ የሚሰሩ የእግዚአብሔርን ሰዎች መፈተን እና መፈተሽ የዲያብሎስ ሥራ ነው። ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ በማያቋርጥ ፈተና ውስጥ ይኖራሉ። ብዙ ሰዎችም ይቅር ባለማለት፣ በፍትወት፣ ትዕግስት በማጣት እና በሌሎች ፈተናዎች ይወድቃሉ።

## 5. ሰዎችን ማስፈራራት

**በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤**

1ኛ **ጴጥሮስ** 5፥8

ሁሉም የፍርሃት ዓይነቶች ከዲያብሎስ ናቸው። ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ሙሉ በሙሉ በፍርሃት ቁጥጥር ስር ናቸው። ፍርሃት ተጽዕኖ የሚፈጥር እና የሚመራ መንፈስ ነው። በመጨራሻው ላይ ራስህን ወደምትጎዳበት መንገድ ሊመራህ እና አቅጣጫ ሊያሲዝህ ይፈልጋል።

## 6. ሰዎችን ማማለል

**ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።**

**2ኛ ቆሮንቶስ 11፥3**

**ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።**

**ራእይ 12፥9**

የክርስቲያኖችን ልብ በመመረዝ ዲያብሎስ በደንብ የታወቀ ነው:: ብዙዎች በጥርጣሬ፣ በምሬት፣ በአታላይነት፣ ታማኝ ባለመሆን እና በአወዛጋቢነት ተመርዘዋል:: ወደ ክርስቲያኖች ልብ ሊወረወሩ ከሚችሉት ገዳይ መርዞች አንዱ ክስ ነው:: ብዙ ሰዎች የዋህነታቸው የሚጠፋው ሳይጣን በልባቸው ውስጥ በሚጨምረው መርዝ ምክንያት ነው:: ባጋጠማቸው ነገር በጣም የተጎዱ ሰዎችን ስታገኛቸው ምናልባትም በዲያብሎስ ተመርዘው ሊሆን ይችላል::

## 7. ማታለል

**እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።**

**ዮሐንስ 8፥44**

መዋሸት እና ማታለል የዲያብሎስ ሥራ ነው:: የሚዋሽ ሰው ሲያጋጥምህ የሆነ ተስፋ መቁረጥ ነገር ይሰማሃል:: ውሸታም ሰው ሁሌም ሌባ ነው የሆነ ነገርም እየሰረቀ ነው:: ግማሽ እውነት የሚናገሩ እና በማይሆን አኳኋን የሚመሩህ ሰዎች ሊያሳናክሉ እና ሊያጠፉህ ከሳይጣን የተላኩ ናቸው::

በህይወት ዘመንህ እና አገልግሎትህ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ያጋጥሙሃል:: እነርሱ ሊያጠፉህ የተላኩ የዲያብሎስ ወኪሎች ናቸው::

ማንኛውም የወንጌሉ አገልጋይ ሊያታልለው የሚሞክረውን ነገር ወይም ሰው ሊያስተውለው ይገባዋል:: ሳይጣን ሁሌም አቅጣጫ ሊያስትህ፣ በማይሆን መንገድ ሊመራህ፣ ሊያዘናጋህ እና ሊያሳስትህ ይሞክራል:: የሆነ ነገር ደብቆብህ ሁሌም በጨለማ፣ በድንቁርና እና በመታለል ሕይወት ውስጥ እንድትመላለስ ለማድረግ ይሞክራል:: ይህ የዘወትር እና የማይለወጥ የእርኩሳን መናፍስት ሥራ ነው:: ለዚህ ነው እንግዲህ ዘወትር ለጥበብ፣ ለመረዳት፣ ለእውቀት፣ ለምክር፣ ለብርሃን እና መገለጥ መጸለይ ያለብህ:: ዳንኤል ከአታላይነት ጨለማ ነጻ የወጣ ሰው ተብሎ ይታመናል:: የበራለት፣ አስተዋይ እና ጥበብ ያለው ሰው ተብሎ ተገልጿል:: በንጉሱ ተመርጦ የተሾመው በተገለጠለት ብርሃን፣ ባለው መረዳት እና ጥበብ ምክንያት ነበር:: ለዚህ የተጠራው ጨለማውን ሰብሮ ከእግዚአብሔር ብርሃን እና መገለጥን ስለተቀበለ ነው:: በጣም ኃይለኛ የሆኑ ሰዎች በዓለም ያለውን ጨለማ ተቋቁመው ከእግዚአብሔር ብርሃን የተቀበሉ ናቸው::

> **የቅዱሳን አማልክት መንፈስ ያለበት ሰው በመንግሥትህ ውስጥ አለ፤ በአባትህም ዘመን እንደ አማልክት ጥበብ ያለ ጥበብና ማስተዋል እውቀትም ተገኘበት፤ አባትህ ንጉሡ ናቡከደነፆር የሕልም ተርጓሚዎችና የአስማተኞች የከለዳውያንና የቃላተኞች አለቃ አደረገው። መልካም መንፈስ፥ እውቀትም፥ ማስተዋልም፥ ሕልምንም መተርጐም፥ እንቈቅልሽንም መግለጥ፥ የተቋጠረውንም መፍታት ንጉሡ ስሙን ብልጣሶር ብሎ በሰየመው በዳንኤል ዘንድ ተገኝቶአልና። አሁንም ዳንኤል ይጠራ፥ እርሱም ፍቺውን ያሳያል።**
>
> **ዳንኤል 5፥11-12**

**ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።**

**ራእይ** 12፥9

## 8. መስረቅ

**ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።**

**ዮሐንስ** 10፥10

ገንዘብ መስረቅ፣ የራስህ ያልነሆነውን ነገር መውሰድ ከዋነኞቹ የዲያብሎስ እና እርኩሳን መናፍስት ሥራዎች አንዱ ነው:: አንድ ሰው ሲዘረፍ አጋንንታዊ የሆነ ተስፋ መቁረጥ እና አጋንንታዊ የሆኑ እንቅፋቶች ይለቀቁበታል:: በራስህ ህይወት እና በዙሪያህ የዲያብሎስን ሥራ ታፍነው ዘንድ በሕይወትህ ላይ የሚከሰተውን ማንኛውንም የስርቆት ዓይነት መቆጣጠር አለብህ::

## 9. አሳልፎ መስጠት እና ታመኝ አለመሆን

**እራትም ሲበሉ ዲያብሎስ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው** አሳብ ካገባ በኋላ፥

**ዮሐንስ** 13፥2

ግንኙነቶች ሲበላሹ ዲያብሎስ ጠንክሮ እሰራ መሆኑ ይታወቃል:: መልካም ወዳጆችን እና ደስተኛ ጥንዶችን ለመለያየት ሲችሉ ስኬታማ ናቸው:: የቤተክርስቲያን መፍረስ የዲያብሎስ ሥራ ነው:: ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ሲገነባ ዲያብሎስ ደግሞ ያፈርሳል:: በሙስና እና ዝሙት የወደቁት አገልጋዮች በሙሉ በእርግጥ የወደቁት በዲያብሎስ ነው:: ሥጋ ለባሽ ሰዎች ሙስና እና ሰብዓዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን ሲያደርጉ አይተህ ይሆናል:: ይሁን እንጂ እውነታው ግን የታጎረ የአጋንንቶች ሥራ ነው::

## 10. መግደል

**ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።**

**ዮሐንስ 10፥10**

የኢየሱስ ክርስቶስ መሞት የተቀነባበረው በዲያብሎስ ነው። ማንኛውም ዓይነት ስርቆት፣ ግድያ እና ጥፋት ከዲያብሎ ነው። ሰይጣን ነፍሰ ገዳይ ነው፣ ዋነኛ ዓላማውም እኛን ሁላችንንም መግደል ነው። እድሉን ቢያገኝ እያንዳንዳችንን በበሽታ ያጠቃናል፣ አደጋ ሊያደርስብን እና ሊያሳዝነን ይፈልጋል። ማንኛውም በሽታ፣ ማንኛውም እንቅፋት እና ማንኛውም አሳዘኝ ነገር የሚፈጸመው የእግዚአብሄርን ሥራ ለመቃወም እና ለማጨናገፍ በአጋንንቶች ተቀነባብሮ ነው።

# ምዕራፍ 3

# የማይታዩ ጠላቶች ልዩ ዒላማዎች

**ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ከዮርዳኖስ ተመለሰ፥ በመንፈስም ወደ ምድረ በዳ ተመርቶ፥**

**አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ። በነዚያም ቀኖች ምንም አልበላም፥ ከተጨረሱም በኋላ ተራበ።**

**ሉቃስ 4፥1 - 2**

በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ በዲያብሎስ ልዩ ዒላማ ውስጥ የገቡትን እናያለን። ኢየሱስ በአገልግሎቱ ውስጥ እንዴት ከዲያብሎስ ጋር ሲገናኝ እንደ ነበር ማየት የሚያስስገርም ነው። የሚገርመው ኢየስስ ዲያብለሎስን ያገኝ የነበረው በቤተ ክርስቲያን እና የኃይማኖታዊ ሰዎች ዙሪያ ነበር። በከፍተኛ አመራር ላይ ባሉት ውስጥም ዲያብሎስ አጋጥሞታል። ምናልባት ዲያብሎስን ያገኘው በመጠጥ ቤቶች እና በሴተኛ አደሪዎች መንደር ውስጥ ነው ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። በሚገርም ሆኔታ ግን አብዛኛዎቹን አጋንንቶች የተገኙት ግን በቤተክርስቲያን እና የቤተክርስቲያን ሰዎች ውስጥ ነው። የታጠቁ ዘራፊዎች፣ ሴተኛ አዳሪዎች እና ሰካራም ጠጪዎች በሰላም በመኖታቸው ሲተኙ ኢየሱስ በእየሩሳሌም ውስጥ ባሉ መጋቢዎች እና ቄሶች መሰቀሉ የሚያስደንቅ አይደለም። በእርግጥ ብዙ አጋንንቶች በቤተክርስቲያን እና የቤተክርስቲያን ሰዎች ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። ሰይጣን ዓለማዊያንን አስቀድሞ ተቆጣጥሯቸዋል። እኛ እንደ ቤተክርስቲያን ለእርሱ ልዩ ዒላማው እንደሆንን ማወቅ ያስፈልጋል።

## 1. በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ የቤተ ክስቲያን አባላቶች የዲያብሎስ ልዩ ዒላማ ነበሩ

**በዚያን ጊዜም በምኩራባቸው ርኩስ መንፈስ ያለው ሰው ነበረ፤**

**እርሱም፦ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ፥ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ። ኢየሱስም፦ ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው።**

ማርቆስ 1፥23-25

ኢየሱስ እርኩሳን ማናፍስትን በምኩራብ ውስጥ አግኝቷቸዋል:: ኢየስስ ክርስቶስ አጋንንቶችን በቤተክርስቲያን አባሎች ውስጥ አግኝቷቸዋል:: ካለባቸው እርኩሳን መናፍስት የተነሳ አንዳንድ የቤተክስቲያን አባላት ኢየሱሰ በመስበክ ላይ እያለ ይጮኹ ነበር:: አንዳንድ እርኩሳን መናፍስቶች ደግሞ ሰዎች መሬት ላይ እንዲንከባለሉ፣ እንዲያጓሩ እና እንዲንቀጠቀጡ ያደርጋሉ::

**ወደ እርሱም አመጡት። እርሱንም ባየ ጊዜ ያ መንፈስ ወዲያው አንፈራገጠው፤ ወደ ምድርም ወድቆ አረፋ እየደፈቀ ተንፈራፈረ።**

ማርቆስ 9፥20አመት)

በአንተ ዙሪያ ለሚፈጸሙት አብዛኞዎቹ ክፋቶች መንስዔው አጋንንቶች ናቸው:: አጋንንቶች በኢዮብ ላይ እሳትን፣ የተዳራጁ ታጣቂ ዘራፍዎችን፣ ስርቆትን እና የቤተሰቡን ሞት አስነስተዋል:: በሕይወታችን ላይ ለሚከሰቱ ብዙ ጥፋቶች ትክክለኛ መነሻ አጋንንቶች ናቸው:: በዚህ ምድር ላይ ኖረህ እነዚህ ነገሮች እንደ ሌሉ አድርጎ ማሰብ ራስን ለጠላት እጅ አሳልፎ መስጠት ነው::

## 2. በኢየሰስ ክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ ኃይማኖተኞች እና የቤተክርሰቲያን መሪዎች የአጋንንቶች ልዩ ዒላማ ነበሩ::

**እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።**

**ዮሐንስ 8፥44**

ሳይጣን ቤተክርስቲያን እና መሪዎቹን መውረር ይወዳል:: ኢየሱስ ፈሪሳውያንን በዲብሎስ ቁጥጥር ስር መሆናቸውን ነግሯቸው ነበር:: የኃይማኖት መሪዎች መሆናቸው ኢየሱስን ግራ አላጋባውም ነበር:: የሰነባበቱ የእግዚአብሔር ቤት ሰዎች መሆናቸው ኢየሱስ ክርስቶስን ግራ አላጋባውም ወይም አላታለለውም:: ጴጥሮስ ልክ የቤተክርስቲያኗ መሪ ሆኖ ሲሾም ዲያብሎስ ወዲያውኑ አጠቃው:: ወደ መስቀሉ ስለነበረው ጉዞ ላይ ተቃውሞ ሲናገር ኢየሱስ በጴጥሮስ ውስጥ አልፎ አይቶ ነበር:: አዲስ የተሾመውን የኃይማኖት መሪ ዲያቢሎስ እንደተቆጣጠረው አውቆ ነበር:: ክፉ መናፍስት የብዙ ኃይማኖት መሪዎችን ህይወት ሲቆጣጠሩ ማየት ያሳዝናል:: ከጌታ እድገትን ስትቀበል ከዲያብሎስ ደግሞ ውጊያ እንደሚመጣ መጠበቅ አለብህ::

**ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።**

**እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።**

**የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።**

**ያን ጊዜም እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለማንም እንዳይነግሩ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው።**

**ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና**

**ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር።**

**ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ፦ አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።**

**እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፦ ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።**

**ማቴዎስ** 16፥17-23

የመለየት ስጦታን ገንባ! እንደ ኢየሱስ ሁን! የመንፈሳዊ መሪዎችን የኃይማኖታዊ ሽፋናን እና ግብዝነታቸውን አልፈህ ማየት መቻል አለብህ::

## 3. በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ፣ የቅርብ ረዳቶቹ የአጋንንቶች ዒላማ ነበሩ

**ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ፦ አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።**

**እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፦ ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።**

**ማቴዎስ** 16፥22-23

የወደቁ መላዕክቶች፣ ዲያብሎስ እና ሎሎች እርኩሳን መናፍስቶች የቅርብ ባልንጀሮችን ማጥቃት ይወዳሉ:: ኢየሱስ በጴጥሮስ ውስጥ የነበረውን ዲያብሎስ ለይቶታል:: ሳይጣን ይሁዳን ተቆጣጥሮት ነበር::

**ቍራሽም ከተቀበለ በኋላ ያን ጊዜ ሰይጣን ገባበት። እንግዲህ ኢየሱስ፦ የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ አለው።**

**ዮሐንስ** 13፥27

አንተም በህይወትህ ውስጥ ያሉትን ዲያብሎስ፣ “ጴጥሮስን”

እና "ይሁዳን" መለየት መቻል አለብህ:: የጴጥሮስ ለኢየሱስ ቅርብ መሆን እና የእርሱ እስትራቴጂካዊ ቦታው ለዲያብሎስ ኃይለኛ ዒላማ ተጋላጭ አድርጎታል:: በራስህ ህይወት እና አገልግሎት ውስጥ "ጴጥሮስ" ይኖርሃል:: ይህ "ጴጥሮስ" ባልንጀራህ ወይም ረዳት መጋቢህ ወይም ጓደኛህ ሊሆን ይችላል:: በጣም በምትመካባቸው እና በምትቀርባቸው ረዳቶችህ እና ጓደኞችህ ውስጥ አልፎ ዲያብሎስ ሲናገር መለየት መቻል ስለ ዲያብሎስ ትልቅ መረዳትን እና ከፍተኛ እውቀት ማወቅን ይጠይቃል:: ይሁዳ ውስጥ ሰይጣን ሲገባ መለየት ትችላለህ? ከባልንጀሮችህ አንዱ በእርኩሳን መናፍስት ሲወረር ልታውቅ ትችላለህ?

## 4. በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ፣ የቅርብ ጓደኞች እና ረዳቶች የአጋንንቶች ዒላማ ነበሩ::

ኢየሱስ በጴጥሮስ ውስጥ የነበረውን አጋንንት በለየ ጊዜ ያኔ ኢየሱስ ለእርሱ በጣም የቅርብ የሆነና ቤተኛ የሆነውን እየለየ ነበር:: ዛሬ በህይወትህ ውስጥ ላንተ በጣም የቅርብህ እና ቤተኛ የሆነ ሰው ሚስትህ ነች:: ብዙ አገልጋዮች ሚስቶች የዲያብሎስ ዒላማ ናቸው:: ከትዳር ጋር የተያያዘ ተግዳሮት መስሏቸው ብዙ አገልጋዮች ከሚስቶቻቸው ጋር ትግል ውስጥ ናቸው:: ከሳይጣን ወይም ከወደቁ መላዕክቶች ጋር ፊት ለፊት እየተጋጠሙ መሆናቸውን ግን አይረዱትም::

**ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ፦ አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።**

**እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፦ ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።**

**ማቴዎስ 16፥22-23**

# ምዕራፍ 4

# አምስቱ የእርሰኩሳን መናፍስት የተልዕኮ ግዛቶች

## 1. አጋንንቶች በማይታየው ዓለም ላይ ይሠራሉ

የማይታይ ዓለም አለ። በዚህ በማይታየው ዓለም ውስጥ መላዕክቶች፣ አጋንቶች፣ የወደቁ መላዕክት፣ የተዳቀሉ ፍጡራን፣ ዙፋናት፣ ገዦች፣ ሥልጣናት፣ ኃይላት፣ ክፉ መናፍስት እና የተለያዩ የመንፈሳዊ እንስሶች አሉ። ሙሴ ሊያሸንፍ የቻለው የማይታየውን ዓለም ስለ ተረዳ ነው።

**የንጉሡን ቍጣ ሳይፈራ የግብፅን አገር የተወ በእምነት ነበር፤ የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና።**

**ዕብራውያን** 11፥27

ከማይታይ ጠላት ጋር ስትዋጋ ጠላትህን ለማወቅ እና ለመረዳት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብሃል። ከብዙ ዓመታት በፊት ኬኔት ሃገን በአጋንንቶች ዙሪያ ያስተማሩትን ትምህርት እየሰማሁ ነበር። አጋንንቶች ዛሬ እንዴት ክርስቲያኖችን እንደሚያጠቁ ያብራሩ ነበር። በራዕይ ያዩትን ሲያብራሩ አንድት ትንሽዬ ፍጡር በአንድ መጋቢ ሚስት ትክሻ ላይ ሆና ሀሳብ ሲታስገባባት ያዩ ነበር ። መንፈስ አዕምሮዋ እና ልቧ ውስጥ እስኪገባ ድረስ ሴትዬዋ በሀሳቡ ደስ እየተሰኘች በመቀበል ታስተናግደው ነበር። ያን ጊዜ ይህቺ ሴትዬው በአጋንንት ሙሉ ቁጥጥር ስር ስትውል ባሏን ጥላው ወደ ዓለም ገባች።  መጨረሻ ላይ ኢየሱስን እስከምትክድ ድረስ ከብዙ ወንዶች ጋር ዝሙት ትፈጽም ነበር። እርሳቸውም ይህቺ ሴት በጠላት ቁጥጥር ስር የወደቀችበትን ሂደቱን አስረዱ። ይህ

ታሪክ በልቤ ውስጥ የቀረ ሲሆን እኔም በጨለማው ዓለም የሚደረገውን እንቅስቃሴ በተሻለ ሁኔታ መረዳት ጀመርኩ።

ሁሉንም የምታውቅ አይምሰልህ። ብዙዎቹ የምትታገልባቸው ነገሮች ከጀርባቸው አጋንንታዊ አሰራሮች መኖራቸውን ትደርስበታለህ። ስለ ጠላትህ እያንዳንዷ ገጽታ ለማወቅ ያላሰለሰ ጥራት አድርግ።

## 2. አጋንንቶች በመንፈሳዊው ዓለም ላይ ይሰራሉ

**በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያስተውለው የለምና፥ በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል፤**

**1ኛ ቆሮንቶስ 14፥2**

ጳውሎስ በልሳን ስለ መጸለይ ሲያስተምር ስለ መንፈሳዊ ዓለም ይናገራል። በልሳን መናገር ማለት በመንፈሳዊ ዓለም ላይ ሥራ መሥራት(መንቀሳቀስ) መሆኑንም ያብራራል። በመንፈስ ምሥጢርን እናገራለሁ ይላል። በሥጋ ሆኖ ሚሥጢር አይናገርም። ለዚህም ነው ልሳን በዲያብሎስ የሚፈራው። በልሳን መናገር በቀጥታ አጋንንቶች ባሉበት መንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ያስገባሃል።

መንፈሳዊ ዓለም መናፍስትን ይዟል። ሥጋ እና ደም በዚህ ዓለም ላይ ሊሰሩ አይችሉም። አንድ በጎ ክርስቲያን በሥጋ እና ደም ከመዋጋት ወጥቶ በመንፈሳዊ ዓለም መዋጋት አለበት። ጳውሎስ እንዲህ ይላል "መጋደላችን ከደም እና ከሥጋ ጋር አይደለምና"። ከደም እና ከሥጋ ጋር የማንጋደል ከሆነ የምንጋደለው ከመንፈስ ጋር ነው።

**መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካሉ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።**

**ኤፌሶን 6፥12**

**በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን፥ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤**

**2ኛ ቆሮንቶስ** 10፥3

### *3. አጋንንቶች በጨለማው ዓለም ላይ ይሰራሉ*

የጨለማ ዓለም አለ፡፡ ይህ ዓለም “መንፈሳዊ ጨለማ” ይባለል፡፡ አንድ ክርስቲያን ስለ እርኩሰ ፍጡራን፣ እርኩሳን ማናፍስት እና ሥራቸውን ለማወቅ ልዩ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ በጨለማው ዓለም የታሰሩ ብዙ ፍጡራን አሉ፡፡ የሚሰሩትም ከዚያ ሆነው ነው፡፡ በዚያ ዓለም የሚሰሩት ሥራ ብዙ ይጎዳናል፡፡

> **መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል።**

**ይሁዳ** 6

እነዚህ ክፉ ፍጡራን ከዚያ የጨለማው ዓለም እስራት ሆነው እንኳን ይዋጉናል፡፡ “የጨለማው ዓለም ገዦች” ተብለው የሚጠሩ ፍጡራን አሉ (ኤፌሶን 6፡12)፡፡ እነዚህ ፍጡራን በጨለማው ዓለም ውስጥ ሌላውን ፍጥረቶች የሚገዙ ናቸው፡፡ በእርግጥ ድነት የሚጀምረው በጨለማው ዓለም ካሉ ኃይላት ነፃ ስትወጣ ነው፡፡

> **እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።**

**ቆላስይስ** 1፥13

### *4. አጋንንቶች ከምድር የጨለማ ሥፍራ ይሰራሉ*

**ወደ ኪዳንህ ተመልከት፥ የምድር የጨለማ ስፍራዎች በጎጥኣን ቤቶች ተሞልተዋልና።**

**መዝሙር** 74፡20

በእርኩሳን ቁጥጥር ስር ያሉ የምድር ክፍሎች አሉ። እነዚህ ስፍራዎች የአጋንንታዊ እንቅስቃሴዎች መወንጨፊያዎች ናቸው። አጋንንታዊ አስተሳሰቦች ወደ ተቀረው ዓለም የሚላኩት ከእነዚህ ስፍራዎች ነው። የምድር የጨለማ ሥፍራዎች እርኩሰት የሚተገበርበት ቦታዎች ናቸው። በዚህ የምድር ጨለማ ስፍራ ክፋት ይገዛል እርኩሰት ይነግሳል። የእግዚአብሔር ቃል ስብከት ወደ እነዚህ የጨለማ ስፍራዎች ሲመጣ በቀላሉ ሊረዱት አይችሉም። ኢየሱስ ይህን አውቆ ተንብዮ ነበር። እንዲህ አለ፤ ይህ ፍርድ ነው። ብርሃን ወደ ዓለም መጣ ይሁን እንጅ ሰዎች ከብርሃን ይልቅ ጨለማን አብልጠው ወደዱት።

**ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም።**

**ዮሐንስ** 1፡5

**ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤**

**ዮሐንስ** 3፡19-20

### *5. አጋንንቶች በጨለማ ይሰራሉ*

**ሁላችሁ የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና። እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ አይደለንም፤**

1**ኛ ተሰሎንቄ** 5፡5

**ሰዎቹ ሲተኙ** ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ።

ስንዴውም በበቀለና በአፈራ ጊዜ እንክርዳዱ ደግሞ ያን ጊዜ ታየ።

የባለቤቱም ባሮች ቀርበው፦ ጌታ ሆይ፥ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ? አሉት።

እርሱም፦ ጠላት ይህን አደረገ አላቸው። ባሮቹም፦ እንግዲህ ሄደን ብንለቅመው ትወዳለህን? አሉት።

ማቴዎስ 13፤25-28

"ጨለማ" ጳውሎስ የተጠቀመበት ሌላኛው ሁኔታ ነው:: ይህ የቀን አለመኖር ነው:: ምሽት ሲመጣ ክፉ ደግሞ ብቅ ብቅ ይላል:: አብዛኛዎቹ ሌቦች ሥራቸውን ለመጀመር ምሽትን ይጠባበቃሉ:: በቀን በቀላሉ መሥራት አይችሉም:: ብዙዎቹ የዓለማችን ኃጢአቶች የሚደረጉት በሌሊት እና በጨለማ ነው:: ይህ ሰዓት ሰዎች የሚተኙበት ጊዜ ነው:: ሰዎች ሲያርፉ እና ሲተኙ፤ ሌሊትም ሲሆን ሰይጣን ደግሞ ሥራውን ይጀምራል:: በምትዝናናበት እና በእረፍት ጊዜህ ተጠንቀቅ ምክንያቱም ያ ሰዓት እርኩሳን መናፍስት የሚሰሩበት ጊዜ ነው::

## *ምዕራፍ 5*

# የአጋንንት መኖር ምልክቶች

**እነርሱም፦ መምህር ሆይ፥ እንግዲህ ይህ መቼ ይሆናል? ይህስ ይሆን ዘንድ እንዳለው ምልክቱ ምንድር ነው? ብለው ጠየቁት።**

ሉቃስ 21፥7

*አጋንንትን መዋጋት የማይታይ ጠላትን መዋጋት ነው! የእርኩሳን መናፍስት መኖራቸውን እና ሥራቸውን ለይቶ ማወቅ ለአንድ ክርስቲያን ስኬት ቁልፍ ነው። የወንጌል አገልጋይ ደግሞ በበለጠ ሁኔታ የእርኩሳን መናፍስት መገኘትን እና ሥራቸውን የማወቅ ብቃት ሊኖረው ይገባል። ጠላትህን የተደበቀበትን ካወቅህና ከለየህው መደምሰስ ከቻልክ ጠላትህን ድል ትነሳዋለህ።*

*አጋንንትን መዋጋት የማይታይ ጠላትን መዋጋት ነው። የማይታይ ጠላትን መዋጋት የማይቻል እንደሚመስል ከባድ አይደለም። ዶክተሮች ይህን ለዘመናት እያደረጉ ነው!*

*የማይታይ ጠላትን መዋጋት ከዶክተሮች ሥራ ጋር ይመሳሰላል ምክንያቱም ዶክተሮች የሚዋጉት የማይታዩ ባክቴሪያን፣ ፓረሳይትን እና ቫይራሶችን ነው።*

*ለዘማናት ዶክተሮች የማይታዩ ጠላቶችን ለመዋጋት ተገድደዋል። ከዓመታቶች ልምድ በኋላ ዶክተሮች የማይታዩ ጠላቶችን የተደበቁበትን ማወቅ፣ መለየት እና እነርሱን እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው ደርሰውበታል።*

*የወንጌል አገልጋይም እንደ ዶክተሮች መሆን አለበት። የእርኩሳን መናፍስትን መገኘትን በቶሎ ለመለየት እስክትችል*

ድረስ በመንፈሳዊ ህይወት ጉዞህ ማደግ አለብህ:: ዲያብሎስ እና አጋንንቶች ሲሰሩ ራእይን የሚያዩ እና መገለጥን የሚያገኙ በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው:: ብዙ ዶክተሮችም አንዳንድ ቫይረሶችን እና ባክቴሪያን ባያዩም ግን ውጤታማ በሆነ መንገድ መዋጋት ችለዋል::

ጠላትህን ለማሸነፍ ማየት አይጠበቅብህም! ነገር ግን ጠላትህ በዚያ በስፍራው መኖሩን ማወቅ አለብህ! ምን እየሠራ መሆኑን በእርግጠኝነት ማወቅ መቻል አለብህ! ጠላትህ እንዴት እንደሚንቀሳቀስ ማወቅ አለብህ! *በምልክት እና በዱካው የማይታይን ጠላት መኖሩን ማወቅ ይቻላል*::

የአጋንንታዊ ሥራ ምልክቶቹ ብዙዎች ናቸው:: የዲያብሎስን ሥራ ለማወቅ ብቸኛው መንገድ ስለሆኑ ማንኛውም የወንጌል አገልጋይ እነዚህን ምልክቶች ሊያውቃቸው ይገባል:: የበሽታ ምልክቶች እና ዱካቸው ጠንቅቀው ለዶክተሮች የታወቀ ነው:: አንድ ታካሚ በማታ የሚያልበው ከሆነ፣ ክብደት ከቀነሰ እና የማያቋርጥ ሳል ካለው አብዛኛዎቹ ዶክተሮች በቀጥታ የሳንባ በሽታን ይጠራጠራሉ:: ለምን? ምክንያቱም ባክቴሪያው ባለበት ሰው ሁሉ ላይ የሚታየው ምልክት ተመሳሳይ ስለ ሆነ ነው:: አንድ ሰው በምዕራብ አፍሪካ የሚኖር ከሆነ እና ራስ ምታት፣ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ ማለት እና ሙቀት ተስምቶት የሚያልበው ከሆነ ዶክተሮች ወባ ይሆናል ብለው ያስባሉ:: የወባን ፓራሳይት ማየት አይቻልህም፣ ነገር ግን ወባው እንዳለ ታውቃለህ:: ትኩሳቱ ወረድ ብሎ ከአርባ ስምንት ሰዓት በኋላ ወደ ላይ ተመልሶ ከመጣ ወባ መሆኑን በደንብ እየተረዳህ ትመጣለህ ምክንያቱም የወባ ፓራሳይት እራሳቸውን ለማባዛት በጉበት ውስጥ ሆነው ከአርባ ስምንት ሰዓታቶች በሃላ ወደ ሰውነት ክፍሎች ይለቀቃሉ::

አንድ ህፃን ልጅ የትንፋሽ መቆራረጥ ካለበት፣ በትንሽ እንቅስቃሴ ድካም የሚሰማው ከሆነ፣ የገረጣ ከንፈር እና ምላስ ካለው፣ ከመወለዱ ጀምሮ ያለ የልብ ድካም መሆኑን አብዛኞቹ ዶክተሮች ይገምታሉ። ዶክተሮች የምልክቶቹን አካሄድ እንደሚያውቁት እንደዚያው ክርስቲያኖችም የአጋንንታዊ ሥራን ምልክቶች እና አሰራሮች ማወቅ አለባቸው።

**አይሁድ መልሰው፦ ሳምራዊ እንደ ሆንህ ጋኔንም እንዳለብህ በማለታችን እኛ መልካም እንል የለምን? አሉት።**

**ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እኔስ ጋኔን የለብኝም ነገር ግን አባቴን አከብራለሁ እናንተም ታዋርዱኛላችሁ።**

**ዮሐንስ 8፥48-49**

የሰው ልጆች ዲያብሎስን ለማጋለጥ ብዙ መንገዶችን ፈልገዋል። ክርስቲያኖች አንዳንዴ ይካሰሱ እና አንተ "ሳይጣን አለብህ" ይባባላሉ። ያ ወንድም በአጋንንት የተያዘ ነው! ያቺ እህት የአጋንንት ማደሪ ነች! ባሌ በአጋንንት ተይዟል! ሚስቴ በውስጧ ዲያቢሎስ አለ! እነዚህ ብዙ ጊዜ በክርስቲያኖች የሚባሉ አባባሎች ናቸው። ነገር ግን በእርግጥም ትክክል ናቸውን?

አጋንንቶች ልክ እንደ አይጦች ናቸው። በእኛ መኻከል ይኖራሉ። ምግባችንን ይበላሉ። ንብረቶቻችንን እያወደሙ ምቾት ይነሱናል። ነገር ግን ሁሌም ወደ ጨለማ እየሸሹ ከእኛ ይደበቃሉ። ቢሆንም ግን አንዳንድ ጥለው በሚያልፉት ምልክቶች መኖራቸውን ማወቅ ይቻላል። በሚያሳዝን ሁኔታ ፈሪሳውያን ኢየሱስን ዲያብሎስ አለብህ ብለው ከሰሱት። አጋንንት እንዳደረበት እና በእነርሱ ኃይል እንደሚሰራ አድርገው ከሰሱት። ይህ ለአንድ የእግዚአብሔር ሰው እንግዳ ክስ አይደለም። የሚያሳዝነው ግን የዓለም ሁሉ አዳኝ የሆነው በተመሳሳይ ክስ መከሰሱ ነው። የእግዚአብሔር አገልጋይ

ከሆንክ የተሻለ ነገር አትጠብቅ።

ኢየሱስ ግን ዲያብሎስ አለበት የተባለውን ክስ በብርቱ አጣጥሎታል። አባቱን እንዳከበረ እና ዲያብሎ እንደሌለበት ለእነርሱ ጠቆመላቸው። ዲያብሎስ ያለባቸው ሰዎች አባቶቻቸውን አያከብሩም። ዲያብሎስ ያለበትን ለመጠቆም ስተሞክር ስህተት መፈጸም የለብህም። የአጋንንቶችን መኖር ለማወቅ ጥርት ያሉ ምልክቶችን ማወቅ መቻል አለብህ። አባትን ማክበር የዲያብሎስ መገኛ ማሳያ ምልክት አይደለም።

# የዲያብሎስ መገኛ ምልክቶች

**ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።**

**ራእይ 12፡9**

የዲያብሎስ ሥራ ምልክቶችን ለመለየት ቀላሉ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዲያብሎስ የተሰጡትን ስሞችና መጠሪያዎችን መጠቀም ነው። ከሰይጣን ስሞች አንዱን ወደ አዕምሮህ የሚያመጣ ማንኛውንም አጋጣሚ ማስተዋል አለብህ። ስሞችና መጠሪያዎች የሚሰጡት ያን ሰው ለመግለጽ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው 'የፖፕ ሙዚቃ ንጉስ' ተብሎ ቢጠራ ያ ሰው ምን እንደ ሆነ እና ምን እንደሚሠራ በድንብ ይገልጸዋል። የፖፕ ሙዚቃ በሚጫወትበት በማንኛውም ቦታ ልትጠብቀው ትችላልህ። አንድ ሰው 'የሬጌ ሙዚቃ ንጉስ' ነው ከተባለ እርሱን ወይም ባለንጀሮቹን ሬጌ ሙዚቃ በሚጫወትበት ቦታ ልትጠብቀው ትችላለህ። የእርሱን ተፅዕኖ ሬጌ ሙዚቃ በሚዜምበት ቦታ ልታስተውል ትችላለህ።

ሰይጣን ብዙ ስሞች አሉት። እያንዳንዱ የሰይጣን ሰሞች አንድን የሆነ ሥራውን የሚገልጹ ናቸው። እያንዳንዱ ስሞቹ

በመገኘቱ የሚፈጠሩ ምልክቶች እና ዱካዎችን የሚያሳዩ ናቸው። አንድ የወንጌል አገልጋይ የሰይጣንን ስም ወደ አዕምሮው የሚያመጡ አጋጣሚዎችን ልብ ማለት አለበት። ስሞቹን በማወቅ በእርሱ የሚፈጸሙ ነገሮች ምን እንደሆኑ ወደ መረዳት ትመጣለህ።

## 1. የውሸት እና የማታለል ምልክት።

**ሰይጣን የሚጠራው ወሸታም እና የወሸት አባት ተብሎ ነው፡ የወሸት እና የማታለል ምልክቶችን** አስተውል። "እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ… ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና" (ዮሐንስ 8፡44)። ብዙ ወሸት እና ማታለል ባለበት ቦታ ብዙ አጋንንታዊ ሥራዎች አሉ።

ብዙ ወሸት እና ማታለል ያለበትን ሀገሮች ተጠንቀቁ! እነዚህ ሀገራት ዲያብሎስ በብዛት የሚገኝባቸው ናቸው። ሰዎች ሳያቋርጡ የሚዋሹበት እና እርስ በእርስ የሚተታለሉበትን አገር ታውቃለህ?

በአንድ ወቅት አንድ ሀገር ለጀማ ስብከት ሄድኩ። ሀገሪቷ በውሸት እና በአታላይነቷ ትታወቃለች። ሌሊት ላይ ሌላ ቦታ አጋጥሞኝ የማያውቅ የዲያብሎስ ውጊያ ተሰማኝ። በጣም ገረመኝ ምክንያቱም ይህቺ ሀገር በክርስትና አንቅስቃሴዋም በጣም ስለምትታወቅ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያረጋግጥ ነበር። ብዙ ወሸት እና ማታለሎች ከአጋንንተዊ ሥራዎች ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።

ማታለል እና ወሸት ካለበት ሥራ ተጠንቀቅ! ሰዎችን በመዋሸት እና በማታለል ሥራ የሚሰራበትን ማንኛውንም ሥራ ታውቃለህ? እንደዚህ ዓይነት ሥራዎች ከጀርባቸው አጋንንታዊ አሰራሮች ጋር የተያያዙ ናቸው! አሳዛኙ ነገር

ፖሎቲካ አብዛኛውን ጊዜ ውሸት መናገር እና ህዝብን ማታለል ነው። ትክክለኛ አካሄድ ባይሆንም ብዙ ፖለቲከኞች ለመመረጥ መዋሸት እንዳለባቸው አድርገው ያስባሉ። አንዱ ሌላውን ለማታላል ሲሞክር የአጋንንቶች መንጋ የፖለቲካውን ዓለም ይወሩታል። ክርስቲያኖች ወደዚህ የፖለቲካው ዓለም ሲገቡ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

## 2. የመግደል ምልክት።

ሰይጣን ነፍሰ ገዳይ ተብሏል፡ **የግድያ ምልክቶችን አስተውለህ እይ።** “እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ… እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ …” (ዮሐንስ 8፡44)

የነፍስ ግድያ የበዛባቸውን ሀገራት አስተውል! በዚያ ሀገር ብዙ የዲያብሎስ ሥራ አለ።

ብዙ ሰዎችን ስለሚገድሉ አስተውል!

ያለ ምንም እፍረት እና በኃይለኝነት ንጹሃን ሰዎችን የሚገድሉትን አስተውል!

ያለ ምንም ምክንያት የሚገድሉ፣ አካል የሚያጎድሉ እና የሚያጠፉ ርህራሄ አልባ ነፍሰ ገዳዮችን አስተውል!

እነዚህ ምክንያተቢስ የሆኑ ተግባሮች የሳይጣን ሥራን ከማጋለጥ ሌላ የሚገልጹት ነገር የለም።

ተከታታይ እና ያልተለመዱ ግድያዎች ሲኖሩ ወዲያውኑ ሰይጣንን ማሰብ አለብህ። የሰዎች በጭካኔ መገደል፣ አንገታቸው መቀላት፣ መሰቃየት ወዘተ፣ ስትሰማ የዲያብሎስን መገኘት ማሰብ አለብህ። ለሰዎች ትርጉም የሌሽ ሞት መንስኤ የሆኑ ብዙ ጦርነቶች እና አብዮቶች ነበሩ። ለምሳሌ ለሃምሳ

ሚሊዮን ሰዎች ሞት ምክንያት የሆነው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ትርጉም የለሽ ጦርነት ነበር። በዚህ ጦርነት ምክንያት በምድሪቷ ላይ የደረሰው አሰቃቂ እልቂት የዲያብሎስ ንቁ እንቅስቃሴ ዓይነተኛ ማሳያ ነው።

## 3. የክስ ምልክት

**ሰይጣን የወንድሞች ከሳሽ ተብሏል፤ በህይወትህ እና አገልግሎትህ የሚያጋጥሙህን የክስ ምልክቶች አስተውለህ እይ።** "ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦ አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና"(ራእይ 12፡10)። ተከታታይ እና ያልተለመዱ ክሶች ባሉበት የሰይጣን ሥራ መሆኑን ማስተዋል አለብህ! በማንኛውም ነገር ላይ ተከታታይ ክሶች እያጋጣሙህ ነው? ምናልባትም የሰይጣን ሥራ እየተጋፈጥከው ነው!

## 4. የተቃውሞ ምልክት

**ሰይጣን ባላጋራችሁ ተብሏል፤ በአገልግሎትህ ውስጥ የሚያጋጥሙህን የተቃውሞ ምልክቶችን አስተውለህ እይ።** "በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና" (1ጴጥሮስ 5፡8)። በህይወትህ እና በአገልግሎትህ ተከታታይ እና ያልተለመዱ ተቃውሞዎች ሲገጥሙህ ወዲያውኑ ስለ ሰይጣን ማሰብ አለበህ። የሚቃወሙህ ኃይላት እና የሚከላከሉህ ሰዎች በሰይጣን የሚታገዙ ናቸው። ብዙ የወንጌል አገልጋዮች የሚዋጋቸው የተቃውሞ መንፈስ ይላክባቸዋል። እነዚህ የተቃውሞ መናፍስት ያዘገዩአቸዋል ነገሮቻቸውንም አስቸጋሪ ያደርጉባቸዋል። በአገልግሎትህ ውስጥ ያለውን ተቃውሞዎች፣ ችግሮች፣ መዘግየቶች እና መሰናክሎችን አስተውለህ

ተመልከታቸው። አብዛኛው የሚያዘገዩህ ነገሮች አጋንንታዊ ምንጭ አላቸው። የሚዋጉህ እና የሚቃወሙህ ሰዎች በዲያብሎስ የታለኩ ናቸው።

## 5. የፈታና ምልክት

**ሰይጣን ፈታኙ ተብሎ ተጠርቷል፤ የፈተና ምልክቶችን አስተውለህ እያቸው።** "ፈታኝም ቀርቦ፦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው" (ማቴዎስ 4:3)። ተከታታይ እና ያልተለመዱ ፈተናዎች ሲያጋጥሙህ የሰይጣን ሥራ አጋንንታዊ ሥራ አስብ። ፈተናዎች የሚጠነሰሱት በዲያብሎሰ ነው። ወደ ህይወትህ ሊፈትኑህ ከሚመጡት አብዛኞዎቹ ሰዎች ጀርባ ሰይጣን አለ።

## 6. የአለመታመን ምልክት

**ኢየሱስም፦ እኔ እናንተን አሥራ ሁለታችሁን የመረጥኋችሁ አይደለምን? ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነው ብሎ መለሰላቸው።**

**ዮሐንስ 6፥70**

የአስቆርቱ ይሁዳ ለጌታው እና ለአለቃው ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ አልነበረም። ማታለል የታማኝ አለመሆን ጥግ ነው። የማይታመኑ እና እምነት የማይጣልባቸው ሰዎች ባሉበት ቦታ አጋንንታዊ እንቅስቃሴዎች አሉ። አጋንንቶች ታማኝ ባልሆኑ እና በአታላይ ሰዎች በኩል ቤተክርስቲያንን ይወርሩ እና ያጠፉታል። የቤተ ክርስቲያን አባላት መሪዎቻቸውን በሚተቹበት እና በሚንቁበት ቦታ በዚያ አጋንንቶች በገፍ አሉ ማለት ነው። ትችት፣ ክስ፣ ማንሾካሾክ፣ ሀሜት እና ስህተት ፍለጋ ባለበት ቦታ በዚያ ብዙ አጋንንቶች ሥራ ላይ አሉ ማለት ነው። ብዙ መጋቢዎች ካለማስተዋላቸው የተነሳ በአንሾካሿኪዎች፣ በስህተት ፈላጊዎች፣ በተቺዎች እና በከሳሾች በኩል አጋንንቶች ሙሉ ሥራ ላይ መሆናቸውን አይረዱትም።

ሰዎቹ ጥሩ ባህሪ የላቸውም ብለው ያስባሉ፡፡ ኢየሱስ “ከእናንተ ውስጥ አንዱ ዲያብሎስ ነው” አለ፡፡ ይህ በሌላ አባባል ከእናንተ ውስጥ አንዱ ይክደኛል ማለቱ ነው፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ ይተቸኛል፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ ከጣለቶቼ ጋር ያማኛል ማለቱ ነው፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ ይጎዳኛል ማለቱ ነው፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ አያመሰግነኝም ማለቱ ነው፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ ያደርግኩላትን ይረሳል ማለት ነው፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ ከውስጥ ይወጋኛል ማለቱ ነው፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ ለትንሽ ገንዘብ ለጠላቶቼ አሳልፎ ይሸጠኛል ማለቱ ነው፡፡

ታማኝ አለመሆን ጠንክረህ የሰራኸውን ሥራ መና የማስቀረት መንገድ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የሚገነቡ ሰዎች አሉ፣ በአንድ ታማኝ ባልሆነ እና አታላይ በሆነ ረዳታቸው ይወድምባቸዋል፡፡

ሰይጣን ቤልሆር ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ዋጋ ቢስ ማለት ነው፤ **የዋጋ ቢስነት ምልክትን አስተውል።** የቤልሆር መንፈስ ወደ አንተ ሲመጣ የለፋህበት አገልግሎትህ ሁሉም መና ይቀራል፡፡ ድካምህን በዜሮ የሚያባዛ እና የሚያንኮታኩት ማንኛውም ነገር አጋንንታዊ ነው፡፡ ምንም፣ ዋጋ የለለህ፣ የማትጠቅም፣ የማትረባ የሚያደርግህ አጋንንት ነው፡፡ ቤልሆር የዋጋ ቢስነት መንፈስ ነው፡፡ መኖርህን እና አስፈላጊነትህን የሚያከሽፍ፣ ባዶ እና ትንሽ የሚያደርገው አጋንንት ነው፡፡

አንድ ማህበረሰብ ራሱን ለአደንዛዥ ዕፅ፣ ለወንጀል፣ ለመጠጥ፣ ለሴተኛ አዳሪ እና ለመሳሰሉት አሳልፎ ሲሰጥ በዚያ ብዙ የአጋንንት መገኘት አለ ማለት ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች የሰውን ልጆች በማሰነስ ዋጋ ቢስ ያደርጋሉ፡፡ ዋጋ ቢስ የሚያደርግህ ነገር ሁሉ ከዲያብሎስ ነው፡፡ ለድህነት፣ ለአደንዛዥ ዕፅ ለወንጀል እና ለመጠጥ ሱስ ተላልፈው የተሰጡ

የሰዎችን ታውቃቸዋለህን? በእንደዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የእርኩሳን ማናፍስቶች አሉ:: እርኩሳን መናፍስቶች የሰውን ልጅ በማሳነስ ዋጋ ቢስ ማድረግ ይፈልጋሉ::

"ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው?..."(2 ቆሮንቶስ 6:15):: ተከታታይ እና አንዳንድ አጋጣሚዎች ህይወትህን ዋጋ ቢስ ማድረግ በሚፈልጉበት ጊዜ የዲያብሎስ ሥራ መሆኑን አስብ:: አንድን ማህበረሰብ ዝቅ እና የማይጠቅም የሚያደርጉ ሁኔታዎች ባሉበት ቦታ የአጋንንት ሥራ እንዳለ አስተውል::

## 7. የአድመኝነት፣ የጭቅጭቅ እና የጦርነት ምልክቶች

> **ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፥ በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን፥ እንዲያስታቸው ከሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው።**
>
> **ራእይ** 20፡7-8

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምታየው ሰይጣን ከእስራቱ እንደተፈታ ህዝቦችን ለጦርነት ይሰበስባል:: የሰይጣን ሥራ የሰው ልጆችን መሰብሰብ እና ለጦርነት ማደራጀት ነው:: አድመኝነት እና ሁከት የዲያብሎስ የመኖሩ ምልክቶች ናቸው:: አጋንንታዊ አሠራር ባለበት ቦታ ሁሉ ጥል፣ አለመግባባት፣ ሁከት እና ማንኛውም የክፉ ሥራ አለ::

> **ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ስራ ሁሉ አሉና።**
>
> **ያዕቆብ** 3፡16

አጋንንቶች አድመኝነትን፣ ጥል እና አለመግባባትን ያነሳሳሉ ለሚባለው እውነታ ቦታ መስጠት አለብህ:: ይህ ግንዛቤ

ከአድመኝነት እንድትርቅ ያደርግሃል። ይህን ግንዛቤ መውሰድህ ከግጭት እና አላስፈላጊ አድመኝነት ለመራቅ እንድትችል ያደርግሃል። በቤተክርስቲያኖች እና በትዳሮች ውስጥ የምታየው አድመኝነት አጋንንቶች የመኖራቸው ምልክት ከሆኑት አንዱና እርግጠኛው ምልክት ነው።

8. **ተፈጥሮዋዊ ያልሆነ ነገር ምልክት። የተፈጥሮ ሕግጋትን ያልተከተለ መሆኑን በማየት የአጋንንት ሥራን መለየት ትችላለህ።**

**ከታንኳይቱም በወጣ ጊዜ፥ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ከመቃብር ወጥቶ ወዲያው ተገናኘው፤ እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር፥ በሰንሰለትም ስንኳ ማንም ሊያስረው በዚያን ጊዜ አይችልም ነበር፤**

**ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበርና ዳሩ ግን ሰንሰለቱን ይበጣጥስ እግር ብረቱንም ይሰባብር ነበር፥ ሊያሸንፈውም የሚችል አልነበረም፤ ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር።**

**ማርቆስ 5፡2 - 5 (አመት)**

የዚህ በርኩስ መንፈስ የተያዘው እብድ ሰውዬ ታሪክ ብዙ ያልተለመዱ፣ ምክንያታዊ ያልሆኑ፣ ተከታታይ ክስተቶች አጋጋንንታዊ ሥር እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። ያልተለመዱ ክስተቶች የዲያብሎስ መገኘትን የሚገልጡ ናቸው። ነገሮች እንዲሄዱ የሚጠበቁበት መንገድ አለ።

ሁላችንም ከአንድ ጤነኛ የሰው ልጅ አንድ የተለመደ ባህሪይ እና ምላሽ እንጠብቃለን። ምንም ትርጉም የማይሰጥ ያልተለመደ ባህሪ ስታይ አጋንንታዊ አሰራር ከጀርባው መኖሩን አስብ። ለምሳሌ የጌርጌሴኖኑ እብድ ሰው በመቃብር መኻል ነበር የሚኖረው። "... እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር ..." (ማርቆስ 5፡3)። ጤነኛ ሰው በተራሮች እና በሞቱ ሰዎች መኻከል አይኖርም። ይህ በመቃብር መኻል የመኖር

ያልተለመደ ፍላጎት የአጋንንቶች መኖርን የሚገልጥ ነው።

በሺህዎች በሚቆጠሩ አጋንንቶች የተያዘው የጌርጌሴኖኑ እብድ ሰው ሰውነቱን በድንጋይ ይቧጭር ነበር። “ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር” (ማርቆስ 5፡5) ። ጤነኛ ሰው ሰውነቱን በድንጋይ አይቧጭርም ምክንያቱም ያማልና። የአንድ ሰው ሰውነቱን በድንጋይ መቧጨር በጣም ያልተለመደ ነው። ጎጂ እና አሉታዊ የሆኑ ያልተለመዱ ነገሮችን ሲታይ እርኩሳን መናፍስት ከጀርባ አሉ።

## 9. የነገሮች ያለማቋረጥ መቀጠል ምልክት። ችግሮች ሳያቋርጡ በመቀጠላቸው የአጋንንትን ሥራ ማየት ትችላለህ።

የነገሮች ያለማቋረጥ የመቀጠላቸው ድግግሞሽ ልብ በል! ያልተለመዱ ክፋቶች ጸንተው ለረጅም ጊዜ መቆየታቸው የአጋንንታዊ አሠራር ምልክት ነው። ኢዮብ በቤተሰቡ፣ በህይወቱ እና በጤናው ላይ የጸና ውጊያ አጋጥሞት ነበር። ኢዮብ ተከታታይ እና የጸና የመጥፎ ዕድል ባለቤት የሆነ ያህል እነዚህ ነገሮች አንዱ ሌላውን ተከትሎ ተፈጸመበት። በኢዮብ ህይወት ላይ የተከሰተው ደርጊት ሁሉ የሰይጣን ቀጥተኛ ጥቃት እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። “እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ እነሆ ለእርሱ ያለው ሁሉ በእጅህ ነው፥ ነገር ግን በእርሱ ላይ እጅህን አትዘርጋ አለው። ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ” (ኢዮብ 1፡12)።

አጋንንቶች የማያቋርጡ እና የጸኑ ናቸው። ሙሉ ጊዜያቸውን አጥፊዎች፣ ፈታኞች እና ከሳሾች ናቸው። የማያቋርጥ እርኩስ መንፈስ ተከታታይ እና የጸና የትንኮሳ፣ የማስፈራሪያ፣ የፈተና እና የችግር ድግግሞሽን ይተዋሉ። ጸንቶ ረጅም ጊዜ በቆየ እና መፍትሄ ባጣ ችግር የምትታወክ ከሆነ ከዚህ ሁሉ ጀርባ ዲያብሎስ እንዳለ ልታውቅ ይገባሃል።

## ምዕራፍ 6

# አጋንንታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዴት ይመረመራል

1. **አጋንንታዊ እንቅስቃሴዎችን በራእይ እና በመገለጥ መመርመር ትችላለህ::**

**እርሱም ታላቁን ካህን ኢያሱን በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ቆሞ አሳየኝ፥ ሰይጣንም ይከስሰው ዘንድ በስተ ቀኙ ቆሞ ነበር።**

**እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ ሰይጣን ሆይ፥ እግዚአብሔር ይገሥጽህ፤ ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሔር ይገሥጽህ፤ በውኑ ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን? አለው።**

**ኢያሱም እድፋም ልብስ ለብሶ በመልአኩ ፊት ቆሞ ነበር። እርሱም መልሶ በፊቱ የቆሙትን፦ እድፋሙን ልብስ ከእርሱ ላይ አውልቁ አላቸው። እርሱንም፦ እነሆ፥ አበሳህን ከአንተ አርቄአለሁ፥ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ አለው።**

ዘካርያስ 3፥1 - 4

እግዚአብሔር ስለ ዲያብሎስ መለኮታዊ መገለጥን የሚሰጥበት ጊዜ አለ:: እግዚአብሔር በራእይ እና በህልም ዲያብሎስ ምን እየሰራ እንዳለ ሊያሳይህ ይችላል:: እንደዚህ ዓይነት መገለጦች እየተጋፈጥክ ያለህው ችግር ላይ ብቻ እንድታተኩር ይረዱሃል::

አንድ ሰው ኃይለኛ ራእይ ያያል በራእዩም ውስጥ የአንድ መጋቢ ሚስት ህይወት ውስጥ እርኩስ መንፈስ እንዴት እየሰራ እንደሆነ ያያል:: በራእይ ውስጥ ይህ እርኩስ መንፈስ ባለትዳሮቹ እንዲፋቱ ያደርጋል:: ደግሞም መንፈሱ ይህቺ ሴት ለባለቤትዋ ታማኝ እንዳትሆንም ያደርጋታል:: ትዳሩ

በመበላሸቱ መጋቢው በህይወቱ እና በአገልግሎቱ ብዙ ችግር ውስጥ ያልፋል። በራእይ ውስጥ በመጋቢው ላይ የደረሰው ሁሉም ትንኮሳ እና ማስፈራሪያ በእርኩሳን መናፍስቶች የተደረጉ ነበሩ!

በራእዩ መሰረት መጋቢው የትዳሩ ችግር የስር መሰረት ምክንያት የሆነውን ለይቶ መጋፈጥ ችሎ ነበር። የዲያብሎስን ስራ ለሚገልጠው ለራእይዎች እና መገለጦች እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!

## 2. በውስጥህ እርግጠኛነት ሲሰማህ የዲያብሎስን እንቅስቃሴ መመርመር ትችላለህ።

**እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፦ ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።**

**ማቴዎስ 16፥23**

ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ዞር ሲል ሰይጣን በእርሱ ውስጥ እያወራ መሆኑን ያውቅ ነበር። ኢየሱስ ራእይ አላየም። ሰይጣን ተመራጩን ደቀ መዝሙሩን እየተጠቀመ ስለመሆኑ በውስጡ እርግጠኝነት ነበረው።

እግዚአብሔር ስለ ዲያብሎስ ስራ በውስጥህ እርግጠኝነት የሚሰጥበት ጊዜያቶች አሉ። እንደዚህ ያሉ የልብ እምነቶች ለማረጋገጥ ይከብዳሉ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ስለ እርኩሰ መንፈስ በሰጠህ የውስጥ እርግጠኝነት በእምነት መመላለስ አለብህ። የውስጥ እርግጠኝነት የራእይን ያህል ኃይለኛ መሆኑን አስታውስ። እኔ ወደ አገልግሎት የመጣሁት በውስጤ ባለ እርግጠኝነት እንጂ በራእይ አልነበረም።

በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስም! እግዚአብሔር በሚያሳይህ ነገር ላይ እምነት ሊኖርህ ይገባል። ሰባት እርኩሳን

መናፍስቶች እየተከታታሉኝ መሆናቸውን የውስጥ እርግጠኝነት ያደረብኝ ጊዜ ነበረ። በልቤ እነዚህ እርኩሳን መናፍስቶች ምን ሊያደርጉብኝ እንደነበር አውቅ ነበረ። የእነዚህ ፍጥረቶች በህይወቴ መገኘታቸው እና ስለ ሴራቸው ጠንካራ የልብ እምነት አጎለበትኩ። ሳላቋርጥ እንዳስታውሳቸው እና እንዳስራቸውም ስም ልሰጣቸው ወሰንኩ። ይህ በህይወቴ እና አገልግሎቴ ላይ ያነጣጠረውን ልዩ ውጊያ የመከላከል አቅም እንዳጎለብት ረድቶኛል።

ምንድነው እየተከታተለህ ያለው? የሚተናኮልህ ምንድነው? ምን ዓይነት የማይቋረጥ ትግል ውስጥ ነህ? ምናልባት በትክክለኛ መንገድ እንድትጋፈጣቸው መንፈስ ቅዱስ የእርኩሳን መናፍስትን ማንነቶች እየገለጠልህ ይሆናል።

## 3. አጋንንት በሰው ውስጥ አልፎ ሲያወራ እንቅስቃሴውን ልትመረምር ትችላለህ።

**እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፦ ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።**

**ማቴዎስ 16፥23**

የጴጥሮስ ድምፅ ነገር ግን የሰይጣን ቃላቶች ነበሩ። የሚናገረው ጴጥሮስ ነበር ነገር ግን ኢየሱስ ከሰይጣን በስተቀር ሌላ ማንም እንዳልሆነ ያውቅ ነበር። ሰው ባወራ ቁጥር መንፈስ ሊያወረ ይችላል። ጴጥሮስ መስቀልን ተቃውሞ ሲያወራ ሰይጣን በእርሱ ሲያወራ እንደ ነበር ኢየሱስ ያውቅ ነበር። ዛሬ በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው ሰይጣን በሰዎች እንደሚያወራ በጠነከረ ሁኔታ ለይተው ማወቅ የሚችሉት። በአንድ ወቅት ትልቁ ስህተቴ በከፍተኛ መጋቢዬ ሚስት ላይ የነበረውን የኤልዛቤል መንፈስ ለይቼ አለማወቁ ነው ካለኝ መጋቢ ጋር አወጋሁ። ይህ መጋቢ ያ ስህተቱ ሥራውን፣

የሥራ መደቡን፣ ገቢውን፣ ህይወቱን እና አገልግሎቱን እንዳሰከፈለው አወጋኝ።

በእውነተኛ የመንፈሰ ቅዱስ መለየት ተሞልተህ ከሆነ መንፈስ ሲያወራ ታውቃለህ።

ምን ማለት ማወቅ እንዳለባቸው እንዳይፈሩ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እዴት እንዳበረታታቸው ታስታውሳለህ? እንዲህም አላቸው "የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁም፤ የአባታችሁ መንፈስ በእናንተ ይናገራል እንጂ"። በሌላ አነጋገር ሳታውቅ መንፈስ በአንተ ሊናገር ይችላል።

**በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፥ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።**

**ማቴዎስ** 10፥20

ቅርብ ጊዜ የሆነ ሰው ሲናገር ሰማሁና ሰይጣን በእርሱ እየተናገረ መሆኑን አወቅኩ። በብዙ ሰዎች ውስጥ አልፎ ሰይጣን ሲናገር ሰምቻለሁ። አንዳንዴ የከሳሹን ድምፅ፣ አንዳንዴ የገዳዩን ድምፅ፣ አንዳንዴ የጥላቻ ድምፅ እሰማለሁ። እነዚህን ድምጾች የምትሰማው ስታውቃቸው ነው። አንድ ቀን የአንድ ወጣት ልጅ ድምፅ ሰማሁ እና ወዲያው የሰይጣን ድምፅ መሆኑን አስተዋልኩ። ልጁ የተናገራቸው ነገሮችን ቀል በቃል አይደለም። ሌላ ሰው እያወራ መሆኑን መናገር ትችላለህ!

# ምዕራፍ 7

# አጋንንቶች እና ሀሳብ መስጠታቸው

**የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤**

**የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥**

2ኛ ቆሮንቶስ 10፥4-5

አጋንንቶች ሳያቋርጡ በሰው አእምሮ ሀሳብ ያስገባሉ። መጥፎ ሀሳብ ወደ አንተ ከመጣ እርከሳን ማናፍስት ወደ አንተ መጥተዋል ማለት ነው። ሀሳብ የመንፈስ መገኘትን ያሳያል። *አጋንንቶች ሳያቋርጡ ለአእምሮህ ሀሳብ ይሰጣሉ።*

ከሁሉም የሚበልጠው መንፈሳዊ ውጊያ የሚገጥምህ በአእምሮ ሀሳብ ውስጥ ነው።

ከሁሉም የሚበልጥ መንፈሳዊ መሞላት የሚሆንልህ በአእምሮ ውስጥ ሀሳብን ማስገባት ነው።

ከፍተኛው የዲያብሎስ መኖር ምልክቱ መጥፎ ሀሳብ ወይም አስተያየት ነው። መጥፎ ሀሳቦች ከመጥፎ መናፍስት ጋር የመነካካት ውጤት ነው!

# መንፈስ ቅዱስ እና ሀሳብ መስጠቱ

መልካም ሀሳቦች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የመገናኘት ውጤት ነው!

የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ትልቁ ምልክት መልካም ሀሳብ ወይም አስተያየት ዋነኛው ነው።

ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሰጠው ተስፋ አብዛኛው ሰው የሚያስበው የሰዎችን መውደቅ እና የአውሎ ንፋስ ድምጽ ነው። የአውሎ ንፋስ ድምጽ እና የሰዎች መውደቅ ተከስቶ የነበረው መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ የመጣ ጊዜ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ የነገረን መንፈስ ቅዱስ ሀሳብን ወደ አእምሮአችን እንደሚያመጣ ነው።

**አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል (ሃይፖሚምኔስኮ) ።**

**ዮሐንስ 14፥26**

ሀሳቦች መንፈስ የመገኘቱ መለያ እና ምልክቶች ናቸው። የአይጥን ዓይነምድር በክፍልህ ውስጥ የማየት ዓይነት ማለት ነው። የአይጥዋን በዚያ መኖርዋን ለማወቅ አይጥዋን ማየት አይኖርብህም። መሬት ላይ ያየሃቸው ዓይነምድሮች የመኖሯ ምልክት ናቸው።

መገለጦች የሆኑ ሀሳቦች የመንፈስ ቅዱስ መገኘትን ያመላክታሉ። ጥቅሱን አንብብ፡ “አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል(ሃይፖሚምኔስኮ)” (ዮሐንስ 14:26)።

# ሃይፖሚምኔስኮ፡ ሀሳቦችን ወደ ውስጥ ማስገባት(ማስረጽ)

**አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል (ሃይፖሚምኔስኮ) ።**

**ዮሐንስ 14፥26**

"ሃይፖሚምኔስኮ" ማለት የሀሳቦችን ወደ ውስጥ ማስገባት ማለት ነው።

"ሃይፖሚምኔስኮ" ማለት የሆነ ነገር አዕምሮህ ውስጥ ማድረግ ነው።

"ሃይፖሚምኔስኮ" አንድን ነገር እንድታስታውስ ማድረግ ነው።

"ሃይፖሚምኔስኮ" አንድን ሰው ማስታወስ ነው።

የሆነ ነገር በአእምሮህ ውስጥ ማስቀመጥ በማንኛውም መንፈስ ሊሰራ የሚችል ነው። *ለዚህ ነው ልታገኘው የምትችለው ዋነኛው መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ በአእምሮህ ውስጥ የሆነ ሀሳብ ማግኘት ነው።* ለአእምሮህ ሀሳብ የመስጠት ሥራ በማንኛውም መንፈስ ሊደረግ ይችላል። ስለዚህ ከመንፈስ ጋር የቀረበ ግንኙነት የሚኖርህ የሆነ ሀሳብ በአእምሮ ውስጥ እንዲቀመጥ ነው። የሆነ ነገር ወደ አእምሮህ ማስረጽ በመንፈስ ቅዱስ ሊደረግ ይችላል።

የሆነ ነገርን ወደ አእምሮህ ማስረጽ ማለት ሃይፖሚምኔስኮን መለማመድ ነው።

ሁለት ዓይነት ሃይፖሚምኔስኮዎች አሉ። ሁለት ዓይነት የሀሳብ ስጦታዎች ወደ ማንኛውም ሰው አእምሮ ይመጣሉ።

አንዳንዶቹ ይሰጡና እና በቀላሉ የሚታወቁ ቀጥተኛ ሀሳቦች ናቸው። እነዚህ የሚሰጡ እና በቀላሉ የሚታወቁ ቀጥተኛ ሀሳቦች አደገኞች ነገር ግን ደግሞ በቀላሉ የሚለዩ ናቸው።

አንዳንድ የሚሰጡ ሀሳቦች ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆኑ፣ የማይታወቁ፣ ቀስ በቀስ የሚቆጣጠሩ አስተሳሰቦች እና እምነቶች ናቸው። እነዚህ የሀሳብ ስጦታዎች ደግሞ በእርግጥ እጅግ አደገኞች ናቸው!

የቆዩ ሀሳቦች እና ልማዶች የረጅም ጊዜ የመንፈስ ተጽዕኖ ማሳያዎች ናቸው። ፈላስፎች ሀሳብን፣ አስተሳሳብን እና ልማድን ወደ ዓለም የሚያስገቡ እና የሚያከፍሉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች የሚዛመት አስደናቂ አስተሳሰቦች እና ልማዶችን ወደ ዓለም ሊለቁ ይችላሉ።

ስመጥር የአስተሳሰብ እና ሀሳብ የማካፈል ዓይነተኛ ምሳሌዎች ዳርዊን እና ሮበርት ኢንጌርሶል የሚባሉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች በጣም ለተዛመተው እና ቀስ በቀስ አውሮፓን ለተቆጣጠረው በምንም የማያምን እና ሰብዓዊነት ይተቻሉ። (ሰብዓዊነት ሰዎች በእግዚአብሔር የማመን አስፈላጊነትን በመተው ሰብአዊ አመክንዮት፣ ሰብአዊ ምሉእነት፣ ሰብአዊ ስኬት፣ ሰብአዊ ሳይንስ ላይ እንዲያተኩር የሚያስረግጥ የአስተሳሰብ መስመር ነው)።

ቤተክርስቲያንን ያጥለቀለቀው፣ የተቆጣጠረው እና ቀስ በቀስ የታዘመተው የታማኝ አለመሆን ባህል የሆነ ኃይለኛ እርኩስ መንፈስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከትን፣ አለመደሰት፣ ሽንጋይነት፣ ማንሾካሾክን እና አለመታመንን የሰጠ መኖሩን የሚያሳይ ነው። የረከሰውን ነገር የመቀበል ባህል በዓለም ሁሉ ማዛመቱ እርኩሳን መናፍስት በሁሉም ቦታ የመገኘታቸው ማሳያ ነው።

አንዳንድ ቦታዎች ላይ በባለስልጣናት ላይ የማመጽ የተበከለ ባህል አለበት። ፕሬዝዳንታቸውን ጨምሮ ማንኛውንም መሪ ይሳደባሉ እንዲሁም ምንም እንዳላደረጉ ሆነው ይቀጥላሉ። በእንደዚህ ዓይነት ቦታ ምን መድረግ እንዳለበት ለሰው የመንገር ሀሳብ ዘበት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ባለመታዘዝ እና ባለመከባበር አመጽ የተበከለ ባህል የሆነ የሚያስፈራ እርኩስ መንፈስ አንድን ሀሳብ እና ጠባይ ለብዙኃኑ ስለማካፈሉ ማስረጃ ነው።

የእግዚአብሔር ፍቅር የተስፋፋበት፣ ለእግዚአብሔር ሥራ ፍቅር የተስፋፋበት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ታላቅ እምነት እና ለወንጌል ለመናገር ያለ ታላቅ ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ምልክት ነው። መንፈስ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ሀሳብ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያስገባል። ከዓመታት በፊት ለእግዚአብሔር ፍቅር ራስን አሳልፎ የመስጠት ባህል እንደነበርህ ታስታውሳለህ። ስለ መስቀሰሉ ያለህ ሃሳብ መቀነሱ እና ህይወትህን ለኢየሱሰ አሳልፈህ የመስጠቱን ሀሳብ ማጣትህ መንፈስ ቅዱስ ማጣትህን ያሳያል።

# ሰዎች ሀሳብ ሊሰጡህ ይችላሉ

**ሀሳብን ወደ አእምሮህ ማስገባት በሰዎች በኩል ሊደረግ ይችላል፤**

> **አላቸውም፦ ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ። በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል ለእናንተም ይጨመርላችኋል።**
>
> ማርቆስ 4፥24

# መንፈስ ቅዱስ ሀሳብ ሊሰጥህ ይችላል

**ሀሳብን ወደ አእምሮ ማስገባት በመንፈስ ቅዱስ ሊደረግ ይችላል፤**

**አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።**

**ዮሐንስ 14፥26**

# መላእክቶች ሀሳብ ወደ ውስጥህ ሊስገቡ ይችላሉ

**ሀሳብን ለአእምሮ መስጠት በመላእክቶች ሊደረግ ይችላል፤ መገለጥ በመላእክቶች ሊሰጥ ይችላል።**

**ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ።**

**ራእይ 1፥1**

# አጋንንቶች ሀሳብ ሊሰጡህ ይችላሉ

**አጋንንቶች ለአእምሮህ ሀሳብ ሊሰጡህ ይችላሉ፤**

**የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን።**

**2ኛ ቆሮንቶስ 10፥5**

# ምዕራፍ 8

# አጋንንታዊ ሥራዎች እና ሴራዎች

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ አጋንንታዊ ሴራዎችን እና ሥራዎችን ትመለከታለህ:: አጋንንታዊ ሥራ አጋንንት በአንተ ላይ የሚያረደረገው እንቅስቃሴ ማለት ነው:: ሰይጣን በተለያዩ ሰዎች ላይ የተለያዩ ነገርችን ማድረግ ይሻል:: አንዳንዴ ይጨቁናል:: አንዳንዴ ደግሞ ይይዛል! አንድን ሰው መያዝ ማለት ያን ሰው ሙሉ በሙሉ የራስ ማድረግ ማለት ነው:: አንዳንዴ ዲያብሎስ ሰዎችን የራሱ አያደርግም ነገር ግን ክፉ ሥራ እንዲሰሩ ያስታቸዋል::

ሌላ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ውስት ይገቡ እና ከዚያ ሰው ጋር ተዋህደው በአጋንንት የተበረዘ ሰው ይሆናሉ:: እነዚህ የሰው እና የአጋንንቶች ዲቃላዎች የአጋንንቶች ሰውን ዘር በክፉ መንፈስ የመበረዝ ውጤት ናቸው::

በእርግጥ መልካም ሰዎች መለኮታዊ በሆነ ሁኔታ ለተከታታይ አጋንንታዊ ትንኮሳዎች የሚጋለጡበት ጊዜያቶች አሉ:: እነዚህ ተከታታይ ትንኮሳዎች አጋንንታዊ ግርፋት ይባላሉ::

1. **አጋንንታዊ ጭቆና**

**እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ከዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና።**

**የሐዋርያት ሥራ** 10፥38

አጋንንታዊ ጭቆና ህመም እና በሽታ ነው! ሁሉም በሚባልበት ሁኔታ በሽታዎች የአጋንንታዊ ጭቆና ውጤቶች ናቸው:: አንድን ሰው መጨቆን ማለት አንድን ሰው በብርቱ መቆጣጠር ማለት ነው:: አጋንንታዊ ጭቆና የሰው ልጆችን በአጋንንታዊ ሸክም እና አሰቃቂ ችግሮች መቆጣጠር ማለት ነው:: አጋንንታዊ ጭቆና አንድ ሰው በከባድ የበሽታ ሸክም ስር ሲሆን ማለት ነው::

## 2. በአጋንንት መያዝ

አጋንንት ያደረበት ማለት አጋንንት ሙሉ በሙሉ አንድን ሰው መቆጣጠር ሲችል ማለት ነው:: ራሱን እካልተቆጣጠርክ ድርስ አንድን ሀገር፣ አንድን ሰው ወይም አንድን ድርጅት መቆጣጠር አይቻልም:: አጋንንት ያደረበት የሚባለው አጋንንቶች የዚያን ሰው ራስ፣ ጭንቀላት ወይም አዕምሮ መቆጣጠር ሲችሉ ነው::

አጋንንቶች አንድን ሰው ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠሩት የራሳቸው አድርገው ደስ ያላቸውን ነገር እንዲያደርግ ያደርጉታል:: አጋንንት ያደረበት ሰው የህክምና ባለሙያዎች ስኪዞፌሬኒያ/ Schizophrenia/ ብለው የሚጠሩት ዓይነት ልዩ ምልክቶች ይታዩበታል:: አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ እብድ ሲሆን አጋንንት አድሮበታል ማለት ነው:: እነዚህ አጋንንቶች ይህን ያበደ ሰው ይከሱታል፣ ይሰድቡታል፣ ይመሩታል:: እብዶች ልብሳቸውን ያወልቃሉ፣ ከእውነታ ጋር ይለያያሉ፣ ኃይለኞች በመሆን ሙሉ በሙሉ ወደ እንስሳነት ይቀየራሉ:: በእብድ ሰው ውስጥ ዲያብሎስ እድሉን ቢያገኝ ምን ሊያደርግብህ እንደሚወድ ማየት ትችላለህ:: አጋንንቶች ወደ አንተ እንዳይገቡ ማድረግ የሚገባህን ሁሉ ማድረግ አለብህ:: አጋንንቶች በአንድ ሰው ውስጥ ከገቡ ሙሉ በሙሉ ሊያድሩበት እና ሊረከቡት ይፈልጋሉ::

**ወደ ኢየሱስም መጡ፥ አጋንንትም ያደሩበትን ሌጌዎንም የነበረበትን ሰው ተቀምጦ ለብሶም ልቡም ተመልሶ አዩና ፈሩ። ያዩት ሰዎችም አጋንንት ላደሩበት ሰው የሆነውንና ስለ እሪያዎቹ ተረኩላቸው።**

**ማርቆስ 5፡15-16**

3. *አጋንንታዊ ማሳቻ*

**መንፈስ ግን በግልጥ፦ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው...**

**1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1**

ማሳቻ በአጋንንቶች ወደ መቅበዝበዝ መመራት ማለት ነው:: ማሳቻ ሆን ብሎ አንድን ሰው የማማለል ሂደት ነው! ማሳት ማለት አንድን ሰው በግንኙነት ውስጥ በማስገባት ወደ መቅበዝበዝ መምራት ማለት ነው:: አሳቺ መንፈሶች ከሥራህ እና ትክክል ከሆነው ነገር ይለዩሃል:: አሳቺ መንፈስ ሊያበላሽ ወይም ኃጢያት በሆነው ወሲባዊ ግንኙነት ውስጥ እንድትገባ ያግባባሃል:: አሳቺ/ሴዳክሽን/ ማላት በላቲን ቋንቋ ወደ መቅበዝበዝ ህይወት መምራት ማለት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያስቱ መናፍስቶች በግልጽ ይናገራል:: እነዚህ መናፍስቶች ከአንተ ጋር ውይይት በማድረግ ውሸት የሆነውን እንድታምናቸው ሊያግባቡህ ይሞክራሉ:: በአጋንንት ተታለው፣ ተደልለው በመጨረሻም የጠፉ የብዙ ሰዎች ምሳሌዎች አሉ:: ሔዋን ወደማይረባ መንገድ የሄደችው በአጋንንት ስለ ተሳሳተች ነበር:: አክአብ ወደ ጥፋቱ የተመራው በእርኩስ መንፈስ ነበር:: ማሳሳት በጣም አደገኛው የዲያብሎስ ሴራ ነው ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ከመመራት ይልቅ ወደ ጥፋት መንገድ ይመራሃልና::

# ሔዋን ስታለች

የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች።

1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥14

እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት። ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፦ በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት፦ ሞትን አትሞቱም።

ዘፍጥረት 3፥1-4

# አክአብ ስቷል

እግዚአብሔርም፦ ወጥቶ በሬማት ዘገለዓድ ይወድቅ ዘንድ አክዓብን የሚያሳስት ማን ነው? አለ። አንዱም እንዲህ ያለ ነገር፥ ሌላውም እንዲያ የለ ነገር ተናገረ።

መንፈስም ወጣ በእግዚአብሔርም ፊት ቆሞ፦ እኔ አሳስተዋለሁ አለ።

1ኛ ነገሥት 22፥20-21

ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።

2ኛ ተሰሎንቄ 2፥11-12

# ሰይጣን ኢየሱስን ለማሳት ሞክሯል

ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፥ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ።

ፈታኝም ቀርቦ፦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው።

**እርሱም መልሶ፦ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።**

**ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ወደ ቅድስት ከተማ ወሰደውና እርሱን በመቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ፦**

**ማቴዎስ** 4፥1-4

## 4. አጋንንታዊ ጊዜያዊ ቅጥር

አጋንንታዊ ጊዜያዊ ቅጥር ማለት ሰይጣን ሰዎችን በጊዜያዊነት ተጠቅሞ ሲያወራህ ማለት ነው:: ሰይጣን ሰዎችን ተጠቅሞ ሲናገር ድምጹን መለየት መቻል አለብህ:: የኢየሱስ ከፍተኛ ራዳት የነበረው ሐዋውያው ጴጥሮስን በጊዜያዊነት ተጠቅሞ ክርስቶስን ለማውራት ሞክሮ ነበር:: ማንም ራሱን የሰጠ ሰው የሰይጣን ድምጽ ሊሆን ይችላል:: ሴቶች በጊዜያዊነት በዲያብሎስ ስለመጠቀማቸው ጢሞቴዎስ እና ቲቶ ማስጠንቀቂያ ተስጥቷቸው ነበር:: የመጋቢዎች ሚስቶች እና አሮጊቶች ሰም አጥፊ እና የውሸት ከሳሾች ሲሆኑ በጊዜያዊነት የዲያብሎስ ቅጥር ሆነዋል::

**ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ፦ አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።**

**እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፦ ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።**

**ማቴዎስ** 16፥22-23

**እንዲሁም ሴቶች ጭምቶች፥ የማያሙ (ዲያቢሎስ) ፥ ልከኞች፥ በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል።**

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥11

**እንዲሁም አሮጊቶች ሴቶች አካሄዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የሚገባ፥ የማያሙ (ዲያቢሎስ) ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ፥ በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ።**

**ቲቶ** 3፥11

## 5. *አጋንንታዊ መግቢያ*

አጋንንታዊ መግቢያ ዲያብሎስ ወደ ሰው ሲገባ ነው:: አብዛኛውን ጊዜ ይህ የሚሆነው ዲያብሎስ የሆነ ሰውን ሲያባብል እን ሲተናኮስ ለተወሰነ ጊዜ ከቆየ በኋላ ነው:: አጋንንታዊ መግቢያ ለብዙ ዘመናት ሲሻ የነበረው ትልቁ ጥሶ መግባት ነው:: ሰይጣን አንድ ሰው ውስጥ ሲገባ በዚያ ሰው ውስጥ በመኖሩ የባሰ ክፋት መፈጸም ይችላል:: ይሁዳ ውስጥ በገባ ጊዜ የኢየሱስ ክርስቶስን ግድያ ፈጽሟል::

**ሰይጣንም ከአሥራ ሁለቱ ቍጥር አንዱ በነበረው የአስቆሮቱ በሚባለው በይሁዳ ገባ፤ ሄዶም እንዴት አሳልፎ እንዲሰጣቸው ከካህናት አለቆችና ከመቅደስ አዛዦች ጋር ተነጋገረ።**

**ሉቃስ** 22፥3-4

**ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎችን አጋንንት ከእርሱ ጋር ይወስዳል፥ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል። ለዚህ ክፉ ትውልድ ደግሞ እንዲሁ ይሆንበታል።**

**ማቴዎስ** 12፥45

## 6. *አጋንንታዊ ውህደት*

አጋንንታዊ ውህደት እርኩሳን መናፍስትን እና የሰው ልጆችን ቀላቅሎ ከሰውም የሚልቅ እና ዲቃላ መፍጠር ነው:: የሰው ልጆችን ከመንፋስ ጋር ቀላቅሎ ዲቃላ መፍጠር በቤተ ክርስቲያን የሚታወቅ ጽንሰ ሃሳብ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ማርያም ላይ በመውረዱ ነው:: ማርያም ሰው ነበረች መንፈስ ቅዱስ ደግሞ መንፈስ

ነው::

ረጅሙ የእርኩሰት ታሪክ የሚያረጋግጠው የሰው ልጆች ከእርኩስ መንፈስ ጋር ተቀላቅለው በዘመናት ውስጥ የበለጠ እርኩስ መፍጠራቸውን ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሰዎች ከዲያብሎስ ጋር መቀላቀላቸውን የሚያረጋግጥ ክፍል አለው:: የሄኖክ መጽሐፍም ይህን ያስተምራል::

**የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ከራሳቸው ወሰዱ። እግዚአብሔርም፦ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፥ እርሱ ሥጋ ነውና፤ ዘመኖቹም መቶ ሀያ ዓመት ይሆናሉ አለ። በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥2 - 4**

## 7. አጋንንታዊ ጉሰማ

አጋንንታዊ ጉሰማ ዲያብሎስ ለልዩ ዓላማ ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ ሰው ነጻ መተላለፊያ ሲያገኝ ነው:: እግዚአብሔር የራሱን ልጆች እንዲያሰቃዩ ዲያብሎስን እንደ መላክ ነው::

ኢዮብ ይህንን በአስከፊ መንገድ ተለማምዶታል:: እንዲህ ዓይነቱ ጉስሚያ ህመምን፣ ሞትን፣ ዝርፍያን እና አሳዛኝ ነገሮችን የሚያመጡ ናቸው:: ሰይጣን ኢዮብን አንዲፈትነው እንጂ እንዲገድለው አልፈቀደለትም::

ሐዋርያው ጳውሎስ የሰይጣንን ጉስሚያ ክስተቶችን ተለማምዷል:: ትሁት ሆኖ እንዲቀጥል እርኩስ መንፈስ እንዲጎስመው ፈቃድ ተሰጠው::

# ጳውሎስ እና አጋንንታዊ ጉስሚያ

**ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው። ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ።እርሱም፦ ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ። እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ።**

2ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 - 9

# ኢዮብ እና አጋንንታዊ ጉስሚያ

**እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም፤ በከንቱም አጠፋው ዘንድ አንተ በእርሱ ላይ ምንም ብታንቀሳቅሰኝ፥ እስከ አሁን ፍጹምነቱን ይዞአል። ሰይጣንም መልሶ እግዚአብሔርን፦ ቍርበት ስለ ቍርበት ነው፤ ሰው ያለውን ሁሉ ስለ ሕይወቱ ይሰጣል። ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ አጥንቱንና ሥጋውን ዳብስ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል አለው። እግዚአብሔም ሰይጣንን፦ ሕይወቱን ተወው እንጂ እነሆ፥ እርሱ በእጅህ ነው አለው። ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፥ ኢዮብንም ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቍስል መታው።**

ኢዮብ 2፡3 - 7

# *ምዕራፍ 9*

# አጋንንታዊ ማባበል

***መንፈስ ግን በግልጥ፦ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች* የሚያስቱ መናፍስትንና *በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን* ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው፥**

1ኛ ጢሞቴዎስ 4፥1

*ከዲያብሎስ ጋር ስትወያይ እውነት ያልሆነውን እንድታምን ትማለላለህ:: ዲያብሎስ በጣም ሲቀርብህ በሀሳብ የመዋዠቅ ሂደት ውስጥ ትገባለህ:: በዲያብሎስ የመሳት ውጤቱ የሚገርም ነው:: ለማውራት ፈቃደኛ የሆነውን ማንኛውንም ሰው ለማሳት ዲያብሎስ ተዘጋጅቶ ይጠብቃል:: ሔዋን በሰይጣን ስታ ጠፍታለች:: አክዓብ በእርኩስ መንፈስ ስቶ ሞቷል:: ሰይጣን ኢየሱስንም ለማሳት ሞክሮ አልታሳካለትም:: ሰይጣን ሁሌም አሳስቶ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሊያርቅህ ይሞክራል::*

## *ሔዋን ስታለች*

**የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች።**

1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥14

**እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት። ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፦ በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፦**

እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት፦ ሞትን አትሞቱም።

ዘፍጥረት 3፥1-4

## አክአብ ስቷል

እግዚአብሔርም፦ ወጥቶ በሬማት ዘገለዓድ ይወድቅ ዘንድ አክዓብን የሚያሳስት ማን ነው? አለ። አንዱም እንዲህ ያለ ነገር፥ ሌላውም እንዲያ የለ ነገር ተናገረ።

መንፈስም ወጣ በእግዚአብሔርም ፊት ቆሞ፦ እኔ አሳስተዋለሁ አለ።

1ኛ ነገሥት 22፥20-21

ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።

2ኛ ተሰሎንቄ 2፥11-12

## ሰይጣን ኢየሱስን ለማሳት ሞክሯል

ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፥ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ።

ፈታኝም ቀርቦ፦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው።

እርሱም መልሶ፦ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።

ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ወደ ቅድስት ከተማ ወሰደውና እርሱን በመቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ፦

ማቴዎስ 4፥1-4

## የአጋንንታዊ ማታለል ውጤቶች

ከዲያብሎስ ጋር አጭር ውይይት ወደ መታላል

ይመራሃል። እርኩሳን መናፍስቶች ሰዎችን የማውደም እና የመበከል ተጽዕኖ አላቸው። የእርኩስ መንፈስ መኖር ሰውየውን ባልተጠበቀ ሁኔታ ይቀይረዋል። ስልጠናውን ወስደህ ከሆነ ሰዎች ከዲያብሎስ ጋር ግንኙነት እንዳለቸው መናገር ትችላለህ። አጋንንቶች በሰው ህይወት ላይ ሊያመጡ የሚችሉትን ተጽዕኖ ለማወቅ ጥሩ መንገድ በአዳም እና ሔዋን ህይወት ላይ ያደረሱትን ተጽዕኖ መመርመር ነው።

ከሰይጣን ጋር የተደረገው አጭር ውይይት ቅድመ አያቶቻችንን ለዘላለም ለውጧቸዋል። አዳም እና ሔዋን ከሰይጣን ጋር ያደረጉት አጭር ቆይታ የሰውን ዘር ሁሉ ለዘላለም ቀይሮታል። ከዲያብሎስ ጋር የምታደርገው ማንኛውም ቆይታ ህይወትህን ባላሰብከው መልኩ ይቀይረዋል። ከዲያብሎስ ጋር የሚደረገው ማንኛውም ቆይታ የእርሱን ማንነት እና ባህሪያት ተካፋይ ወደ መሆን ይመራሃል። ከእርሱ ጋር በመቆየት የሰው ባህሪ ራሱ የሚለወጥ ይመስላል። ውይይቱ የሚዘልቅ ችግር ጥሎ የሚያልፍ ይመስላል። የአዳም እና ሔዋን በሰይጣን የመታለል አውዳሚ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?

## 1. አጋንንታዊ ማታለል የመሸሸግ አባዜ ያስከትላል

**እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።**

**ዘፍጥረት 3፥8**

ከሰይጣን ጋር ከነበራቸው ቆይታ በኋላ አዳም እና ሔዋን የሰጡት ምላሽ በዛች መኻከል መደበቅን ነበር። በብዙሃኑ መኻል መደበቅ ፈለጉ። ከዛፎቹ በአንዱ ተመስለው እግዚአብሔር እንደያየቸው ተመኙ። ተደባልቀው የማይታወቁ ለመሆኑ ፈለጉ።

ምንም የማይናገሩ ዝምተኞች እና ከዛፍ ጀርባ የሚደበቁ ሰዎችን ልብ በል። በሆነ ክፉ ነገር የተጠቁ ናቸው። ዛሬ ብዙ ሰዎች የመደበቅ አባዜ አለባቸው። አንዳንድ ሰዎች እንዴት ከኋላ መቀመጥ እና በቤተክርስቲያን መታየት እንደማይፈልጉ ታስተውላለህ።

"በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበርክ?"

"አዎ እዛጋ ነበርኩ እኮ"

"ግን አላይሁህም እኮ።"

"አይ እዚያጋ ነበርኩ።"

ከእንደዚህ የተደበቁ አባላት ጋር የሚኖርህ ቆይታ ይህን ይመስላል።

ከጀርባ ተደብቀው ይቆዩና መጨረሻ ላይ አምልኮ ሲያልቅ ለሰላምታ ብቅ ማለት ይፈልጋሉ። ሰው ከጀርባ የሚደበቅበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። መጥፋት፣ መደበቅ እና ድብቅ መሆን የአጋንንታዊ ጥቃት ምልክቶች ናቸው። በሌላ በኩል ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሲነኩ ደግሞ ፊት ለፊት መቀመጥ ይፈልጋሉ። በደስታ፣ ፍንድቅድቅ እያሉ እና ሆነ ብለው ፈገግ ይሉልሃል። ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ያናግሩሃል፣ ራሳቸውንም በደስታ ከአንተ ጋር ያዛምዳሉ።

መነጋገር እና ከሰው ጋር ራሳቸውን ማቀራረብ ባህላችን ይከለክላል የሚሉትን ሰዎች ልብ በል።

የመደበቅ አባዜ በግልጽነት መቀየር አለበት። ራስህን ለመሆን፣ ግልጽ ለመሆን፣ ተጋላጭ ለመሆን እና ለመታወቅ ወስን። ይህ ሰይጣን ከህይወትህ የሆነ ነገር አለማርከሱን፣ አለማበላሸቱን እና አለማጥፋቱን የሚያሳይ ነው።

## 2. አጋንንታዊ ማታለል ፍርሃትን ያስከትላል

**እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው።**

**እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም።**

**ዘፍጥረት** 3፥9 - 10

ሁሉንም ነገር የሚፈሩትን ልብ በላቸው! ፍራቻ መንፈስ ነው! ፍራቻ ድባብ፣ ጠባይ ወይም ስሜት አይደለም! ፍራቻ እርኩስ መንፈስ ነው! በዲያብሎስ የተጠቁ ሰዎች ሁሉም ነገር ፍራቻ አላቸው:: የማይታወቅ ፍርሃት! የነገ ፍርሃት! የሰዎች ፍርሃት! የሴቶች ፍርሃት! የሞት ፍርሃት! የድህነት ፍርሃት!

እነዚህ ህይወትህን ከሚያጠቁት ፍርሃቶች ውስጥ ትንሾቹ ናቸው:: ትንሽ ልጅ እያለህ ምንም ነገር እንደማትፈራ አስታውስ! በዚህ ዓለም ላይ እያደግክ መጥተህ ከዲያብሎስ ጋር መነካካት ስትጀምር የተለያየ ፍርሃቶችን እያዳበርክ መጣህ:: ፍርሃት እርኩስ መንፈሰ ነው! ፍርሃት ጸባይ ወይም ድባብ አይደለም:: ፍርሃት ጎጂ በመሆኑ ዳዊት ከፍርሃት ነጻ ለመውጣት ጸልዮአል::

**እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም፥ ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ።**

**መዝሙር** 34፥4

በድህነት ፍርሃት የሚመሩ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ብዙ ህገ ወጥ ነገሮችን ያደርጋሉ:: ብዙ ሴቶች ቆሞ ቀር መሆንን ከመፍራት የተነሳ ያገባሉ:: እንደዚህ ዓይነት ትዳር ከመሰረቱ እርኩስ መንፈስ ያለበት ነው:: ማግባት ያለብሽ ከፍቅር መሆን አለበት! እውነተኛ ፍቅር ፍርሃትን ያስወግዳል ስለዚህ ፍርሃት ለፍቅር በጣም ደካማው ምትኩ ነው::

## 2. አጋንንታዊ ማታላያ ለአንድ ነገር ከሚገባ በላይ ንቁ እንዲሆን ያደርጋል

**እግዚአብሔርም አለው፦ ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?**

**ዘፍጥረት 3፥11**

አዳም እና ሔዋን ራቁታቸውን ስለመሆናቸው ነቁ:: ራቁትነት ከእነርሱ ጋር የቆየ ነገር ነበር::

የሚደበቁ አካሎቻቸው እና ኀፍረተ ሥጋቸው ከእነርሱ ጋር ወዲህ እና ወዲያ በነፃነት ለዘመናት ይወዛወዝ ነበር:: ከዲያብሎስ ጋር ከነበራቸው ቆይታ በኋላ ግን ድንገት ስለ ኀፍረተ ሥጋቸው ወደ ማወቅ መጡ:: አንዳንድ ነገሮችን የመንቃት ጉደይ ከዲብሎስ ጋር ቆይታ የማድረግ ምስጢር ማሳያ ነው:: ዛሬ ስለ ብዙ ነገር መንቃታችን ከዲያብሎሰ ጋር ቆይታ እንደ ነበረን ወይም የእነርሱ ተፅዕኖ እንዳለብን የሚገልጡ ናቸው::

በአንዳንድ የዓለማችን ክፍል ላይ ሰዎች ስለ ቀለም ብዙ ንቃት አላቸው:: አንተ ነጭ ነህ፣ ጥቁር ነህ፣ ቢጫ ነህ ወይም አረንጓዴ ነህ? አንዳንድ ሰዎች ስለ ቀለም ብዙ ስለ ነቁ ሌላ ቀለም ላለው ሰው ደንታ የላቸው:: ሰውን በምድራች ላይ ወደ ተፈጸሙት የክፋት ሥራዎች ሁሉ የመራው ስለ ቀለም ያለው ንቃት ነው:: የቆዳ ቀለሜን ካወቁ መጽሐፌን የማያነቡ ብዙ ሰዎች አሉ:: እንደዚህ ዓይነት የቀለም ንቃት በእርግጥ አጋንንታዊ ነው:: በአንድ ወቅት ነጮችም ጥቁሮችም በሚኖሩባት በአንድ አገር ክሩሴድ ነበረን:: በክሩሴዱ እንዲሳተፍ ግብዣ ያደረግንለት መጋቢ ፈገግ አለ እና ለክሩሴዱ ዳይሬክተር እንዲህ አለ “ልትጋብዙን ስለደፈራችሁ በጣም አደንቃችኋለሁ:: ይሁን እንጂ ክሩሴዱ በጥቁር ስለተዘጋጀ የእኛ ነጭ የቤተክርስቲያን አባሎቻችን

አይሳተፉም"። አቤት ምን ዓይነት አስደንጋጭ ነው! ሌላ ጊዜ አንድ ነጭ አሜሪካዊ ያዘጋጀው ክሩሴድ ላይ የእነዚህን ነጭ መጋቢዎች እና ነጭ የቤተ ክርስቲያን አባላት በብዛት መገኘትን ለማየት ቻልኩ።

በብዙ ሀጋራት የተለያዩ ብሔሮች መኖራቸውን ብዙ ሰዎች አይነቁም። ይሁን እንጂ ከምርጫ በኂላ ግን የተመረጠው ሰው የየትኛው ብሔር ስለ መሆኑ ብዙ ንቃቶች መነሳት ይጀምራሉ። ይህ ከየትኛው ብሔር መሆንህን መንቃት የሚገልጠው የዲያብሎስ መኖርን ነው። የብሔር ጉዳይ የሚያስነሳ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የአጋንንት ተጽዕኖ መገለጫ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ሳለሁ ብዙ የቅርብ ጓደኞቼ ከሆነ ብሔር ነበሩ። እኔ ስለ ብሔራቸው ምንም የማውቀው አልነበረኝም። ከምርጫ በኂላ ግን አብዛኞዎቹ ጓደኞቼ ከሆነ ብሔር መሆናቸውን ተገነዘብኩ። ከዚያ በፊት ስለ ማንም ብሔር የማውቀው አልነበረኝም።

ልዑል እግዚአብሔር አዳም እና ሔዋንን የጠየቀው ጥያቄ ይሄ ነበር። "ዕራቁትህን እንደ ሆንክ ማን ነገረህ?" ራቁትነትህን እንድታውቅ ያደረገህ ማን ነው? ነጭ መሆንንህን ማን ነገረህ? ነጭ እንደ ሆንክ የነቃኸው መቼ ነበር? ጥቁር መሆንህን ማን ነገረህ? ከዚህ ብሔር መሆንህን ማን ነገረህ? በሀገርህ ውስጥ ስላሉ ብሔሮች እንድታውቅ ማን አደረገህ?

ሩዋንዳ ውስጥ ሰዎች ሁቱ ወይም ቱትሲ ስለመሆናቸው በጣም በቂ ንቃት አላቸው። ሰዎችን እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው የሆነ ነገሮች ከመጠን ያለፈ ንቃት እንዲኖራቸው የሚያደርገው ሰይጣን ነው። በሩዋንዳ የሁቱ እና ቱትሲ ልዩነት ከመጠን በላይ ማወቅ በክፉ ለሚታወሰው እና ለአንድ ሚሊዮን ሰዎች እልቂት ምክንያት ለሆነው የዘር ፍጅት

ምክንያት ሆኗል።

አንዳንድ መጋቢዎች ስለ ሀብታም እና ዝነኛ ሰው ከመጠን ያለፈ ንቃት አላቸው። ልዑል እግዚአብሔር ሊጠይቃቸው የሚችለው “ለምን ስለ ሀብት ስለ ኃይል እና ስለ ገንዘብ ንቃት ፈለግክ?” ነው። ከሰይጣን ጋር የነበረህ ቆይታህ ልትነቃ ስለማይገቡ ነገሮች እንድትነቃ አድርጎሃል።

የሰው ልጆች ስለ ብልተ ወሊዶቻቸው እና ስለ ተፈጥሯዊ ልዩነቶቻቸው ያላቸው ንቃት ከመጠን ላለፈ የወሲብ እውቀት እና ከወሲብ ጋር ለተያያዘ መዛባቶች እና ለኃጢአት መበራከት ምክንያት ሆኗል። የትኛውም እንስሳ እኛ እንደምንደብቀው ኀፍረተ ሥጋውን የሚደብቅ የለም። እኛ እንደምናደርገው ተደብቀው ወሲባዊ ግንኙነት አያደርጉም እንደ እኛም እርኩሳትን አይፈጽሙም። ይህም እንስሳት እኛ ሰዎች በሳይጣን እና ኃጢአት እንደ ተጠቃን ስላልተጠቁ ነው።

ህይወትህን መርምር።

ምንድነው ከመጠን በላይ ነቅተህ የምታስበው ምንድን ነው? የትኛው አጋንንታዊ ቆይታህ ነው ስለ ቀለም፣ ስለ ብሔር፣ ስለ ገንዘብ፣ ስለ ወሲብ ትክክል ባለሆነ መንገድ እንድትነቃ ያደረገህ?

# ምዕራፍ 10

# አጋንንታዊ መግቢያ፤ አጋንንቶች ወደ አንተ መግባት ለምን ይፈልጋሉ

**ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፥ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፥ አያገኝምም። በዚያን ጊዜም፦ ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል።**

**ማቴዎስ 12፥43-44**

## አጋንንቶች ወደ ሰዎች ስለ መግባታቸው ማስረጃ

ተራ በሚመስሉ በአከባቢህ ባሉ ሰዎች ውስጥ አጋንንቶች አሉ:: በአገልግሎቴ ውስጥ ብዙ አጋንንት ያደረባቸው እና የሚነዳቸው የተለመዱ ሰዎች አጋጥመውኛል::

አጋንንቶች ወደ ሰዎች ስለ መግባታቸው እና ስለመበራዛቸው አራት ማስረጃዎች እንዲከተለው ቀርበዋል::

**1. የሰው ዘር ባህሪይ በእርኩሳን ማናፍስት ስለ መበረዙ ትልቅ ማስጃ ነው:: የምድራችን ኃጢአት እና ክፋት በኖህ ዘመን ከነበረው ክፋት ጋር ይመጣጠናል::** ሰለሞን ይህን እውነታ እንዲህ አለ "... ደግሞም የሰው ልጆች ልብ ክፋትን ትሞላለች፥ በሕይወታቸውም ሳሉ እብደት በልባቸው ነው፥ ከዚያም በኋላ ወደ ሙታን ይወርዳሉ" (መክብብ 9፡3):: ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ አለ ዓለምም በሞላው በክፉ

ተይዟል፡፡ “ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን” (1ኛ ዮሐንስ 5፡19)

2. **ኢየሱስ ክርስቶስ በምኩራብ ውስጥ ሲያስተምር ከሚያመልኩት አንዱ እርኩስ መንፈስ ነበረበት፡፡** ይህ እርኩስ መንፈስ በዚህ አምላኪ ሰው ውስጥ ተደብቆ የኖረ ነው ነገር ግን በኢየሱስ መገኘት ለመውጣት ተገደደ፡፡ “በዚያን ጊዜም በምኩራባቸው ርኵስ መንፈስ ያለው ሰው ነበረ፤ እርሱም፦ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ፥ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ፡፡ ኢየሱስም፦ ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው” (ማርቆስ 1፡23-25)

3. **ኢየሱስ ከአንድ ሰው ውስጥ እስከ ስድስት ሺህ የሚደርሱ አጋንንቶችን አስወጥቷል፡፡** ሌጌዎን ማለት ስድስ ሰዎች ማለት ነው፡፡ የጌርጌሴኖውን እብድ ሰው ስድስት ሺህ አጋንንቶች ነበሩበት፡፡ “አንተ ርኵስ መንፈስ፥ ከዚህ ሰው ውጣ ብሎት ነበርና፡፡ ስምህ ማን ነው? ብሎ ጠየቀው፡፡ ብዙዎች ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው አለው” (ማርቆስ 5፡8-9)

4. **ጳውሎስ በሰዎች ውስጥ ሆነው እውነትን የሚተነብዩ አጋንንቶች አጋጥመውታል፡፡** አንድ ቀን ወደ ጸሎት ስፍራ ስንሄድ፣ በጥንቁላ መንፈስ ትንቢት የምትናገር አንዲት የቤት አገልጋይ አገኘችን፤ እርሷም በዚህ የጥንቆላ ሥራዋ ለአሳዳሪዎችዋ ብዙ ገንዘብ ታስገኝላቸው ነበር፡፡ ይህችው አገልጋይ ጳውሎስንና እኛን እየተከተለች “እነዚህ ሰዎች የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ፣ የልዑል እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው!” በማለት ትጮኽ ነበር፤ ይህንም ብዙ ቀን ደጋገመችው፤ ጳውሎስ ግን በዚህ እጅግ በመታወኩ ዘወር ብሎ ያን መንፈስ “ከእርሷ እንድትወጣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዛለሁ” አለው፤ መንፈሱም በዚያው ቅጽበት ወጣላት፡፡

# አጋንንቶች ወደ ለምን ሰው መግባት ይፈልጋሉ?

## 1. አጋንንቶች ወደ ሰው መግባት የሚፈልጉት ከሰው አካል ውጪ ሲሆኑ ይጠማሉ።

**ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፥ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፥ አያገኝምም።**

ማቴዎስ 12፥43

የሰው አካል ለአጋንንቶች ምግብ ያቀርባል። ጥማታቸው እና ፍላጎታቸው የሚረካው ከሰው ልጅ ወይም ከእንስሳ በመጠጣት ነው። ከሰው አካል ውጪ ሁሉም ቦታ ለእነርሱ ደረቅ ቦታ ነው።

አጋንንቶች በተባዮች እና በዝንቦች እንደ ተነጻጸሩ ማስታወስ አለብህ። አብዛኛዎቹ ተባዮች የሆነ ነገር የሚጠጡት ከሰው አካል ነው። አኖፌልስ የሚባሉ የወባ ትንኞች ለምሳሌ ደም የሚጠጡት ከሰው ነው።

እነዚህ ትንኞች ከሰው አካል ላይ ሲጠጡ እና ሲበሉ ወደዚህ አካል በሽታ እንዲገባ ያደርጋሉ። ያ ሰውነት በትክክል መስራቱን ያቆማል ትኩሳቱም ይጨምራል። ተባዮች ከሰው አካል ይባሉ እና ይህ ነው የማይባል ምቾት የሚነሳ ጣጣ እና በሽታ ይተውልናል።

እርኩሳን መናፍስት ጥማቸውን ለማረካት ከሰው ስጋ እና ደም ሲጠጡ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን፣ በሽታዎችን እና ሕገ ወጥነትን በሰው ልጆች ላይ ያስከትላሉ። የአንድት በሳንባ ነቀርሳ ልትሞት የደረሰች ሴት ምስክርነት አስታውሳለሁ። ጥቂት ቀናቶች ይቀሩአት ነበር። ሐኪሞች ተስፋ የቆረጡባት የቆዳ እና አጥንት ሻንጣ ሆናለች። በአምስተኛው ቀን

የተዓምራት አገልግሎት ላይ መጋቢው እጁን ሲጭንባት ራእይ አየ:: አንድ ትንሽየ ፍጡር ደረቷ ላይ ተንጠልጥሏል:: በግልጽ ይህ ፍጡር ህይወትዋን ልክ እንደ ተባዮች እየመጠጠ ነው:: መጋቢው የሴትየዋን አካል ለቅቆ እንዲወጣ ሲያዝ ዘሎ መሬት ላይ ወረደ ከቤተ ክርስቲያን መውጣት ጀመረ:: ይህቺ ለሞት ጥቂት ቀናቶች ቀርተዋት የነበረችው ሴት እንደገና አጋግማ፣ ኪሎ እየጨመረች፣ ሙሉ በሙሉ ካንሰር መፈወሷን ማመን ትችላለህ::

እርኩሳን መናፍስትን ልክ እንደ ታባዮች ህይወትን የሚመጡ፣ ትኩሳትን የሚያስከትሉ፣ ክብደት መቀነስን የሚያመጡ፣ የሰውነት መጫጫንን እና አጠቃላይ በሽታዎችን የሚያስከትሉ አድርገህ ከሳልካቸው ከማን ጋር እይተጋፈጥክ መሆኑን ትረዳለህ::

## 2. አጋንንቶች ሊገቡብህ ይፋልጋሉ ምክንያቱም ከሰው አካል ውጪ እረፍት የላቸውም::

የሰው ልጅ ለአጋንንቶች ትልቅ ምቾት እና እረፍት ይሰጣቸዋል:: የሰው ልጅ የሚያርፈው በተላመደው የምቾት ቀጠናው መኻል ነው:: አጋንንቶች በሰው ልጆች ይሳባሉ ምክንያቱም በሰው ልጅ ውስጥ የተላመዱት እና ዘና እንዲሉ የሚያደረጋቸውን ነገሮች ስለሚያገኙ ነው::

አንዴ በአንድ አካል ውስጥ ከሆኑ አእምሮ፣ የሚያወሩ አንደበቶች፣ የፍትወተ ሥጋ አካላት፣ የውስጣዊ ስሜት፣ ፍላጎት፣ የስሜት ሀዋሳት እና የተላመዱት ማንነት ይኖራቸዋል:: ብዙ የተለያዩ ሰዎች ውስጥ በመኖራቸው የሰው ብልት እና አካል ውስጥ ቤተኛ ይሆናሉ::

**ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፥ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፥ አያገኝምም።**

**ማቴዎስ 12፥43**

አጋንንቶች ሰዎች ቅጥ ያጣ ማንነት፣ ቅጥ ያጣ ባህሪ፣ ቅጥ ያጣ ምላሽ፣ ቅጥ ያጣ ወሲብ፣ ቅጥ ያጣ ምኞት እና ቅጥ ያጣ ስሜት እንዲኖራቸው ሲያደርጉ ማስተዋል አለብህ።

ሰዎች የካንሰር ዓይነት በሽታዎች፣ እብጠቶች እና የተለያየ የሰውነት ክፍል ብግነቶች እንዲኖራቸው ሲያደርጉም ማወቅ መቻል አለብህ።

ሰዎች ሐዘኔታ እንዳይኖራቸው፣ ነፍሰ ጋዳዮች፣ ገዳዮች እና ዘራፊዎች እንዲሆኑ የሚያደረጉትም እርኩሳን መናፍስቶች ናቸው። ሰዎች ነፍሰ ገዳዮች፣ አቁሳዮች እና እንዳገኙ የሚገድሉ ሲሆን ማንነታቸው በአጠቃላይ የተበላሸ ይሆናል።

ቅጥ ያጣ የወንዶች እና የሴቶች የወሲብ ፍላጎትም የሚመነጨው እነዚህን የአካል ክፍሎች በማነቃቃት ምቾት በሚያገኙ አጋንንቶች ናቸው። አጋንንቶች ማረፍያቸውን በወሲብ አካላት ውስጥ በማድረግ የሰዎችን የወሲብ ምኞት ይጨምራሉ። ቅጥ የለሽ የወንድ ለወንድ እና የሴት ለሴት የወሲብ ምኞትንም ይፈጥራሉ። የአጋንንቶች መበረዝ እና ክፋት በዓለማችን ላይ በመብዛቱ፤ ያልተለመደ እና የተዛባ ከእንስሳ ጋር የሚፈጸም የወሲብ ተግባርም እየጨመረ መሆኑን አስተውል። እነዚህ ቅጥ የለሽ ምኞቶች እና ቅጥ ያጡ ስሜቶች የሚመነጬት ከእነዚህ የአካል ክፍል የሚመገቡ እና ማነቃቃትን በሚፈጥሩ አጋንንቶች ነው።

## 3. አጋንንቶች ወደ አንተ መግባት ይፈልጋሉ ምክንያቱም እንደ ቤት ያዩሃል።

እርኩሳን መናፍስቶች እንደ ቤት ያዩሃል። ብዙ ተባዮች እና ህዋሳት በሰው ውስጥ ይኖራሉ። በማይክሮባዮሎጂ ጥናት መሰረት በሰው ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታት የሰውን አካል እንደ ቤት ወይም እንደ አስተናጋጃቸው ያዩታል። ብዙ ተባዮች በእንስሳት ውስጥ ይኖራሉ እንዲሁም እንደ ቤታቸው ይቆጥሩታል። ውሾች ቁንጭር/*leishmaniasis*/ የሚያመጣ የሌይሽማኒያ ኢንፋንተም/*leishmania infantum*/ተሸካሚ ወይም ቤት ናቸው። አሳማ የሴስቶዳ ትል /*cestode worms*/ ተሸካሚ ነው። ቀንድ አውጣ የሺስቶሶሚያሲስ/*schistosomiasis*/ ተሸካሚ ነው። ዳክየዎች የ አቪያን ኢንፌሉዌንዛ /*avian influenza*/ ተሸካሚዎች ናቸው። እንደሚታየው እነዚህ በሽታ አምጭ ፍጥረቶች ሌሎች እንስሳትን አንደ ቤታቸው ያዩአቸዋል።

**በዚያን ጊዜም፦ ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል።**

**ማቴዎስ 12፥44**

ብዙ ጥገኛ ህዋሳቶች፣ ባክቴሪ እና ቫይረስ ጭምር በሰው ወስጥ በመኖር ሰውን እንደ ቤታቸው ይቆጥራሉ። አንተ በእነርሱ በኩል ባለፍክ ቁጥር እርኩሳን ማናፍስቶች በናፍቆት ዓይን ያዩህ እና ለራሳቸው አንዲህ ይላሉ "እርሱ ውስጥ መኖር ብችል፤ ወይኔ ቤት ቢሆን" ብለው ይመኛሉ። ልክ የሰው ልጅ በሀብታሞች ሰፈር ሲያልፍ የተንጣለለ ቤት አይቶ በስስት እንደሚያይ አጋንንቶች ያዩህ እና አንተ ውስጥ ለመኖር ይመኛሉ።

እርኩሳን መናፍስቶች አንተ ውስጥ የመኖር ዕድል እንዳያገኙ መከላከል አስፈላጊ ነው። ንባብህን ስትቀጥል እርኩሳን መናፍስቶች ወደ አንተ እንደይገቡ እንዴት እንደምትከላከል ታያለህ። አጋንንቶች ቤት እንዲኖራቸው

በጣም ስለሚሹ ከአካል ወጪ ከሚሆኑ አሳማ ወስጥ መግባትን ይመራጣሉ:: ኢየሱስን ወደ አሳማ እንድንገባ ፍቀድልን ብለው ለመኑት:: በክፍት ቦታ እና ዛፎች ላይ ከመኖር ይልቅ አሳማ ወስጥ መኖርን መረጡ:: ስጋን ስትበሉ መጸለይ ያለባችሁ ብዙ እንስሶች በእርኩሳን መናፍስት የተሞሉ ስለሆነ ነው:: ሰዎች የተባለሽ ስጋ በልተው የምግብ መመረዝ የሚይዛቸው ህይወት ያለው ባክቴሪያ የሚባል ፍጡር ሰውነታቸው ውስጥ ለመኖር ስለገባ ነው::

4. **አጋንንቶች ወደ አንተ መግባት ይፈልጋሉ ምክንያቱም ከሌሎች አጋንንቶች ጋር እና ከሌሎች ከተደራጁ አጋንንቶች መንጋ አብረው ህብረት ማድረግ ስለሚችሉ ነው::**

አጋንንቶች አንተን መልካም የአጋንንቶች ህብረት ማዕከል አድርገው ያዩሃል:: የአጋንንቶች የተደራጀ መንጋ በአንድላይ ሰው ውስጥ ይኖራሉ:: ከሌሎች አጋንንታዊ ፍጥረቶች ጋር ከፍተኛ ምቾት አላቸው:: ኢየሱስ አንድ እርኩስ መንፈስ ሰባት ሌሎች ክፉ መናፍስቶችን በመሰብሰብ ኑሮአቸውን አንድ ሰው ውስጥ አደረጉ ይላል::

> **ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎችን አጋንንት ከእርሱ ጋር ይወስዳል፥ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል። ለዚህ ክፉ ትውልድ ደግሞ እንዲሁ ይሆንበታል።**
>
> **ማቴዎስ** 12፥45

አጋንንቶች በአንድ ሰው ውስጥ በበዙ ቁጥር ጣጣ እና ችግርም በዚያ ሰው ላይ እንዲሁ ይበዛል:: ኢየሱስ የዛ ሰውየ ሁኔታ የባሰ ሆነ ይላል ምክንያቱም አሁን ሰባት ተጨማሪ ሆነው ስለገቡበት ማለት ነው:: ሌጌዎን አጋንንቶች በአንተ ወስጥ አሉ ማለት የማይቆጠሩ እርኩሳን ማናስቶች አሉብህ

ማለት ነው። ይህ ዲያብሎስ "ሙሉ በሙሉ መያዝ" ወደሚባለው ይመራል ማለት ነው። አንድ ሰው በአጠቃላይ የዲያብሎስ ቁጥጥር ስር ከወደቀ ሁሉም የአካሉ ክፍል በአንድ ወይ በሌላ እርኩሰ መንፈስ የተያዘ በመሆኑ ሰውየው ትክክለኛ ሰው የመሆን ዕድሉ ጠባብ ነው።

አጋንንቶች በቡድን ወይም በመንጋ መኖርን ይመርጣሉ፤ ባይሆንም ኖሮ ያው እርኩሰ መንፈስ ተመልሶ ተመልሶ በራስ ወዳድነት ለሌች እርኩሳን መናፍስቶች በር ዘግቶ መኖር ይችል ነበር። የተፈጠረው ግን ይህ አይደለም። አጋንንቱ ሰባት ሌሎችን አግኝቶ ቤቱን ሞቅ ያለ እና የደራ ለማድረግ ደስተኛ ነበረ።

እርኩሳን መናፍስቶች ወደ ቡድን እና መንጋ ራሳቸውን የሚያሳድጉት ለዚህ ነው።

# ምዕራፍ 11

# አጋንንታዊ ጭቆና፤ ምንድነው?

**እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ከዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤**

**የሐዋርያት ሥራ** 10፥38

አጋንንታዊ ጭቆና የህመሞች እና የበሽታዎች ምንጭ ነው:: ስለ እርኩሳን መናፍስቶች ማወቅ አለብህ ምክንያቱም በሽታን የሚያመጡት እነርሱ ናቸውና:: በሽታዎች የሚመጡት በአጋንንታዊ ጭቆና ነው:: ዘመናዊ ሳይንስ ስለማይታዩት አካላዊ የበሽታ አምጭዎችን ብዙ አሳይቶናል:: ብዙ ህመሞችን የሚፈጥሩ ባክቴሪዮች፣ ቫይረሶች እና ፓረሳይቶች አሉ:: በሳይንስ ካለመንክ የባክቴሪያን፣ የቫይረስን እና የፓራሳይቶችን መኖር ልታምን አትችልም:: ኢቦላ በቀላሉ በአፍሪካ ውስጥ የተዛመተበት ምክንያት ብዙ ሰዎች ሳይንሳዊ የበሽታ ምንጩን ስላለመኑ ነው:: ሰዎች በኢቦላ የሞተውን ሰው አካል በመንካት ኢቦላ ይተላለፍባቸዋል::

በተመሳሳይ ሁኔታ መንፈሳዊ ሰው ካልሆንክ ብዙ ህመሞች በእርኩሳን መናፍስት ጭቆና ይመጣሉ የሚባለውን አታምንም:: አየህ ከእነዚህ ባክቴሪያ፣ ቫይረሶች እና ፓራሳይቶች ጀርባ እርኩሳን መናፍስቶች አሉ::

ዛሬ የሆኑ ቡድኖች አሉ በሳይንስ ወይም በመንፈሳዊ ዓለም የማያምኑት:: ሁለቱም ቡድኖች ስህተት እየሰሩ ነው:: ባክቴሪያ፣ ፓራሳይት፣ ቫይረሶች፣ አጋንንቶች እና የወደቁ

መላዕክቶች በጣም እውነት ናቸው! ማይክሮስኮፕ(አጉሊ በመጽር) ከመፈጠሩ በፊት ለብዙ ዘመናት የሰው ልጆች የባክቴሪያ እና የፓራሳይቶችን መኖር አያውቁም ነበር። ዛሬ በማይክሮስኮፕ(በአጉሊ በመጽር) እና ሌንሶች መፈልሰፍ ምክንያት ፓራሳይቶችን እና ባክቴሪያን ማየት ችለናል። አንድ ቀን ምናልባት አጋንንቶች እና ሌሎች ፍጥረቶች ያለቡትን መንፈሳዊውን ዓለም ከፍቶ በግልጽ የሚያሳይ ነገር ይፈለሰፍ ይሆናል። የሰው ልጆች የብዙ ችግሮችን መንስኤ በማወቅ ይደመማሉ፣

ኢየሱስ ሰዎችን ሲፈውሳቸው አጋንንትንም ያስወጣለቸው ነበር። አጋንንቶች ሰዎችን እንደሚያስጨንቁ እና የደንቆሮነት እና የዲዳ በሽታዎች መንስኤ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ይገስጻቸው ነበር። እንደ ክርስቶስ መሆን የምትፈልግ ከሆነ የኢየሰስን መንገድ መከተል አለብህ። በአገልግሎትህ ውስጥ የፈውስ እና የተዓምራት ቅባት እንዲሰራ ከፈለግክ አጋንንቶችን ማስወጣት አለብህ። አንዳንድ የሕክምና እውነታዎችን ማወቅህ ዛሬ በዓለማችን ያለውን የአጋንንታዊ ጭቆና እውነትን ሊያስቀረው አይችልም። በኢየሱስ ጊዜ እንዴት አጋንንቶች የበሽታች መንስኤ እንደ ነበሩ ብዙ ምሳሌዎችን ላሳይህ እፈልጋለሁ። እያንዳንዱ ሁኔታ አጋንንታዊ ጭቆናዎች ላመጡት በሽታ ምሳሌ ነው።

## 1. የዲይብሎስ ጭቆና የሚጥል በሽታን ያመጣል።

**ከሕዝቡ አንዱ መልሶ፦ መምህር ሆይ፥ ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ልጄን ወደ አንተ አምጥቼአለሁ፤ በያዘውም ስፍራ ሁሉ ይጥለዋል፤ አረፋም ይደፍቃል፥ ጥርሱንም ያፋጫል ይደርቃልም፤ እንዲያወጡለትም ለደቀ መዛሙርትህ ነገርኋቸው፥ አልቻሉምም አለው።**

**እርሱም መልሶ፦ የማታምን ትውልድ ሆይ፥ እስከመቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ወደ እኔ አምጡት**

አላቸው። ወደ እርሱም አመጡት። እርሱንም ባየ ጊዜ ያ መንፈስ ወዲያው አንፈራገጠው፤ ወደ ምድርም ወድቆ አረፋ እየደፈቀ ተንፈራፈረ።

አባቱንም፦ ይህ ከያዘው ስንት ዘመን ነው? ብሎ ጠየቀው። እርሱም፦ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ነው፤ ብዙ ጊዜም ሊያጠፋው ወደ እሳትም ወደ ውኃም ጣለው፤ ቢቻልህ ግን እዘንልን እርዳንም አለው።

ኢየሱስም፦ ቢቻልህ ትላለህ፤ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል አለው።

ወዲያውም የብላቴናው አባት ጮኾ፦ አምናለሁ፤ አለማመኔን እርዳው አለ።

ኢየሱስም ሕዝቡ እንደ ገና ሲራወጥ አይቶ ርኩሱን መንፈስ ገሠጸና፦ አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ፥ እኔ አዝሃለሁ፥ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት አለው። ጮኾም እጅግም አንፈራግጦት ወጣ፤ ብዙዎችም፦ ሞተ እስኪሉ ድረስ እንደ ሙት ሆነ።

ማርቆስ 9፥17-26

2. የዲያብሎስ ጭቆና የአጥንትና መገጣጠሚያ በሽታን ያመጣል::

በሰንበትም በአንድ ምኵራብ ያስተምር ነበር። እነሆም፥ ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች፥ እርስዋም ጐባጣ ነበረች ቀኀታም ልትቀም ከቶ አልተቻላትም።

ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና። አንቺ ሴት፥ ከድካምሽ ተፈትተሻል አላት፥ እጁንም ጫነባት፤ ያን ጊዜም ቀጥ አለች፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነች።

ጌታም መልሶ፦ እናንተ ግብዞች፥ ከእናንተ እያንዳንዱ በሰንበት በሬውን ወይስ አህያውን ከግርግሙ ፈትቶ ውኃ ሊያጠጣው ይወስደው የለምን?

ይህችም የአብርሃም ልጅ ሆና ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ ሰይጣን ያሰራት በሰንበት ቀን ከዚህ እስራት ልትፈታ አይገባምን? አለው።

ሉቃስ 13፥10-13፣15-16

3. የዲያብሎስ ጭቆና የደንቆሮነት እና ዲዳነት በሽታ ያመጣል::

ኢየሱስም ሕዝቡ እንደ ገና ሲራወጥ አይቶ ርኩሱን መንፈስ ገሠጸና፦ አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ፥ እኔ አዝሃለሁ፥ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት አለው።

ማርቆስ 9፥25

4. የዲያብሎስ ጭቆና እውርነትን ያስከትላል::

ከዚህም በኋላ ጋኔን ያደረበትን ዕውር ዲዳም ወደ እርሱ አመጡ፤ ዕውሩም ዲዳውም እስኪያይና እስኪናገር ድረስ ፈወሰው።

ሕዝቡም ሁሉ ተገረሙና፦ እንጃ ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን? አሉ።

ማቴዎስ 12፥22-23

ሁለቱም ሰዎች እጃቸውን ዘርግተው ሎጥን ወደ እነርሱ ዘንድ ወደ ቤት አገቡት መዝጊያውንም ዘጉት።

በቤቱ ደጃፍ የነበሩትንም ሰዎች ከታናሻቸው ጀምሮ እስከ ታላቃቸው ድረስ አሳወሩአቸው፤ ደጃፉንም ለማግኘት ሲፈልጉ ደከሙ።

ዘፍጥረት 19፥10-11

5. የዲሰይብሎስ ጭቆና የብዙዎችን ህማም ያስከትላል::

በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ፤ በነቢዩ በኢሳይያስ፦ እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፥ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ።

ማቴዎስ 8፥16-17

ፀሐይም በገባ ጊዜ በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙ በሽተኞችን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡአቸው፤ እርሱም በእያንዳቸው ላይ እጁን ጭኖ ፈወሳቸው።

አጋንንትም ደግሞ፦ አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እያሉ እየጮኹም ከብዙዎች ይወጡ ነበር፤ ገሠጻቸውም ክርስቶስም እንደ ሆነ አውቀውት ነበርና እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም።

ሉቃስ 4፥40-41

ከተማይቱም ሁላ በደጅ ተሰብስባ ነበር።

በልዩ ልዩ ደዌም የታመሙትን ብዙዎችን ፈወሰ፥ ብዙዎችንም አጋንንት አወጣ፥ አጋንንትም ክርስቶስ መሆኑን አውቀው ነበርና ሊናገሩ አልፈቀደላቸውም።

ማርቆስ 1፥33-34

# ምዕራፍ 12

# አጋንንታዊ ጭቆና፤ እንዴት ነጻ መሆን ትችላለህ

ከአጋንንታዊ ጭቆና በኢየሱስ ክርስቶስ አጋልግሎት ነጻ መውጣት ትችላለህ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጋንንታዊ ጭቆና እንዴት ነጻ መውጣት እንደሚቻል የተለያዩ ዘዴዎችን አሳይቷል። ዛሬም በአገልግሎትህ እነዚህን ዘዴዎች ተጠቅመህ ሰዎችን ከአጋንንታዊ ጭቆና ነጻ ማውጣት ትችላለህ።

1. **በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ከአጋንንት ኃይል ነጻ መውጣት ትችላለህ**

**በዚያም ቀን ሸክሙ ከጫንቃህ ቀንበሩም ከአንገትህ ላይ ይወርዳል፤ ቀንበሩም ከውፍረት የተነሣ ይሰበራል።**

**ኢሳይያስ** 10፥27

**እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤**

**የሐዋርያት** ***ሥራ*** 10፥38

ቀንበር የሚሰበረው በቅባት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ከመጋረጃ ጀርባ የሚሰራ እና የእግዚአብሔርን ቃል የሚያጸና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። ያለ እግዚአብሔር ኃይል አንተም እኔም ተራ ሰዎች፣ ተራ ኃጢአተኞች እና ተራ ወዳቂዎች እንጂ ምንም አይደለንም። በህይወትህ ውስጥ የሚሰራው የእግዚአብሔር ኃይል የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የእግዚብሔርን ሥራ ለመስራት በኃይል እና በመንፈስ ቅዱስ መቀባት አስፈልጎት ነበር።

ኢየሱስ ለመፈወስ ተቀብቷል ስለዚህ አንተም ለመፈወስ መቀባት ይኖርብሃል። ያለ ቅባቱ ኢየሱስ አናጺ ሆኖ ይቀር ነበር። ያለ ቅባት ኢየሱስ ቁምሳጥን፣ በር እና የተለያዩ መቀመጫችን እየሰራ ይቀጥል ነበር። ያለ ቅባት ኢየሱስ የቀብር ሣጥኖችን እየሰራ፣ ኮርንሶችን እየጠገነ እና የተለያዩ የእንጨት ምሶሶዎችን እያስተካከለ ይቆይ ነበር። ይህ ማለት ማንኛውም አናጺ የሚሰራው ስራ ስለሆነ ነው።

ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሲቀባ ወደ ሌላ ሰው ተለወጠ። በጣም የምናውቀው የተቀባው አዳኛችን ሆነ። እንደምታየው ቅባት ከተዓምራት ጀርባ ያለው ምስጢር ነው! ቅባት ከስኬት ጀርባ ያለው ምስጢር ነው። ቅባት ከኃይል ጀርባ ያለው ምስጢር ነው። ቀንበር የሚሰብረው ቅባት ነው!

## 2. በተነገረው ቃል ከአጋንንት ኃይል ነጻ መውጣት ትችላለህ።

**በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ፤ በነቢዩ በኢሳይያስ፦ እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፥ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ።**

ማቴዎስ 8፥16

## 3. እጅ በመጫን ከአጋንንት ኃይል ነጻ መውጣት ትችላለህ።

**በሰንበትም በአንድ ምኵራብ ያስተምር ነበር። እነሆም፥ ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች፥ እርስዋም ጐባጣ ነበረች ቀንታም ልትቆም ከቶ አልተቻላትም።**

**ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና። አንቺ ሴት፥ ከድካምሽ ተፈትተሻል አላት፥ እጁንም ጫነባት፤ ያን ጊዜም ቀጥ አለች፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነች።**

**ጌታም መልሶ፦ እናንተ ግብዞች፥ ከእናንተ እያንዳንዱ በሰንበት በሬውን ወይስ አህያውን ከግርግሙ ፈትቶ ውኃ ሊያጠጣው ይወስደው የለምን?**

**ይህችም የአብርሃም ልጅ ሆና ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ ሰይጣን ያሰራት በሰንበት ቀን ከዚህ እስራት ልትፈታ አይገባምን? አለው።**

**ሉቃስ 13፥10-13፣ 15-16**

ይህ ጉዳይ ዲያብሎ ምን ያህል እርኩስ መሆኑን ያብራራል። ኢየሱስ ይህቺ ሴት የድካም መንፈስ እንዳለባት ይነግረናል። ይህ እርኩስ መንፈስ ሴቷ አጎንብሳ ከዚያ በኋላ ለአስራ ስምንት ዓመት ቀና ብላ እንዳትሄድ ያደረገ ነው። በምድር ላይ ብዙ ክፉ አምባገነኖች ቢኖሩም በጣም ጥቂቶቹ ናቸው እንዲህ ዓይነት ኢ-ሰብዓዊ ነገር ለብዙ ዘመናት በሰዎች ላይ በማድረስ የሚታወቁት።

በዓለም ዙሪያ ባሉት አዳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሰነበቱ ተማሪዎች በአዲስ ተማሪዎች ላይ ኃይለኛ አምባገነናዊ ቅጣት ያደርሳሉ። ከእነዚህ ክፉ ተማሪዎች ውስጥ ግን ማንም የጀርባ አጥንትን ለአስራ ስምንት ዓመት የማጣመምን የሚያክል ቅጣት የሚያደርስ የለም።

የጀርባ አጥንት ለተጣመመበት ሰው አስራ ስምንት ዓመት በጣም ረጅም ጊዜ ነው። በዚህ ረገድ የተገለጠው የኢየሱስ አዛኝነት ብቻ ሳይሆን የእርኩስ መንፈስ ክፉነትም ነው።

**4. ዲያብሎስን በመገሠጽ ከአጋንንት ኃይል ነጻ መውጣት ትችላለህ።**

**ወደ ሕዝቡም ሲደርሱ አንድ ሰው ወደ እርሱ ቀረበና ተንበርክኮ፦ ጌታ ሆይ፥ ልጄን ማርልኝ፥ በጨረቃ እየተነሣበት ክፉኛ ይሣቀያልና፤**

**ብዙ ጊዜ በእሳት ብዙ ጊዜም በውኃ ይወድቃልና። ወደ ደቀ መዛሙርትህም አመጣሁት ሊፈውሱትም አቃታቸው አለው።**

**ኢየሱስም መልሶ፦ የማታምን ጠማማ ትውልድ ሆይ፥ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ወደዚህ ወደ እኔ አምጡት አለ። ኢየሱስም ገሠጸው ጋኔኑም ከእርሱ ወጣ፥ ብላቴናውም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ።**

**ማቴዎስ 17፥14-18**

ሰይጣን የሚሰማው የምትናገራቸውን ቃላቶች ነው:: ስትገስጸው ይገሠጻል! ስታባርረው ይባረራል! ስታስወግደው ይወገዳል! ስታስረው ይታሰራል! ስትከለክለው፣ ይከለከላል! በዲያብሎስ ላይ የእግዚአብሔርን ቃል መናገር አስፈላጊ ነው:: ካለህበት አባርራቸው:: እርኩሳን መናፍስትን በኃይለኛው ገስፃቸው:: አንተ ካለህበት ቦታ ገስጸህ አባራቸው:: ፍርድን ተናገርባቸው:: በመንፈስ ተዋጋቸው እና ከልክላቸው:: የእምነት ቃል ተጠቅመህ በምትኖርበት አካባቢህ ያሉትን በማይታይ ዓለም ላይ ያሉትን ፍጥራታት ሁሉ ታላቅ የእሳት ፍርድ አዋጅ አውጅባቸው::

## 5. ጾም እና ጸሎትን የህይወት ዘይቤህ በማድረግ ከአጋንንት ኃይል ነጻ መውጣት ትችላለህ::

**ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ ኢየሱስ ቀረቡና፦ እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው? አሉት።**

**ኢየሱስም፦ ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ፦ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም። ይህ ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው።**

**ማቴዎስ 17፥19-21**

ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስን ለማስወጣት አዲስ ጾም እና ጸሎት እንዳልጀመረ መታወቅ አለበት:: የጾም እና ጸሎት ህይወት ነበረው እናም ኃይልን ከላይ ተቀበለ:: አንድም ተጨማሪ የጾም ቀን ሳይኖረው ነው ወጣቱን ልጅ ከጨለማ

ኃይል ነጻ ያወጣው፡፡ ጾም እና ጸሎት ለመንፈሳዊ ሰው የህይወት ዘይቤው ነው፡፡ መንፈሳዊ ሰው እንደ ማንኛውም ሰው መብላት እና እንደ ማንኛውም ሰው ማህበራዊ ህይወት ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡ ጸሎት የእግዚአብሔርን ኃይል በህይወትህ ውስጥ ያስለቅቃል ምክንያቱም ጸሎት እግዚአብሔርን ወደ ህይወትህ እና ሁኔታህ ይጋብዛልና፡፡ እግዚአብሔርን ወደ ህይወትህ ሳትጋብዝ የእግዚአብሔር ኃይል እና በሁኔታህ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት አይኖርህም፡፡

# ምዕራፍ 13

# በአጋንንት መያዝ

**ወደ ማዶም ወደ ጌርጋሴኖን አገር በመጣ ጊዜ፥ አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች ከመቃብር ወጥተው ተገናኙት፤ እነርሱም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ እስኪሳነው ድረስ እጅግ ክፉዎች ነበሩ።**

**ማቴዎስ 8፥28**

በአጋንንት መያዝ የሚጀምረው ዲያብሎስ የሰውን ልጅ ሲቆጣጠረው ነው። አዕምሮውን ሳትቆጣጠረው የሰውን ልጅ መቆጣጠር አትችልም። ዲያብሎስ የሰውን ልጅ ሲቆጣጠረው የአጋንንት ማደሪያ ያደርገዋል።

የአጋንንት ማደሪያ መሆን የሚመጣው የዲያብሎስ የመገኘቱ ጠቋሚ ልዩ ምልክቶች ጋር ነው። በአጋንንት የመያዝ ምልክቶች እና ጠቋሚዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ። እነዚህ ለየት ያሉ ባህሪያት አጋንንቶች የሰውን አዕምሮ ሙሉ በሙሉ እስከሚቆጣጠሩት ድረስ በትጋት እንደሚያጠቁ ያሳያል። ሰውየው ሙሉ በሙሉ ሲወሰድ ነው ያ ሰው ተይዟል(ተቆጣጥሮታል) የሚባለው።

በመሰረቱ በአጋንንት ሙሉ በሙሉ መያዝ ዕብደትን ያመጣል መባል ይቻላል። የአንድ ሰው አዕምሮ በዲያብሎስ ስር ሲወድቅ አጋንንት አደረበት ይባላል። የአጋንንታዊ ማደሪያን ባህሪያትን እናስተውል። የአጋንንት ማደሪያ ሁሉም ባህሪያት በጌርጌሴኖ እብድ ሰውዬው ላይ የሚታዩት ናቸው፣ ሁኔታው በዝርዝር የማርቆስ ወንጌል ውስጥ የተገለጸው ነው። ይህን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ "የአጋንንት ማደሪያ" ሲለው የሕክምና ሙያ ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን የተደበላለቀ ምልክት

ስኪዞፍሬኒያ/schizophrenia/ ይለዋል።

1. የአጋንንት ማደሪያ በብዙ ፍርሃት ይታወቃል

**እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር፥ በሰንሰለትም ስንኳ ማንም ሊያስረው በዚያን ጊዜ አይችልም ነበር፤**

**ማርቆስ 5፥3**

አጋንንት ያደረበት ሰው የፍርሃት ህይወት ይኖራል። ዲያብሎስ ስለሚያስፈራራው የፍርሃት የቅዠት ሄኔታ ውስጥ ይኖራል። የዲያብሎ ስራ ፍሃትን ይፈጥራል። እግዚአብሔር የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም። ፍርሃት መንፈስ ነው። አጋንንት በአዕምሮህ ላይ የሚያደርሰው ጥቃት ወደ ፍርሃት ይመራሃል። የጌርጌሴኖው እብድ ሰው በጣም አስፈሪ እና ጭር ባለው ማንም በማይኖርበት መቀብር መኻከል ይኖር ነበር።

2. የአጋንንት ማደሪያ በእልኸኝነት እና ከንቱ እምነት ይለያል።

**ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበርና ዳሩ ግን ሰንሰለቱን ይበጣጥስ እግር ብረቱንም ይሰባብር ነበር፥ ሊያሸንፈውም የሚችል አልነበረም፤**

**ማርቆስ 5፥4**

አጋንንት ያደረበት ሰው እልኸኛ ነው። አጋንንት ያደረበት ሰው አይገራም። መጭበርበር እንዳይረጋጋ ያደርገዋል። መጭበርበር በእልኸኝነት ትክክል ያለሆነውን ነገር ማመን ነው። አጋንንታዊ ስራ ትክክል ባልሆነው ነገር ላይ ጠንካራ እና እልኸኛ እምነት እንዲኖርህ ያደርጋል። በተቃራኒው ማስረጃ ቢቀርብ እንኳን አዕምሮአቸወን መቀየር አይፈልጉም። ማስረጃ ባለበት አዕምሮን ለመቀየር አለመቻል የአዕምሮ ህመም ልዩ ምልክት ነው።

## 3. የአጋንንት ማደሪያ ቅዠት ይለያል።

**ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር።**

**ማርቆስ 5፥5**

አጋንንት ያደረበት ሰው ሌላ ሰው የማይሰማውን ድምፅ ይሰማል ሌላው ያላየውን ነገር ያያል። የጌርጌሴኖኑ እብድ ሰው ራሱን በድንጋይ እንዲቧጭር የሚሰጠውን ትዕዛዝ እየሰማ ይፈጽም ነበር። የሚሰድባቸውን፣ የሚያወራቸውን፣ የሚመክራቸውን ወይም የሚሰድባቸውን ድምፅ ሊሰሙ ይችላሉ። ሰዎችን አይተው ትክክል ያልሆነውን ነገር ወይም በፍጹም የሌለውን ነገር ያስተውላሉ።

መቃዠት የሌለውን ነገር አለ ብሎ መለማመድ ነው። የሆነ ሰው እውነት ያልሆነውን ሊያይ ይችላል፤ እውነት ያልሆነውን ሊሰማ ይችላል። ዲያብሎስ በአዕምሮአቸው ላይ ጠንካሩ ጥቃት የሚፈጽምባቸው ሰዎች በቁሳዊ ዓለም ላይ የሌለወን ነገር ማየት እና መስማት ይጀምራሉ።

## 4. የአጋንንት ማደሪያ በድብርት ይለያል።

**ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር።**

**ማርቆስ 5፥5**

አጋንንት ያደረበት ሰው ድብርት ውስጥ ነው። የጌርጌሴኖኑ እብድድ ሰውዬ ሳያቋርጥ ብቻውን በመቃብር ስፍራ ያለቅስ እና ይጮህ ነበር። አዕምሮው ጥቃት ውስጥ ያለ ሰው የሀዘን ወቅቶች፣ ተስፋ የመቁረጥ፣ የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ ለህይወት ደንታ ቢስ መሆን እና የእንቅልፍ ጊዜ መዛባት ሊያጋጥመው ይችላል።

5. **የአጋንንት ማደሪያ የሆነ ሰው ቅጥ ባጣ ባህሪይ ይለያል።**

**ወደ ማዶም ወደ ጌርጋሴኖን አገር በመጣ ጊዜ፥ አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች ከመቃብር ወጥተው ተገናኙት፤ እነርሱም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ እስኪሳነው ድረስ እጅግ ክፉዎች ነበሩ።**

ማቴዎስ 8፥28

አጋንንት ያደረበት ሰው ብዙ ቅጥ ያጣ ባህሪያትን ያሳያል። የጌርጋሴኖን አገር እብዶች ሰዎች አደገኞች ነበሩ። ማንም በእነርሱ ድንበር በኩል እንዲያልፍ አይፈቅዱም ነበር። አጋንንታዊ ጥቃት ውስጥ ያለ ሰው ትንሽ ወይም ምንም ስሜት አለማሳየት(affective flattening)፣ ትንሽ ወይም ምንም አለመናገር (alogia)፣ ትንሽ ወይም ምንም ዓይነት ተነሳሽነት፣ ሰበብ ደርጊት ወይም ፍላጎት(avolition) የማሳየት አሉታዊ ምልክቶች ሊታዩባቸው ይችላሉ። አንድ ሰው ትንሽ ወይም ምንም ዓይነት ስሜት ሳይኖረው ሲቀር በቀላሉ ነፍሰ ገዳይ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ለሚገድላቸው ወይም ለሚጎዳቸው ሰዎች ምንም ዓይነት ስሜት አይኖረውምና።

6. **የአጋንንት ማደሪያ የሆነ ሰው ከማህበረሰብ በመገለል ይለያል።**

**ወደ ኢየሱስም መጡ፥ አጋንንትም ያደሩበትን ሌጌዎንም የነበረበትን ሰው ተቀምጦ ከብሶም ልቡም ተመልሶ አዩና ፈሩ።**

ማርቆስ 5፥15

አጋንንት ያደረበት ሰው የከፋ ከማህበረሰብ የመገለል ችግር ያጋጥመዋል። የጌርጋሴኖኑ እብድ ሰውዬ ማህበራዊ ኑሮው የተበላሸ ነበር። ራቁቱን በመቃብር ቦታ ከማህበረሰቡ ተለይቶ ይኖር ነበር። በዲያብሎስ ጥቃት ውስጥ ያለ ሰው ራሱን የመንካበከብ፣ የአለባባስ፣ የስራ፣ የትምህርት እና የራሱ

**ህይወት ፍላጎት ሊያጣ ይችላል፡፡**

# ምዕራፍ 14

# አጋንንታዊ ጉስሚያ

**ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው።**

**2ኛ ቆሮንቶስ 12፥7**

አጋንንቶች አንዳንዴ ለልዩ ዓላማ የእግዚአብሔር ቅዱስ ወደ ሆነ ሰው ለመግባት መለኮታዊ ፈቃድ ያገኛሉ:: እግዚአብሔር ልጆቹ በእርኩሳን መናፍስት እንዲፈተኑ፣ እንዲቸገሩ እና እንዲጎሰሙ ያደረገበት ጥቂት ምሳሌዎች ይገኛሉ::

ዲያብሎስ ለመስረቅ፣ ለመግደል እና ለማጥፋት ዝግጁ ነው:: መስረቅ፣ መግደል እና ማጥፋት የክፉው የዲያብሎስ ቅጽበታዊ የግድየለሽ ሥራዎች ናቸው::

ምንም እንኳን ወደ ሽንፈቱና ጥፋቱ ቢያመራውም ሰይጣን ግን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ከማስገደል ሊታቀብ አልቻለም ነበር:: የገደራው እብድ ሰው ውስጥ የነበሩት አጋጋንቶች በሙሉ የገቡበትን አሳማ እንኳን ከመግደል አልተቆጠቡም ነበር:: አዲሱን ማደሪያቸው የነበሩትን አሳማዎችን እንኳን በግድየለሽ ቅጽበታዊ ድርጊታቸው ገድለዋቸዋል:: ሶስት በጣም የሚታወቁ ሰይጣናዊ የጉስሚያ ሁኔታዎች አሉ:: አጋንንታዊ ጉስሚያ በጳውሎስ ህይወት፣ አጋንንታዊ ጉስሚያ በኢዮብ ህይወት እና አጋንንታዊ ጉስሚያ በቆሮንቶስ ሴሰኞች ላይ::

## 1. የጳውሎስ አጋንንታዊ ጉስሚያ

ሐዋርያው ጳውሎስ ጉስሚያን የተለማመደው በአደገኛ መንገድ ነው:: ከእርሱ እንዲለይ ሶስት ጊዜ ወደ ጌታ ጸልዮአል:: በሚያሳዝን ሁኔታ ግን እግዚአብሔር ያን የጠላት መልዕክተኛን ከህይወቱ ሊያስወግድ አልመረጠም:: ይህ የሰይጣን መልዕክተኛ ጳውሎስ ላይ ብዙ ችግር እና ድካም እንዲያደርስበት የተፈቀደለት ነበር:: ይህ ጳውሎስን ሲያዳክም እና ሲያሳዝን የነበረ ሲሆን አገልግሎቱን ግን ሊያደናቅፍበት አቅም አልነበረውም:: አጋንንታዊ ጉስሚያን በተከታታይ የሚለማመዱ ብዙ አገልጋዮች አሉ:: ትሁት እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ብዙ ችግሮች ቢኖርባቸውም አገልግሎታቸውን ግን በተሳካ ሁኔታ ያስቀጥሉታል:: ጳውሎስን ከሚመስሉት አገልጋዮች ጋር ብትጫወት ምን ያህል በብዙ ድካም እና ችግሮች እንደሚሰቃዩ ይገለጥልሃል:: በጣም የሚገርመው ግን እነዚህ ችግሮች እያሉባቸው ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን አገልግሎት ማስቀጠል መቻላቸው ነው::

**ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው።**

**ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ።**

**እርሱም፦ ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ። እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ።**

**2ኛ ቆሮንቶስ 12፥7 - 9**

## 2. የኢዮብ አጋንንታዊ ጉስሚያ

ኢዮብ ጉስሚያን የተለማመደው በአደገኛ መንገድ ነው:: ኢዮብ አጋንንታዊ ጉስሚያን መቋቋም በመቻሉ ስመጥር ነው:: ይህ መለኮታዊ ፈቃድ ያለው ጉስሚያ በሽታን፣ ሞትን፣

መዘረፍን እና አሳዛኝ ነገሮችን ሊያስከትል ይችላል:: ሰይጣን ኢዮብን ለመፈተን የተወሰነ ፈቃድ አግኝቶ ነበር:: ፈተናው ግን በጣም አስከፊ፣ የቤተሰቦቹን ሞት እና የንብረቱ እና ስራው መውደምን ያካተተ ነበር:: ኢዮብም በህይወቱ ላይ የተፈቀደውን ጉስሚያ ችሎ በማለፉ ስመጥር ሆነ::

**እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ ከወዴት መጣህ? አለው። ሰይጣንም፦ በምድር ላይ ዞርሁ፥ በእርስዋም ተመላለስሁ ብሎ ለእግዚአብሔር መለሰ።**

**እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም፤ በከንቱም አጠፋው ዘንድ አንተ በእርሱ ላይ ምንም ብታንቀሳቅሰኝ፥ እስከ አሁን ፍጹምነቱን ይዞአል።**

**ሰይጣንም መልሶ እግዚአብሔርን፦ ቍርበት ስለ ቍርበት ነው፤ ሰው ያለውን ሁሉ ስለ ሕይወቱ ይሰጣል።**

**ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ አጥንቱንና ሥጋውን ዳብስ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል አለው።**

**እግዚአብሔም ሰይጣንን፦ ሕይወቱን ተወው እንጂ እነሆ፥ እርሱ በእጅህ ነው አለው።**

**ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፥ ኢዮብንም ከእግሩ ጫማጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቍስል መታው።**

**ኢዮብ 2፤3 - 7**

## 3. የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አጋንንታው ጉስሚያ

ከሥጋ ዘመዶቻቸው ጋር ዝሙት የፈጸሙት የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ለአጋንንታዊ ጉስሚያ ተላልፈው ተሰጥተዋል:: በሌላ አገላለጽ ሰይጣን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጾታው ግንኙነት ወዳደረጉ ሰዎች የመግባት ልዩ ፈቃድ አግኝቷል:: በእርግጥ ሰይጣን ወደ አንተ የማለፍ ፈቃድ ካገኘ ይሰርቃል፣ ይገድላል እንዲሁም ያጠፋል:: መስረቅ፣ መግደል

እና ማጥፋት የእርሱ የደመ ነፍስ ስራዎች ናቸው።

**እኔ ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆን፥ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ፥ ከእናንተም ጋር እንዳለሁ ሆኜ ይህን እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጀበታለሁ፤ እናንተና መንፈሴም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ጋር ተሰብስበን፥**

**መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዬ ነው።**

1ኛ ቆሮንቶስ 5፥3-5

# ምዕራፍ 15

# አጋንንታዊ ውህድ

**የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ከራሳቸው ወሰዱ።**

**ዘፍጥረት 6፥2**

አጋንንታዊ ውህድ የአጋንንት መናፍስት ከሰው ስጋ ጋር ተዋህዶ ከሰውም የሚልቅ እና በምድር ላይ የሰው ልጆች መኻከል የሚመላለስ አጋንንታዊ ዲቃላ ሲፈጠር ነው:: ይህ መጽሐፍ ጠላትህ የሚኖረውን ማንኛውንም መልክ ትረዳው ዘንድ እንዲረዳህ የተጻፈው ነው:: ዲያብሎስ ቢሆን፣ እርኩሳን መናፍስት ቢሆኑ፣ እርኩሳን የተጣሉ ወፎች እና ፍጡራን ቢሆኑ፤ ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ዲያብሎስን በሚኖረው ማንኛውም ዓይነት መልክ ተረድተህ እንድትቋቋመው ነው:: ይህ መጽሐፍ የተጻፈው እርኩሳን መናፍስትን በምንም ዓይነት መልኩ እና ፋሺን እንድትዋጋው ሊረዳህ ነው:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እርኩስ መንፈስ እንዴት ከሰው ልጅ ጋር ተቀላቅሎ ከሰው የሚልቅ እርኩስ እና ዲቃላ እንደተፈጠረ ነው:: ከሰው የላቀ ማለት ሰውን የሚመስል ግን ደግሞ ትክክለኛ ሰው ልጅ መልክ የሌለው ማለት ነው:: ዲቃላ ማለት በቀላሉ መንፈስ እና ሰው ወይም የመንፈስ እና የእንስሳ ውህደት ማለት ነው:: የእነዚህየአጋንንት ድቅያዎች እንዴት እንደሚገለጹ የሚያሳየውን ደረጃ በደረጃ እንመልከት::

1. **አጋንንታው ውህድ፤** የወደቁ መልአክቶች ከሴቶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ፈጽመው ግማሽ መልአክ፣ ግማሽ ሰው (ከሰው የላቁ) ፍጥረትን ፈጠሩ::

**ሰዎች በምድር ላይ እየበዙ ሲሄዱ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው። የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች የሰዎችን ሴቶች ልጆች ውብ ሆነው አዩአቸው፤ ከመካከላቸውም የመረጧቸውን አገቡ። እግዚአብሔርም (ያህዌ) ፣ "ሰው ሟች ስለ ሆነ መንፈሴ እያዘነ ከእርሱ ጋር ለዘላለም አይኖርም፤ ዕድሜውም 120 ዓመት ይሆናል" አለ።**

**የእግዚአብሔር ልጆች የሰዎችን ሴቶች ልጆች ተገናኝተው ልጆች በወለዱ ጊዜም ሆነ ከዚያም በኋላ ኔፊሊም የተባሉ ሰዎች በምድር ላይ ነበሩ። እነርሱም በጥንቱ ዘመን በጅግንነታቸው ከፍ ያለ ዝና ያተረፉ ናቸው። እግዚአብሔር አምላክ የሰው ዐመፅ በምድር ላይ የበዛና የልቡም ሐሳብ ዘወትር ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመለከተ። እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ልቡም እጅግ አዘነ።**

**ስለዚህም እግዚአብሔር "የፈጠርሁትን የሰው ዘር ከምድረ ገጽ አጠፋለሁ፤ከሰው እስከ እንስሳ በምድር ላይ ከሚሰቡ ፍጡራን እስከ ሰማይ ወፎች አጠፋለሁ፤ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና" አለ። ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን አገኘ።**

**ዘፍጥረት 6፥1-8 (አመት)**

በኖኅ ዘመን የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች (የወደቁ መላእክቶች፣ መንፈሳዊያን ፍጥረቶች) የሰውን ልጆች በግብረስጋ ግንኙነት ወረሯቸው:: ይህ የእርኩሳን መናፍስት እና የሰው ልጆች ህብረት ሶስት ዓይነት ፍጥረቶችን አመጣ፤ ኔፊሊሞች(ግዙፋን)፣ ጊቦር(አምባገነኖች)፣ እና ሴም(ዝነኛ ሰዎች)::

**እንዲህም ሆነ ሰዎች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው፤**

**የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ።**

**ዘፍጥረት 6፥1-2**

መላእክቶች ከሴቶች ጋር ወሲብ የመፈጸማቸው ጽንሰ ሀሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ለመጽሐፍ ቅዱስ አዲስ እንግዳ የሆነ ጽንሰ ሀሳብ አይደለም። አንድ አንድ ሰዎች መልአክቶች የግብረስጋ ግንኙነት ማድረግ የማያችሉ ተደርጎ ይሰማቸዋል።

ሰዎች እግዚአብሔርን ሲፈልጉ ሰይጣን ወደ ቅናት ገባ። በሁሉም ቦታ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱ ሰይጣን ሲያይ ተገረመ። ሰይጣን ሰዎች ፈጣሪያቸወን ለመፈለግ ሲሹ ሲያይ ይገረማል። እኛ እግዚአብሔርን ስለምንወድደው ከዚህ የተነሳ ሰይጣንን በቅንዓት፣ በጥላቻ እና በእብደት ይሞላል። ሰይጣን ሁሉም እግዚአብሔርን የሚወዱና የሚያገለግሉትን ፍጥረቶች መግደል እና ማጥፋት ይፈልጋል።

ይህ የሰው ልጆች እና የወደቁ መላእክት ጥምረት ምድርን ያረከሷት እርኩሳን ፍጥረቶችን ፈጠረ። የኢየሱስ መምጣት እየተቃረበ በሚመጣ ቀናት ውስጥ በኖኅ ዘመን ከተከሰተው የሚልቅ ነገር እንደሚፈጸም መጠበቅ እንችላለን።

የሰው ልጆች የረከሱ እየሆኑ መጡ ምክንያቱም የዲብሎስ እና የሰው ቅልቅል ስለሆኑ። እንደ ዲያብሎስ የሚመላለሱ ብዙ ሰዎች አሉ። ያለ ምንም ጥረት እና ሀዘኔታ ሳይሰማቸው ይሰርቃሉ፣ ይገድላሉ እንዲሁም ያጠፋሉ።

ግዙፍ ሆነው የተፈጠሩት ከመላእክት እና ከሰዎች የተገኙት ያልተለመደ ጽንስ፣ የሚያስፈራሩ እና የልተለመዱ ታዋቂ ሰዎች ሆኑ። በእርግጥ ከመላዕክት እና ከሰዎች መኻከል የተወለዱት ለየት ያሉ ስለ ነበሩ ታዋቂዎች ሆኑ። የእነዚህ ታዋቂ የዝና ሰዎች ታሪክ ዛሬም ድረስ በመላው ዓለም ዙሪያ ይወራል። የምድር ላይ ቆይታቸው እና ሥራቸው የሚረሳ አይደለም።

ከሰው ሁሉ የላቀ የስፖርት፣ የአትሌትክስ፣ የፖለቲካ እና የጦርነት ችሎታ አላቸው የሚባሉት ታዋቂ ሰዎች ግማሽ ሰው ግማሽ መልዓክ ናቸው ተብሎ ይታመናል።

እርኩሳን ጠላቶች ወደ አንድ ከተማ ሲገቡ፤ የቻሉትን ሁሉ በማጋየት ያወድሙታል። ምክንያቱም ሰይጣን ፍጥረትን ማውደም እንጅ መግዛት አይችልም።

ግማሽ ሰው ግማሽ ዲያብሎስ የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ። ሰይጣን ገዳይ፣ ሀሰተኛ እና አርካሽ በመሆኑ ይታወቃል። የወደቁት መላእክቶች እርኩሰትን ወደ ዓለም አስገቡት። ይህ ግማሽ ሰው ግማሽ ዲያብሎስ የመሆን ሁኔታ ዲያብሎስ በሰዎች ውስጥ ከማደር በባሰ ሁኔታ ገዳይ ነው ምክንያቱም ሰው በምድር ላይ የሚሰራው ልክ እንደ ዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ሰዎች ውስጥ መግባትን አንድ እርምጃ ወደ ፊት አስኬደው ማለት ነው።

## መጽሐፈ ሄኖክ

የሄኖክ መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ስለ ወደቁት መላእክቶች ስራ ይዘረዝራል። የዘፍጥራት መጽሐፍ አሳጥሮ ከሄኖክ መጽፍን ጠቅሶ አስቀምጧል። የወደቁ መላዕክቶች ያደረጉት ከሴቶች ጋር ወሲብ ከማድረግ ያለፈ ነገር ነበር።

በእርግጥ የዘፍጥረት ምዕራፍ 6 የመጀማሪያዎቹ ስምንት ቁጥሮች አጠር ባለ መልኩ የሄኖክ መጽሐፍ ከሚባለው ምዕራፍ ስድስት፣ ሰባት እና ስምንት የተወሰደ መሆኑን ትረዳለህ። የአጋንንቶችን አፈጣጠር ሙሉ ገጽታ ለማግኘት በሄኖክ ተጽፏል ተብሎ የሚታመነውን አንዱን የክርስቲያኖች መጽሐፍ መጽሐፈ ሄኖክን ማየት አለብህ። ከዚህ መጽሐፍ የምጠቅሰው ከሌሎች ክርስቲያን ጸሐፊዎች እንደሚጠቅስ ሰው ነው። በሌሎቹ መጽሐፍቶቼ ላይ ከተለያዩ ክርስቲያን

ጸሐፊዎች ላይ የጠቀስኩትን ማስተዋል ትችላላችሁ። ብዙ ሰዎች የሄኖክን መጽሐፍ ከክርስቲያናዊ ስነ-ፅሁፍ በላይ አድርገው እንደሚወስዱት እና እንደ መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚያዩት አውቃለሁ። በእርግጥ የሄኖክ መጽሐፍ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ተብሎ የሚታወቀው አንድ ክፍል ነው።

ይሁን እንጅ በዚህ ረገድ ሊነሳ የሚችለውን እሰጥ አገባ ወይም ውይይቶች ውስጥ ላለመግባት የሄኖክን መጽሐፍ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን እንደ አንድ ክርስቲያናዊ የምርምር ጽሁፍ ወይም እንደ አንድ እማኝ ጸሃፊ ውሰደው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ያገኘነው ጭላንጭል ሙሉ ስዕሉን ለመሳል በቂ ነው። ከሄኖክ መጽሐፍ የተወሰደው ጥቅስ መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ እንድትረዳው አንዳንድ ክፍተቶችን ለመሙለት ነው። ስምንቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የሄኖክ መጽሐፍ ሃያ ጥቅሶች ማጠቃላያ መሆናቸውን እና ብዙ አስፈላጊ እውነታዎች ከዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ መቅረታቸውን ትገነዘባለህ።

የወደቁት መላእክት መሪ የሆነው ሰምጃዛ እና አጋሮቹ የሰው ልጅ ላይ ያደረሱትን ለራስህ አንብበው።

**መላእክቱም ሟርትን፣ ምታት ማሳየተትን አስተማሩዋቸው፣ ስርማመስን ቅጠል መበጠስን አመላከቷቸው... ትልቅም ጥፋት ሆነ፣ ከእግዚአብሔርም ሸሹ፣ ሴሰኑ፣ ወደ መጥፎ መንገድ ዞሩ እንዲሁም መንገዳቸው ሁሉ የተበላሸ ሆነ።**

ሄኖክ 7፥2፣8፥2 (ከእግሊዘኛው በቀጥታ የተተረጎመ)

**አዛሚራክ ጋኔን መሳብንምታት ማሳየትን ስር ማመስን ሁሉ አስተማር፣ አርማሮስም ጋኔን መሳብን አስተማረ፣ በረቅእልም ኮከብ መቁጠርን አስተማረ፣ ኮከብኤልም ምልክት ማሳየትን አስተማር፣ ጥሞኤልም ኮከብ መቁጠርንአስተማር፣አራቂኤል የመሬትን አካሄድ፣ ሻምስኤል የጸሐይን አካሄድ አስራድኤልም የጨረቃን**

**አካሄድ አስተማር። በሰዎችም ጥፋት ሰዎች ጩሁ፣ ቃላቸውውም ወደ ሰማይ ደረሰ።**

**ሄኖክ 8፥3 (ከእግሊዘኛው በቀጥታ የተተረጎመ)**

የሰው ማህበረሰብ የማርከስ እና የማጥፋት ሥራ የተጠነሰሰው ከክብር በወደቁት እና እግዚአብሔር የሰራውን ሁለ ለማጥፋት በቆረጡት የጨለማው መላእክቶች ነው።

እግዚአብሔር በኢየስስ ደም በሰይጣን ከመርከስ እና የእርሱ ከመሆን ዋጅቶ አዳነን። ወንጌልን በመስበክ ሰዎችን ከሰይጣን የእርኩሰት ጫና ማዳን የእኛ ስራ ነው። የሰውን ልጅ እነዚህ የሰውን ዘር ለማጥፋት ግብ ካላቸው የእርኩሰት ልጆች እክናስመልጥ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር እና መስበክ ስራችን ነው።

2. **ኢጋንንታዊ ውህድ፤** የወደቁ መላዕክቶች ከእንስሳት ጋር ወሲብ አድርገው ግማሽ ሰው፣ ግማሽ እንስሳን ፈጠሩ (የመልዓክ እና የእንስሳ ዲቃላ)

**ሁሉም ሄደው ለራሳቸው ሚስቶችን ወሰዱ፣ እያንዳንዱ ለራሱ አንድ ወሰደ፣ ወደእረሱም እየደረሱባቸው በወሲብ አረከሷቸው…**

**እንዲሁም አውሬዎችን ወፎችን እና ከአሳዎችንና ተሐዋስያንንም እያመለኩ ይበድሉ ጀመር። እር በርሳቸውም ሥጋቸውን ተበላሉ፣ ደምም ጠጡ።**

**ሄኖክ 7፥1-5**

የመልዓክ እና የእንስሳ ዲቃላ የመልአክቶች እና የእንስሶች ቅልቅል ስለ ሆነ ልዕለ ተፈጥሮአዊ እና መንፈሳዊ እንስሳን ፈጠሩ።

መልዓክቶች ከእንስሳ ጋር ወሲብ በመፈጸም የሰሩት ኃጥአት ግማሽ መልአክ ግማሽ እንስሳ የሆነ ዲቃለ ወደ መፍጠር አመራ። መጽሐፍ ቅዱስ አንበሳ ስለ ሆነ የሰው ፍጡር

ይጠቅሳል። ይሄው ክፍል መደበኛው አንበሳ ስላልሆነ አንበሳም ያወራል(2ኛ ሳሙኤል 23፡20)። ይህ የሚያሳየው ሰው መሳይ አንበሶች ከትክለለኛው አንበሳ እንደሚለዩ ነው። አንበሳ የሚመስል ሰው ሲሞት የፍጡሩ መንፈሳዊ አካል ምን የሚሆን የመስላችኋል?

> **ዳንኤልም ተናገረ እንዲህም አለ፦ በሌሊት በራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ አራቱ የሰማይ ነፋሳት በታላቁ ባሕር ላይ ይጋጩ ነበር።**
>
> **አራትም ታላላቅ አራዊት ከባሕር ወጡ፥ እያንዳንዲቱም ልዩ ልዩ ነበረች።**
>
> **መጀመሪያይቱ አንበሳ ትመስል ነበር፥ የንስርም ክንፍ ነበራት፤ ክንፎችዋም ከእርስዋ እስኪነቀሉ ድረስ አይ ነበር፥ ከምድርም ከፍ ከፍ ተደረገች፥ እንደ ሰውም በሁለት እግር እንድትቆም ተደረገች፥ የሰውም ልብ ተሰጣት።**
>
> **እነሆም፥ ሁለተኛይቱ ድብ የምትመስል ሌላ አውሬ ነበረች፥ በአንድ ወገንም ቆመች፥ ሦስትም የጎድን አጥንቶች በአፍዋ ውስጥ በጥርስዋ መካከል ነበሩ፤ እንደዚህም፦ ተነሥተሽ እጅግ ሥጋ ብዪ ተባለላት።**
>
> **ከዚህም በኋላ፥ እነሆ፥ ነብር የምትመስል በጀርባዋም ላይ አራት የወፍ ክንፎች የነበሩአት ሌላ አውሬ አየሁ፤ ለአውሬይቱም አራት ራሶች ነበሩአት፥ ግዛትም ተሰጣት።**
>
> **ከዚህም በኋላ በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ የምታስፈራና የምታስደነግጥ እጅግም የበረታች፥ ታላላቅም የብረት ጥርሶች የነበሩአት አራተኛ አውሬ ነበረች፤ ትበላና ታደቅቅ ነበር፥ የቀረውንም በእግርዋ ትረግጥ ነበር፤ ከእርስዋም በፊት ከነበሩት አራዊት ሁሉ የተለየች ነበረች፤ አሥር ቀንዶችም ነበሩአት።**
>
> **ዳንኤል 7፥2 - 7**

በቀብጽኤል የነበረው ታላቅ ሥራ ያደረገው የጽኑዕ ሰው የዮዳሄ ልጅ በናያስ የሞዓባዊውን የቀብስኤልን ሁለት ልጆች ገደለ፤ በአመዳዩም ወራት ወርዶ በጕድጓድ ውስጥ አንበሳ ገደለ

(2ኛ ሳሙኤል 23፡20)፡፡

የእግዚአብሔርን ፍጥረት ማርከስ እና ማውደም ከሰይጣን ወንጀሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ለዚህ ይቀጣበታል፡፡ ተፈጥሮን እና ፍጥረትን የሚያጠፉትን ሰዎች ልበ በላቸው፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር ማጥፋ ኃጢአት ነው፡፡

በ1ኛ ቆሮንቶስ ላይ የሚያሰተምረን፣ ዝሙትን የምታደረግ ከሆነ በሥጋህ ላይ ኃጢአትን ትሰራለህ፡፡ "ከዝሙት ሽሹ፡፡ ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል" (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡18)፡፡

ስለዚህ መላዕክቶች ከወፎች፣ አውሬዎች፣ ከሚሳቡ እስሳት እና ዓሳዎች ላይ ኃጢአትን ሲሰሩ ከእነርሱ ጋር ዝሙት እየፈጸሙ ነበር፡፡

በተጨማሪም፣ የተለያዩ የአንስሳ ዘሮች ከዛራቸው ውጪ ካለው እንስሳ ጋር ወሲብ እንዲፈጽሙ አድረገው ያልተለመደ ዘር እንዲፈጠር እንዳደረጉ ይታመናል፡፡ እነዚህ ኃጢአቶች ሁሉ እንስሶቹን በማርከስ የተለየ የእንሳስት ዘር ፈጥሯል፡፡ ሰይጣን ይህን የተለያዩ እንስሳ ዘሮችን የማዳቀል እና የማርከስ ስራን አስተባብሯል፡፡ የሄኖክ መጽሐፍ እንደሚያስተምረን የወደቁ መላእክቶች በእንስሳት፣ በወፎች፣ በሚሳቡ እንስሳት እና ዓሶች ላይ ኃጢአትን ሰርተዋል፡፡

ከወደቁ መላእክቶች እና እንስሶች ህብረት የተራቡት ፍጥረቶች ጥለኞች እና እርኩሰት የሞላባቸው ናቸው፡፡ ከፍተኛ የሆነ እርኩሰት እና የስጋ መርከሰን ወደዚህ ዓለም አምጥተዋል፡፡ ስጋን ሁሉ ማርከስ ማለት ፍጥረትን መበከል፣ ማዳቀል እና ማበስበስ ነው፡፡ ዳይኖሰሮች የእነዚህ ህገወጥ የመልዓኮች እና አንስሳት እንዲሁም ሌሎች ልዕለተፈጥሮዓዊ

የሆኑ እንስሶች መዳቀል ውጤት ነው። ዳይኖሰር ማለት የሚሰቡ እንስሶች እና የወፎች ውህደት መሆኑን አውቀሃል? ዳይኖሰሮች እንደ ወፎች ቀዳዳ አጥንቶች እና የዳሌ ውቅር አላቸው። ደይኖሰሮች በመልካቸም፣ በአኗኗራቸውም ግዙፍ እንሽላሊት እና አዞ ነው የሚመስሉት። የዳይኖሰሮች ግዝፈት ከእንስሳት ጋር ለነበረው የመላዕክቶች ጣልቃ ገብነት ምልክት ነው። ጁራሲክ ፓርክን የመሳሰሉ ፊልሞች ስለ እነዚህ በአንድ ወቅት በምድር የኖሩ፣ የተዳቀሉና የረከሱ ፍጥረቶች ባህሪይን የሚገልጡ ናቸው። ጁራሲክ ፓርክ ፊልምን ካየህ ዳይኖሰር የሚበር ወፎች እና የሚሳቡ እንሳሶች ድብልቅ መሆኑን ታስተውላለህ።

መላዕክቶች ከሰዎች ጋር ወሲብ ሲያደርጉ ግዙፍ ሰዎች እንደተወለዱ አስታውስ። የእነዚህን ግዙፍ እንስሶች አመጣጥም የመላዕክቶች ጣልቃ ገብነት ሊሆን ይችላል። እነዚህ ልዕለ እንስሶች መንፈሳዊም ስጋዊም ፍጥረቶች ናቸው። ይህ እንግዳ ነገር ሊሆንብህ አይገባም ምክንያቱም ዛሬ ብዙ ሰዎች ከእንስሳ ጋር ወሲብ ያደርጋሉና።

*የፍጥረት መርከስ የመጣው በሰዎች እና በመላዕክት፣ በመላዕክት እና እንስሳት፣ በሰዎች እና በእንስሳት፣ እና በተለያዩ የእንስሳት ዘሮች መኻከል በተደረገ ህብረት ነው።*

3. **አጋንንታዊ ውህድ፤** እርኩሳን መናፍስት (ያደፉ እንስሶችን የሚመስሉ መናፍስት) የተፈጠሩት በመላእክቶች እና እንስሶች መደባለቅ እና የተለያዩ የተዳቀሉ እንስሳት ከሌላ ዛር ጋር በፈጠሩት መደባለቅ ነው።

**ሰማይም ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ፤ በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት።**

**ጴጥሮስ ሆይ፥ ተነሣና አርደህ ብላ የሚልም ድምፅ ወደ እርሱ መጣ።**

**ጴጥሮስ ግን፦ ጌታ ሆይ፥ አይሆንም፤ አንዳች ርኩስ የሚያስጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ።**

**ደግሞም ሁለተኛ፦ እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ።**

**ሐዋርያት ሥራ** 10፥11-15

**ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጉንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤**

**ራእይ** 16፥13

በዚህ ጥቅስ፣ ጴጥሮስ ስለ ተለያዩ ንጹህ ስላልሆኑ እንስሶች ይናገራል:: ንጹህ ያልሆኑ እንስሶች ሙሴ አትብሉ ያላቸው የእንስሶት ቡድን ናቸው:: አጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እርኩሳን መናፍስት ትሰማለህ:: እነዚህ ንጹህ ያልሆኑ እስሳትን የሚመስሉ መናፍስት መሆን አለባቸው:: ለዚህም ነው እርኩሳን መናፍስት የተባሉት::

እርኩሳን መናፍስቶች አይሁዶች እንደማይመገቧቸው ልክ እንደሚሳቡ እንስሳት፣ የሚያጠቡ ወፎች፣ አዕዋፋት እና የፈረሶች ምድብ ናቸው:: እርኩሳን መናፍስትን የሚገልጽ አንድ ጥቅስ/ክፍል ብቻ ነው ያለው እርሱም እንደ እንቁራሪት ነው የሚገልጸው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጨላማው ዓለም ላይ ስላሉት እና እንስሳትን ስለሚመስሉ እርኩሳን ማናፍስት ታነባለህ:: እርኩሳን መናፍስት የአንስሳት ባህሪይ/መገለጫ እንዳለቸው የሚያሳይ በቂ የሆነ ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ:: እነዚህ መንፈሳዊ እንስሶች ከየት ነው የመጡት? እግዚአብሔር ፈጥሯቸው ነው? እንዴት ተፈጠሩ? ይህ ምዕራፍ እነዚህን ያብራራል:: እግዚአብሔር ሆነ ብሎ እነዚህን እርኩሰ ፍጡራንን ፈጥሯቸው ነው? መንፈሳዊ ክፉ የሆኑ እንስሶች አሉ፤ስለመኖራቸው ደግሞ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ በመጽሐፍ

ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል።

መንፈሳዊ እንስሳ የሆኑ እርኩሳን መናፍስቶች የተፈጠሩት የወደቁ መላእክቶች ከእንስሳ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ሲያደርጉ እና የዚህ ግንኙነት ውጤት የሆኑት ደግሞ እርስ በእርስ ባደረጉት ወሲባዊ ግንኙነት ነው። የወደቁ መላዕክቶች ከአዕዋፋት እና እንስሳት፣ ከዓሶች እና የሚሳቡ እንስሳት ጋር ኃጢአትን ሰሩ። ከእነዚህ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት በማድረግ፣ እርስ በእርሳቸው ፍትወተ ሥጋ የሚያደርጉ ጽንሶችን ፈጠሯቸው። እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነት እርኩሳን(እንስሳዊ) መናፍስት የሚባሉ ባለክፉ መንፈስ እስሳት ፍጥረቶችን ፈጠረ።

(የወደቁ መናፍስት ሰዎችን እንዴት አስማት እንደሚሰሩ፣ እንዴት እንደሚጠነቁሉ እና እንደሚሟርት አስተማሯቸው። የጣኦት አምልኮ እና አጋንንታዊ ስራዎች በብዛት ባሉበት አካባቢ ሁሉ የስጋ ትስስር ባላቸው ሰዎች መኻከል የግብረስጋ ግንኙነት ማድረግ፣ ጥንቆላ፣ አስማት እና ምዋርት ይኖራሉ። የሚያመልኩት ጣኦታት የአጋንንቶቹ ትክክለኛ መልክ ናቸው። ለዚህ ነው አጋንንት የሚለው ቃል መለኮት ወይም ጣኦት በመባል የሚተረገመው። የሚቀጥለውን ከሄኖክ መጽሐፍ ልበ በል፡

> **ሁሉም ሄደው ለራሳቸው ሚስቶችን ወሰዱ፣ እያንዳንዱ ለራሱ አንድ ወሰደ፣ ወደእረሱም እየደረሱባቸው በወሲብ አረከሷቸው።**
>
> **መላእክቱም ሟርትን፣ ምታት ማሳየተትን አስተማሩዋቸው፣ ስርማመስን ቅጠል መበጠስን አመላከቷቸው።**
>
> **እርሱም ፀንሰው ረጃጅም አርበኞች ልጆችን ወለዱ፣ ቁመታቸውም ሶስት ሶስት ሺህ ክንድ ነው። አባት እናቶቻቸው እነሱን መመገብ እስኪሳናቸው ድረስደርሰው እነዚህ ሰው የደከመበትን ገንዘብ ሁሉ በሉ። ረጃጅሞቹ ልጆች እናት አባቶቻቸውን ይበሏቸው ዘንድ ወደመብላት ተመለሱ። እንዲሁም አውሬዎችን ወፎችን እና ከአሳዎችንና ተሐዋስያንንም እያመለኩ ይበድሉ ጀመር።**

**እር በርሳቸውም ሥጋቸውን ተበላሉ፣ ደምም ጠጡ። ያን ግዜም ምድር በደለኞችን ከሰሰቻቸው።**

ሄኖክ 7፥1 - 6

ግማሽ ሰው ግማሽ ግማሽ መልዓክ የሆኑ ፍጥረታት ሲሞቱ ምን ይሆናል? መልአክቶች መንፈስ ስለ ሆኑ እነዚህ ግማሽ እንስሳ እና ግማሽ መልዓክ መኖር ይቀጥላሉ።

እነዚህ አስቀያሚ ግማሽ መልዓክ ግማሽ አንስሳ ፍጥረታት ሲሞቱ፣ የመልዓክ እና የእንስሳ ቅልቅል የሆነው ግራ አጋቢው መንፈሳቸው በጨለማው ግዛት ውስጥ ይኖራሉ። እንስሳ ቢሆኑ ኖሮ ልክ እንደ ሌላው እንስሰሳ ሞተው መሬት ውስጥ በስብሰው ወደ መሬትነት ይቀየሩ ነበር። ይሁን እንጂ የእንስሳ እና የመልዓክቶች ውህደት ስለ ሆኑ በጨለማው የመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ መኖር ይቀጥላሉ። (ጨለማ የማይታየው ግዛት ስም ነው)።

እነዚህን ፍጥረት መሳዮች በቤትህ እና በምትኖርበት አካባቢ ባለው በጨለማው ዓለም ላይ በብዛት ይገኛሉ። ከመወለድህ በፊትም እዛው ነበሩና የትም የመሄድ ፍላጎት የላቸውም። እነዚህን ፍጥረቶችህ በቤትህ እና በአከባባህ አስተውለህ ከሆነ ነቅተህ አንድትጸልይ እና እንቅስቃሴአቸውን እንድታስር እና ሥራቸው እና ሴራቸው ህይወትህ ላይ እንዳይፈጸም ለመከልከል ሊያነሳሳ ይገባል።

እያወራሁ ያለሁት በጣም ለየት ስላሉ መንፈሳዊ ፍጥረት ስለሆኑ አጋንንቶች ነው። የወደቁ መላዕክት እና የእንስሳት ዲቃላ ናቸው። ዲቃላ መንፈስ ናቸው። ለዚህም ነው በግሪክ በጣም ለየት ያለ ስም ያላቸው። በግሪክ ቋንቋ *ዲያሞኒየንስ* ይባላሉ።*ዲያሞኒየን* ማላት ጣኦት እና እርኩስ መንፈስ ማለት ነው።

ሜርሜይድ/Mermaids/ ለምሳሌ የሰው እና የዓሳ ድብልቅ ነው። ግማሽ ሴት ግማሽ ዓሳ የሆነ ፍጥረት ያጋጣማቸውን ሰዎች አውቃለሁ።

ሞሎክ ሰው መስዋእት የሚያቀርቡ በተለይም ህፃን ልጅ የሚሰዋለት የአሞናውያን ጣኦት ስም ነው። ምስሉ ከነሃስ የተሰራ የኮርማ ሰንጋ ጭንቅላት እና የተዘረጋ የሰው እጅ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሙሉ እግዚአብሔር ልጆች አህዛቦች የሚያመልኩትን የአጋንንቶች ምስልን እንዳያመልኩ ያስጠነቅቃል።

**ትሰግዱላቸውም ዘንድ የሠራችኋቸውን ምስሎች እነርሱንም የሞሎክን ድንኳንና ሬምፋም የሚሉትን የአምላካችሁን ኮከብ አነሣችሁ፤ እኔም ከባቢሎን ወዲያ እሰዳችኋለሁ ተብሎ እንዲህ ተጽፎአል።**

**የሐዋርያት *ሥራ*** 7፥43

በታሪክ ውስጥ ታዋቂ የሆኑት ጣኦቶች እና የአህዛብ አምላኮች ምስሎቻቸው አስቀያሚ የሰው እና የእንስሳ ቅርጾች እንዳለቸው አስተውለሃል? የሰው ልጆች እነዚህን ምልክቶች ጣኦቶች ቀርጸው እንዲያመልኩአቸው አጋንንቶች አስተምሮዋቸዋል። *ጠኦት ሁሌም በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ያለው የፍጥረት ምልክት ነው።* ሰይጣን የሰው ልጆች እርሱን እንዲያመልኩ ይመኛል። ሰይጣን ከእግዚአብሔር ላይ ትኩረት እንዲነሳ ይፈልጋል። እነዚህ አጋንንታዊ ፍጥረቶች የሚገኙት በጨለማው ውስጥ ነው፤ እንግዲህ በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ የምንዋጋቸው እነዚህን ነው።

እነዚህ በጥንታዊው ታሪክ ውስጥ በኪነ ጥበብ የታዩት ፍጥረቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹ የእርኩሳን ፍጥረቶች አምሳያዎች ናቸው። ለምሳሌ ራእይ ላይ "አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች

ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ።….ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር" (ራእይ 13፡1፣11)። በጸሎት ውስጥ ሆነህ እኚህን የእርኩሳን ፍጥረቶችን እና አካልን ስትጋፈጥ ከማን ጋር እይተዋገህ እንደ ሆነ እነዚህን ፍጥረታት በአዕምሮህ ውስጥ ሳለቸው።

**አይደለም፤ ነገር ግን አሕዛብ የሚሠዉት ለአጋንንት እንዲሆን እንጂ ለእግዚአብሔር እንዳይሠዉ እላለሁ፤ ከአጋንንትም ጋር ማኅበረተኞች እንድትሆኑ አልወድም።**

**1ኛ ቆሮንቶስ** 10፥20

እነዚህ ፍጥረታት ሊመለኩ እና ሰዎች የእነርሱን ምስል እንዲሰሩ ይፈልጋሉ። ለዚህ ነው በዓለማችን ያሉት ብዙዎቹ ጣኦቶች ግማሽ ሰው ግማሽ እንስሳ የሚመስሉት። ጣኦት አምላኪዎች የእነዚህን ፍጥረቶች ምስል ቀርጸው እንዲሰግዱባቸው ይገደዳሉ። በእርግጥ አጋንንት የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ዴይቲ/መለኮት/ ማለት ሲሆን ትርጉሙም ጣኦት ማለት ነው። ለጠኦት ስትሰዋ ለአጋንንት እየሰዋህ ነው።

# ምዕራፍ 16

# የአጋንንት እና እንስሳ ዲቃላ ምሳሌዎች

እነዚህ የአጋንንት እና እንስሳ ዲቃላዎች በታሪክ፣ በኪነ-ጥበብ እና ባህል ውስጥ በጣም የታወቁ ጠኦቶች ናቸው:: ለዚህ ነው የማትረዳቸውን ምስሎችና ሰው ሰራሽ የስጦታ እቃዎችን ወደ ቤትህ ማምጣት ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብህ ምክንያቱ ይሄ ነው:: ብዙዎቹ እነዚህ አፈታሪኮች ሲመለኩበት የነበሩ የአጋንንታዊ እንስሳ ዲቃላ ምስሎች ናቸው:: የሰይጣን ዓላማ ሁሌም በእግዚአብሔር ፊንታ መመለክ ነው:: እነዚህን አስቀያሚ ፍጥረቶችን በመፍጠር ሰዎች እንዲያከብሩአቸውና እንዲያመልኳቸው ይሰጣቸዋል::

ሞሎክ



ሞሎክ ግማሽ ሰው፣ ግማሽ ፍየል የነበረ ሲሆን ከእግዚአብሔር ዘወር ባሉ ጊዜ እስራኤሎች ሲያመልኩ የነበረ ጣኦት ነው:: የሞሎክ አምላኪዎች ከሚያደርጉት ነገር አንዱ ልጆቻቸውን መሰዋት ነው::

## ሚኖተር



ሚኖተር ግማሽ ሰው ግማሽ በሬ ሆኖ በሰው አካል እና በበሬ ጭንቅላት ተመስሏል። ንግስት ፓሲፋ ለኮርማ የነበራት ያልተለመደ ሥጋዊ መሻት ውጤት ነው ይባላል። የዚህ ህብረት ውጤት ሚኖተር ነው።

## ሌዳ



ይህ ምስል የውሃ ውስጥ ዶሮ/ዳክዬ ንግስት ሌዳን ሲያማልላት የሚያሳይ ነው። ሌዳ እርኩሰትን ያመጣችው የትሮይዋ ሄሌን እናት ነበረች።

## አኪለስ



ይህ ምስል የሚያሳየው አኪለስ የሚባል መልከመልካም እና ጦረኛ የነበረ ከፐለስ እና ባህር ውስጥ ትገኛለች ተብሎ ከሚገመተው የወጣት ሴት መልክ ካለው መንፈስ የተወለደ ነው።

## ኤኪንዳ



ይህ ምስል የሚያሳየው ግማሽ ሴት፣ ግማሽ እባብ የሆነ ጭራቅ ነው። ሰውን ከእነ ነብሱ ትበላ ነበር። የግሪክ አፈ-ታሪክ እንደሚለው ኤኪደና የፎርሲይስ እና የሴቶ ሴት ልጅ ነች። ግማሽ አካሉ እባብ ከሆነ ታይፉን ጋር ተጣምራ ሃይድራ፣ ሰርቤረስ እና ኪማየራን ወልዳለች ይባላል።

## ሜዱሳ



ይህ ምስል ሜዱሳ የምትባል በጸጉር ምትክ ነፍስ ያላቸው ማርዛማ እባቦች ያላት ሴት ነች።

## ሲፊንክስ



ሲፊንክስ ግማሽ ወፍ ግማሽ ሴት ልጅ የሆነ ነው። በተራሮች መግቢያ አከባቢ ትኖራለች ተብሎ ይታወቅ ነበር። መንገደኞችን እንቆቅልሽ ጠይቃ መመለስ ካልቻሉ ትባላቸው ነበር።

## ሴንታወር



ሴንታወር ግማሽ ሰው ግማሽ ፈረስ የሆነ ፍጡር ነው።

## አመን



አመን ጭንቅላቱ ላየ መስበሪያ ያለው የግብጻውያን ጣኦት ነው።

## አናቢስ



አናቢስ የተኩላ ጭንቅላት ያለው የግብጾች አምላክ ስም ሲሆን የሞተ ሰው አካልን ሳይበላሽ ከማቆየት ጋር የያያዘ እንደሆነ በግብጾች አፈ ታሪክ ይነገራል።

ባስቴት



ባስቴት የለማዳ ድመት ጭንቅላተ ባላት ሴት የተመሰለለች አማልክት ነች።

ኪማየራ



ኪማየራ እሳት የሚተነፍስ የአንበሳ አካል፣ የእባብ ጭራ እና መኻል ላይ የፍየል ጭንቅላት ያለው አውሬ ነው። ይህ ኪማየራ የኪማየራን ተራራ ያሸበረ እና መጨረሻ ላይ ቤሌርፎን የተባለ ጀግና የተኮሰበት ሊድ ከአፉ በሚወጣው እሳት ውስጥ ቀልጦ ውስጡን በማቃጠል የተገደለነው።

ሆሩስ



ሆሩስ የጭልፊት ፊት እና የሰው አካል ያለው ጣኦት ነው። የግብጽ ነገስታት ራሳቸውን ከዚህ ጋር ያያይዙታል። በግብጾች ዘንድ ሆረስ በጣም ጠቃሚ ከሆኑት መኻከል አንዱ ምክንያቱም ፈረኦን የዚህ ጣኦት አካላዊ መገለጫ ነው ብለው ያምናሉ።

**የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና።**

**ማቴዎስ 24፥37 (አመት)**

በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ነን! ምናልባት የመጨራሻው ቀናት የመጨረሻ ሰዓታት ውስጥ ነን! በኖኅ ዘምን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል። በኖኅ ዘመን የነበረው እና የሰፈነው ሁኔታ ሁሉም የሰው ልጅ ሲመጣ የሚሆን ይሆናል። ዓለም ሙሉ ክብ ዞራ ኖኅ በኖረበት ዘመን ወደ ነበረችበት ተመልሳለች።

ኖኅን ምን ነበረ ያጋጠመው? በኖኅ ዘመን የተንሰራፋው ሁኔታ ምን ነበር? ኢየሱስ እንደ ነገረን፣ የኖኅ ዘመን ሰዎች ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡ የነበረ ሲሆን ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃደ አላወቀም ነበር።

> **በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥**
>
> **የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።**

**ማቴዎስ 24፥38-39**

ይሁን እንጂ በማቴዎስ ሃያ አራት ላይ ከተገለጸው ባለይ በኖኅ ዘመን የሆኑ ብዙ ነገሮች ነበሩ። ለጥፋት ውኃው ሰበብ የነበረው የሰው ልጅ እርኩሰት ነበር። በዓለም ላይ ታላቅ ክፋት ነበረ። ታላቅ እግዚአብሔር ያለመፍራት በሰው ዘር ውስጥ ነበረ። ከኖኅ ዘመን በፊት ሰዎች ልክ ያለሆነ ወሲብ በመፈጸም የሰው እና እንስሳ ዲቃላ ይወልዱ ነበር። ዛሬም ሰዎች እንስሳ ለማግባ ፈቃድ ይሻሉ።

ቅርብ ጊዜ እናቴን የዓለም ክፋት እርሷ ወጣት ልጅ በነበረችበት 1940ዎቹ አሁን በልጧል ወይ ብየ ጠየቅኳት። "ዓለም እኔ ወጣት ልጅ ከነበርኩበት ጊዜ በበለጠ ሁኔታ አሁን

ክፉ ሆናለች" ብላ መለሰችልኝ።

ለነገሩ ዓለም ከዚህ በፊት ከነበረው ይልቅ ክፉ እየሆነች መሆንዋን ማየት በጣም ቀላል ነው። ከሰላሳ ዓመት በፊት ይሰሩ የነበሩትን ፊልሞች ካየህ የእርኩሰት ደረጃውን ልዩነት በፊልሞቹ ውስጥ በቀላሉ የማየት ትችላለህ። ፋልሞች ሁሌም የገሃዱ ዓለም ነጸብራቆች ናቸው። የዛሬ ፍልሞች ውስጥ የሚታየውን የግድያ ስልት፣ ድግግሞሽ እና ደረጃ ከሠላሳ ዓመት በፊት ይሰሩ ከነበሩት ፍልሞች ሁሉ ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው። በእርግጥ የዛሬ ፍልሞች በከፍተኛ ደረጃ ያደገውን የሰው ልጆች እርኩሰት የሚገልጡ ናቸው። በፊልሞቻችን ውስጥ ከፍተኛ የሆኑ የዝሙት፣ የሴተኛ አዳሪነት፣ የመደራት፣ የግብረሰዶም፣ የግድያ፣ የአስገድዶ መድፈር፣ የዝርፍያ፣ የክህደት፣ የዘር ፍጅት፣ የጥል፣ የጭካኔ፣ የእርኩሰት እና የሁሉም ዓይነት ጦርነት ገጽታዎች ፍንትው ብለው ይታያሉ። ስልሳ በመቶ የበይነ-መረብ /ኢንተርኔት/ ፍለጋዎች የሊቅ የግብረስጋ ግንኙነት የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል/ፖርኖገራፊ/ ሲሆን ሰባ ከመቶ የሚሆኑ ወንዶች ደግሞ ይህን ተንቀሳቃሽ ምስል ባለማቋረጥ ያያሉ።

**እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ።**

**ዘፍጥረት 6፡5**

በኖኅ ዘመን እንደነበረው የሰዎች ክፋት በትልቁ እንደሚጨምር ይጠበቃል። ግድያ፣ ኃጢአት እና ግብረሰዶማዊነት ሺህ እጥፍ ሊጨምር እንደሚችል መጠበቅ እንችላለን። የኖኅ ዘመን ክፋት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት ዘመን ነበር።

# ምዕራፍ 17

# ልዕለ ሰዎች(የሰው ድብልቆች) እንዴት ተፈጠሩ

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥4አመት)**

ከፍጥረት በላይ የሚመስሉ ሰዎች ስለመኖራቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ግን ይኖራል? መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከፍጥረት በላይ፣ ስላልተለመደው ወይም ስለልዕለ-ህልውናዎች ይናገራል? ስለ ግማሽ-ሰው፣ ግማሽ-እንስሳ ተጠቅሷልን? አዎ፣ አለ! ስለ እንዚህ ፍጥረታት የሚያስተምሩ ብዙ ጥቀሶች አሉ::

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥4**

መጽሐፍ ቅዱስ ላይ መላእክቶች ከሰዎች ጋር ወሲብ ሲያደርጉ ያልተለመዱ ፍጥረቶች ወደዚህ ዓለም መጥተዋል:: እነዚህን ፍጥረታት ነው ልዕለ-ሰዎች የምንላቸው:: የዕብራይስጥ ቋንቋ ለእነዚህ ፍጥረታት ሶስት ዓይነት ስሞችን ይሰጣል፡ *ኒፍሊሞች*፣ *ጊቦራውያን* እና *ሴሞች*::

እነዚህ ሶስት ልዕለ ከፊል ሰዎች እርኩሰትን ለዚህ ዓለም አስተዋውቀዋል::

***ኔፊሊሞች*** ግዙፎች ነበሩ። ግዙፍ የሚባሉት ቁመተ ራጅም እና ወፍራም የሆኖ ታላላቅ ሰዎች ናቸው። በዚያ ዘመን ለአደን እና ለድብድ ግዙፍ ሰውነት ብልጫ ነበረው። ይሁን እንጂ ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር በተያያዘ ትልቅነት ጠቃሚነቱን እያጣ ሄዷል።

***ጊቦራውያን*** ግዙፍ ያልሆኑ ግን ደግሞ አምባገነን እና ኃይለኛ ሰዎች ናቸው። የተለመደ ዓይነት ቁመና ያላቸው ነገር ግን ክፉ፣ ኃይለኞች እና ትልቅ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ናቸው። አንዳንዶቹ የዘመናችን ክፉ ሰዎች በቀላሉ ***ጊቦራዊያን*** ሊሆኑ ይችላሉ። አዶልፍ ሂትለር፣ ገነጂስ ካህንና ዮሴፍ ስተንሊን በቀላሉ ***ጊቦራዊያን*** ሊሆኑ ይችላሉ።

***ሴም*** ታወቂ የዝና ሰዎች ናቸው። በሰሩት ሥራ ታዋቂ ለመሆኑ የበቁ ብዙ ሰዎች አሉ። ዛሬ በሰው ልጅ አቅም ሊሆን የማይችለውን ያሳኩ ብዙ አትሌቶች፣ ድምጻውያን፣ ቦክሰኞች አሉ።

እነዚህ ሶስቱ የልዕለ ሰዎች ቡድን በዓለም የተዛመተውን እርኩሰት አስተዋውቀወል። በምድር ላይ ተፈተው የተለቀቁ ሶስት የተለያዩ ክፉ ፍጥረቶች አሉ።

የሰው ዘር ታሪክ በዚህ ምድር ላይ በኖሩ ግዙፍ፣ አምባገነን፣ የሚያስፈሩ እና በዓዕምሮ ለማሰብ የሚከብድ ክፋትን በሰሩ ሰዎች ታሪክ የተሞላ ነው። ታሪካችን በዚህ ምድር ስለኖሩ እና ቅንጣት ታህል ሰብዓዊ ርህራሄ ወይም ሀዘኔታ ስላልነበራቸው ብዙ ሰዎች ያብራራልናል። አብዛኞዎቹ እነዚህ ሰዎች ልዕለ ከፊል ሰዎች ናቸው። ዛሬ ራሱ ሰዎች በራሳቸው ባልንጀራ ላይ ጭካኔ የተሞላበት አያያዝ ሲያደርጉ ማየት እንችላለን። እንዲህ ዓይነት ክፋትን ባልንጀራቸው ላይ የሚያደርሱት እውነት ሰዎች ናቸው? ብለህ እንድትጠይቅ ያደርግሃል። ምንም አይሰማቸውም? ምንም አይገዳቸውም?

በታሪክ ውስጥ ብዙ ሰዎች "እነዚህ አምባገነኖች ባልንጀራቸው የሆነውን ሰውን ሲያሰቃዩ ግን ምንም አይሰማቸውም?" ብለው ጠይቀዋል። እነዚህ ሰዎች ምንም ዓይነት ስሜት እንዳይኖራቸው የሚያደረገው ዋናው ነገር ግማሽ ሰው፣ ግማሽ የወደቀ መልዓክ ስለ ሆኑ ነው። ግማሽ መንፈስና ግማሽ ሰው!

የሆነ ሰው ግማሽ መንፈስ ግማሽ ሰው የመሆኑን ሃሰብ አትንቀፍ። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የተወለደው ከድንግል ማርያም ነው። ኢየሱስ ግማሽ ሰው ግማሹ ደግሞ ሰው ያልነበረ ነው ምክንያቱም የተወለደው ከድግንል ማርያም እንጅ ከሰው ዘር አይደለም። እርሱ አምላክ-ሰው ነበረ። ልዕለ-ልማዳዊ የሆነ አቅም እንደ ነበረው ማየት ትችላለህ። የሰው ልጅ ያልሆነን ሰው ልዕለ-ሰው አድርጎ መጠበቅ ተፈጥሮአዊ ነው።

ዓለም-ቀያሪ ክስተት የሆነው መልአክቶች ከሰው ልጆች ጋር ወሲብ አድረገው ልዕለ ሰዎችን የመፍጠር ታሪክ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ በቻ ነው በጨረፍታ የተጠቀሰው። በይሁዳ እና ጴጥሮስ መጽሐፎ ውስጥም ዋቢ ተደርጓል። የዚህ ክስተት ታሪክ መጀመሪያ የመጣው መጀመሪያ ከተጠቀሰበት ከሄኖክ መጽሐፍ ይመስላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ በጣም አሳዛኝ ነገር ግን ወሳኝ የሆነ ኩነት በጨረፍታ ማስቀመጡ ቅር ያሰኛል። ይሁን እንጅ በጨረፍታ መጠቀሱ አስፈላጊነቱን አይቀንስም ምክንያቱም ሌሎቸ በጣም አስፈላጊ የሆኑት እንደ ዳግም መወለድ የመሳሰሉት ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዴ በአንድ መስመር ብቻ ተጠቅሷል።

የልዕለ ከፊል ሰዎች መፈጠር እና ከዚያ ደግሞ ዛሬ እንደምናውቃቸው የአጋንንቶች መፈጠር መንገድ የመሩትን ደረጃዎች እንይ።

# የልዕለ ሰዎች( ሴም፣ ጊቦራውያን እና ኔፊሊሞ) አፈጣጠር ሂደቶች

1. የሉሲፌር በእግዚአብሔር ላይ ማመጽን ተከትሎ መላእክቶች ከሳማይ ላይ ወደቁ

**ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።**

ራእይ 12፥9

2. የወደቁ መላዕክቶች ቦታ ይዘው የዚህ ዓለም ገዢ ሆኑ

**ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር፤**

1ኛ ቆሮንቶስ 2፥8

3. አንድ አንዶቹ የወደቁት መላዕክቶች ቆንጆ ሴት ልጆችን በማየት ከእነርሱ ጋር ወሲብ ለማድረግ ተመኙ

**እንዲህም ሆነ ሰዎች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው፤**

**የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ።**

ዘፍጥረት 6፥1-2

የእግዚአብሔር ልጆች የሚባሉት ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆኑ ፍጥረቶች ከቆንጆ ሴቶች ጋር ወሲብ ፈጽመው ግዙፎች እና ኔፊሊሞች የሚባሉትን ያልተለመዱ ፍጥረታትን ወለዱ:: እነዚህን የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉትን የወደቁ መላዕክቶች ብለን እንወስዳቸዋለን ምክንያቱም ሰይጣን ከእነርሱ ጋር ተያይዞ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሷል::

መላዕክቶቹ ከእግዚአብሔር ክብር ቢጣሉም አንድ አንድ

የተጣሉ መላእክቶች ደግሞ የባሰ ጥልቅ ክፋት ውስጥ ሰጠሙ። ከወደቁ መላዕክቶች መኻከል በጣም ኃጢአተኞች የሆኑ ከእግዚአብሔር ፊት ርቀው የተጣሉ መልአክቶች አሉ። የእነዚህ ቡድን ነው ከሰዎች ጋር ወሲብ የፈጸሙት። ቆንጆ ሴቶችን ካዩ በኋላ አንድ አንዶቹ የወደቁ መላእክቶች ወደ ፊት ተራምደው የሰው ልጆች በወሲባዊ ግንኙነት ያገኙትን ልምምድ ለመለማመድ ወሰኑ። ይህ ውሳኔ የተወሰነው በሁለት መቶ የወደቁ መላዕክቶች ቡድን ነበር። ክሰተቱ በመጽሐፈ ሄኖክ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል።

መላዕክቶች ከሰዎች ጋር የግብረስጋ ግንኙነት የማድረጋቸው ሁኔታ እንግዳ ሊሆንብህ አይገባም ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መልአክቶች የሰዎችን መልክ በመልበስ ሰዎች የሚያደርጉትን እንደ መብላት፣ መጠጣት እና መተኛት ያደርጋሉ። ይህ ክሰተትም ብዙ ሰዎች ከመጽሐፈ ሄኖክ እንደ ተወሰደ የሚያምኑት የይሁዳ መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎአል። "መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል"(ይሁዳ 1:6 )።

በመጽሐፈ ሄኖክ ውስጥ ከሰዎች ጋር ወሲብ ለማድረግ የወሰኑትን የመላዕክቶች ስም ዝርዝር እንኳን እናገኛለን። በመጽሐፈ ሄኖክ ውስጥ ያለውን መዝገብ በዘፍጥረት ውስጥ ካለው መዝገብ ጋር ልታናጻጽረው አትችልም። በሰማይ ያለውን ሁለንተናቸውን ትተው ወደ ባሰው እርኩሰት ለመግባ የወሰኑትን የመልእክቶች መሪ ስም እናገኛለን።

> **እንዲህም ሆነ ሰዎች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው፤**
>
> **የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ።**

እግዚአብሔርም፦ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፥ እርሱ ሥጋ ነውና፤ ዘመኖቹም መቶ ሀያ ዓመት ይሆናሉ አለ።

በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።

እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ።

እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ።

እግዚአብሔርም፦ የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፥ ከሰው እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቼአለሁና አለ።

ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ።

ዘፍጥረት 6፥1 - 8 (አመት)

ያን ጊዜ ሁሉም አንድ ሆነው ሁሉም እርስ በርሳቸው ተለያይተው ማሉበት ሁሉም ሁለት መቶ ሆኑ። እርዲስ ወደሚባል ቦታም ወረዱ ይኸውም የአርሞንኤም ተራራ ራስ ነው እርስ ብርሳቸው ተለያይተው ምለውበታልና የአርሞንኤምንም ተራራ በማላ ተራራ ብለው ጠሩት። አለቆቻቸውም ስማቸው ይህ ነው መጀመሪያው አለቃቸው ስማዝያ ነው። ዑራኪበራምኤል፣ አኪቢኤል፣ ጣምኤል፣ ራሙኤል፣ ዳንኤል፣ ኢዚቃኤል፣ ሱሩቃያል፣ አስኤል፣ አርሞርስ፣ በጥርኤል፣ አናንኤል፣ ዘቂቢ፣ ሳምሳፒኤል፣ ስርትኤል፣ ጡሩኤልያም፣ ያኤል፣ እራዝያል፣ ነው የሁለቱ መቶ አለቆች አለቆቻቸው እኒህ ናቸው።

ሄኖክ 6፥1 - 8

4. የወደቁ መላእክቶች ብዙ ክፉቶችን ለሰው ልጆች ያስተማሩ እና ደም ማፍሰስን፣ ምዋርትን እና የተለያዩ እርኩሰትን ለሰዎ ልጆች አስተዋውቀዋል።

በመጽሐፈ ሄኖክ ውስጥ ተለይተው ክፋትን ያስተማሩት

መላእክቶች ተጠቅሰዋል። ብዙ ታላላቅ ክፋቶች ወደዚህ ዓለም የመጡት በወደቁ መላዕክቶች መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። የተወሳሰቡ ኃጢአቶች እና የተወሳሰቡ የመተላለፍ ሚስጥራት ሊብራሩ የሚችሉት በመኻከላችን ባሉት አስሰከፊዎቹ የክፋት ፍጥረታት መገኘት ብቻ ነው። ዓመፃ ሚስጢር ነው ምክንያቱም በአንድ በጎ አሳቢ ሰው ለመግለጽ ያደግታልና።

ብዙ ሰዎች ዛሬ የሚያደርጓቸው ነገሮች የተተዋወቁት በወደቁ መላዕክቶች ነው። እነዚህ ነገሮች በሰው ዘር መኻከል ክፋትን ለማስፋፋት ጠቅሟል። ሰዎች እርስ በእርስ ለመገዳደል የሚያስችላቸውን የጦር መሳርያ መሰራትን ተምረዋል። ሰዎችን ወደ ዝሙት እና ኃጢአት ለመምራት ሰዎች ራሳቸውን ማስጌጥ እና ማስዋብን ተምረዋል። ሰዎች ስለ ጥንቆላ፣ አስትሮሎጂ፣ ምዋርት እና የቅጠላ ቅጠል እና መድኃንት አጠቃቀምን ተምረዋል። በእርግጥ ዛሬ እንደ ቀላሉ የምናያቸው ብዙ ነገሮች ወደዚህ ዓለም በወደቁ መላእክቶች በኩል የተተዋወቁ ክፉዎች ናቸው።

**አዛዝዔልም ለሰዎች ሾተልና ሰይፍ *መሥራትን* ጋሻ መሰጐድንም ጥሩር *መሥራትን*ም አስተማራቸው። ከነሱ በታች የሚሆኑ *ሥራ*ቸውንም ሌላ ጌጽና አምባሮችን ቅንድብ መሸለልንና ዓይን መኳልን ከተመረጠና ከከበረ ዕንቊ ሁሉ የሚበልጥ ዕንቊንም እንሶስላ መሞቅን ሁሉ የዓለምንም ለውጥ አሳይዋቸው/ፈረሱን በቅሎውን ሰው ማድረግ/። ፅኑ በደል ብዙ ሰሰንም ተደረገ ሳቱ ሰሰኑ *ሥራ*ቸውም ሁሉ ጠፋ። አሚዛራክ ጋኔን መሳብን ምታት ማሳየትን *ሥ*ር መማስን ቅጠል መበጠስንም ሁሉ አስተማረ፣ አርማሮስም ጋኔን መሳብን አስተማረ።**

**በረቅእልም ኮከብ መቊጠርን አስተማረ። ኮከብኤልም ምልክት ማሳየትን አስተማረ። ጥሞኤልም ኮከብ መቊጠርን አስተማረ። አስራድኤልም የጨረቃን አካሄድ አስተማረ። በሰዎችም ጥፋት ሰዎች ጮሁ ቃላቸውም ወደ ሰማይ ደረሰ።**

**ሴቶቻቸውም ግዙፎቹን ወለዱ፣ ከዚያም የተነሳ ምድር ሁሉ በክፋት ደም የተሞላች ሆነች።**

**ሄኖክ 8፡1 - 3፣9፡9**

## 5. የወደቁ መላእክቶች ከቆንጆ ሴቶች ጋር ወሲብ በማድረግ ኔፍሊሞች (ግዙፎች) የሚባሉ ግማሽ መንፈስ-ግማሽ ሰው የሆኑትን ሰዎች ወለዱ

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፡4**

በወደቁ መላእክቶች እና በሰዎች ህብረት ሶስት ዓይነት ከፍል ሰዎች ተልደዋል:: የመጀመሪያዎች ከፍል ሰዎች ኔፍሊሞች ይባላሉ:: እነዚህ ኔፍሊሞች ግዙፍ ወይም እጅግ ታላቅ ሰዎች ናቸው:: መላዕክቶች ከቆነጃጅት ሴቶች ጋር ወሲብ ሲፈጽሙ አረገዙ እና ግማሽ መልአክ እና ግማሽ ሰው የሆኑ ህፃናትን ወለዷቸው::

ምናልባት ይህን መላእክቶች ከሰዎች ጋር ወሲብ አደረጉ የሚለውን ሀሳብ መጀመሪያ ስትሰማ ሊያስቅህ ይችላል:: ኢየሱስ ግን መላዕክቶች አያገቡም ሲል ወሲብ መፈጸም አይችሉም ማለቱ አይደለም:: ብዙ ሰዎች አሉ ባያገቡም ወሲብ ግን የሚያደርጉ:: በግልጽነት እነዚህ መላእክቶች የበሲብ ብልቶች ያላቸው ሲሆን ከሴቶች ጋርም ግንኙነት ለማድረግ ችለዋል::

በመላእክቶች እና ሰዎች ግንኙነት የተወለዱት ግዞፎች በጣም ትልቅ ተክለ ሰውነት ያላቸው ሰዎች ስለሆኑ በዚህ መጠናቸው ምድርን ተቆጣጠሯት:: ባልሰለጠነው ዓለም ግዙፍ መሆን የበላይ መሆን ነበር:: በማንኛውም ግጥሚያ ውስጥ

የሰውነትህ መጠን በራሱ አብላጫ ያስሰጥሃል። ጎልያድ ለእስራኤላውያን ታላቅ ስጋት የነበረው ለዚህ ነው። ግዙፎቹ በጣም ክፉዎች እና በማስበርገግ ባህሪያቸው የታወቁ ሆኑ። እነዚህ ሰዎች ግማሽ የወደቁ መላዕክት ግማሽ ደግሞ ሰዎች እንደነበሩ አስታውስ።

እነዚህ የልዕለ-ሰዎች ዘር ከሰው ዘር ጋር ሲገናኝ ያልተለመደ ፍጥረቶች ተፈጠሩ። እነዚህ ያልተለመዱ ፍጥረታት የልዕለ-ሰው/ልዕለ-ልማዳዊ ሰው መልክ ያላቸው ሲሆን ስድስት የእጅ ጣት መስመር ያላቸው፣ ስድስት የእግር ጣት መስመር ያላቸው እና ሁለት የጥርስ መስመር ያላቸው ሆኑ። የሚያስፈሩ፣ አስቀያሚ፣ ለማየት የሚያስደነግጡ ዓይነት ፍትረቶች ሆኑ።

እስራኤሎች በግዙፎቹ ሰዎች ምክንያት ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት መፍራታቸው የሚገርም አይደለም። ሙሴ እስራኤላውያንን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲመራቸው አስሩ ሰላዮች እነዚህን ግዙፍ ሰዎች አይተዋቸው ፈሩ። ሰላዮቹ በዚያ ምድር በጣም ግዙፍ ሰዎች አሉ ሲሉ እኮ ቆርጠው እየቀጠሉ አልነበረም። የሚገጥሙአቸው እውነተኛ ግዙፍ ሰዎች ነበሩ። ዳዊትም ራሱ ጎልያድ ከሚባል ግዙፍ ሰው ጋር መግጠም ነበረበት። ጎልያድ ግዙፍ የሆኑ ወንድሞችም ነበሩት። እነዚህ ዛሬ ጨርሶ የማይታመኑ የሚመስሉ ነገር ግን ደግሞ በእውነት ሆነው ያለፉ ታሪኮች ናቸው።

የሚገርመው፣ የምድር ዘር ሁሉ በአንድ ወቅት ግዙፍ ዘራቸው በምድሪቷ ላይ እንደ ኖረ የሚያሳይ ታሪክ እንዳለቸው ማንኛውም ተራ ምርምር ይገልጣል። ጃክ እና ቤያንስቶክ፣ የገሊቨር ጉዞ እና ሄርኪውልስ የመሳሰሉ ታሪኮች የመጡት ግዙፎች በአንድ ወቅት በዚህ ምድር ላይ መኖራቸውን የሚያሳዩ ናቸው። በጋና ውስጥም አሴቡ አመንሬ የሚባል

ዝነኛ ግዙፍ ሰው እንደኖረ የሚተርክ ታሪክ አለ።

በግዙፎቹ እና ወደዚህ ምድር ባመጡት እርኩሰት ላይ የነደደው የእግዚአብሔር ቁጣ ለኖኅ ጎርፍ ምክንያት ሆኖ አልፏል። በሚገርም ሁኔታ ሁሉም የምድር ህዝብ ቡድን የታላቅ ጎርፍ ታሪክ አላቸው። የታሪኮቹ ዝርዝር ትንሽ የተለያየ ቢሆኑም ፍሬው ነገር ግን በእነዚህ ጎርፎች ምክንያት ብዙ ሞቶ ጥቂት ሰዎች እና እንስሳት ብቻ ቀርተዋል። አብዛኛዎቹ ታሪኮች የሚጠቁሙት እግዚአብሔር ሰውን ማስጠንቀቁ ነው። አውስትራሊያ፣ ባቢሎን፣ በርማ፣ ጉያና፣ አይስላንድ፣ ካናዳ፣ ግሪክ፣ ህንድ፣ ጣሊያን፣ ሚክሲኮ፣ አላስካ፣ ሩሲያ እና ሀዋይ ምድርን ስላጥለቀለቀው ታላቅ ጎርፍ አፈ-ታሪኮች እና ታሪኮች አሏቸው።

## 6. የወደቁ መላዕክቶች ከቆነጃጅት ሴቶች ጋር ወሲብ አድርገው ‘ሴም’ (ታዋቂ ሰዎች) የሚባሉ ግማሽ የወደቀ መልዓክ እና ግማሽ ሰው ወለዱ።

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥4**

ሁለተኛው በወደቁ መላዕክቶች እና ሰው ዘር ግንኙነት አማካይነት የተፈጠሩት የግማሽ ሰው ዓይነት ሴም ይባላሉ። ሴሞች በአጭሩ ታዋቂ ሰዎች ናቸው። ታዋቂነታቸው የተፈጠረው ባላቸው የተለየ ብቃት ነው። እነዚህ ሰዎች የልዕለ-ሰው ብቃት አላቸው። በክፉ ነገር እዲታወቁ እና ታዋቂ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምን ሰርተው እና ምን አከናውነው ነው? እስቲ ዛሬ ሰውን ታዋቂ የሚያደርገው ምን እንደ ሆነ ራስህን ጠይቀው።

አንድ አንድ ሰዎች በፈጠራቸው ታዋቂ ይሆናሉ። ሌሎቹ በገነቡት ነገር ታዋቂ ይሆናሉ። አንድ አንዶቹ ደግሞ ባሸነፉት ጦርነት ታወቂ ሰዎች ይሆናሉ። ሌሎቹ ደግሞ ታዋቂ ሙዝቀኞች፣ ታዋቂ ተዋናዮች፣ ታዋቂ አትሌቶች፣ ታዋቂ ድምጻውያን፣ ታዋቂ ስፖርተኞች፣ ታዋቂ ተዋጊዎች፣ ታዋቂ ነፍሰ ገዳዮች፣ ታዋቂ ተከታታይ ገዳይ፣ ሴሜት የሌላቸው ታዋቂ ሰዎች። አንድ አንዶቹ እንዲያውም በሚሰሩት የወሲብ ፊልም፣ ወሲባዊ ጀብዱ እና ብቃታቸው ይታወቃሉ።

በእርግጥ የምትሰማቸው አንድ አንድ ታዋቂ ሰዎች የተለመደው የሰው ልጅ ሳይሆን ሴሞች ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ አንድ ሊያጋጥሙህ የሚችሉ ሴቶች በወሲባዊ አደራራግ እና ባህሪያቸው ልዕለ-ሰዎች ናቸው።

# እየጠፉ ያሉ ልዕለ-ሰዎች

ሰዎች ያልሆኑ ሰዎች አሉ? አንድ ሐሙስ ማታ ከቤተክርስቲያን በኋላ ብዙ ሰዎች በተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ላይ ወዲህ ወደዚያ ይሉ ነበር። አንዲት የቤተክርስቲያኔ አባል የሆነች የህግ ባለሙያ ሴት መኪናዋን አስነስታ ከማቆሚያ ስፍራ ለመውጣት መንዳት ጀመረች። ዋና በሩን ለቅቃ ሳትወጣ ከጉባዔው የወጣች የምትመስል አንዲት ሴት ሸኚኝ ብላ ምልክት ሰጠቻት።

የህግ ባለሙያዋ “በዚህ መንገድ ነው የምትሄጅው?” ብላ ጠየቀቻት። ወጣትዋ ሴት ልጅም አንገትዋን ነቅንቃ ስትመልስ በቃ ከኋላ መቀመጫ ላይ ግቢ ብላት እየነዱ የቤተክርስቲያንን ግቢ ለቅቀው ወጡ። አንድ ሁለት ኪሎ ሜትር እነደሄዱ የህግ ባለሙያ ሴቷ የወጣቷ ዝምታ ያልተለመደ ሆነባት። ምን እንደሆነች ለማየት ወደ ኋላ ዘወር ብላ አየቻት። ልጅቷ መኪና ውስት አለመኖርዋን ስታውቅ ሰማይ እና ምድር ጨለመባት። በአየር ወስጥ ጠፋች። የህግ ባለሙያዋ ሴት በጣም ደነገጠች

ምክንያቱም ከጥቂት ደቂቃ በፊት መክናዋን የተሳፈረችው እውነተኛ ሴት ልጅ ከእይታ ተሰወረችባት። በእርግጥ በጣም አስደንጋጭ አጋጣሚ ነበር እና እኔ ራሴ ቤቷ ሄጄ ማረጋጋት እና ሊያጠቋት ከፈለጉት እንግዳ ነገሮች እንድትጠበቅ መጸለይ ነበረብኝ። የማልረሳው ሌሊት ነበር። የተረዳሁት ነገር 'ሰዎች' ያለሆኑ ሰዎች መኖራቸውን ነው!

# የ "ዓሳዋ ሴት"

አንድ ቀን አንድ የቤተክርስቲያናችን አባል ዳግም ከመወለዱ በፊት ያጋጠመውን ገጠመኝ አጫወተኝ። የሳምንቱን መጨረሻ ከእርሱ ጋር ለማሳለፍ የምትፈልግ አንዲት ቆንጆዬ ልጅ አገኘሁ አለ። ገና ከመጀመሪያው የሆነ ያልተለመደ ነገር አይሁባት አለ። ምግብ ባቀረበ ቁጥር ጾም ላይ መሆንዋን ትነግረዋለች። እንግዳ ነገር ሆኖበት እያለ እንደ ማንኛውም የሴት ጓደኛ ከእርሱ ጋር ወሲብ ለማድረግ ግን ፈቃደኛ ነበረች።

በሁለተኛው ሌሊት ተነሳና ይህቺ ሁሌም የምትጾመውን አድሲቷን ፍቅረኛውን ማሻሸት ይጀምራል። አንሶላ ውስጥ ሆኖ ከደረቷ ጀምሮ ወደ ታች እያሻሸ ይወርዳል። እጁ ጭኗ አካባቢ ሲደርስ የሆነ እርጥብ እና ቀዝቃዛ ነገር ተሰማው። ደነገጠ እና ከአንሶላው ስር ምን እንደሆነ ለማየት ወሰነ። እዛው በህይወቱ አጋጥሞት በማያቅ ሁኔታ ደነገጠ። ከወገቧ በታች ቱና የምትመስል ዓይነት ዓሳ ነች! ማመን አቅቶት አፍጥጦ ሲያያት ዓሳ ከሆነች ሴት ጋር አልጋ ውስጥ መሆኑን አረጋገጠ። ከአንተ ጋር አልጋ ውስጥ ያለቸው ሴት እውነተኛ ሰው አለመሆንዋን ስታውቅ አትፈራም?

ከትንሽ ቆይታ በኋላ በዚያኑ ዕለት ወደ እውነተኛ ሰው የተመለሰች የምትመስለው ሴትየዋ ማስጠንቀቂያ ሰጠችው። "ማታ ያየሄውን ነገር እንዳትናገር።" ከቤቱም ወጥታ ሄዴች

ከዚያ በኂላ አይቷት አያውቅም:: ይህ ምስክርነት እውነተኛ ሰዎች ስላልሆኑ ሰዎች ሌላኛው ምሳሌ ነው:: እነዚህ 'ከፊል-ሰው' የምንላቸው ናቸው!

***የሴሞች*** እና የኔፊሊሞች ልዩነት ***ኔፊሊሞች*** ግዙፍ የሆኑ ሰዎች ናቸው ***ሴሞች*** ደግሞ የተለመደ ቁመና ያላቸው ነገር ግን ታዋቂዎች ናቸው:: ***ኔፍሊሞች*** በቁመናቸው ምክንያት እንደ ጠፉ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ ***ሴሞች*** እየኖሩ እና ሳይነቃባቸው ቀጥለዋል::

ዛሬ ግዙፍ ሰዎ የሉንም ይሁን እንጂ ልዕለ-ልማዳዊ እና የከፊል-ሰው አቅም ያላቸው ብዙ ታዋቂ ሰዎች አሉ:: ያልተለመደ ብቃት ያላቸው ሯጮች፣ ቦክሰኞች፣ ድምጻውያን፣ ተዋንያን እና ነፍሰ ገዳዮች አሉን:: ዳይኖሰሮች በቁመናቸው ምክንያት ጠፍተዋል ይሁን እንጂ የተመጠነ ቁመና ያላቸው እባቦች፣ ጉንዳኖች፣ አጋዘኖች፣ ድመቶች፣ ውሾች፣ አንበሶች በህይወጥ ቀጥለዋል:: በጣም ግዙፍ የሆነ ነገር ለማጥፋት የተመቸ ዒላማ ይሆናል::

**7. የወደቁ መላዕክቶች ከቆንጆ ሴቶች ጋር ወሲብ በመፈጸም 'ጊቦራውያን' (አምባገንኖች እና አስፈሪዎች) የሚባሉትን ወለዱ::**

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥4**

ሶስተኛው የተፈጠሩት የከፊል ሰዎች ዓይነት *ጊቦራውያን* ይባላሉ:: ይህ የተለያየ ትርጉም የሚሰጥ የተለየ የዕብራይስጥ ቃል ነው:: *ጊቦር* ማላት አምባገነን ማለት ነው:: አምባገነን በጨቋኝነት፣ በኢ-ፍትሃዊነት እና በማን አለብኝነት ኃይልን

ተጠቅሞ የሚገዛ ነው። ሁላችንም የእንደዚህ ዓይነት መሪዎች ብዙ ምሳሌዎች አሉን። እነዚህ አምባገነኖች ሲሞቱ የወደቁ መላዕክቶች እና የእነርሱ ልጆች በዚህ ምድር ላይ አጋንንቶች ሆኑ።

በሰለጠነው ዘመን እንደ ሀኒባል፣ አዶልፍ ሂትለር፣ ሰታሊን፣ ጁሊየስ ቄይሳር፣ ካሊጉላ የመሳሰሉ ሰዎች አምባገነኖች ሲሆኑ ምህረት አልባ በሆነው የሰው ህይወት ጥፋት ይታወቃሉ። እነዚህ ሰዎች በምድር ላይ እየኖሩ ያሉ *ጊቦራውያን* ሳይሆኑ አይቀሩም።

# ጉልበተኞች እና አምባገነኖች

ስሜት እና ርህራሄ የሌላቸው ብዙ ሰዎች በእኛ መኻከል ኖረዋል። የኮሚኒዚም መስራች የሆነው ሌኒን እንዲህ ስል አስታወቀ "በአስቸኳይ እና በድብቅ ሽብሩን ማዛገጀት አስፈላጊ ነው።" ህዝባዊ ሽብር ለመፍጠር ቴልግራሞችን ልኳል። ይህ ከቴልግራሞች አንዱ ነው፡

"ጓዶች! በአምስቱ ግዛቶቻችሁ የተቀሰቀሰው የኩላክ አመጽ ያለ ምንም ርህራሄ መጨፈለቅ አለበት...እነዚህን ሰዎች ምሳሌዎ ልታደጓቸው ይገባል። (1) በትንሹ 100 የሚሆኑትን ኩላኮች፣ ሀብታሞችን እና የታወቁ ደም መጣጮችን ስቀሏቸው(ማለቴ ሰው እንዲያያቸው በአደባባይ ስቀሏቸው)። (2) ስማቸውን አሳትሙ (3) እህሎቻቸውን ያዙ። (4) ታጋቾችን በትላንቱ ቴሌግራሜ ትዕዛዝ መሰረት ለዩአቸው። በኪሎሜትሮች ርቀት ላይ ሆኖ ሰዎች አይተው እንዲረዱ፣ እንዲሸበሩ፣ እና ደም መጣጭ ኩላኮችን እየገደልን መሆናችንን እና እንደምንቀጥል ለራሳቸው እንዲነገሩ አድርጉ። ከሠላምታ ጋር - ሌኒን። ማሳሰቢያ፡ ጠንካራ ሰዎችን ፈልጉ።"

ፖሊሶች እና መርማሪዎች አሰቃቂ የምርመራ ዘዴዎችን

እንደሚጠቀሙ ብዙ ሪፖርቶች አሉ። ባልንጀሮቻቸውን ሲገድሉ እና ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ሁኔታ ሲያሰቀዩአቸው እነዚህ ሰዎች ግን ቅንጣት ታክል ርህራሄ ይኖራቸዋል ያሰኝሃል።

በኦዴሳ መኮንኖች በዝግታ እቶን ውስጥ እንዲገቡ ወይም የሚፈላ የውሃ ታንከር ውስጥ እንዲጣሉ ተደርገዋል።

በካርኪብ የራስ ቆዳን መግፈፍ እና የእጅ ቆዳን መላጥ የተለመደ ነው፤ ቆዳቸው ተልጦ ጓንት ይሰራበታል። ውሃ የቋጠረው የእጅ ቆዳ መላጥ እስኪችል የተጠያቂውን እጅ በፈላ ውሃ ያቃጥሉታል፣ ይህ እንግዲህ ተጠያቂውን በሚደማ እና በተገለጠ የእጅ ስጋ ብቻ ሲያስቀረው አሰቃቂዎቹን ደግሞ 'የሰው ቆዳ ጓንት' ያጎናጽፋቸዋል።

ሰዎች ራቁታቸውን በሚስማር በተጠቀጠቀበት ማርሜል ውስጥ ገብተው እንዲገለባበጡ ይደረጋል። ተጠያቂዎች በዲንፐሮፔርትሮቭስክ ተስቅለዋል ወይም ደግሞ በድንጋይ ተወግረው ሞተዋል።

በክሬመንሽክ የቤተክህነት ሰዎች ተወግተው ሲሞቱ ገበሬዎች ደግሞ በቁማቸው ተቀብረዋል። በኦሬል ክረምት መንገድ ላይ በታሰሩት እስረኞች ላይ የበረዶ ግግር እስኪሆኑ ድረስ ውሃ ፈስሶባቸዋል።

በአርማቪር ውስጥ በቆዳ ጠፍር ጫፍ ጫፍ በታሰሩ እና በሚዋጉ የብረት ጣውላ ውስጥ የሰው አንገት አስገብተው የራስ ቅላቸውን ሰብረው ገድለዋቸዋል።

በኪየቭ በአንድ በኩል በተዛጋ የብረት ቱቦ ውስጥ አይጥ በማስቀመጥ የተከፈተ አፉን ደግሞ የእስረኛ አካል ላይ በመሰካት አይጥዋ የእስረኛውን ገላ ቦርቡራ ለማምለጥ አስክትሞክር ድረስ ቱቦውን በኤሌክትሪክ ገመድ ያግሉታል።

በአዶልፍ ሂትለርሰ ስር ናዚዎች ሰብዓዊ ስሜት ያላቸው አይመስሉም ነበር።አንድ አንድ ሰዎች ሂትለርን ለመገልበጥ ሙካራ ሲያደርጉ ጠንሳሾቹ ተይዘው ተቀጡ። ተሰቃይተው እስኪሞቱ ድረስ በካሜራ የቀረጹ ነበር። አንድ አንዶች በካሜራ ፊት ታንቀው ሲሞቱ ሌሎቹ ደግሞ በካሜራ ፊት የስጋ ማንጠልጠያ ወይም የፒያኖ ገመድ ላይ ተሰቅለው ሞቱ።

እንደዚህ ዓይነቱ የተጠቃለለ ክፋት ነበር የኖኅ ዘመን ጎርፍን ያስከተለው። እግዚአብሔር የሰውን ዘር በውኃ ውስጥ በማስጠም ከፊል ሰዎችን እና የተበከሉ የሰው ዘርን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ተገደደ። ከላይ ያልኳቸው በሙሉ በስምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች የተጠቃለለ ነው። ከላይ የጠቀስኳቸው የመጽሐፈ ሄኖክ ሃያ ቁጥር ማጠቃላያዎች ናቸው። መጽሐፈ ሄኖክ እና ዘፍጥራት በእነዚህ መገለጦች ምክንያት ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ነው። እነዚህ ሁለት መጽሐፎች የእርኩስ መንፈስ መኖርን እና የእርኩስ ሰዎች መኖርን ለማብራራት ይጠቅማሉ። እነዚህ ጽሑፎች ለእርኩሰ ፍጥረታት መፈጠር ምክንያት የሆኑትን ያብራራሉ።

8. **እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ የላከው ኔፊሊሞችን (ግዙፎች)፣ ጊቦራውያንን(አምባገነን እና ጉልበተኞች)ና ሴሞችን(ታዋቂ ሰዎችን) ለማጥፋት ነበር።**

> **እግዚአብሔርም ምድርን አየ፥ እነሆም ተበላሸች፤ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና።**
>
> **እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፦ የሥጋ ሁሉ ፍጻሜ በፊቴ ደርሶአል፤ ከእነርሱ የተነሣ ምድር በግፍ ተሞልታለችና፤ እኔም እነሆ ከምድር ጋር አጠፋቸዋለሁ።**
>
> **ዘፍጥረት 6፣12-13**

የከፊል ሰዎች በመገኘት ምክንያት የምድር እርኩሰት እጅግ ስለበዛ፤ እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ አጥፍቶ እንደገና

ለመጀመር አሰበ:: የጥፋት ውኃው ሲመጣ ሁሉም የሰው ዘር፣ ሁሉም ግዙፎች፣ ሁሉም ታዋቂ ሰዎች እና ጉልበተኞች በውኃው ሰጥመው አለቁ:: ዓለም በኖኅ እና ሶስቱ ልጆቹ ብቻ ቀረች:: ሁሉም ነገር ስለ ጠፋ ከዚያ በኋላ ግዙፎቹ፣ አምባገነኖቹ እና ጉልበታሞቹ አልነበሩም:: ሁሉም ጊቦራውያን፣ ሴሞች እና ኔፊሊሞች ከምድረ ገጽ ላይ ሙሉ በሙሉ ተጠረጉ::

> **ያን ጊዜም ልዑል ገናና የከበረ ፈጣሪ ተናገሪ ወደ ላሜክ ልጅ ወደ ኖኅም ሱርያልን ላከው። በኔ ስም አምነህ ራስህን ከማየ አይህ ሰውር በለው ምድር ሁሉ ትጠፋለችና የሚመጣ የመከራውን መጨረሻ ግለጽለት አለው በዚችም ምድር ሁሉ ላይ የጥፋት ውሀ የመጣ ዘንድ አለው በውስጧም ያለው ሁሉ ይጠፋል።**

ሄኖክ 10፥1-2

9. **ኔፊሊሞች (ግዙፎቹ)፣ ጊቦራውያን (አምባገነን እና ጉልበታሞቹ) እና ሴሞች (ታዋቂ ሰዎች) ከጥፋት ውኃ በኋለ እንደገና ታዩ::**

ጊቦራውያንን፣ ሴሞችን እና ኔፍሊሞችን ካጠፋው የጥፋት ውኃ ብዙ ዓመታት በኋላ አሁንም በምድር ላይ ስላሉ ግዙፎች እናነባለን:: ከዚህ በታች ከጥፋት ውኃ ረጅም ዓመት በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናነባቸውን የግዙፎች ረጅም ዝርዝር አለ:: ሴሞች፣ ኔፊሊሞች እና ጊቦራውያን በጥፋት ውኃው ጊዜ የሚያገግሙበትን መንገድ ማግኘታቸው በጣም አሳሳቢ ነው:: በጣም ስለ ታወቁና ከኖኅ የጥፋት ውኃ በኋላ የነበሩትን የግዙፎች ዝርዝር አብረን እንመልከት::

***አክመን፡*** "ካሌብም ሦስቱን **የዔናቅን ልጆች** ሴሲንና **አኪመንን** ተላሚንም ከዚያ አሳደደ( ኢያሱ 15፡14)::"

***ዔናቅ፡*** "ስለ ሰለሉአትም ምድር ክፉ ወሬ ለእስራኤል ልጆች እያወሩ፦ እኛ ዞረን የሰለልናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች

የምትበላ ምድር ናት፤ በእርስዋም ዘንድ ያየናቸው ሰዎች ሁሉ ረጃጅም ሰዎች ናቸው። በዚያም ከኔፊሊም ወገን የሆኑትን ኔፊሊም፥ **የዔናቅን** ልጆች፥ አየን፤ እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን፥ ደግሞም እኛ በዓይናቸው ዘንድ እንዲሁ ነበርን አሉ” (ዘኁልቁ 13፡32-33)

***አርባቅ:*** “ከይሁዳ እና ከስምዖን ነገዶች ደግሞ ከዚህ በታች በስም የተጠቀሱትን ከተሞች በዕጣ መበደቡላቸው። እነዚህም ከተሞች የሌዊ ልጆች፣የቀዓት ጎሳዎች ለሆኑት ለአሮን ዝርያዎች የተመደቡ፤ የህም የሆነው የመጀመሪያው ዕጣ ለእነርሱ ስለ ወጣላቸው ነበር፤ እነርሱም በተራራማው የይሁዳ ምድር ያለችውን ኬብሮን የተባቸውን ቂርያት አርባቅን በዙሪያዋ ካለው መሰመሪያ ጋር ሰጧቸው፤ አርባቅ የዔናቅ አባት ነበረ”(ኢያሱ 21፡9-11 አመት)

***ጎልያድ፡*** “ከፍልስጥኤማውያንም ሰፈር የጌት ሰው ጎልያድ፥ ቁመቱም ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነ፥ ዋነኛ ጀግና መጣ። በራሱም የናስ ቍር ደፍቶ ነበር፥ ጥሩርም ለብሶ ነበር፤ የጥሩሩም ሚዛን አምስት ሺህ ሰቅል ናስ ነበረ።” (1ኛ ሳሙኤል 17፡4-5)

***ይሽቢብኖብ፡*** “ከራፋይም ወገን የነበረው ይሽቢብኖብ ዳዊትን ይገድል ዘንድ አሰበ፤ የጦሩም ሚዛን ክብደት ሦስት መቶ ሰቅል ናስ ነበረ፥ አዲስም የጦር መሣሪያ ታጥቆ ነበር።” (2ኛ ሳሙኤል 21፡16)

***ለሕሚ፡*** “ደግሞም ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሰልፍ ነበረ፤ የያዒርም ልጅ ኤልያናን የጦሩ የቦ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የነበረውን የጌት ሰው የጎልያድን ወንድም ለሕሚን ገደለ።” (1ኛ ዜና መዋዕል 20፡5)

***ሳፍ፡*** “ከዚህም በኋላ እንደ ገና በጎብ ላይ ከፍልስጥኤማውያን

ጋር ሰልፍ ሆነ፥ ኩሳታዊውም ሴቦካይ ከራፋይም ወገን የነበረውን ሳፍን ገደለ።" (2ኛ ሳሙኤል 21፡18)

***ሴሲን፡*** "ካሌብም ሦስቱን የዔናቅን ልጆች ሴሲንና አኪመንን ተላሚንም ከዚያ አሳደደ።" (ኢያሱ 15፡14)

***ተላሚን፡*** "ካሌብም ሦስቱን የዔናቅን ልጆች ሴሲንና አኪመንን ተላሚንም ከዚያ አሳደደ።" (ኢያሱ 15፡14)

***ዐግ፡*** "ከራፋይም ወገን የባሳን ንጉሥ ዐግ ብቻውን ቀርቶ ነበር፤ እነሆ፥ አልጋው የብረት አልጋ ነበረ፤ እርሱ በአሞን ልጆች አገር በረባት አለ፤ ርዝመቱ ዘጠኝ ክንድ ወርዱም አራት ክንድ በሰው ክንድ ልክ ነበረ።"(ዘዳግም 3፡11)

***የጌት ግዙፍ፡*** ደግሞም ጌት ላይ በተደረገ ሌላ ጦርነት፣ በእጆቹ እና በእግሮቹ ላይ ስድስት ስድስት ጣት በድምሩ ሃያ አራት ጣት የነበሩት አንድ ግዙፍ ሰነበረ፤ይህም እንደዚህ ከራፋይም ዘር ነበረ።(1ኛ ዜና መዋዕል 20፡6-አመት)

ስለዚህ ለምን እና እንዴት ግዙፎች ከጥፋት ውሃ በኋላ ሊኖሩ ቻሉ? የጥፋት ውሀው እንዳነበብነው ገድሏቸው ከሆነ እነዚህ ግዙፎች እንደገና ሊታዩ እንዴት ቻሉ? ለዚህ እንቆቅልሽ መልስ አለ! ካነበብነው እንደተረዳነው፣ ጥፋት ውሃው ሲመጣ የወደቁ መላዕክቶች እና የሰዎች ጥምረት እርኩስ መናፍስቶች ከእነዚህ ግዙፎች እና ፍጥራታት ወጡ እና ውሃው እስከሚደርቅ ጠበቁ። ሰዎች በምድር ላይ እንደገና መብዛት ሲጀምሩ እነዚህ እርኩሳን መናፍስቶች ሰዎችን በመውራር ግዙፍ እና ያልተለመዱ ሰዎችን ማርባት ጀመሩ። ይህን ምን እንደተፈጠረ በደንብ የሚተነትን ሌላ እንድናየው የሚፈልገው መጽሐፍ አለ። ስለዚህ "መልአክቶች እና አጋንንቶች ከፍጥረት እስከ አርማጌዶን" ከሚለው የዮሴፍ ላምኪን መጽሐፍ የቀነጨበውን እናንብብ እና በኖህ ዘመን

ስለሆነው የጥፋት ውሃ ካነበብን በኋላ አጋንንቶች እንዴት ወደ ዓለም እንደተመለሱ እናያለን።

"ጌታ የሰማይን ሰባቱን የጎርፍ ማፍሰሻ በር ከፈተ፣ እንዲሁም በቁጥር ሰባት የሚሆኑ ጥልቅ የውሃ ምንጮች አፍንም ከፈተው። እናም የጎርፍ ማፍሰሻ በሮች 40 ቀንና 40 ሌሊቶችን ከሰማይ ወደ ታች አፈሰሱ። ጥልቁ የውሃ ምንጭም ምድር በውሃ እስከምትጥለቀለቅ ድረስ ወሃን ወደ ላይ አፈሰሱ።

ወሃው በምድር ላይ በአስራ አምስት ክንዶች(1ክንድ 18 ኢንች አካባቢ ነው) ጨመረ የምድር ከፍታ ከሆኑት ታራሮችም በላይ ሆነ። መርከቧም ከፍ ብላ በውሃው ላይ ተንሳፈፈች።

ውሃውም የምድርን ገጽ ለአምስት ወራት ሸፈነው፣ ይህም አንድ መቶ ሃምሳ ቀናት አካባቢ ማለት ነው። ስጋ ለባሽ ሁሉም ጠፋ፤ **የእርኩስ መናፍስቶች ግን አልጠፉም ነበር።** የኖሩበት አካላት ከሞቱ በኋላ **የግዙፎች መንፈስ እና የታዛቢዎች ልጆች አምልጠው የሚገቡበትን ይጠብቁ ነበር።**

መርከቧ ሄዳ ከአራራት ተራሮች አንዱ በሆነው የሉባር አናት ላይ አረፈች። በአራታኛው ወር አዲሷ ጨረቃ ስትወጣ የጥልቁ የወሃ ምንጮች ሲዘጉ የሰማይ የጎርፍ ማፍሰሻ በሮች ደግሞ ቀነሱ፤ በሰባተኛው ወር የአዲሷ ጨረቃ ላይ የግርጌ ኪዳን የሌለው የምድር ወሽመጥ ተከፍቶ ወሃው ወደ ታች መፍሰስ ጀመረ። በአስረኛው ወር በአዲስ ጨረቃ ቀን የተራራው ጫፍ ታየ እንዲሁም በአዲስ ጨረቃ በመጀመሪው ወር በአዲስ ጨረቃ መሬት በግላጭ ላየች። በሰባተኛው ዓመት በአምስተኛው ሳምንት ውሃ ከምድረ ገጽ ላይ መጥፋት ሲጀምር ሁለተኛው ወር በአስራ ሰባተኛው ቀን ደግሞ ምድር ደረቅ ሆነች።

በሃያ ሰባተኛውም መርከቧ ተከፈተች አውሬዎችና የዳልጋ ከብቶችና ሁሉም የሚንቀሳቀሱት ተለቅቀው ወጡ፡፡ **የክፉት መናፍስቶች እንደ ገና እንስሳትን እና ሰዎች ውስጥ መግባት ጀመሩ።"**

የሰው ልጆች እና እንስሳት ከጥፋት ውሃ በኋላ መኖርያ እንደሆኑአቸው ከጽሑፉ ማየት እንችላለን፡፡ ይህ ዛሬ የሚታየውን ክፋት በኖኅ ዘመን ከታየው ክፋት ጋር ለማነጻጸር ያስችለናል፡፡

## 10. ኔፊሊሞች (ግዙፎች) ጠፍተዋል፤ይሁን እንጂ ግቦራውያን (አምባገነኖችና ጉልበታሞች) እና ሴሞች (ታዋቂ ሰዎች) እስከ ዛሬ ድረስ ዘልቀዋል፡፡

የወደቁ መላእክቶች ሰዎች ውስጥ በማደር ጭራቆችን መፍጠር ችለው ከነበረ ዛሬም ያን የማድረግ ብቃቱ ይኖራቸዋል፡፡ የሰው ልጆችን ወርረው የሰውን ዘር ለማጥፋት የማይፈልጉበት ሰበብ አይታየኝም፡፡ ይህ ድርጊት እስከ አሁን ድረስ እየቀጠለ ያለ ይመስላል፡፡

ይሁን እንጂ በትናንሽ ሰዎች በተሞላው ዓለም ላይ ግዙፎች መዝለቅ ሊከብዳቸው ይችላል፡፡እንደሚታውቀው ግዙፍ ሆነህ ለረጅም ጊዜ መቆየት ይከብዳል፡፡ በቀላሉ ዒላማ ውስጥ ትገባለህ በእያንዳንዱ ደግሞ ትጠላለህ፡፡

ዛሬ አሜሪካ በብዙ ሀገሮች የምትጠላው ሁሉም ያላት ታላቅ ልዕለ ኃያል ሀገር ስለሆነች ነው፡፡ የግዙፎች እና የዳይኖሰሮች መጥፋት ምናልባት ከሰውነት መጠናቸው ብቻ ጋር የሚያያዝ ይመስላል፡፡ ምናልባት ተጠቅተው መኖር ከብዷቸው በዘዴ እንዲጠፉ ተደርገው ሊሆን ይችላል፡፡ ግዙፍ ለሆነ ፍጡር በዚህ ምድር መቀጠል ቀላል አይሆንለትም፡፡

ይሁን እንጂ ለአምባገነኖች እና ታወቂ ሰዎች ተስማምቷቸው በዚህ ምድር መኖር ይቀላቸዋል፡፡ በታሪክ

ውስጥ በዓለማችን ብዙ ነገር የሰሩ በክፋታቸው የሚታወቁ አመባገነኖች እና ታዋቂ ሰዎች ኖረዋል።

ማህበረሰቡ ውስጥ ገብተው ስለተዋሃዱ ወራሪዎቹ የወደቁ መላእክቶች ዛሬ እንደ ታዋቂ እና አምባገነን ሰዎች ይቆጠራሉ። አብዛኛዎቹ በዓለማችን ያጋጠሙን ክፉ፣ ጨካኝ እና ግፈኛ አምባገነኖች ከፊል አጋንንት፣ ከፊል ሰው የመሆናቸው ዕድል በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ነው እነዚህ ሰዎች ሰብዓዊ ደግነት እና ርህራሄ ያጡት።

## 11. የከፊል ሰው፣ ከፊል መልዓክ የሆኑት መንፈሶች(አጋንንቶች) ኔፊሊሞች፣ጊቦውያን እና ሴሞች ሲሞቱ ወደ ዓለም ሁሉ ተለቀቁ።

የሶስቱ ከፊል ሰዎች ማለት *ጊቦራውያን* (አምባገነን እና ጉልበተኞች)፣ *ሰሜች*(*ታዋቂ ሰዎች*) እና *ኔፊሊሞች*(ግዙፎች) ዲቃላ መናፍስት አንዱ ሰው በሞተ ቁጥር በዚህ ዓለም ላይ ይቀራሉ። የእነዚህ ከፊል ሰው አምባገነኖች፣ ግዙፎች እና ታወቂ ሰዎች መንፈሳዊ ክፍል እንደ እርኩሰ መናፍስት መኖር ይቀጥላሉ። እነዚህ ግዙፍ ልዕለ-ልማዳዊ መልዓክ-ሰዎች ሲሞቱ የከፊል-ሰው ከፊል መልዓክ የሆነው መንፈሳቸው መኖሩን ይቀጥላል።

የሰው ልጅ ሲሞት ወደ ለዘላለም ለመኖር ወይ ወደ ገነት ወይም ደግሞ ወደ ገሃነም ይወርዳል እነዚህ ያልተለመዱ ከፊል ሰዎች ግን የሆነ ቦታ ላይ ይኖራሉ። የወደቁ መላዕክቶች ከገነት በር ውጪ ይኖራሉ። ከፊል ሰው በሞተ ቁጥር መንፈሱ በአጋንንትነት በምድር ላይ ተወስኖ ወዲያና ወዲህ ይዞራል።

**አሁንም ወገኖቻቸው ከሚሆኑ ከደቂቀ ሴት የተወለዱ ረጃጅሞች ሰዎች በዚህ ዓለም ክፉ ልጆችን ይባላሉ። ማዳሪያቸውም በዚህ ዓለም ይሆናል። አባቶቻቸው ከደብር ቅዱስ ከወረዱ ከደቂቀ ሴት ተወልደው ነበርና ወገኖቻቸው ከሚሆኑ ከደቂቀ ሴት ክፉ ልጆች**

**ተወለዱ። ቀድሞ የንጽሕና መሠረት የነበረ እነዚህም በዚህ ዓለም ክፉ ልጆች ይሆናሉ፤ ክፉ ልጆችም ይባላሉ።**

**ሄኖክ** 15፥8-10

በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ከዲያብሎስ እና አጋንንቶች ጋር ተጋፍጧል:: እነዚህ ግን አንድና ተመሳሳይ አይደሉም::

በእንግሊዘኛ (አማርኛም) ቃላቶችን ቀላቅለን ዲብሎስ፣ ጋኔን፣ ሰይጣን እና አጋንንቶችን እየቀያየርን እንጠቀማለን::

ኢየሱስ ሁለት ዓይነት እርከሳንን ገጥሟል፡ *ዲያቦሎስና ዲያሞኒዮን*:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስት *'ዲያብሎስ'* የሚለው ቃል የመጣው *'ዲያቦሎስ'* ከሚባለው ቃል ሲሆን 'አጋንንት' ደግሞ *'ዲያሞኒዮን'* ከሚለው ቃል ነው የመጣው:: ዲያቦሎስ እና ዲያሞኒዮን ሁለት ዓይነት ህልውናዎች ናቸው::

አጋንንቶች ታዲያ ምንድን ናቸው ምንስ ይመስላሉ? ምን ይመስላሉ ከወዴት ነው የሚመጡት? ሰይጣን፣ የወደቁ መላእክት እና የጨላማው ገዢዎች ከየት እንደ ሆኑ እናውቃለን:: አጋንንቶች ታዲያ ምንድናቸው? እነርሱም የወደቁ መላዕክቶች ናቸው?

አጋንንቶች *ዲያሞኒየን* የሚባሉ ኢየሱስ የተጋፈጣቸው ሌሎች ዓይነት ፍጡራን ናቸው:: እነዚህ ህልውናዎች የወደቁ መላእክቶች ዓይነት አይደሉም:: ካላይ ባየናቸው ነጥቦች መሰረት አጋንንቶች የተፈጠሩት ከፊል ሰዎች ሲሞቱ ነው::

ከወደቁ መላዕክቶች አስከፊው የሰዎቸ ወረራ በኋላ ውጤቱ ከፊል ሰዎች እና ዛሬ እርኩሳን መናፍስት ብለን የምንጠራቸው የዲቃላ ፍጥረቶች መፈጠር ሆነ::

በዓለማችን የሚኖሩት የአጋንነቶች መሰረት እንግዲህ ይህ

ነው። በጨለማው የዓለም ክፍል ውስጥ ስላሉ አይታዩም። መጽሐፈ ሄኖክ ሰዎች ውስጥ ስለሚኖሩት የወደቁ መላዕክቶች አጣ ፈንታን በተመለከተ በግልጽ ያስቀምጣል። በመላእክቶች እና የሰው ልጆች ህብረት የተፈጡርት የግዙፎች፣ ጉልበተኛች እና አምባገነኖች መንፈሳዊ ክፍላቸውም እንደ እርኩስ መንፈስ መኖር እንደሚቀጥሉም ግልጽ ያስቀምጣል።

መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል።

ይሁዳ 1፥6

ጌታን ባንደበቱ ጠርቶ ሄኖክ ወደዚህ ቅረብ ለከበረ ቃሌም ታዘዝ አለኝ። አንሥቶም እስከ ደጃፉ ድረስ አቀረበኝ እኔ ግን ፊቱን ደፍቼ ወደታች እመለከት ነበር። ደግ ሰው የምትሆን ሕግን በሰው ልቡና የምትጽፍ ሄኖክ በቃሉ ስማ አትፍራም አለኝ። ወደዚህ ቅረብ ቃሌንም ስማ ለነሱ ልትለምንላቸው ለላኩህ ለኃጢአት ለሚተጉ ለደቂቀ ሴትም ሂደህ ንገራቸው አለኝ። እናንተ ለሰው ልትለምኑ ይገባችሁ ነበር፣ ሰው ግን ለናንተ ሊለምንላችሁ አይገባውም ነበር። ከፍ ያለ ደብር ቅዱስን ዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር መንግሥተ ሰማያትን ስለምን ተዋችሁት በላቸው።

ከሴቶችም ደረሳችሁ ከቃየልም ልጆች ጋር ረከሳችሁ። ለናንተ ሚስት አገባችሁ የቃየልም ልጆች እንደሚያደርጉት አደረጋችሁ ረጃጅም ልጆችንም ወለዳችሁ። ረቂቃን የምትሆኑ የከበራችሁ ዘላዓለም ጸንቶ በሚኖር ሕይወት /መንፈስ ቅዱስ/ ደጎነኞች የምትሆኑ እናንተ ግን በሴቶች ረከሳችሁ። በደማዊ በሥጋዊ ሥራም እንደ ወለዱ አደረጋችኋቸው እናንተም ሥጋዊ ደማዊ ሥራን ወዳዳችሁ እነሱ ሥጋዊ ደማዊ ሥራን እንዲሠሩ እናንተም እንደነሱ ሠራችሁ።

እነዚህም የሚሞቱ የሚጠፉ ናቸው፣ የሚሞቱ ስለሆነ ዘራቸውን በነሱ ይዘሩ ዘንድ ልጆችም ከነሱ ይወልዱ ዘንያ ሴቶችን ሰጠኋቸው። በዚህ ዓለም እንደዚህ እንደዚህ ያለ ሥራ ሲሠራ ይኖራል። እናንተግን ከዚህ አስቀድሞ ረቂቃንን ዘላለም ጸንቶ በሚኖር በልጅ ልጅ ዘመንም በማያልፍ በመንፈስ ቅዱስም ሕያዋን ሁናችሁ ነበር። የረቂቃን መላእክት ማደሪያቸው በሰማይ ነውና ስለዚህ ነገር ሴቶችን ለናንተ

**ሚስቶች አላደረግኋቸውም። አሁንም ወገኖቻቸው ከሚሆኑ ከጻድቃን ሴት የተወለዱ ረጃጅሞች ሰዎች በዚህ ዓለም ክፉ ልጆችን ይባላሉ። ማደሪያቸውም በዚህ ዓለም ይሆናል። አባቶቻቸው ከጻብር ቅዱስ ከወረዱ ከጻቂቀ ሴት ተወልደው ነበርና ወገኖቻቸው ከሚሆኑ ከጻቂቀ ሴት ክፉ ልጆች ተወለዱ።**

**ቀድሞ የንጽሕና መሠረት የነበረ እነዚህም በዚህ ዓለም ክፉ ልጆች ይሆናሉ፤ ክፉ ልጆችም ይባላሉ። በሰማይ የሚኖሩ ረቂቃን መላእክት ማደሪያቸው በሰማይ ይሆናል በዚህ ዓለም የተወለዱ በምድር የሚኖሩ ሰዎችም ማደሪያቸው በምድር ይሆናል። *ከደመና የሚደርሱ ረጃጅሞች ሰዎችም ፈጽመው ይጠፋሉ እስበሳቸውም ይጣላሉ በዚህ ዓለም ሰውን የጠፉሉ። በሰውም ኃዘንን ያደርጋሉ እነሳቸውም የሚበሉተን እህል ምንምን አያገኙም። ማየ አይህን ይጨልጣል እንጂ አይጠሙም በመኖሩም አይታወቁም። ጥፋትና ስልፍ በታዘዘበት ወራት ተወልደዋልና እነዚህ ሰዎች ኑረው በሴቶችና በወንዶትላይ በጠላትነት አይነሱም አለ።***

ሄኖክ 15፥1-12

***አውሬዎችንና ወፎችን፣ ዓሳዎችን፣ ተሐዋስያንን እያመለኩ ይበድሉ ጀመር። እርስ በእርስ ሥጋቸውን ተባሉ፣ ከሷም ደምን ጠጡ።***

ሄኖክ 7፥5-6

*ለጆሮህ የተለመዱ ብዙ ስሞች አሉ:: ሄርኩልስ፣ አኪለስ፣ ሳይክሎፕስ እና ሜዱሳ የሚባሉት በደንብ የምናውቃቸው ስሞች ናቸው:: በግሪክ፣ በሮማወያን እና በግብጾች ታሪክ መሰረት እነዚህ ስሞች ልዕለ-ሰዎች እና ከፊል-ልማዳዊ ዲቃላ ፍጥረቶች መሆናቸውን የምንረዳው ጥቂት ሰዎች ነን::*

*በእርግጥ ግሪኮች ከእንስሳ ጋር ወሲብ እንደሚያደርጉ የሚጠቁሙ ብዙ ታሪኮች አሉ:: ለምሳሌ ዜስ የሚባል ፍጡር በኮርማ ሰንጋ መልክ ኢሮፓን ደፍሮአት ክሬታን ባህል የፈጠሩ ሶስት ወንዶች ልጆችን ወልደዋል::*

እስከ አሁን የሚወለዱት ሽሎች እነዚህን ፍጥረቶች ይመስላሉ በማለት ስለእነዚህ ፍጥረቶች ታሪክ ያስረዳሉ። አንድ አንዶች ደግሞ የእነዚህ ፍጥረታት ታሪክ የመጣው ትክክለኛ ባልሆነ የቅሪተ አካል ምልከት ነው ይላሉ።

ምንም ይሁን ምን እነዚህ አፈታሪኮች እንደዚህ ዓይነት ህብረት መኖሩን ያመለክታሉ።

እነዚህ ልዕለ-ልማዳዊ ፍጥረቶች በጣም ታዋቂ እና በክፋት ስለሚነሱ ስማቸው በዘመነው ዘመን ውስጥ ይታወቃል። እነዚህ ዲቃላ ፍጥራቶች መኖራቸውን አምናለው ምክንያቱም መኖራቸው ከዘፍጥረት እና መጽሐፈ ሄኖክ ጋር ስለሚስማማ ነው። ሰዎች ያልሆኑ መላዕክቶች ከሰው ልጆች እንስሳት ጋር ወሲብ ፈጽመው ዲቃላ ፍጥረታት መፈጠራቸውን እና እነርሱም ሲሞቱ ክፍ እርኩሳን መናፍስት መሆናቸውን እናውቃለን።

> **አሁንም ወገኖቻቸው ከሚሆኑ ከደቂቀ ሴት የተወለዱ ረጃጅሞች ሰዎች በዚህ ዓለም ክፉ ልጆችን ይባላሉ። ማደሪያቸውም በዚህ ዓለም ይሆናል። አባቶቻቸው ከደብር ቅዱስ ከወረዱ ከደቂቀ ሴት ተወልደው ነበርና ወገኖቻቸው ከሚሆኑ ከደቂቀ ሴት ክፉ ልጆች ተወለዱ። ቀድሞ የንጽሕና መሠረት የነበረ እነዚህም በዚህ ዓለም ክፉ ልጆች ይሆናሉ፤ ክፉ ልጆችም ይባላሉ። በሰማይ የሚኖሩ ረቂቃን መላእክት ማደሪያቸው በሰማይ ይሆናል በዚህ ዓለም የተወለዱ በምድር የሚኖሩ ሰዎችም ማደሪያቸው በምድር ይሆናል። ከደመና የሚደርሱ ረጃጅሞች ሰዎችም ፈጽመው ይጠፋሉ እስበሳቸውም ይጣላሉ በዚህ ዓለም ሰውን የጠፋሉ። በሰውም ኃዘንን ያደርጋሉ እነሳቸውም የሚበሉትን እህል ምንምን አያገኙም። ማየ አይህን ይጨልጣል እንጂ አይጠሙም በመኖሩም አይታወቁም። ጥፋትና ሰልፍ በታዘዘበት ወራት ተወልደዋልና እነዚህ ሰዎች ኑረው በሴቶችና በወንዶት ላይ በጠላትነት አይነሱም አለ።**
>
> **ሄኖክ 15፡8-12**

# ምዕራፍ 18

# የግዙፎች(ኔፊሊም) ምሳሌዎች

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥4**

መላዕክቶች ከሰዎች ልጆች ጋር ግንኙነት ሲያደሩጉ ሶስት ዓይነት ፍጡሮች ተፈጠሩ፡ 1. ግዙፎች 2. ታወቂ ሰዎች 3. አምባገነኖች:: ይህ ምዕራፍ በአንድ ወቅት ስለ ኖሩት ስለ ግዙፎች ያወጋል::

የግዙፍ አጽሞች ድርድር



የሴሞች(ታወቂ ሰዎች)፣ የጊቦራውያን(ጉልበተኞች እና አምባገነኖች) እና የኔፊሊሞች(ግዙፎች) ብዙ ምሳሌዎች በሰው ታሪክ ውስጥ አሉ። እነዚህ ሰዎች ያልተለመዱ ስለ ሆኑ በቀላሉ አይረሱም። የኔፊሊሞችን እውነተኛ የህይወት ምሳሌዎችን እንመልከት።

## 1. በግብጽ የተገኘው ግዙፍ ጣት

እንደ የጀርመኑ ጋዜጣ ቢልድ አንድ ግሪጎር እስፖሪ የሚባል ተመርማሪ ደርቀው የቆዩትን ብዙ የጣት ፎቶዎችን አቀረበ። እነዚህ አስደናቂ ምስሎች ለህዝብ ሲቀርቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ጣቱ 38 ሴንቲ ሜትር/15 ኢንች/ የሚረዝም ሲሆን እውነት ከሆነ ደግሞ ከ4.88 ሜትር/16 ጫማ/ በላይ የሚረዝም ሰው ነው ይባላል።

ግዙፍ ጣት



ደርቆ የቆየ ጣት፡ ፎቶው የተወሰደው በ1988 በቁፋሮ በተገኘበት ወቅት ነው

ምናልባት ትላልቆቹ የግብጽ ፒራሚዶች፣ የስቶንሄንጅ ውቅሮች፣ የኢስቴር ደሴት፣ የኦርካዲያን ድንጋዮች እና ሌሎችም ቅርሶች በእነዚህ ግዙፎች ተገንብተው ይሆን? እንደ ሰው ልጆች እነዚህ ድንጋዮች በማይታመን ሁኔታ ትላልቆች እና ለዝሪየችን የሚከብዱ ናቸው:: እነዚህን ትላልቅ ድንጋዮች እና ብሎኮች ለመያዝ እና ለማስቀም የተለየ የሜካኒካል አብላጫ ማስፈለጉ ሳይታለም የተፈታ ነው:: እነዚህ ትላልቅ ድንጋዮች ባሉበት ሁሉም የምድር ክፍሎች ተመሳሳይ የአማካይ ቁመት ላይ ናቸው::

እነዚህ ድንጋዮች ፈልፍለው፣ ሰርተው ካቆሚቸው ሰዎች በበለጠ ረጅም ላይሆኑ ይችላሉ::

## 2. ግዙፍ የራስ ቅል?



ይህ ብዙ ያወዛገበ የግዙፍ ሰው የራስ ቅል ሊሆን ይችላል የተባለው ምስል ነው:: ይህ በአንድ የጀርመን አርኪዮሎጂስት ተገኘ የተባለው "የጎሊያድ የራስ ቅል" በብዙ ጋዜጦች የፊት ገጽ ዜና ሆኖ ነበር::

## 3. ኢራቅ ውስጥ የተገኙ ግዞፎች

ከታች በሚገኘው የድንጋይ ምስል ላይ እንደሚታየው በሱሜሪያኖች/ኢራቅ/ ጽሑፍ እና ምስሎች ውስጥ የግዙፎች ዝሪያ ማስረጃዎችን እናያለን፡፡



ግዙፍ ንጉስ የተቀመጠበት የሱሜሪያኖች የድንጋይ ምስ

ይህ ንጉስ ተነስቶ ቢቆም ቁመቱ ምን ያህል ሊሆን ይችላል? ምስሉን ባጠናህ ቁጥር ብዙ የውክልና ምልክቶችን ታገኛለህ፡፡ የንጉሱ ልብስ ላይ ያሉትን ዝርዝር ነገሮችና በሽክላ ላይ የተጻፈውን ጽሑፍ ልበ በል፡፡

## 4. የደቡብ አሜሪካ ግዙፎች



የመጀመሪያው በደቡብ አሜሪካ የፓሲፊክ ጠረፍ ላይ በሚኖሩት ግዙፎች ላይ የተጻፈው ጽሁፍ የተገኘው የፌርድናንድ ማጄላንን የ1520 ጉዞን በቅደም ተከተል ባስቀመጠው የአንቶኒዮ ፒጋፌታ መዝገብ ላይ ነው፡፡

ፒጋፌታ ዝሪያቸው በሙሉ በጣም ረጃጅሞች ስለሆኑ ሲናገር የአውሮፓኖቹ ሙሉ ልብስ ወጋባቸው ጋር ብቻ ነው የሚደርሰው ይለናል።

አለቃቸው ማጄለን ሰዎቹን "የእግረ ረጃጅሞች ምድር" ለማለት "ፓታጎኒያ" ብሎ ሰይሟቸዋል። ሌሎቹን ሰዎች ከተገናኘ በኋላ እነዚህን ሰዎች ወደ አውሮፓ ለማምጣት በጣም ፈልጎ ነበር ይበላል። የራሳቸውን ኃያላን ሰዎችን ልኮ ሁለት ሰዎችን መማረክ ችሎ ነበር አሉ ይሁን እንጂ ሁለቱም ወደ አውሮፓ ጉዞ በማድረግ ላይ ሳሉ ታመው መንገድ ላይ ሞተዋል።

የሰር ፍራንሲስ ደሬክ የወንድም/እህት ልጅ ስለ አጠቃላይ ጉዙአቸው ባሳተመው መዝገብ ውስጥ በጣም ግዙፍ ሰዎችን ማግኘታቸውን ተናግሯል። የመኽከለኛው 17ኛው ክፍለ ዘመን የብርቲሽ ንጉስ የባህር ኃይሉ የዮሐንስ ቢይሮን ጉዞም ይህን ታሪክ ወደ ማረጋገጡ የተጠጋ ነው። ከመርከቧ መመለስ ሁለት ዓመት በኋላ የታተመው መጽሐፍም ስለ ግዞፎቹ የበለጠ ታሪክ ያወሳል።

## 5. የዌልሶች ግዙፎች

በሰሜን ዌልስ በምትገኘው የባህር ዳር ከተማዋ ላንዱድኖ ውስጥ የጥንት የመዳብ ማዕድን ስፍራ አለ። ይህ ቦታ ከአይርሽ ወንዝ የ220 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ሲሆን ታላቁ የኦርም መዳብ ማውጫ ስፍራ በመባል ይታወቃል። የናስ ዘመን በሚባለው ከ3500 ዓመታት በፊት የነበረ ነው። ከ2500 በላይ መዶሻዎች በዚህ ቦታ ተገኝተዋል።

እስከ ስድስት ኪሎሜትሮች የተለካ ቢሆንም የቁፋሮው ቦታ ግን ለብዙ ኪሎሜትሮች የተዘረጋ መሆኑ ይታመናል። ዘጠኝ ደረጃዎች ያሉት ሲሆን ከ1700 ቶን በላይ የሚመዝኑ

መዳቦች መውጣታቸው ታውቋል፡፡ የኃይል መሳሪያዎችን ወይም ዛሬ እንደምናውቀው የኃይል መሳሪያ ሳይጠቀሙ በዘመኑ ለነበሩት ማህበረሰቦች በጣም አስገራሚ አፈጻጸም ነው፡፡

ዛሬ የተለመዱ ትላልቅ የድንጋይ መስበሪያ መዶሻዎች በአማካይ 9 ኪሎ/20 ፓውንድ/ የሚመዝኑ ቢሆንም በብዙ ቦታዎች የሚገኙት መዶሻዎች ግን 4.5 ኪሎ/10 ፓውንድ/ አካባቢ ክብደት ያላቸው መዶሻዎች ናቸው፡፡ የጀርባ ህመም ችግር የሌለበት ሰው እስከ 9 ኪሎ መዶሻን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ መሸከም/መጠቀም ይችላል፡፡

በመዳብ ማውጫ ስፍራው አርኪዮሎጅስቶች ያገኙት መዶሻ ግን እስከ 29 ኪሎ ግራም /64 ፓውንድ/ የሚደርስ ክብደት ያለው ነበር፡፡ 29 ኪሎ የሚመዝን እና 2.74ሜትር የሚደርስ እጀታ ያለውን መዶሻ መጠቀም ከሰው አቅም በላይ ነው፡፡ በኃይል ማንቀሳቀስ ደግሞ በፍጹም አይቻልም፡፡

ይህን በይደውት የነበሩት ታዲያ እነ ማን ናቸው? የጥንት ሰዎች ይሄን መጠቀም ይችላሉ ብለን ብናስብ እና በዚህ መሰረት መጣናቸውን ብናሰላ አንድ ሰው ርዝመቱ ከ3.66 እስከ 5.49 ሜትር የሚረዝም ወይም ደግሞ ከዛሬው የሰው ልጅ ቁመና ሶስት እጥፍ የሚረዝም ማለት ነው፡፡ በድንብ ለወረዳት ያህል፣ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ የተገነቡት ቤቶች በሆነ ክፍል ውስጥ ያለው የግድግዳ ቁመት 2.44 ሜትር ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ውስጥ በዘመኑ ግዙፎች በምድሪቷ ላይ ነበሩ ተብሎ የተጠቀሱት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 6. በግሪኮች ታሪክ ውስጥ ያሉት ግዙፎች

### ሳይክሎፕስ



በግሪኮች እና ሮማውያን ታሪክ ውስጥ ሳክሎፕ በግንባራቸው ላይ አንድ ዓይን ያላቸው የግዙፎቹ ዝሪያ አባል ነው፡፡

# ምዕራፍ 19

# የታዋቂ ሰዎች ምሳሌዎች(ሴሞች)

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥4**

## የሴሞች ምሳሌ (ታዋቂ ሰዎች)

መላዕክቶች ከሰው ልጆች ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ ሶስት ዓይነት ፍጡሮች ተፈጥረዋል፤

1. ግዙፎች፣

2. ታዋቂ ሰዎች እና

3. አምባገነኖች::

ይህ ምዕራፍ በአንድ ወቅት ስለ ነበሩት ታወቂ ሰዎች ያወራል::

ብዙ የታዋቂ ሰዎች(ሴሞች) ምሳሌዎች አሉ:: ሁሉም ታዋቂ ሰዎች ዲቃላ ወይም ከፊል-ሰዎች ሳይሆኑ አንድ አንዶቹ ግን ናቸው:: ሴሞች ምናልባት በብዛት እየኖሩ ካሉት ከፊል ሰዎች ውስጥ በዛ ያሉ መደቦች ናቸው:: ኔፊሊሞች(ግዙፎች) ዓለምን ሲገዟት የነበረ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል:: በእርግጥ የእስራኤል ልጆች ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት የፈሩት በእነዚህ በጣም

ግዙፍ በሆኑት ሰዎች ምክንያት ነው። ግዙፎች(ባለ ትላልቅ ቁማና ሰዎች) ዳይኖሰሮች(ባለ ትላልቅ ቁመና እንስሳት) በሌሉበት ተመሳሳይ ምክንያቶች ዛሬ በምደር ላይ የሉም።

ኔፊሊሞች(ግዙፎች) ጠፍተዋል።

ጉልበተኞች እና አምባገነኖች እስከ ዛሬ ድረስ ቢኖሩም በዓለም ላይ ዲሞክራሲ በመስፋፋቱ ምክንያት ውስኖች ሆነዋል። በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ጉልበተኞችን እና አምባገነኖችን የሚታገስ የለም። ጉልበተኞች እና አምባገነኖች መስፋፋት (ማደግ) የሚሆሆንላቸው ዲሞክራሲ ባልዳበረበት እና ዲሞክራሲ እውነተኛ ባለሆነባቸው የዓለማችን ክፍሎች ነው።

ዛሬ በዓለማችን በተላየየ ምክንያቶች በበጎ ጎን ታዋቂ የሆኑ እና በመጥፎ ነገሮች ታዋቂ የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ። **ሰዎችን ታዋቂ የሚያደርገው ብዙ ነገሮች አሉ። አንድ አንዴ ሰዎች ዝናን የሚያገኙት ልዕለ ሰው በመሆናቸው እና በሰው ዘንድ የማይቻለውን እና ያልተለመደ ነገር በመስራት ነው።** የሰዎቸ እና መላዕክቶች ዲቃላ የሆኑ ሰዎች ያልተለመደ ብቃት በማዳበር በተወሰነ ዘርፍ ላይ ክብረወሰኖችን ይይዛሉ። በፈጠራቸው ታዋቂ የሚሆኑ ሰዎችም ደግሞ አሉ። ሌሎቹ ደግሞ በስፖረታዊ ስኬታቸው፣ በሀብታቸው፣ በቴሌቪዥን፣ በፈጠራ፣ በሚሰሩት ሙዚቃ፣ በጻፉት መጽሐፍ እና በክወና ታዋቂ ይሆናሉ።

1. **በፈጸሙት የነፍስ ግድያ ታዋቂ የሚሆኑ ሰዎች አሉ።**

ሴቶችን አፍኖ ወደ አላስካ በረሃ ውስዷል የተባለ ሰው አለ። ልብሳቸውን አስወልቆ ይለቃቸው እና አድኖቸው በአደን ቢላ እና ጠምንጃ ተኩስ ይገድላቸዋል። በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ 17 ሴቶችን መግደሉን እና 30 ሴቶችን መድፈሩን አምኗል።

ሌላ ሰው ደግሞ አለ አውሮፕላንን በመጥለፍ እና ከተራራ ጋር በማጋጨት ውስጡ የነበሩትን 150 ተሰፋሪዎችን በመግደል ታዋቂ የሆነ። ይህን ከማድረጉ በፊት የሴት ጓደኛውን የሆነ ታዋቂ የሚያደርገውን ነገር እንደሚሰራ ነግሯት ነበር።

## 2. በክፉ መጽሐፋቸው እና በክፉ ተጽእኖአቸው ታዋቂ የሆኑ ሰዎች አሉ።

የሆነ ሙግት ጽፈው ሚሊዮኖችን ከእግዚአብሔር ዘወር ያደረጉ እና ክርስትናን መሳለቂያ ያደረጉ ሰዎች አሉ። ከእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ውስጥ አንዱ አሟሟቱ የሚያሳፍር ሲሆን በዚያ በመጥፎነቱ በሚታወቅ መጽሐፉ ብዙዎችን ከእግዚአብሔር ቤት በማስኮብለሉ በቀሰቀሰው ቁጣ ምክንያት ቀብሩ ላይ የተገኙት ሰዎች እንኳን ስድስት ብቻ ነበሩ።

## 3. ወሲባዊ ግንኙነትን በግልጽ የሚያሳዩ [ተንቀሳቃሽ] ምስሎችን (ፖርኖግራፊ) ለዓለም በማስተዋወቅ ታዋቂ የሆኑ ሰዎች አሉ።

በፖርኖገራፊ ቤታቸው፣ የፖርኖግራፊ ፊልማቸው እና በፖርኖግራፊ ትዕይንታቸው ታዋቂ የሆኑ ሰዎች አሉ።

## 4. የወሲባዊ ግንኙነት ክብረወሰኖችን በማስመዝገብ ታዋቂ የሆኑ ሰዎች አሉ።

አንዲት አሜሪካዊት የወሲብ ፊልሞች ተዋናይት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ919 ሴቶች ጋር ወሲብ በማድረግ ዝነኛ ሆናለች። ይህን የሳካችው በዋርስዎ ፖላንድ እ.ኤ.አ. በ2004 ነበር። ይህ ማንም ሴት ልትደፍረው አትችልም የተባለለት ሴከት ነው ተብሏል።

በ1995 አንዲት መኻከለኛ ገቢ ያላቻው ቻይናዊያን ጥንዶች ሴት ልጅ የሆነችው ልጅ በአስር ሰዓት ጊዜ ውስጥ ከ251

ወንዶች ጋር በካሜራ ፊት ወሲብ ፈጽማለች፡፡ በዚህ የተሰራው ቪዲዮም ከ40,000 በላይ ኮፒዎች ተሸጧል፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ እንዲከፈላት ስምምነት ላይ የተደረሰው 10000 ዶላር አልተከፈላትም ነበር፡፡ ስለዚያ ቀን እና የተማሪነት ህይወቷን የሚተርክ ዘጋቢ ፊልም ተዘጋጅቶ ነበር፡፡

## 5. በክፉ የንድፈ ሀሳቦቻቸው የሚታወቁ ሰዎች አሉ፡፡

የፀረ-ክርስቲያናዊ አሳብ የሆነው የዝገምተኛ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ/ Theory of Evoluation/ ለብዙ ምዕተ-ዓመታት ሰዎችን ከእግዚአብሔር ዘወር ለማድረግ በነበረው ኃይል ታዋቂ ነበረ፡፡

## 6. በአታላይነታቸው እና በሽንገላቸው ታወቂ የሆኑ ሰዎች አሉ፡፡

የአስቆሪዮቱ ይሁዳ ኢየሱስን በመካዱ ታዋቂ ነው፡፡ አለቃው ላይ በነበረው ሽንገላ በዓለም ታዋቂ ነበረ! የመንግስታቸውን ምስጢር በመሸጥ፣ ስልጣኔን በመካድ እና ዓለምን ለኒውክሌር ጦርነት በማጋለጥ የሚታወቁ ሰዎች አሉ፡፡

## 7. በክፉ ሙዚቃቸው የሚታወቁ ሰዎች አሉ

አንድ አንድ ሙዚቀኖች ትውልዱን ለዝሙት መንፈስ፣ ግራ መጋባት፣ እብደት እና ለአድንዛዥ ዕፆች ያጋለጡ የሙዚቃ አልበሞችን በሚሊዮን በሚቆጠር ኮፒዎች ሸጠዋል፡፡

## 8. በእርቃንነታቸው የሚታወቁ ሰዎች አሉ፡፡

አንዲት ንግስት ባሏ የታክስ ቅነሳ እንዲያደርግ ለማሳመን ራቁቷን ከተማ ውስጥ ፈረስ ጋልባለች፡፡ እርስዋ ስታልፍ ማንም ማየት እንደሌለበት ንጉሱ ማስጠንቀቂያ አውጥቶ ነበር፡፡ ይህ ማስጠንቀቂያ በመጋረጃ ውስጥ ባየው አንድ ቶም በሚባል ሰው ተጥሷል፡፡ ክስተቱም አጮላቂው ቶም/'Peeping Tom'/

ለሚል ስም መውጣት ምክንያት ሆኗል።

## 9. ባስጀመሩት ክፉ አብዮት የሚታወቁ ሰዎች አሉ

አንዱ የፈረንሳይ አብዮት መሪ ንጉሱ እዲገደሉ የተከራከረ ሲሆን በመኳንንቶቹ ላይም ህዝቡ እንዲነሳሳ ቀስቀሷል። ሌላው የፈረንሳይ አብዮት መሪ ደግሞ ጠላቶቹ በጉሎቲን የሞት ቅጣት ያለፍርድ እንዲሞቱ አበረታቷል። ንጉስ ሉዊስ 16ኛን እና ንግስት ሜሪ አኖቶኔትን ጨምሮ ወደ 40000 የሚጠጉ ሰዎች  ተገድለዋል ወይም ደግሞ በሞት ተቀጥተዋል።

## 10. የአይሁዶችን ስደት በመቀስቀስ የሚታወቁ ሰዎች አሉ

ለካቶሊክ ቤተክርስቲያን ስጋት ናቸው ያሏቸው ሰዎች ተነቅለው እንዲጠፉ ለማድረግ የፍርድ ሸንጎ በማስጀመር ታዋቂ የሆኑ ሰዎች አሉ። ሃያ ሺህ የሚደርሱ አይሁዳውያን እንጨት ላይ ታስረው በመቃጠል ወይም በሌላ ዓይነት አሰቃቂ ቅጣቶች ተገድለዋል።

# ምዕራፍ 20

# የአምባገነኖች እና ጉልበታሞች ምሳሌዎች (ጊቦራዊያን)

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥4**

መላዕክቶች ከሰው ልጆች ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ ሶስት ዓይነት ፍጡሮች ተፈጥረዋል፤

1. ግዙፎች፣
2. ታዋቂ ሰዎች፣ እና
3. አምባገነኖች።

ይህ ምዕራፍ ስለ አምባገነኖች እና ጉልበታሞች ያወራል።

በዘመናት ውስጥ ብዙ አምባገነኖች እና ጉልበተኞች ሰዎች ኖረው አልፈዋል። አብዛኛዎቹ እነዚህ ሰዎች ወይ ዲያብሎስ ያደረባቸው ሰዎች ናቸው ወይም ደግሞ ጊቦራወውያን ናቸው። ጊቦራውያን በመላዕክቶች እና በሰዎች ግንኙነት ምክንያት የተፈጠሩ ሰዎች ናቸው። ጊቦራዊ ናቸው ማለት ከፊል ሰው ከፊል ልዕለ ተፈጥሮአዊ ናቸው ማለት ነው።

በሰብዓዊነት ላይ የተደረገ ወንጀል፣ ጭካኔዎች፣ ክፋት እና

ርህራሄ ማጣት የሚያመልከተው ከከወደቁ መላዕክቶች እና ከሰው ልጆች ጋር በተደረገ ግንኙነት ከተፈጠሩት ልዕለ ከፊል ሰዎች የሚመጣ ያልተለመደ ባህሪ ነው።

በእርግጥ እነዚህ ልዕለ-ሰው ዲቃላዎች እውነተኛ ሰዎችም ላይሆኑ ይችላሉ። ያልተገደበ ስልጣን ሲኖራቸው የፈለጉትን የሰዎች ብልት ቆርጠዋል፣ ገድለዋል፣ አሰቃይተዋል። ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ የወደቁ መላዕከቶች እና የሰው ልጆች ውህድ የሆኑ ልዕለ ሰው ዲቃላዎች ናቸው። አንድ አንድ ጉልበታሞች እና አምባገነኖች ለሚያሳዩት ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች እና የስሜት ማጣት ዋነኛው ማብራሪያ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ ቀጥሎ ዓለማችን አይታው ያሳለፈቻቸውን ጥቂቶቹን አምባገነኖች እና ጉልበታሞችን አቃርባለው። ብዙ የአምባገነኖች እና ጉልበታሞች ምሳሌዎች አሉኝ ይሁን እንጅ በአንድ አንድ ምክንያቶች አብዛኛዎቹን ትቼአቸዋለሁ።

ይህ በጣም ጥቂት የአምባገነኖች እና የጉልበታሞች የናሙና ዝርዝር ነው። ከእነዚህ አምባገነኖች እና ጉልበታሞች መኻከል አንዳንዶቹ ልዕለ ሰው ዲቃላዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሰብዓዊነት የማይሰማቸው ክፉዎች መሆናቸውን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ። በታሪክ ውስጥ ብዙ ሰዎች እንደ ልዕለ ሰዋዊ ጉልበታሞች እና አምባገነኖች ኖረዋል። ዛሬም ደግሞ የከፊል ልማዳዊ ምልክቶችን በግልጽ የሚያሳዩ ብዙ ሰዎች አሉ። ምናልባት ብዙዎቹ እነዚህ ክፉ አምባገነኖች እና ጉልበታሞች ጊቦራውያን ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ አንዶቹ የወደቁ መላዕክቶች እና የሰው ልጆች ጥምረት ልዕለ ሰዎች መሆናቸው የታወቀ ነው። ስለ እነርሱ ትንሽ ስታነብ መልካም ስሜት እና ርህራሄ ያላቸው ተራ ሰዎች ናቸው ወይስ ልዕለሰው ናቸው የሚለውን ትለያለህ። ከታሪክ የመረጥኳቸውን የእያንዳንዱን ግለሰብ ታሪክ አንብብ እና ምን

ዓይነት ሰዎች በዓለማቸእን እንደ ኖሩ ራስህን አስተምር። ዛሬ ክርስቲያኖች መጋፈጥ ያለባቸው ዲያብሎስ የሚጨቁናቸውን እና እርኩስ መንፈስ ያደረባቸውን ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ከፊል ዲያብሎስ ከፊል ሰው የሆኑትንም ጭምር ነው!

*የሚቀጥሉት ሰዎች ከፊል ሰዎች ከፊል ዲያብሎስ ናቸው እያልኩ እንዳልሆነ ለሳስብህ እወዳለሁ።* እያልኩ ያለሁት ከፊል ዲያብሎስ ከፊል ሰው ሊሆኑ ይችላሉ ነው። እራሰህ ብትፈርድ እና ከፊል ሰው ከፊል ዲያብሎስ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን አስበህ ብትወስን መልካም ነው።

## 1. ጋየስ ጁሊየስ ቄይሳር አውጉስጦስ ጀርመኒከስ(12-41ዓ.ዓ.) (ካሊጉላ)

ካሊጉላ ለአራት ዓመት የገዛ የሮማን ንጉሥ ነገሥት ነው። በሰው ልጅ እና ግብረገብነት ላይ በፈጸመው አፀያፊ፣ እብደት የተሞላበት እና የሚረብሽ ነውረኛ ወንጀሎች ይታወሳል።

በተራ ነገሮች እንኳን እርሱን የሚቃወሙትን ወይም ደግሞ ከእርሱ ጋር የማይግባቡት እንዲገደሉ ትዕዛዝ በማስተላለፍ ነበር የጀመረው። በጣም ጥሩ የማስታወስ ችሎታ ነበረው። የገዛ ሚስቱን እንድትሰደድ በማድረግ እንደ አፖሎ ለብሶ ራሱን አምላክ፣ ቬነስ/አማልክት/፣ሜርኩሪ እና ሄርኪውልስ ብሎ ሰያመው።

ከህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል እስክ ጥበቃ፣ ከእንግዶች እስከ የአደባባይ ህዝብ የእርሱን መገኘት እንደ መለኮት እንዲቀበሉ ሁሉንም አስገደዳቸው። ኢንክታተስ የተባለውን የሚወደውን ፈረሱን እንደ ልዑል እና አማካሪ ለመሾም በመሞከር ተቀምጦበት የማያውቀው ወንበር እና ሶፋ የተሟላለት የሚያምር የእምነበረድ ጉሮኖ እንዲሰራለት ትዕዛዝ አስተላልፎ ነበር።

በአንድ ወቅት በመክሲመስ የሰርከስ ትርዕት ላይ ከእንስሳት ጋር እየተላፉ ህዝቡን የሚያዝናኑ ወንጀለኞች አለቁ። የሚቀጥለው ትዕይንት ደግሞ ምርጫው ከሆኑት ከአንበሶች ጋር ነበር። ለዚህም በመጀመሪያው አምስት መስመር ላይ የሚገኙትን ተመልካቾች ወደ መጨዋቻ ስፍራ እንዲያስገቡአቸው ጠባቂዎቹን አዘዛቸው እነርሱም እንዲሁ አደረጉ። ለእርሱ ደስታ ሲባል እነዚህ ሰዎች ሁሉም በአንበሳ ተበልተው አለቁ። በአንድ ወቅት አንዱ ዜጋ በኃይለኛ ቁጣ ሰደበው ካሊጉላም የመለሰለት ሰውየው ታስሮ በወፍራም ሰንሰለት እንዲገረፍ በማድረግ ነበር። የበሰበሰው የሰውየው ጭንቀላት ሽታ ተመልካቾቹን እና ካሊጉላን እስኪሰነፍጥ እና እስኪቀላ ድረስ ለሶስት ወራት ከምድር እስር ቤት እየወጣ እንዲገረፍ አስደርጓል።

ሌላው የሰደበው ሰው ደግሞ ከእነቤተሰቡ በአደባባይ ህዝብ ፊት እንዲሰቀል አስደርጓል። ሰውየው እና ሚስቱ መጀሪያ ሲሰቀሉ ታላቁ ልጃቸው እና ሌሎች በቅደም ተከተል። ህዝቡ ተቆጥቶ ሲበተን ብዙዎቹ ግን ለማየት ቆይተዋል። የቤተሰቡ የመጨራሻዋ ተረኛ እንዲታይ በተገደደችው ነገር የምታነባው የ12 ዓመት ሴት ልጅ ነበረች። ከተመልካቾቹ አንዱ ልጃ-ገረድ ስለሆነች እርስዎ እንኳን ትታለፍ ብሎ ጮኸ። ካሊጉላም ፈገግ አለ እና ሰቃዩ ሰውዬ ደፍሯት እንዲሰቅላት አዘዘ እርሱም እንዲሁ አደረገ።

የካሊጉላ ተወዳጅ ማሰቃያ መቁረጥ ነው። የመቁረጫ ብላው የሰውን የጀርባ አጥንት እና ደረትን እስከ ወገብ ድረስ ያላቅቃል። ከላይ ወደ ታች ተዘቅዝቀው ሲታሰሩለት የታሳሪዎችን የወንድ ፍሬ ሳይነክስ ማኘክንም በጣም ይወድ ነበር።

በታላቅ የምሳ ግብዣ እና በትዕይንቶች ላይ አንዴ ደግሞ

ምግብ እየተመገቡ በአደባባይ ከሶስት አህቶቹ ጋር ወሲብ ፈጽሟል። መጨረሻ ላይ በፕራየቶሪያን ጠባቂ እና አንዳንድ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት ከመከሲመስ የሰርከስ ትሪዕት ሲወጣ ተገደለ። አስከሬኑ እንዲበሰብስ መንገድ ላይ የተተው ሲሆን መጨረሻ ላይ ውሾች በልተውታል።

ይህ ሰው ትክክለኛ ሰው ነበረ? የሀዘኔታ ስሜት ነበረው? ካሊጉላ መጽሐፍ ቅዱስ ጉልበታሞች እና አምባገነኖች ከሚላቸው "ከጊቦራውያን" አንዱ ይሆን?

## 2. ንጉሠ ነገሥት ኔሮ (54-68ዓ.ዓ.)

ከ54-68 ዓ.ዓ. የገዛው የሮማ ንጉሰ ነገስት ነበረ። ሁሉንም የቤተሰቡን አባላት በዘዴ ገደላቸው። በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን መርዝ አጠጥቷል፣ ቀልቷቸዋል፣ ወግቷቸዋል፣ አቃጥሏቸዋል፣ ቀቅሏቸዋል፣ ሰቅሏቸዋል። ብዙ ጊዜ ሴቶችን የደፈረ ሲሆን የወንዶችንም የሴቶችንም የደም ቧንቧ እና ሀፍረተ ስጋቸውን ቆርጧል።

ከሚስቶቹ አንዷን በእርግጫ እንደ ገደላት ይነገራል። እናቱ ተወግታ እንድትሞት አዝዟል። ያልተለመደ የብዙ ተጻራሪዎች ቅይጥ ነው፡ አርቲስት፣ ስፖረተኛ፣ ጨካኝ፣ ደካማ፣ ሴሰኛ፣ ተለዋዋጭ፣ አባካኝ፣ በሰዎች ሲቃይ የሚረካ እና ወንዳገረድ ነበረ። ይህ ሰው ለሮም መቃጠል ተጠያቂ መሆን ስላልፈለገ ክርስቲያኖች እንዲከሰሱበት አደረገ። በዚህም ምክንያት ክርስቲያኖችም የአውሬ ቆዳ ለብሰው በውሾች እንዲቦጫጨቁ ተደርጓል። ሌሎች ክርስቲያኖች ተሰቀሉ። ሌሎቹ ደግሞ ማታ እንደ መብራት እንዲያገለግሉ ተቃጠሉ።

አንዳንዴ ደግሞ ክርስቲያኖች ቀና ብለው እንዲቆሙ አገጫቸው ስር መደገፊያ ነገር ገብቶላቸው በሰምና እና በሚቀጣጠል ነገር ተሸፍነው እየተቃጠሉ ለተመልካቾች

መብራት እንዲሆኑ ተደርገዋል።

ይህ ጉልበተኛ እንግዲህ ትክክለኛ ሰው ነው ወይስ ጊቦራዊ? አጋንንት ያደረበት ነው? ንጉሠ ነገሥት ኔሮ ከፊል ሰው ከፍል አጋንንት ነበረ?

## 3. አስፈሪው ኢቫን (1530-1584)

ኢቫን በአስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሩሲያን የገዛ መሪ ነበር። ዛር የተሰኘውን የክብር ስያሜ ለማግኘት የመጀመሪያው ገዢ ነው።

በ1570 የኖቮጎሮድ ከተማ ጉምቱ ሰዎች ወደ ፖላንድ ለመኮብለል አቅደዋል የሚል አሳብ ልቡን ስለሞላ ሊያቆማቸው ጥር 2 ላይ ወታደሮችን እየመራ ዘመተ። የከተማዋ ሰዎች እንደያመልጡ የኢቫን ወታደሮች በከተማዋ ዙሪያ የግንብ አጥር ሰሩ። ወታደሮቹ በየቀኑ ከ500 እስከ 1000 ሰዎችን በመሰብሰብ በኢቫን እና ወንድ ልጁ ፊት ያሰቃዩአቸዋል እንዲሁም ይገድሏቸዋል።

ኢቫን በ1581 እርጉዝ የነበረችውን የልጁ ሚስት ያልተገባ አለባበስ ለብሳለች በማለት ደብድቧት ለውርጃ ዳርጓታል። ልክ እንደ እርሱ ኢቫን የተባለው ልጁ ይህን ሰሞቶ ከአባቱ ጋር ሲነታረክ ጫፉ ሹል በሆነ ዘንግ የልጁን ጭንቅላት በመምታት ልጅ ድንገት እንዲሞት ምክንያት ሆኗል።

ኢቫን የራሱ የሆነ የማሰቃያ እልፍኝ አለው። ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው እየተሰቃዩ ሲሞቱ እንዲመለከቱ ያስገድዳቸው ነበር። ድቦች እና ተኩላቸው ብዙ ሰዎችን እንዲበሉ አድርጓል።

በራሱ ብዙ ሰዎችን እያሰቀየ ረጅም እና ጠንካራ በሆነ ዘንጉ ብዙ ሰዎችን ገድሏል። ብዙ ሰዎች እንዲቀሉ፣ እንዲታነቁ፣ እንዲሰቀሉ፣ አይናቸው እንዲጠፉ፣ እንዲቃጠሉ፣ እንዲወጉ፣

እንዲቀቀሉ፣ አንጀታቸው እንዲጎለጎል፣ በቁማቸው እንዲቀበሩ፣ በስለት እንዲወጉ እና እንዲጠበሱ ትዕዛዝ ሰጥቷል። ሰዎች ላይ እርምጃ ሲወሰድ አንድ አንዶቹ እስከ 15 ሰዓታት ቢቆዩም ሁሌ ይመለከት የነበር።

ይህ ሰው ታዲያ የተለመደ ሰው ነው? የሰብዓዊ ርህራሄ ነበረው? ለምን እንደዚህ ክፉ ሆነ? እንደ ማንኛውም የሰው ልጅ ስሜት አልነበረውም? ልዕለ ሰብዓዊ አምባገነን ነበረ?

## 4. *ንጉሠ ነገሥት* ኮሞደስ (161-192 ዓ.ዓ.)

ኮሞደስ ከ180-192 ዓ.ዓ. የገዛ የሮማውያን ንጉሠ ነገሥት ነበረ። የጭካኔያዊ  አገዛዙ የህዝብ ቁጣ በመቀስቀስ ለ84 ዓመታት የዘለቀውን የሀገሪቷን መረጋጋት እና ብልፅግናን ገትቷል።

የጀመረው እንደ ግላዲያተር ሲሆን ብዙ ሰዎችን በማረድ ነበር። የግላዲያተር ጨወታዎችን እጅግ ከመውደዱ የተነሳ ወንጀለኞችን እና ባሮችን የመሳሰሉትን በመቀላቀል ራሱ እንደ ግላዲያተር ይጫወት ነበር። ይህ መላውን ሀገሪቷን በተለይ ደግሞ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላትን ክፉኛ አስከፍቷል። ከእርሱ ጋር ሊገጠሙ ወደ መወዳደሪያ ቦታው የሚመጡ ሰዎች የሚይዙት የእንጨት መሳሪያ ሲሆን እርሱ ግን በኃይለኛው የታጠቀ ነበር። ወንድነቱን ለማሳየት ባለው ፍሎጎት ብዙ ሰዎቸን አርዷል።

በተቀማጠለው የህይወት ዘይቤው የንጉሡን ካዝና ባዶ ሲያደርግ ህግ የሚተካውም መወሰኛ ምክበር ቤት አባላትን በክህደት በመክሰስ እና ንብረታቸውን በመያዝ ነበር።

ኮሞደስ በአንድ ወቅት በከተማው ውስጥ ያሉትን አንካሶች፣ ጎባጦች እና አቅም ደካማ የሆኑት ተከበው እንዲያዙ ካስደረገ

በኋላ በአንድ ቦታ ተሰብስበው በስጋ መሰንጠቂያ እርስ በእርስ እየተፋጁ እንዲያልቁ ትዕዛዝ ሰጥቷል።

እንስሶችን መግደል በጣም ይወድ ስለ ነበረ አንድ ቀን ለተመልካቹም በሚቀፍ መልኩ 100 አንበሶችን ግድሏቸዋል። ከአንካሶች በተጨማሪ እንደ አንበሳ፣ ሰጎን፣ ጉማሬ፣ ዝሆን፣ እና ቀጭኔ ያሉትን የዱር አራዊትን ይገድላቸው ነበር። አንድ ቀን በመወዳደሪያ ስፍራ ውሰጥ ለብቻው ሶስት ዝሆኖችን ገድሎ እና ሰጎን አርዶ እየሳቀ ከፍ አድርጎ ለሚመለከቱት የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት እየነቀነቀ በማሳየት ቀጥሎ ደግሞ ተራው የእነርሱ መሆኑን ይናገራቸው ነበር። ተመልካቾቹ አስፈሪ አድርገው የማይቆጥሯትን ቀጭኔ በጦር ወግቶ ገድሏታል።

በመወዳደሪያ ስፍራ ውስጥ ተጋጣሚዎች እንደ ንጉሠ ነገሥትነቱ ለኮሞደስ እጃቸውን በመስጠት ህይወታቸው ይተርፍ ነበር። በተደበቀ የግል መወዳደሪያ ቦታ ግን ኮሞደስ ተጋጣሚዎቹን ይገድላቸው ነበር። የቆሰሉ እና አካላቸው የተቆረጠ ወታደሮች ወደ መወዳደሪያ ስፍራ ተሰብስበው እንዲሞቱ ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ ሮማውያን ተቆጡ። ሲቪል የሆኑ እና እግራቸውን በአደጋ ወይም በበሽታ ምክንያቱ ያጡ ሰዎች ኮሞደስ ደብድቦ እንዲገድላቸው ታስረው ይሄዱለት ነበር። ይህ ሮማውያንን ዘገነናቸው።

የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት ሊገድሉት ተማክረው መርዝ ቢሰጡት ወርውሮ ጣለው። ከዚያም የእርሱ ተወዳጅ ተጋጣሚ የሆነውን ናርሲስ የሚባል ግላዲያተር ልከውበት በባኞ ቤት ውስጥ እንቆት ገደለው። የአገዛዝ ስርዓቱ የቆየው ከ180-192 ዓ.ዓ. ድረስ 12 ዓመት ነበር። ይህ ሰዎ እንግዲህ ትክክለኛ የተለመደ ሰው ነበር ወይስ ልዕለ ሰው?

## 5. አሜሪካዊው ሰው-በላ

ሰው ገድሎ የሰውን ስጋ የሚበላ አሜሪካዊ ነበረ። የሚታወቀው በመድፈር፣ በመግደል እና የሰዎቹን አካላት በመገንጣጠል ነበር።

በአስራ ሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አስራ ሰባት ሰዎችን እና ወንደ ልጆችን ገድሏል። የተያዙትን ሰዎች እየደፈረ ከመግደሉ በፊት አካለቸውን ይገነጣጥላል። አንዳንዴም የያዛቸውን የሰዎችን የአካል ክፍል ሁላ ይበላ ነበር። የሰዎቹን አስከሬን ቤቱ ውስጥ ባለው በአስዲ የተሞላ እቃ ውስጥ ይጨምራቸው ነበር። የሰዎቹን ጭንቅላት በማበላሸት ማቀዝቀዣ ውስጥ ያስቀምጣቸው ነበር። የገደላቸውን ሰዎች አስከሬን አድርቆ ያቆያቸው እንደ ነበር ይነገራል። የራስ ቅሎች ግን በጓዳው ተገኝተዋል።

ይህ ሰው እንግዲህ የተለመደ ሰው ነው ወይስ ጊቦራዊ ነው?

## 6. የመቃብር ዘራፊው

በ1990ዎች ውስጥ በአሜሪካ ውስጥ የኖረ አንድ ሰው በአስቀያሚ ተግባሩ ይታወቅ ነበር። ለብዙ ሴቶች መሞት ተጠያቂ የሆነ ነፈሰ ገዳይ ነበር። የመቃብር ቦታዎችን በመዝረፍ የሰው አካልን ያስቀምጥ ነበር። ከሰው የራስ ቅል ጎድጓዳ ሳህን ሲሰራ ከሰው ቆዳ ደግሞ የመቀመጫ ወንበር ይሰፋ ነበር።ከሰው ጡት ደግሞ ቀበቶ ሰርቷል። ሰዎችን በመግደል አካላቸውን በከተማ ውስጥ በየቦታው ይበትን ነበር።

ከወንድሙ እና ከእናቱ ጋር ይኖር የነበረ ሲሆን ለእናቱ በጣም ያገለግላት ነበረ። እርስዋ ስትሞት ግን አዲስ የተቀበሩ የሴቶች አካላትን ለማውጣት የመቃብር ስፍራን መጎብኘት

ጀመረ። የአስከሬኖችን አንድ አንድ የሰውነት ክፍል እንደ ዋንጫ እየቆረጠ ሌላውን አስከሬኑን ክፍል ግን ወደ መቃብሩ ይመልስ ነበር።

ይህ ሰው እንግዲህ ትክክለኛ ሰው ነው ወይስ ጊቦራዊ ሊሆን ይችላል?

## 7. የዘር ፈሳሽ የሚረጨው ነፍሰ ገዳይ

በጎ ባልሆነ ምክንያት በከታማው የሚታወቅ አንድ ሰው ነበረ። 53 ሴቶችን እና ልጆችን ገድሏል። በሰባዎቹ ውስጥ አንዲት የዘጠኝ ዓመት ልጃገረድ ወደ አረጀ ቤት አስገብቶ ሊደፍራት ይሞክራል። ልጅቷ ስትታገለው ወግቷት ገደላት። ሊወጋት በነበረው ሂደት ውስጥ የዘር ፈሳሹን ይረጫል።

ከዚያ ቀን ጀምሮ ሴቶችን እና ልጆችን በመውጋት እና ቆርጦ በመግደል የወሲባዊ ስሜት መነሳሳት እና እርካታ ያገኝ ነበር። ትክክለኛ ሰው ነው ወይስ ጊቦራዊ ነው? ለምንድነው ህፃን ልጅን እየገደለ የዘር ፍሬውን የሚረጨው? እነዚህ ከሰዎች የሚጠበቅ ትክክለኛ ስሜት ናቸውን?

## 8. ነፍሰ ገዳይዋ ሚስት እና እናት

በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በእንግሊዝ ውስጥ የኖረች ሴት ነበረች። የመድን ካሳቸውን ለማግኘት ስትል ከአራቱ ባሎችዋ ወስጥ ሶስቱን ገድላቸዋለች። ከአስራ አራት ልጆችዋ ውስጥ ደግሞ አስራ አንዱን ገድላቸዋለች። ሰዎቹ በኃይለኛ የጨጓራ ህመም እንዲሰቃዩ የአይጥ መርዝ ትጠቀም ነበር።

ይህቺ ሴት ለባልና ለልጅ የሚሰጠውን ሰብዓዊ ርህራሄ እና ፍቅር የሌላት ነች። ይህቺ እግዲህ ትክክለኛ ሴት ነች ወይስ ከክፉም የምትበልጥ አጋጥማን ነው?

## 9. አጫዋቹ

አንድ ተከታታይ ገዳይ እና ቀልደኛ የሆነ አሜሪካዊ ሰው ነበረ። መጀመሪያ ሁለት ጎረምሳ ልጆች ላይ ወሲባዊ ጥቃት በማድረስ ለ10 ዓመት ተፈርዶበት ታሰረ። በሳየው መልካም ጸባይ በምህረት ከተለቀቀ በኋላ 33 ወጣት ወንዶችን ወደ መግደል ተሰማራ። ከገደላቸው በኋላ አካላቸውን በደጀፉ፣ በቤቱ ውስጥ እና በቤቱ አካባቢ በሚገኘው ወንዝ ውስጥ ቀበራቸው።

ቀልደኛ ከመሆኑ የተነሳ እንዲህ ዓይነት ክፉት ይፈጽማል ያለው ሰው አልነበረም። 33 ሰዎችን ገድሎ ቤቱ ውስጥ የሚቀብራቸው ምን ዓይነት ሰው ቢሆን ነው? ይህ ክፉ ቀልደኛ ትክክለኛ ሰው ነው ወይስ ስለ እርሱ ከዚህ የበለጠ የከፋና አደገኛ ነበረ?

## 10. ተኩላ የሆነው ሰውየ

"ተኩላውሰው" ተብሎ የሚታወቅ አሜሪካዊ ነበረ። ከመቶ ህጻናት በላይ እና ከአምስት የሚበልጡ አዋቂዎች ላይ ጾታዊ ትንኮሳ ያደረሰ ሰው ነው። የያዛቸውን ሰዎች እስኪደሙ ድረስ የሚገርፍ ሲሆን የሰውነት አካላቸውን እየቆረጠ ደማቸውን የሚጠጣ እና አንዳንዴ ደግሞ አካላቸውን የሚበላ ሰው ነበረ። አንዳንዴ እንዲያውም አካሎቹን በማብሰል ወጥ ሰርቶ ይበላ ነበር።

ጽኑ የወሲብ ፍላጎት የነበረው ሲሆን ከቆሻሻ ጋር፣ በሽንት አማካይነት ከሚገኘው የወሲብ እርካታ፣ ከልጆች ጋር ወሲብ በማድረግ እና በመሰቃየት የሚገኝ የወሲብ እርካታ ያደርግ ነበር። ለወሲባዊ እርካታ ሲባል በወገቡ ውስጥ እንኳን መርፌ አስገብቷል።

ይህ ሰው እንግዲህ የሚጎዳ የማይመስል ሰው ነው ወይስ ጊቦር?

## 11. የአሲድ ባኞ ነፍሰ ገዳይ

የአሲድ ባኞ ነፍሰ ገዳይ ሰዎችን ገድሎ አሲድ ውስጥ የሚጨምር አውሮፓዊ ነበር። የፈለጋቸውን ሰዎች አባብሎ የሆነ ቦታ ይወስዳቸዋል፣ ይገድላቸው እና አካላቸውን ሰልፈሪክ ኢሲድ ውስጥ ይጨምራል።

አንድ ቀን ድንገት ደም አስፈለገው። እናም ቀጣሪውን በሆነ የዶልዱም ዕቃ ጭንቀላቱን መታው እና አንገቱን ሰንጠቅ አድርጎ የቀጣሪውን ደም ጆግ ውስጥ በማፍሰስ ደሙን ጠጣ። ከዚያ የሰውየውን አካል ባዘጋቸው የሰልፈሪክ አሲድ ባርሜል ውስጥ ጨመረው። የሐሰት ሰነዶችን አዘጋጅቶ የደላቸውን ሰዎች ንብረት በመሸጥ ዳጎስ ያለ ገንዘብም ለማግኘት በቅቷል። ይህ ሰው እንግዲ ትክክለኛ ሰው ነው ወይስ ጊቦር?

## 12. እስያዊው አስማተኛ

በ18 ወራት ውስጥ እስከ አንድ መቶ የሚደርሱ ወንድ ህፃናትን የገደለ እስያዊ ሰው ነበረ። ልጆችን መንገድ ላይ ያገኛቸውና ያማልላቸዋል። ከዚያ ጎትቶ እየደፈረ ያንቃቸዋል። ከገደላቸው በኋላ አካላቸውን በቁርጥራጭ እየቆረጠ የሃይድሮክሎሪክ አሲድ ጋን ውስጥ ይጨምራቸዋል። ቁርጥራጮቹ ፈሳሽ ከሆኑ በኋላ የውኃ ማስወገጃ ቦይ ውስጥ ይቸምራቸዋል።

ይህ ሰው ትክክለኛ የሰው ስሜት ነበረው? እንደ ሰው ልጅ ይሆን ነበረ?

## 13. ሴቷ ጠባቂ

በጦርነት ጊዜ የማጎሪያ ካምፕ ትጠብቅ የነበረች አንዲት ሴት ነበረች። የመብራት ጌጣ ጌጦችን፣ የመጽሐፍት ሽፋኖችን እና በማጎሪያ ካምፕ ውስጥ ከሞቱ የሰዎች ቆዳ የተሰራውን ጓንት የመሰብሰብ ዝንባሌ ነበራት። ከተመሳሳይ ዕቃ የተሰራ የሴቶች የእጅ ቦርሳ ነበራት። በማጎሪያ ካምፑ ውስጥ ያለማቋረጥ ብዙ ሰዎችን እያሰቃየች በመግደል "የካምፕ ነፍሰ ገዳዮች " ናቸው ትል ነበር።

ለየት ያለ ታቱ ያላቸውን ሰዎች ለይታ በመምረጥ ትገድላቸው እና ቆዳቸውን እንዲገፈፍ ታደርጋለች።

ፈረስ ላይ በመውጣት ጅራፍ ይዛ በማጎሪያ ካምፑ ዙሪያ እየዞረች አንደ ወንድ እንኳን ወደ እርስዋ ከተመለከተ እዛው ተገርፎ እንዲገደል በማድረግ ጾታዊ መሲህብነቷን ያለ አግባብ ትጠቀምበት ነበር።

ይህቺ እንግዲህ ትክክለኛ ሴት ነበረች? ከሴት ልጅ እና ከእናት የምንጠብቀው ርህራሄ የት አለ? በማጎሪያ ካምፑ ውስጥ ጉልበተኛ እና አምባገነን ነበረች! ይህቺም ጊቦራዊት ትሁን?

## 14. አፍሪካዊው አራጅ

ጣለቶቼ ያላቸውን ከመግደለም ያለፈ የሚያደርግ አፍሪካዊ አምባገነን ነበረ። ጠላቶቹ ከሞቱ በኋላ እንኳን አርመኔያዊ ድርጊት ይፈጽምባቸዋል። ተሰውተው የአስከሬን ማቆያ ቦታ የተጣሉ የእነዚህ ሰዎች አስከሬን በአሰቃቂ ሁኔታ አካላቸው የተቆረጠ እና ጉበታቸው፣ አፍንጫቸው፣ ከንፈራቸው፣ ወሲባዊ አካላቸው እና ዓይናቸው የወጣባቸው ናቸው። አንድ አንዶቹ ሁለቱም እግራቸው እና እጃቸው ተቆርጦ እጅ በእግር

ቦታ እግር ደግሞ በእጅ ቦታ የተሰፋላቸው ናቸው። የግድያ ትዕዛዝ ሲሰጥ ይህ አምባገነን "አሰቃይታችሁ ግደሉት" ለማለት "የከበረ እንክብካቤ ስጡት" ይል ነበር። ይህ አፍሪካዊው አራጅ ጠላቶቼ ብሎ የፈረጃቸውን ብዙ ባለ ከፍተኛ ማዕረግ መኮንኖችን ግድያ አዝዟል። እንዲሁም በፖሊስ አባላት ላይ፣ በማረሚያ ቤቶች እና በዜጎች ላይ የጅምላ ግድያ እንዲፈጸም ትዕዛዝ አስተላልፏል። ይህ ሰው የትክክለኛ ሰው ስሜት ነበረው? እንደ ትክክለኛ ሰው ይሆን ነበር?ልዕለ ሰው ነበረ?

## 15. አፍሪካዊው ሰው-በላ

በመንግስት ግልበጣ ሥልጣን ላይ የወጣ አፍሪካዊ ርዕሰ ብሔር ነበረ። እያሰቃየ እና የፖሎቲካ ተፎካካሪዎቹን እያስገደለ እና የሎቦችን ጆሮ እየቆረጠ በብረት አፈሙዝ ገዝቷል።

የሚቀርቡበት የሰው ስጋን የመብላት ክሶች የተንሰራፉ ነበር። ይህ ክስ የተቀሰቀሰው አንድ የአውሮፓ መጽሔት በማቀዝቀዣ ውስጥ የሚገኝ የትምህርት ቤት ህፃናት አካል የሚያሳይ ፎቶግራፍ ከለቀቀ በኋላ ነበር።

የፖሎቲካ ተፈካካሪዎቹም እየተጠበሱ ከውጪ ለሚመጡት ጎብኚዎች እንደሚቀርቡ ወይም የግሉ በሆነ መካነ አራዊት ወስጥ ለሚገኙ አንበሶች እና አዞዎች ለምግብነት እነደሚቀርቡም ይነገራል። በተቀናጣው የንግስና ሥነ ስርዓቱ ላይ ራሱን እንደ ንጉሠ ነገሥት ከፍከፍ ለማድረግ ብዙ ሚሊዮን ዶላር አፍስሷል።

ይህ ሰው ትክክለኛ የሰው ስሜት አለው? ይህ ሰው እንደ ማንኛውም የሰው ልጅ ይሆናል? ልዕለ ሰው ነበረ?

## ምዕራፍ 21

# በከፊል ሰዎች ውስጥ ያለውን የዲያብሎስን ስራ መከልከል እንዴት ይቻላል

**በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።**

**ዘፍጥረት 6፥4**

በሚገለጡበት በማንኛውም መልኩ ከፊል ሰዎች ለእግዚአብሔር ልጆች ስጋት ናቸው። የእግዚአብሔርን ጥበብ ተጠቅመህ ልብ ልትላቸው እና የሚያመጡትን አደጋ ልትወጣው ይገባሃል። ከከፊል ሰዎች ጋር የምትጋፈጠው በእግዚአብሔር ጥበብ መሆን አለበት። አንዳንዴ ከእነርሱ በመራቅ ልትቋቋማቸው ይገባሃል። አንዳንዴ ስልጣኔ፣ ዕድገት እና ዲሞክራሲ የከፊል ሰዎችን እና የልዕለ-ሰዎችን ኃይል የተወሰነ አድርጓል። አንዳንዴ የከፊል ሰዎችን የምድር ላይ እንቀስቃሴ ሊገታው የሚችለው የተደራጀ ወታደር፣ ፖሊስ እና መልካም አስተዳደር ነው። ስልጣኔ፣ ዲሞክራሲ እና ፖሊስ ባይኖር ኖሮ ጉልበታሞች እና አምባገነኖች መንገድ ላይ እየተዘዋወሩ ህዝብን ያሸብሩ ነበር። የሚቆጣጠራቸው ከሌለ ከፊል ሰዎች ፍርሃታቸውን እያሰራጩ ሁሉንም ሰዎች ያስገድዷቸው ነበር።

## 1. ግዙፍ የሆኑ የከፊል-ሰዎችን ስራ ከልክል

ግዝፈት ኃይል በነበረበት የድሮ ዘመን ግዙፎች እውነተኛ ስጋቶች ነበሩ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግዙፎች ለእግዚአብሔር ህዝቦች ስጋት ነበሩ። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ከግዙፎቹ ብዙ ስጋቶች የእግዚአብሔር ህዝቦች ላይ ነበረ። አንዳንድ ታዋቂ ግዙፎች ጎልያድን የመሳሰሉ የዳዊትን ህይወት እና አገልግሎት ያስፋራሩ ናቸው። የሙሴን፣ ኢያሱን እና ካሌብን ህይወት እና አገልግሎት ያስፈራሩ ሌሎች ግዙፎችም ነበሩ።

**ከፍልስጥኤማውያንም ሰፈር የጌት ሰው ጎልያድ፥ ቁመቱም ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነ፥ ዋነኛ ጀግና መጣ።**

**1ኛ ሳሙኤል** 17፥4

የዳዊት እና የጎልያድ ታሪክ ልዕለ ግዙፍ ሰዎች ስላስፈራሯቸው ሰዎች እውነተኛ ታሪክ ነው። ጎልያድ የእግዚአብሔርን ህዝብ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ያስፈራራው ልዕለ ሰዋዊ በሆነው ቁመቱ ነው።

የኢያሱ እና ካሌብ የስለላ ቡድንም ከነዓን ውስጥ የሚገኙ ግዙፎችን ፈርተው ነበር።

**ስለ ሰለሉአትም ምድር ክፉ ወሬ ለእስራኤል ልጆች እያወሩ፦ እኛ ዞረን የሰለልናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች የምትበላ ምድር ናት፤ በእርስዋም ዘንድ ያየናቸው ሰዎች ሁሉ ረጃጅም ሰዎች ናቸው።**

**በዚያም ከኤናቅ ወገን የሆኑትን ኔፊሊምን፥ የዔናቅን ልጆች፥ አየን፤ እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን፥ ደግሞም እኛ በዓይናቸው ዘንድ እንዲሁ ነበርን አሉ።**

**ዘኍልቁ** 13፥32-33

ዳዊት እና የእርሱ ኃያላን ሰዎችም የጎልያድን ወንድም ጨምሮ ሌሎች ግዙፎችን መዋጋት ነበረባቸው።

**ደግሞም ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሰልፍ ነበረ፤ የያዒርም ልጅ ኤልያናን የጠሩ የቦ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የነበረውን የጌት ሰው የጎልያድን ወንድም ለሕሚን ገደለ።**

**ደግሞ በጌት ላይ ሰልፍ ነበረ፤ ከዚያም በእጁና በእግሩ ስድስት ስድስት ሁላሁሉ ሀያ አራት ጣቶች ያሉት አንድ ረጅም ሰው ነበረ፤ እርሱም ደግሞ ከራፋይም የተወለደ ነበረ።**

**እስራኤልንም በተገዳደረ ጊዜ የዳዊት ወንድም የሳምዓ ልጅ ዮናታን ገደለው።**

1ኛ ዜና መዋዕል 20፥5-7

እንደ አጋጣሚ ሆኖ በእኛ ዘመን ባለ ትላልቅ መጠን እንስሶች እና ሰዎች ጠፍተዋል፡፡ መጠናቸው በተጻራሪ ተጋላጭ ስለሚያደርጋቸው ትልቅ መጠን ላላቸው የሰው ልጆችም ይሁን እንስሳት መኖር እና መብዛት ይከብዳቸዋል፡፡

2. **ባልተለመደ ጥንካሬ የሚመጣውን የከፊል ሰው ስራን ከልክል፡፡**

**ከታንኳይቱም በወጣ ጊዜ፥ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ከመቃብር ወጥቶ ወዲያው ተገናኘው፤**

**እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር፥ በሰንሰለትም ስንኳ ማንም ሊያስረው በዚያን ጊዜ አይችልም ነበር፤**

**ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበርና ዳሩ ግን ሰንሰለቱን ይበጣጥስ እግር ብረቱንም ይሰባብር ነበር፥ ሊያሸንፈውም የሚችል አልነበረም፤**

ማርቆስ 5፥2-4 (አመት)

ማንም ልዕለ ሰው ጥንካሬ ያለው ሰው አስፈሪ ነው፡፡ መቆጣጠር ስለማይችሉ የገደራው እብድ ሰው ለአከባቢው ሰዎች አስጊ ነበረ፡፡ ጠንካራ ሰዎች ጉልበተኛ እና አምባገነን በመሆኑ ሁሌም ለተቀሩት የአከባቢያቸው ማህበረሰቦች ስጋት ናቸው፡፡

እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዛሬ ያልተለመደ ጥንካሬ ስላለህ በቀላሉ ሰዎችን ማስፈራራት አትችልም። የሰው ልዕለ ጥንካሬ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለዘብ ይደረጋል። እንደ ጠመንጃ፣ ቦምብ እና ፈንጂ ያሉት ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች የተዋጊዎች እና የጉልበተኞችን ልዕለ-ጥንካሬ ያስተንፍሱታል። ስለ ተዋጊዎች እና ጉልበታሞች ለማየት የሚያስደስቱን ብዙ ፊልሞች ተሰርተዋል። ተዋጊዎች እና ጉልበታሞች ብዙ ኃይል ስላላቸው የሰው ልጆች ይወዷቸዋል። በድጋሚ የእግዚአብሔር ጥበብ ያልተለመደ ጥንካሬን የተላበሱ የከፊል ሰዎችን ኃይል ዜሮ ያደርገዋል።

## 3. የከፊል ሰዎችን ልዕለሰዋዊ ክፋትን ከልክል።

> **ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥**
>
> **2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥3**

በጣም ክፉ በመሆናቸው የሚታወቁ ሰዎች አሉ። ታሪክ የእነ ኔሮን፣ ካሊጉላን፣ ሂትለር እና አቲላ ዘ ሁኒን ክፋት አይቶ አልፏል። ክፋታቸው ሲወሳ የሚኖር ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ኃይል ሲኖራቸው ክፋታቸው በሰዎች ላይ ይለቀቃል።

እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ለዓለማቸው ስጋት ናቸው። ርህራሄ የሌላቸው ሰዎች ልዕለሰዋዊ ክፋታቸውን ህዝብ ላይ መፈጸም ሲጀምሩ በሀገሪቷ እንኳን መኖር ቀላል አይሆንም።

ርህራሄ የሌላቸው ሰዎች ለማህበረሰባቸው ስጋት ናቸው። ስልጣን ላይ ሲወጡ ርህራሄ-አልባነታቸውን ህዝቡ ላይ ይለቅቁታል። በሰው ልብ ውስጥ ትንሽ እንኳን ሀዘኔታ ሊኖር ይገባል። ያ ሀዘኔታ ሁሌም ክፋት መከሰትን ይገታዋል።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ፣ የዲሞክራሲ ጥበብ ልዕለ ሰዋዊ ክፋት ያላቸውን የሰዎች ኃይል ያጠፋል። መልካም እና የተዋጣለት

የፖሊስ ኃይል እና ጦር የርህራሄ አልባ ሰዎች ኃይልን ይገታል፡፡ የመልካም ፖሊስ አገልግሎት እና መልካም መንግስትን በመደገፍ መልካም ክርስቲያኖች አጋንንቶችን ሊዋጉ ይገባዋል፡፡ አንዳንዴ ወደ ስልጣን የመጡትን ጉለልበታሞች እና አምባገነኖችን ለመሸሽ ሀገር ጥለህ መሄድ ሊኖርብህ ይችላል፡፡

## 4. የከፊል ሰዎችን የወሲባዊ ምኞት ከልክል፡፡

> **ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤**
>
> **ሮሜ 1፥24 (አመት)**

የከፊል ሰዎች ወሲባዊ ፍላጎት የምንለው ሰዎች ተፈጥሮአዊ ምኞት ሳይኖራቸው ሲቀር ነው፡፡ ትክክል ያልሆነውን ወሲባዊ ፍላጎት ከማጎልበት ራስህን መጠበቅ አለብህ፡፡ አንዳንድ ከፊል ሰዎች የወሲብ ማሽኖች ናቸው፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ብዙ ቅጥ ያጣ ወሲባዊ ግንኙነት ያደርጋሉ፡፡ በየሄዱበት ቦታ ሁሉ ወሲብ የማድረግ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች አሉ፡፡ ብዙዎች ለእነዚህ ወሲባዊ አዳኞች ይወድቃሉ፡፡ ይባስ ብሎ አንዳንዶች ደግሞ ለቅጥ ያጣ ወሲብ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ያገባሉ፡፡

> **ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ከባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ። እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤**
>
> **ሮሜ 1፥26-28 (አመት)**

ከላይ እንደ ተጠቀሰው የከፊል ሰዋዊ የወሲብ ስሜት ሰዎች ተፈጥሮአዊ ፍላቶት ሲያጡ ማለት ነው። ከላይ ባለው ጥቅስ ውስጥ ወንዶች ከሴቶች ይልቅ ሌላ ወንድን ነው የሚመኙት። አንዳንድ የሰው ልጆች ተፈጥሮአዊ ግንኙነት ትተው ትክክለኛ ያልሆነውን ወሲባዊ ምኞት ተቀብለው ለማዳቸው ያደርጉታል። አንዳንዶች ተፈጥሮአዊ ተዛምዶን ትተው ለእንስሳት የወሲባዊ ፍላጎት ራሳቸውን ይሰጣሉ። አንዳንዶች ለአዋቂ የሆነውን ተፈጥሮአዊ ተዛምዶን ትተው ትክክል ያልሆነውን የልጆች ወሲባዊ ፍላጎት ይቀበላሉ።

እርኩሳን መናፍስት በሰዎች ውስጥ ሲያድሩ፣ ተፈጥሮአዊ ያልሆነውን ምኞት "ሰብዓዊ መብት" ይሉታል። ዛሬ ሰዎች እንስሳን የመግባት መብት ለማግኘት ይታገላሉ።

እርኩሳን መናፍስት ሰዎችን ሲቆጣጠሩ፣ የጥንቱን የመጽሐፍ ቅዱሳችንን ክፍል "የጥላቻ ንግግር" ይሉታል። እነዚህ እርኩሳን ማናፍሰቶች ልዕለ ሰዋዊ ባህሪይ እና ሰዋዊ ያልሆኑ ባህሪያት እንደ ትክክለኛ እስከሚታዩ ድረስ ሰዎችን መቆጣጠር ይሻሉ። በእርግጥ ሁለንተናዊ የሰው ባሀሪይ ቀውስ የሚያመጣው የሰዎች በእርኩሳን መናፍስት መወረር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እና የእግዚአብሔር ቃል በሚለው ነገር ላይ ጸንቶ ስትቆም የከፊል-ሰዋዊ ወሲባዊ ምኞት ከባድ ጥቃት ሊጎዳህም ተጽዕኖ ሊያሳድርብህም አይችልም።

# ምዕራፍ 22

# እንስሳ መሳይ አጋንንቶችን እንዴት ድል እንደምትነሳ

**ስምህ ማን ነው? ብሎ ጠየቀው። ብዙዎች ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው አለው፥**

**ማርቆስ 5፥9**

ዲያብሎስን እንዴት እንደምንቋቋመው ኢየሱስ አስተምሮናል! ጠላትን ለመቋቋም ዋነኛው ቁልፍ ማንን እየተቋቋምክ መሆንህን ማወቅ ነው:: ለዚህ ነው ኢየሱስ ከጥያቄዎች ሁሉ በጣም ታዋቂ እና በጣም አስፈላጊ ጥያቄ በስነ-አጋንንት/ዲሞኖሎጂ/ መስክ ላይ የጠየቀው:: "ስምህ ማን ነው?"

ስምህ ማን ነው? ለማን ነው የማወራው? ከማን ጋር እይተጋፈጥኩ ነው? በእርግጠኝነት አንተ ማን ነህ? የዘር ግንድህ ከየት ነው? ከየት ነው የመጣኸው? ልዋጋህ፣ ላደቅቅህ፣ ላስወጣህ እና ልጥልህ እፈልጋለሁ!

## ኢየሱስ "ስምህ ማን ነው?" ብሎ ለምን ጠየቀው

መሰረታዊ የጦርነት መርህ ጠላትህን ማወቅ እና ስለ እርሱ በደንብ ማወቅ ነው:: እርሱን የመውጊያ መንገድ ስሙን ማወቅ እና ስለ እርሱ ማወቅ የሚቻለውን ሁሉ ማወቅ ነው::

ለዚህ ነው ኢየሱስ "ስምህ ማን ነው?" ብሎ የጠየቀው::

በሌላ ቃል "እወራሁ ያለሁት ከማን ጋር ነው? ማንን እየተጋፈጥኩ ነው?"

ጠላቶችህንም ራስህንም እወቅ! እርሱን በደንብ እያወቅክ በመጣህ ቁጥር ከእርሱ ጋር ያለህን ጦርነትም ልታሸንፍ ትችላለህ። አንድን ሰው ምን እንደሚመስል ካለወቅክ እንዴት ትተኩስበታለህ? ስለ መጠኑ፣ ስለሚገኝበት ቦታው እና ስለ እንቅስቃሴው ብዙ ነገር የሚነግርህን ስሙን ማወቅ አለብህ።

ጠላትህን ለማወቅ - የት እንደሚኖር፣ ምን እንደሚመስል፣ ምን እንደሚሰራ፣ ምን እንዳለው እና ልትረዳው - በጣም እንድትተጋ እፈልጋለሁ። ጣላትህ እንዴት እንደ ተፈጠረ እና በዓለማችን ላይ በእርግጥ ምን እየሰራ እንደሆነ እንድታውቅ እፈልጋለሁ።

ሙሴ ሰላዮችን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲልካቸው የሰራው ይህንኑን ነው። ስለ ጠላቶቹ ለማወቅ የተለየ ጥረት ያደርግ ነበር። ሙሴ ስለማንነታቸው ምንም ከማያውቃቸው ሰዎች ጋር ጦርነት መግጠም አልፈለገም ነበር።

**ሙሴም የከነዓንን ምድር ይሰልሉ ዘንድ ላካቸው፥ አላቸውም፦ ከዚህ በደቡብ በኩል ውጡ፥ ወደ ተራሮችም ሂዱ፤**

**ምድሪቱንም እንዴት እንደ ሆነች፥ በእርስዋም የሚኖሩ ሰዎች ብርቱዎች ወይም ደካሞች፥ ጥቂቶች ወይም ብዙዎች እንደ ሆኑ፥ የሚኖሩባትም ምድር መልካም ወይም ክፉ፥ የሚኖሩባቸውም ከተሞች ሰፈሮች ወይም አምባዎች እንደ ሆኑ፥**

**ምድሪቱም ወፍራም ወይም ስስ ዛፍ ያለባት ወይም የሌለባት እንደ ሆነች እዩ፤ ከምድሪቱ ፍሬ አምጡ፤ አይዞአችሁ። በዚያን ጊዜም ወይኑ አስቀድሞ ፍሬ የሚያፈራበት ወራት ነበረ።**

**ዘኍልቁ** 13፥17-20

የሆነ ሰው እንዲህ አለ "ጠላትህን ዕወቅ፣ ራስህንም እወቅና

በመቶ የጦር ግንባሮችም አደጋ ውስጥ አትወድቅም።" ይህ መጽሐፍ ስለ ጣላትህ የበለጠ ዝርዝር ነገሮችን ይነግርሃል። ይህ መጽሐፍ በመንፈሳዊው ዓለም የምትዋጋውን እርኩስ ፍጥረታትን እንድትረዳቸው እና እንድታሸንፋቸው ይግዛሃል።

ምንን እየተዋጋህ እንደ ሆነ ካወቅክ በስም ጠርተህ ታወጣቸዋለህ እንዲሁም ታስራቸዋለህ። አጋንንቶችን በስማቸው ስትጠራቸው መቶ ጊዜ የበለጠ ምላሽ ይሰጣሉ። ማንንም ሰው ጮክ ብለህ ስሙን ስትጠራው ዘልሎ ይነሳል! ስምህ ሲጠራ ስትሰማ ልብህ እንዴት እንደሚመታ ልብ ትላለህ።

ዲያቢሎስም ትክክለኛ ስሙ ሲጠራ የሚሆንበትም ያ ነው። እግዚአብሔር ህልም እና ራእይን የሚሰጠውም ለዚህ ነው። በህይወትህ እና በአገልግሎትህ ትግል እና ችግሮች ጀርባ ያሉትን የክፋት መናፍስትን እንድትገልጣቸው ራእይ ይሰጥሃል። ከመጋረጃው ጀርባ ያለውን ነገር ካወቅክ ማጥቃት ትችላለህ። ስሙን በመጥራት በማስወጣት መርገም፣ መገሰጽ እና እሳት እንዲወርድበት ማዘዝ ትችላለህ።

**የንጉሡን ቍጣ ሳይፈራ የግብፅን አገር የተወ በእምነት ነበር፤ የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና።**

**ዕብራውያን 11፥27**

አሁን አድገን የመንፈሳዊውን ዓለም የምናይበት ጊዜ ነው። ሙሴ መልካም አድርጓል ምክንያቱም የማይታየውን ዓለም ዓይቶ እርምጃ ወስዷልና። ክርስቲያን መሆን ማለት በእምነት መሄድ መቻል ማለት ነው። ክርስቲያን መሆን የማይታየውን ማየት ማለት ነው። የማይታየውን ማየት ትችላለህ? በመጽሐፍ ቅዱስ ያነበብከውን ታምናለህ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹት ፍጡራን እውነታ መሆናቸውን ታምናለህ? የማይታየውን ዓለም አይቶ በእምነት የመሄድ ጊዜ ነው። ጥሩ

ሪፖርት ልታገኝ የምትችለው በዚያ መንገድ ብቻ ነው። ብዙዎቻችን የእርኩሳን መናፍስት ጨለማው ዓለም እንዴት እንደ ተፈጠረ አንረዳውም። እርኩሳን መናፍስቶች ምንድን ናቸው የመጡትስ ከየት ነው?

የተለያዩ ዓይነት እርኩሳን መናፍስቶች አሉ። አንዳንድ እርኩሳን መናፍስቶች የወደቁ መላዕክቶች ናቸው። አንዳንድ እርኩሳን መናፍስቶች ደግሞ ከፊል-ሰዎች ናቸው። አንዳንድ እርኩሳን ማፍሰቶች ደግሞ አማልክቶች ወይም ዲያብሎሶች ናቸው። በጨለማው ዓለም እንኳን የእርኩሳን መናፍስት ክፍሎች አሉ።

እየተዋጋን ያለነውን የጠላት ማናፍስትን ለመረዳት ያለሰለሰ ጥረታ ማድረግ አለብህ። እነማን ናቸው? ምን ይመስላሉ? ከየት ነው የሚመጡት? የት ይኖራሉ? የሚያጠቁን እንዴት ነው? ምን ይሰሩብናል? በእነርሱ በእኛ ላይ ስልጣን አላቸው ወይስ እኛ በእነርሱ ላይ ስልጣን አለን?

ስለ እነዚህ እርኩሳን መናፍስቶች የቻልከውን ያኽል ለማንበብና ለማጥናት ያለሰለሰ ጥረት አድርግ። በአንድ ወቅት የአንዱን የመጽሐፍ ቅድስ ትምህርት ቤት አለቃ እግኝቸው ለሥነ-አጋንንት/ዲሞኖሎጂ/ጥናት የትኛውን መጽሐፍ እንደሚጠቀሙ ጠየቅኩት። እንዲህ አለኝ፤ “በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ አጋንንት የለም! በካሪኩለማችን ውስጥም ዲሞኖሎጂ የሚባል የለም!” ስለ ዲሞኖሎጂ በመጠየቄ ሞኝነት ተሰማኝ።

በእነርሱ መኻከል ስለምትኖር የወደቁ መላዕክቶችን፣ ዲያብሎስን እና ከፊል-ሰዎችን ጨምሮ ስለ ሁሉም ዓይነት የክፋት ፍጡራንን ማወቅ አለብህ። መላው ዓለም በክፋት መኻል ይገኛል። የዓለማችንን ክፋትን የተቆጣጠሩት ከመፈጠራችን በፊት ጀምሮ ያሉት የተለያዩ እርኩሳን

መናፍስቶች ናቸው። እየተቋቋምን ያለነው አንድ ሰይጣን የሚባል ከፍተኛ እርኩሰ መንፈስ እና ሌሎች አጋንንት የሚባሉ በሺህዎች የሚቆጠሩ ዝቅተኛ እርኩሳን መናፍስት ናቸው ማለት ከሚፈለገው በላይ ማቅለል ነው። እየተቋቋምን ያለነው ከዚህም የሚበልጡ ናቸው። እየተቋቋምን ያለነው ብዙ ዓይነት አካላትን፣ ህልውናን፣ ፍጡራንን እና ኃይላትን ነው።

መላው ዓለም በእርግጥ ክፋት ውስጥ የወደቀ ሲሆን የዚህ ዓለም አምላክ ደግሞ ሰይጣን ነው። ዛሬ ሁከት፣ እግዚአብሔርን አለመፍራት እና ኃጢአት በዙሪያችን እየተባዙ ነው። አንተ እና እኔ እየተንቀሳቀስን ያለነው በብዙ የክፉ ኃይላት ቁጥጥር ስር ባለችው ዓለም ላይ ነው።

**ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንኳ ተያዘ እናውቃለን።**

1ኛ ዮሐንስ 5፥19

ባለድል ለመሆን እየኖርክበት ያለኸውን ዓለም ማወቅና መረዳት ያለብህ ሲሆን እነዚህን የማይታዩ ግን ደግሞ እውነተኛ የሆኑ ጠላቶችህን በመቋቋም ስኬታም ልትሆን ይገባሃል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ልንቋቋማቸው የሚገቡን የተለያዩ እርኩሳን መናፍስቶችን ጠቅሷል። አራቱ በጣም የሚታወቁ እርኩሳን መናፍሶቶች አለቆች፣ ኃይላት፣ የጨለማው ዓለም ገዢዎች እና በሰማያዊ ስፍራ ያለ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ናቸው(ኤፌሶን 6፡12)።

ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ብዙ ዓይነት ፍጡራንና አካላት ይገኛሉ። ክፋትን የተሞላ ድቅድቅ ያለ የጨለማው ዓለም አለ። በገሃዱ ዓለም የሚታየውን የሚወስነው ይህ የጨለማው ዓለም ነው። መጽሐፍ ቅዱስህን

በማስተዋል ብታነብ፣ ብዙ የተገለጹ ወይም የተጠሩ የተለያዩ ፍጡራንን ታገኛለህ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጨረፍታ ለተጠቀሰው ክፉ ፍጡር እንኳን ትኩረት ልትሰጠው ይገባሃል። መጠቀሳቸው መኖራቸውንና እየተዋጉህ መሆናቸውን እንድታውቅ ነው።

> **ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና።**
>
> **1ኛ ዮሐንስ 3፥8**

እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ የኢየሱስን ተልዕኮ ማስቀጠል መቻል አለብህ። የኢየሱስ ተልዕኮ ደግሞ የዲያብሎን ስራ ማፍረስ ነው። ምን እንደ ሆነ እና ምን እንደሚመስል ሳታወቅ የዲያብሎስ ስራ እንዴት ልታፈርሰው ትችላለህ? በእርግጥ ስለ እርኩሳን መናፍስት፣ ስለ ኃይላቸው እና ስለ ስራቸው ልታውቅ የሚገባህ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ዛሬ ስለ አጋንንት እንማያጠኑ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች አሉ። በደስታ "በትህምህርት ቤታችን አጋንንቶች የሉም" ይላሉ።

ወዳጄ ያሉትን የተለያዩ የእርኩሳን ፍጥረቶችን እየተዋጋ እንደማትኖር የምታስብ ከሆነ ራስህን እየሸወድክ ነው። ዲያብሎስን፣ አጋንንቶችን፣ አለቆችን፣ ዙፋናትን፣ ዘንዶዎችን፣ እባቦችን፣ ኃይላትን፣ አካላትን፣ መንፈሳዊ ዲቃላዎችን፣ ከፊል ሰዎችን፣ የሌዋታን መንፈስን፣ የወደቁ መላዕክቶችን መቋቋም የክርስትናችን አካል ነው።

**የእንስሳ ማናፍስት የሚሰሩት አካለዊ ተነጻጻሪያቸው የሚሰራውን ነው፤**

1. **ለኤሊያስ የመጡት መንፈሳዊ ኃይሎች ልክ ተፈጥሮአዊ ፈረሶች ለመጓጓዣነት እንደሚውሉ ለሰረገላና ለመጓጓዣነት ውለዋል። በመጽሐፈ ራእይ ላይ ያሉት**

መንፈሳዊ ፈረሶች ልክ እንደ ተፈትሮአዊ ፈረሶች ለግልብያ ግልጋሎት ውለዋል::

ሲሄዱም፥ እያዘገሙም ሲጫወቱ፥ እነሆ፥ የእሳት ሰረገላና የእሳት ፈረሶች በመካከላቸው ገብተው ከፈሉአቸው፤ ኤልያስም በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጣ።

ኤልሳዕም አይቶ፦ አባቴ አባቴ ሆይ፥ የእስራኤል ሰረገላና ፈረሰኞች፥ ብሎ ጮኸ። ከዚያም ወዲያ አላየውም፤ ልብሱንም ይዞ ከሁለት ተረተረው።

2ኛ ነገሥት 2፥11-12

2. መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው እባብ ሔዋንን አታለላት:: በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈትሮአዊ እባቦች መኖራቸውን፣ አለመኖራቸውን፣ የማይጎዱ መሆናቸውን፣ መደበቃቸውንና ከተፈጥሮ ጋር መማሳሰላቸውን ሰዎች ድንገት እስከሚረግጡአቸው ድረስ በመደበቅ ሰዎችን ይሸውዳሉ::

እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው። እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም።እግዚአብሔርም አለው፦ ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?አዳምም አለ፦ ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ። እግዚአብሔር አምላክም ሴቲቱን፦ ይህ ያደረግሽው ምንድር ነው? አላት። ሴቲቱም አለች፦ እባብ አሳተኝና በላሁ።

ዘፍጥረት 3፥9-13

3. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው መንፈሳዊ አንበሳ ልክ እንደ ተፈጥሮአዊ አንበሳ እያገሣ ይዞራል::

በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና።

1ኛ ጴጥሮስ 5፥8

4. መንፈሳዊ አእወፋት ልክ እንደ ተፍጥሮአዊ አእዋፋት ጎጆአቸው ውስጥ ይቆያሉ

በብርቱም ድምፅ፦ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች።

ራእይ 18፥2

5. መንፈሳዊ ዝንቦችና በራሪ ነፍሳቶች ልክ እንደ ተፈጥሮአዊ ዝንቦችና በራሪ ነፍሳቶች በሽታ ማምጣታቸው ግልጽ ነው::

እግዚአብሔርም እንዲሁ አደረገ፤ በፈርዖንም ቤት በባሪያዎቹም ቤቶች ውስጥ ብዙ የዝንብ መንጋ መጣ፤ በግብፅም አገር ሁሉ ላይ ከዝንቡ መንጋ የተነሣ ምድር ጠፋች።

ዘጸአት 8፥24

6. ጊንጦችን ድንገት ረግጠናቸው ይነድፉናል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ኢየሱስ ጊንጦችን እንድንረግጣቸው ኃይል ይሰጠናል::

እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።

ሉቃስ 10፥18-19

## አስር ዓይነት እንስሳ መሳይ አጋንንቶች

1. ዝንቦች ወደ አንተ የሚላኩት ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤

ከኢየሩሳሌም የወረዱ ጻፎችም፦ ብዔል ዜቡል አለበት፤ ደግሞ፦ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ብለው ተናገሩ። እነርሱንም ወደ እርሱ ጠርቶ በምሳሌ አላቸው፦ ሰይጣን ሰይጣንን ሊያወጣው እንዴት ይችላል?መንግሥትም እርስ በርስዋ ከተለያየች ያች መንግሥት ልትቆም አትችልም።

ማርቆስ 3፥22-24

2. የተጠሉ መንፈሳዊ ወፎች የሚላኩብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤ አንድ አንድ አጋንንቶ የተጠሉ ወፎች ይባላሉ።

በብርቱም ድምፅ፦ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች።

ራእይ 18፥2

3. የጓጉንቸር መንፈስ የሚላክብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤ አንድ አንድ አጋንንቶች ጓጉንቸር ይባላሉ።

ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጉንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፥ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ።

ራእይ 16፥13-14

4. ጊንጦች የሚላኩብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤ አንድ አንድ እርኩሳን መናፍስቶች ጊንጦች ይባላሉ።

እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።

ሉቃስ 10፥19

5. ዘንዶዎች የሚላኩብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤ አንድ አንድ እርኩሳን መናፍስቶች ዘንዶ ይባላሉ።

ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።

ራእይ 12፥9

6. መንፈሳዊ እባቦች የሚላኩብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤ አንድ አንድ እርኩሳን መናፍሰቶች እባቦች ይባላሉ።

እነዚህ በጋሃድ የምናያቸው እባቦች ሳይሆኑ መንፈሳዊ እባቦች ናቸው::

**እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተ ኋላዋ አፈሰሰ።**

**ራእይ** 12፥15

7. **መንፈሳዊ ፈረሶች የሚላኩብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤**

**አየሁም፥ እነሆም፥ ሐመር ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ነበረ። ሲኦልም ተከተለው፤ በሰይፍና በራብም በሞትም በምድርም አራዊት ይገድሉ ዘንድ ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው።**

**ራእይ** 6፥8

8. **መንፈሳዊ የባህር ፍጡር የሚላክብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤** አንድ አንድ እርኩሳን መናፍስቶች ሌዋታን ይባላሉ:: ሌዋታን የታወቀ ባለ ብዙ ራስ የባህር ፍጡር ነው::

**የሌዋታንን ራሶች አደቀቅህ፤ ለምድረ በዳ ፍጥረታትም ምግብ አድርገህ የሰጠሃቸው።**

**መዝሙር** 74፥14**አመት**)

9. **ባለ ብዙ ራስ የባህር ፍጡር የሚላክብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤** አንድ አንድ አጋንንቶች በባሕር ውስጥ የሚኖሩ ባለ ብዙ ራሶች ናቸው:: አንዳንዶች የባህር መንፈስ ይሉታል::

**አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ።**

**ራእይ** 13፥1

10. **መሬት ስር የሚገኘው በለ ብዙ ራሶች ፍጡር የሚላክብህ ከመንፈሳዊው ዓለም ነው፤** አንዳንድ አጋንንቶች መሬት

ውስጥ የሚኖሩ በላ ብዙ ራሶች ናቸው:: እነዚህ ምድራዊ መናፍስት ናቸው::

**ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር።**

**ራእይ** 13፥11

# የእንስሳ-መሳይ ዲያብሎስን መኖሩ እንዴት ይታወቃል

በሚያጋጥሙህ የጥቃት ባህሪይ የእንስሳዊ ምልክቶችን በማስተዋል የእንስሳ-መሳይ አጋንንቶች ህልውናን መለየት ቀላል ነው::

1. **የድንገተኛ፣ የደፈጣዎች እና ወጥመዶች ዓይነት ያልተጠበቁ ክፉ ክስተቶች የእባብ ስራን የሚያመልክቱ ናቸው::** እባቦች በድንገተኛ ጥቃታቸው ነው የሚታወቁት:: ሲመጣ አታየውም:: የት እንደተደበቀም አታውቀውም:: የጥቃቱ ድንገተኛነት የእባብ መንፈስ መኖሩን ያሳይሃል::

2. **የሚበክል እና የሚያረክስ የጠላት ጥቃት የሚያሳየው እባብን ነው::** ቤተክርስቲያንን የሚያጠፉ እና በአንድ ወቅት የነበረውን ጣፋጭ ነገሮችን የሚያበላሽ እባብ ነው:: ሁሉንም ነገር በምትቀየረው በአንድ ጠብታ መርዝ የሰው ህይወት ሙሉ በሙሉ ይበላሻል:: ሀሴትህንና ፍቅርህን የሚያበላሹ ነገሮችን ልብ በል:: ቤተክርስቲያንን መልካም የሀሴት፣ የሰላም እና የፍቅር ድባቦችን የሚቀይሩ እና ቤተክርስቲያንን የሚጎዱ ነገሮችን አስተውል:: አለመደሰትን፣ ቅሬታን፣ ማጉረምረምንና ግራ መጋባትን የሚያስከትሉ ነገሮችን ልብ በል:: የሚበክል እና የሚያረክስ የእባብ መንፈስ እንደ ያዙ አምናለሁ!

3. **ድንጋጤን፣ ሽብርንና ፍራቻን የተሞላ የጠላት ውጊያ የአንበሳ መንፈስ ህልውናን ያመለክታል::** አንበሳ ሲያገሳ በቅርበቱ ሰምቶ የማይደነግጥ ማንም ሰው የለም:: አንድ ቀን እውነተኛ ታሪክ ላይ ተሞርኩዞ ስለተሰራና በአንድ ትልቅ የሆስፒታል ድንኳን ውስጥ ስለሚታከሙ ህሙማን ፊልም አየሁ::አንድ አንዶቹ ግሉኮስ ላይ ሲሆኑ አንድ አንዶቹ ደግሞ በከፊል ንቁ ነበሩ:: ፊልሙ የሆነ ቦታ ላይ ሲደርስ አንበሳ ወደ ድንኳኑ ገብቶ ያገሣል:: ይህ በህይወቴ ካየሁት የመጨራሻ ፈጣኑ ተዓምራዊ "የፈውስ አገልግሎት" ነበር:: እያንዳንዱ ተካሚ ከመሞቻ አልጋው ላይ ተነስቶ እግሬ አውጭኝ አለ:: የአንበሳው ግሳት ሁሉንም ነገር ሽፍኖ ወደ እንቅስቃሴ አስገባቸው:: አንበሶች በእርግጥ እውነተኛ ፍራቻን ይፈጥራሉ!

ከትዕብተኛና ብርቱ የሆነ ሰውን የምትቋቋምበት የጠላት ውጊያም የአንበሳ መንፈስ እይተቋቋምክ መሆኑን ይጠቁማሉ:: አንበሶች የሚታወቁት በብርታት ወደ ፊት በመጓዝ እንጂ ፈርተው ወደ ኋላ መሸሽ ወይም ሀሳባቸወን መቀየር የሚባል ነገር አያውቁም:: ትዕብተኛ እና ብርቱ ነኝ የሚለን ልብ በል:: ድመቶች ትዕብተኞች ናቸው፤አንበሳም ድመት ነው!

**የአንበሳ ደቦል ከእንስሳ ሁሉ የሚበረታ፥ የማይመለስ፥ እንስሳንም የማይፈራ፤**

**ምሳሌ** 30፥30

4. **ህመምና በሽታን የሚያካትት የጣላት ውጊያ ከዝንቦች፣ በራሪ ነፍሳት እና በሽታ አምጪ ህዋሳት ጋር የተያያዘ ነው::** በእርግጥ የበራሪ ነፍሳት እና ዝንቦች መንፈሳዊ መገለጫቸው ልክ እንደ አካለዊ መገለጫቸው በሽታን፣ ህመምንና ሞትን በያዙት ሰው ላይ ማስከተል ነው::

አንዱ ሰይጣን የሚታወቅበት ስሙ "የዝንቦች ጌታ" በመባል ነው። የበሽታ ወኪሎች አዛዥ ነው።

5. **ምቾት የሚነሳ ህመምም የጠላት ውጊያ የጎጉንቸር መንፈስ ህልውናን የሚያመለክት ነው።**

**ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጉንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኵሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤ ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፥ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ።**

**ራእይ** 16፥13-14

ጎጉንቸሮች በራሳቸው አጥፊዎች አይደሉም ይሁን እንጂ ጤና አሳጥተው ያሳምሙሃል። የእነርሱ መኖር ሁሉንም ነገር ምቾት የሚነሳ እና የማይሰማማህ ያደርጋሉ። ብዙ ጊዜ ምቾትህ፣ ቅለትህ፣ እረፍትህ በጣላት ውጊያ ይወሰድብሃል። እንደዚህ ዓይነት የጠላት ጥቃት ምናልባትም በአብዛኛው ጊዜ ሊከሰት የሚችለው በጎጉንቸር መንፈስ ነው። የጎጉንቸር መንፈስ ጫና ማስጨነቅ፣ መረበሽ እና በሀሳብ እንድትወጠር ማድረግ ነው። ያለሰላም፣ ያለምቾት እና ያለእረፈት የማታከናውናቸው ብዙ ነገሮች አሉ።

# ምዕራፍ 23

# አጋንንቶች ወዳንተ አካል ውስጥ እንዳይገቡ እንዴት ልታስቆማቸው ትችላለህ

**... ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።**

**ኤፌሶን 4፥27**

ሰይጣን ወደሚያስተው ሰው ገብቶ ኃይለኛ የክፋት ስራ መስራት ይችላል::

**ሰይጣንም ከአሥራ ሁለቱ ቊጥር አንዱ በነበረው የአስቆሮቱ በሚባለው በይሁዳ ገባ፤ ሄዶም እንዴት አሳልፎ እንዲሰጣቸው ከካህናት አለቆችና ከመቅደስ አዛዦች ጋር ተነጋገረ።**

**ሉቃስ 22፥3-4**

**ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎችን አጋንንት ከእርሱ ጋር ይወስዳል፥ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል። ለዚህ ክፉ ትውልድ ደግሞ እንዲሁ ይሆንበታል።**

**ማቴዎስ 12፥45**

ወደ ሆነ ቤት ውስጥ በየትኛው አቅጣጫ መግባት ትችላለህን? ወደ አንድ ቤት የምትገባው በበሩ አይደለምን? እንግዲህ አጋንንቶቸ እንደ ቤት ካዩህ ዲያብሎስ ዒላማ ያደረገው በር አለ ማለት ነው:: ዲያብሎስ በቤቱ በር ለምን ፍላጎት ያሳድራል? ሌቦች የቤቱ በር በየት በኩል እንዳለ ለማወቅ ይፈልጋሉ? ምክንያቱም ወደ ቤቱ መግቢያ መንገድ

ስለሚፈልጉ ነው! ሰዎች የቤታቸውን በር ለምን ያጠነክራሉ? ለምን የደህነነት በሮች ላይ ሰዎች መዋዕለ ንዋያቸውን ያፈሳሉ? ምክንያቱም የክፉና እርኩሳን ሰዎች መግቢያ ኬላ ሊሆን ስለሚችል ነው!

አጋንንቶች ወደ አካል መግባት ከፈለጉ የሚገቡት በመግቢያ ኬላዎች እና በሮች ነው:: ለአጋንንቶች የመግቢያ መንገዶች እንዳይሆኑ አማኞች ስለ እነዚህ በሮች ማወቅ ያስፈልጋቸዋል::

እንደ ሰው ልጆች ስድቱን የአካላችሁን ቀዳዳዎች ዋወቅ አለባችሁ:: እያንዳንዱ ቀዳዳ ወደ ጥልቁ እና የውስጠኛው የአካል ክፍል የሚወስዱ ናቸው:: የሰው አካል ስድስት ዋና ዋና ቀዳዳ ወይም ተከፋች በር አለው:: እያንዳደንዱ ለእርኩሳን መናፍስቶች ዓይነተኛና ምቹ መግቢያ ሊሆኑ ይችላሉ:: በእነዚህ ቀዳዳዎች የሚደረገው ማንኛውም የኃጢአት ስራ እርኩሳን ማናፍስቶች ወደ አካልህ እንዲገቡ በር ይከፍታሉ:: እነዚህን በሮችና ቀዳዳዎች ነቅተህ መጠበቅ አለብህ ምክንያቱም የእርኩሳን መናፍስት ዒላማ ውስጥ የወደቁ ናቸው::

## 1. የጆሮ በር

ጆሮ አጋንንታዊ ምናቦች ወደ አእምሮ የሚተኮሱበት በጣም አስፈላጊ የሆነ በር ነው:: የሰማኸው እንድታስብ ያደርግሃል! ኢየሱስ ለመስማት ስለምንፈቅደው ነገር እንድናስተውል አስጠንቅቆናል::

> **አላቸውም፦ ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ። በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል ለእናንተም ይጨመርላችኋል።አላቸውም፦ ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ። በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል ለእናንተም ይጨመርላችኋል።**
>
> **ማርቆስ 4፡24**

የምታስበው ነገር ወደ ሀሳብና ውስብስ ምናብ ያድጋል::

የማይሆነውን ነገር በመስማት የሰይጣን ሀሳብና ምናብ በአዕምሮህ ውስጥ ይጠነሰሳል። ሰይጣን አእምሮህን በድብርት፣ ስጋት፣ ዝሙትና በቀል ከያዘ በእርሱ ኃይል ስር ትወድቃለህ። አዶልፍ ሂትለር ፀረ ሴማዊና የሃምሳ ሚሊዮን ሰዎች ነፍስ ገዳይ የሆነው ተራ የሆኑ የመንገድ ሰዎች ስለ አይሁዶች የሚያወሩትን መልካም ያልሆነ ነገር በመስማት ነው። እርሱም በሂዳት የአይሁዶች ጥላቻ በውስጡ ተፈጠረ። እምነት በመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው። ምናብም በመስማት የሚመጣ ነው። ሐሳብና አስተያየት የሚመጣው በመስማት ነው። ስለዚህ ጆሮህ ለአጋንንቶች መግቢያ በር ነው። ለዚህ ነው ኢየሱስ "ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ" ብሎ ያስተማረን።

ሰይጣን ወደአንተ መግቢያ እንዴት እንደሚያገኝ ማወቅ ከፈለግክ ከአዳምና ሔዋን ተማር። አብሮነታቸውን እያጣጣሙ ባሉ ሁለት ፍጹም ሰዎች መኻከል ሰይጣን እንዴት ገባ? ሰይጣን አዋራቸው እና ኃጢአት እንዲሰሩ ሞከረ። ልክ ኃጢአት ሰርተው እግዚአብሔርን ሲበድሉ ሰይጣን የህይወታቸው አንድ አካል ሆነ።

ኃጢአት መስራት ማለት ለዲያብሎስ መገዛት ማለት ነው። ለዲያብሎስ "እሺ" ማለት እርሱን በአንተ ላይ አለቃ ወይም አዛዥ እንደ ማድረግ ነው። ሰይጣን አንዴ በህይወትህ ላይ አዛዥ ከሆነ በእርሱ እና በአስተዳደሩ ስር ትሆናለህ ማለት ነው። እንደምታየው በጠላት ምሪት ስር የሆነ ማንኛውም ሰው ወይም ማንኛውም ነገር ኃጢአት አድራጊ፣ ክፉ፣ ጨካኝ፣ ተስፋ የሌለው፣ ድብርት የያዘው፣ የሚያዝን፣ የሚሰቃይ እና ያለ ማቋረጥ ጨለማ ውስጥ የሚሆን ሰው ነው። ሰይጣን አለቃህ እንዲሆን አትፈልግም። ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት በሮችን በመክፈት ለእርኩሳን መናፍስቶች ላቅ ያለ መግቢያ ይሰጣል።

ሰይጣን ወደ ሰው ዘር የገባው ሔዋንን በማናገርና እንደ እግዚአብሔር መሆን የሚመስል ድንቅ ነገር በምናቧ እንድትስል በማድረግ ነበር። በምናቧ የሳለችው ነገር ሲበልጥባት ከእባቡ የመጣባትን ጫና ለመቀበል ወስናለች። ሰይጣን የነገራት ነገር ሁሉ የሚፈጸም እንደ ሆነ አሰበች። ከነበራት ነገር ሁሉ የላቀ መልካም ነገር እንደሚኖራት አሰበች። ይሁን እንጂ ሰይጣን አንድም ቃል የገባውን ነገሮች ፈጽሞ አያውቅም። ጆሮዋን ለዲያብሎስ ሰጥታ ሀሰትን በመስማት የጆሮዋን በር ስትከፍት እርሷ፣ ባሏ እና የሰው ዘር ሁሉ ጠፍቷል። ምን እንደምትሰማ በጣም መጠንቀቅ አለብህ። ከሔዋን የላቀ ጠንካራ ወይም የተሻልክ መስሎ አይታይህ። መስማት የሌለብህ አንድ አንድ ነገሮች አሉ!

ከማውራት ይልቅ ብዙ ጊዜ ስለሚያስቡ ዝምተኛ ሰዎች በአጋንንት የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። የልባቸውን፣ ችግራቸውን እና ስለህይወታቸው ለሌሎች ከማጋራት ይልቅ በማሰብ ክፉና ጨለማ አስተሳሰብን ያብሰለስላሉ። ለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል አሳብን እንድናፈርስ የሚያስተምረን።

> **የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥**
>
> **2ኛ ቆሮንቶስ 10፥4-5**

ምናብ/አሳብ የሚጎለብት፣ የሚያድግ እና የሚሰራጭ ሀሳብ ነው። ከሚገባ በላይ ዝም የሚሉ ሰዎች ሲኖሩ ይጨንቀኛል። ምን እያሰቡ እንደሆነ መናገር ከቶ አልችልም። ይወዱኛል? ይጠሉኛል? እየሸወድኳቸው ያለሁ ይመስላቸዋል? የሆነ ነገር እያቀዱ ነው? ቅርብ ጊዜ በጨለማና ራስን የመግደል ክፉ አስተሳሰብ የተሞላ አንድ አውሮፕላን አብራሪ ሙሉ ሰዎችን ያሰፈረ አውሮፕላንን የፈራንሳይ አልፕስ ተራሮች ጋር

ፈጥፍጧል። የግል ኮምፒውተሩ ሲፈተሽ ብዙ ጊዜ እንዴት ራስን መግደል እንደሚቻል ፈልጎ ሲያጠና እንደነበር ተደርሶበታል! እንደዚህ ዓይነት ሰው በጨለማ አስተሳሰብ የተሞላ ቢሆንም ምን እንደሚያስብ አያጋራም። በአውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ሁሉም በዚህ ሰው የጨለመ የአስተሳሰብ ስጋት ውስጥ ነበሩ። በእርግጥ በረራው ላይ የነበሩ ሰዎች ሁሉም ሰውየው ምን እንደሚያስብ ስለማያውቁ አልቀዋል! ዝመተኛ ሰው መልካም ነገር ያስባል ብሎ መገመት አደገኛ ነው! ዝምተኛ ሰውና ጸባይህ የሚቀያየር (ሙዲ) ሰው ከሆንክ መጠንቀቅ አለብህ ምክንያቱም ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ እርኩሳን መናፍስቶች ሊገቡብህ፣ በውስጥህ ሊያድሩና ነፍስህ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሊመላለሱ የሚችሉበት ስጋት ውስጥ ነህና!

## 2. የዓይን በር

> **የሰውነትህ መብራት ዓይንህ ናት። ዓይንህ ጤናማ በሆነች ጊዜ ሰውነትህ ሁሉ ደግሞ ብሩህ ይሆናል። ዓይንህ ታማሚ በሆነች ጊዜ ግን ሰውነትህ ደግሞ የጨለመ ይሆናል።**
>
> ሉቃስ 11፥34

ዓይን ሊገቡብህ ለሚፈልጉ አጋንንቶች ጋባዥ በር ነው። አብዛኛዎቹ ምናቦች እና አስተሳቦች የዲያብሎስ ኃይላዊ እንቅስቃሴዎ በስራ ላይ ስለመሆናቸው ማስታወስ ግድ ይልሃል። ለዚህ ነው ጳውሎስ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን (2ኛ ቆሮንቶስ 10፡5) ብሎ የሚያስተምረን።

ዓይን ራእይዎች፣ ምስሎችና ሀሳቦች ወደ ጭንቅላት የሚገቡበት በር ነው። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለምናየው ነገር የሚያስጠነቅቀን። ብዙ እርኩሳን መናፍስቶች ወደ ሰዎች የሚፈሱት ሰዎች ፖርኖግራፊና ኢ-ተፈጥሮአዊ የሆኑ ነገሮችን

ሲያዩ ነው:: ልክ ያልሆነ ፍላጎት፣ ልክ ያልሆነ ስሜትና ዝሙት በወጣቶች ውስጥ እያበጠ የሚመጣው ፖርኖግራፊን ለረጅም ሰዓታት ሲያዩ ነው:: ብዙ ሰዎች ህይወታቸው በፖርኖግራፊ ተጽዕኖ ስር ከሆነ በኋላ እንደ በፊቱ ሊሆኑ አይችሉም::

ብዙ ሰዎች የሆነ ፊልም ካዩ በኋላ ነፍሰ ገዳይ ይሆናሉ:: ሰዎች ፊልምን በማየት እንዴት እንደሚገድሉ፣ እንደሚዋጉ እና እንደሚያጠፉ ይማራሉ:: የእነዚህ እርኩሳን መናፍስቶች መኖር ስብዕናቸውን ሙሉ በሙሉ በመለወጥ ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍቅር ውጪ እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል::

ፊልም አይቶ አደራረግን ከመማር ጋር የተያያዙ ብዙ የነፍስ ግድያ ጉዳዮች አሉ:: በዓይን በኩል ምናባዊ አስተሳሳብ አእምሮ ውስጥ ተጠንስሶ የዲያብሎስ ኃይል ይፈጠራል::

ለዚህ ነው ልክ ያልሆነ ነገርን ከማየት ራሳችሁን መጠበቅ ያለባችሁ:: የፍርሃት መንፈስን ከሚያመጣባቸው ፊልሞችም ልጆችህን መጠበቅ ያለብህ ለዚህ ነው:: አንድ አንድ ልጆች የሆነ አስፈሪ ፊልም ካዩ በኋላ እንደ በፊቱ ሊሆኑ አይችሉም:: ብዙ ልጃገረድ ሴቶች የሆነ ፊልም ካዩ በኋላ በፍርሃት መንፈስ ይሞላሉ:: ብዙ ሰዎች ተከታታይ የቴልቪዥን ድራማን ካዩ በኋላ በፍቅር እና በዝሙት መንፈስ የሞላሉ:: ለዓይንህ መጠንቀቅ አለብህ! ራስህን የስብከት ቪዲዎችና መንፈስ ቅዱስ የሞላበትን ፊልሞችን ለማየት ስጥ:: በቀን ውስጥ አብዛኛውን ጊዜውን ፊልም በማየት የሚያስልፍ ሰው በእርኩሳን መናፍስቶች የመጠቃት ዕድሉ ከፍተኛ ነው::

### 3. የአፍ በር

ሞት የልብህ ምት መቆም ማለት ብቻ አይደለም:: ሞት ሰውኛ ነው! ሞት መንፈስ ነው! ሞት ፈረስን የሚጋልብ ነው!

የመንፈስ ወደ ህይወትህ መግባት ማለት ነው። የሞት መንፈስ ነው። ሰይጣን ከመጀመሪያውም ነፍሰ ገዳይ ነው። ይህ ማለት ሰይጣን ከሁሉ አስቀድሞ ገዳይ ወይም ነፍስ የሚወስድ ነው። ሞት ወደ ሰዎች የሚመጣው በአብዛኛው በሚመገቡት ምግብ ነው። ከታች በተጠቀሰው ጥቅስ ሞት እንዴት ፈረስ ጋላቢ እንደሆነ ትመለከታለህ።

**አየሁም፥ እነሆም፥ ሐመር ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ነበረ። ሲኦልም ተከተለው፤ በሰይፍና በራብም በሞትም በምድርም አራዊት ይገድሉ ዘንድ ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው።**

**ራእይ 6፥8**

ወደ አካላቶችህ የአስፈላጊ ነገሮች የመግቢያ ቀዳዳ አፍ ነው። ብዙ እርኩሳን ማናፍስቶችና በሽታዎች ወደ አካል የሚገቡት በአፍ በኩል ነው። ብዙ ውኃ ወለድ በሽታዎችና ውኃ ነክ የሆኑ በሽታዎች ወደ አካል የሚገቡት በአፍ ነው። ብዙ በሽታዎች ወደ ሰውነት የሚገቡት በሚበሉ ምግቦች በኩል ነው። ሳልሞኔሎሲስ፣ ዲያሪያ፣ ኮሌራ፣ ዲይዘንቲሪ እና ታይፎይድ ወደ ሰውነት የሚገቡት በአፍ በኩል ነው። የጊኒ ዎርም ወደ ሰውነት የሚገባው የተበከለ ውኃ ስትጠጣ ነው።

ዛሬ የምንወስዳቸው ጮማ፣ ዘይትና ሌሎች ብዙ ምግቦች እንዴት በሽታን፣ ህመምና ሞትን እንደሚያመጡ ሳይንቲስቶች እያረጋገጡ ነው። ሞት በአፍህ በኩል ወደ ህይወትህ ሊገባ የሚችል ሰው፣ መንፈስ እና ጋላቢ ነው።

ከኢየሱስ የምትማረው አንድ ወሳኝ ነገር ከመብላቱ በፊት አንዴት ያመሰግን እንደ ነበረ ነው። ብዙ እንስሶች እርኩሳን መናፍስት ያደሩባቸው መሆኑና ብዙ እርኩስ ነገሮች ደግሞ በአፋችን በኩል ወደ ሰውነታችን ይገባሉ። የምትበላውን ምግብ ጸልየህ መብላት ከልምምድም ያለፈ ነው። ወደ ሰውነትህ ሊገባ

ያለውን ነገር የመቀደስና የማንጻት ጉዳይ ነው።

## 4. የአፍንጫ በር

አንዱ የእርኩሳን መናፍስት ትልቁ በር አፍንጫ ነው።

ብዙ ጥቃቅን ግን ደግሞ ገዳይ ቫይረሶች ወደ ሰው ልጆች የሚገቡት በአፍንጫ በኩል ነው። በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን የገደሉ ብዙ ዓለም አቀፋዊ ወረርሽኝ ወደ ሰውነት ክፍል የገቡት በአፍንጫ በኩል ነው። ጉንፋን በኢንፍሉዌንዛ ቫይረስ የሚመጣ ነው። ሰዎች ሲያስነጥሳቸው፣ ሲያስላቸውና ሲተነፍሱ አየር ወደ ውስጥ ለሚያስገባ ለሌላኛው ሰው ቫይረሱን ያጋራሉ። ሊገድላቸው የሚችል ቫይረስ ይሁን ባክቴሪያ ወይም በሽታ እንዳይዛቸው አንድ አንድ ሰዎች አውሮፕላን አይሳፈሩም።

ለዚህ ነው በጣም የታመሙ ሰዎች እንዳይበሩ የሚመከሩት ምክንያቱም ለብዙ ሰዓታት ተዘግቶባቸው በሚቆዩበት የአውሮፕላን በረራ ላይ በብዙ በሽታዎች ሊያዙ ስለሚችሉ ነው።

በኢቦላ ቫይረስና በወፎች ጉንፋን ቫይረስ ስንት ሰው እንደ ሞተ አስተውለህ ታውቃለህ? የሞት መንፈስ በአፍንጫ ወደ ሰዎች ይገባል። በሽታንና ሞትን የሚያመጣው ቫይረሶች መሆናቸውን ሳይንስ ያሳየናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተነሳ ደግሞ ሳይንስ ከሚያስተምረን በላይ እናውቃለን።

ልጆች ሲወለዱ የአየር ወለድ በሽታ የሆነውን የሳንባ ነቀርሳ ክትባት ወዲያው ይወስዳሉ። በህክምና ሳይንስ አዲስ የተወለዱ ልጆችን ሊገድልብን የሚፈልግን የሞት መንፈስ መከልከል ችለናል።

በእስትንፋስ እርኩሳትን ወደ ውስጥህ ላለመሳብ በጥበብ

ተመላለስ። በሳይንስ ኃይልና ጥበብ የገዳይ አጋንንቶችን ስራ ትከለክላለህ።

## 5. የሴት ልጅ የብልት በር

ብልትሽ የአጋንንቶች ተመራጭ በር ነው! በእያንዳንዱ ቤት ተመራጭ በር ይኖራል! ወደ አንድ ቤት መግቢያ ሶስት በሮች ቢኖሩ እያንዳንዱ ሰው በማዕድ ቤት በር በኩል አልፎ ይገባ ይሆናል። በተመሳሳይ መልኩ ወደ ሰውነትህ የሚያስገቡ ስድስት በሮች አሉ ይሁን እንጂ የሴት ልጅ ብልት ለአጋንንቶች ተወዳጁና ተመራጩ በር ነው።

የሴት ልጅ ብልት ምንድነው? የሴት ልጅ ብልት ልጅ የሚወለድበት የሴት ልጅ ቀዳዳ ክፍል ነው። በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ እና በዝሙት ኃጢአት ጊዜም ተጥሶ የሚገባ የአካላዊ ክፍል ነው። (በብልት በኩል በሚደረግ ) በኃጢአታዊ የወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ እርኩሳን መናፍስቶች ወደ ሴቶች ይገባሉ።

ብዙ ሴቶች ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ኃይል ወድቀው ሲጮሁ፣ ሲጠቀለሉና ሲያለቅሱ ታያለህ። ብዙ ጊዜ የብልታቸው በር ተከፍቶ እርኩሳን መናፍስቶች ገብቶባቸው ነው። በእርግጥ ዝሙት ከእርኩሳን መናፍስት እና ሌሎች ፍጡራን መግባትና መኖር ጋር በቀጥተ የተገናኘ ብቸኛው ኃጢአት ነው። እርኩሳን መናፍስቶች እንዴትና ለምን ወደ ባቢሎን እንደገቡ የሚናገረውን ይሄን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አስተውል።

> **በብርቱም ድምፅ፦ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤ አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቍጣ ወይን ጠጅ የተነሳ**

**ወድቀዋልና፥ የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ የምድርም ነጋዴዎች ከቅምጥልነትዋ ኃይል የተነሳ ባለ ጠጋዎች ሆኑ ብሎ ጮኸ።**

**ራእይ 18፡2-3**

ባቢሎን የአጋንነቶች ማደሪያ ለምን ሆነች? ሰዎች የአጋንንቶች ማደሪያ ለምን ይሆናሉ? አንድ ሴት የአጋንንቶች ማደሪያ ለምን ትሆናለች? ከጥቅሱ እንደምትመለከተው ብዙ እርኩሳን መናፍስቶችና ፍጥረታት ባቢሎንን የተቆጣጠሩአት በቀላሉ ከዝሙቷ የተነሳ ነው። ይህ ትርጉምና ማብራሪያ የማያስፈልገው ቀጥተኛና ግልጽ ዓረፍተ ነገር ነው።

ዝሙት የሆነ ደረጃ ላይ ሲደርስ የክፋት እርኩሳን መናፍስቶች የሴቷን አካላት በብልቷ በኩል ይወሯትና ገብተውባት ማደሪያቸው ያደርጓታል። በክፋት የእርኩሳን ማነፍስቶች የተወረሩ ሴቶች የላቀ ወሲባዊ መነቃቃት ያላቸው፣ ለወሲብ የሚስቡና የሚጋብዙ ይሆናሉ። ለዚህ ነው እንደዚህ ዓይነት ሴቶች ከረጅም የወንዶች ዝርዝር ጋር ዝሙት ማድረግን የሚቀጥሉት። በአጋንንት የተያዙ ሴቶች ለወሲብ በጣም የሚያማልሉ ስለሆኑ ወንዶች ልክ እንደ ዝንብ ወደ እነርሱ ይሳባሉ። ወንዶች ወደእነዚህ ሴቶች የሚሳቡት ልዕለ-ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ ነው ምክንያቱም መስህብነታቸው ልዐለ-ተፍጥሮአዊና ልዕለ-ሰዋዊ ስለሆነ ነው። የማይጠረጥርና መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ሊቋቋማቸው እንዳይችል አጋንንቶቸ ውበታቸውንና ስሜት ቀስቃሽነታቸውን ያንሩታል። መንፈሳዊ ሰዎች ብዙ ጊዜ በፊታችን በሚንጎማለሉ የወሲባዊ ደስታ እንጅ ምንም በማይመስሉን እነዚህ ውበታቸው የጎመራው ሴቶች ይጸየፏቸዋል።

የዚህ መስህብነት ልዕለ-ተፍጥሯዊ መልክን በዕድሜ የገፉና እምብዛም ሳቢ ያልሆኑ ሴቶች ያለማቋረጥ ወንዶችን ወደራሳቸው ሲስቡ ማየት ይቻላል። በዕድሜ የገፉና የማያምሩ

ሴተኛ አዳሪዎች ለመግለጽ በሚከብድ መልኩ በመቶዎች የሚቆጠሩ ደንበኞችን ወደራሳቸው ሲስቡ አስተውለህ አታውቅም?

ሴቶች ዝሙት ውስት ሲዘፈቁ የሚወሯቸው የክፋት ወሲባዊ መናፍስቶች ብቻ አይደሉም:: የበሽታና የሞት መናፍስቶችም እነዚህ ሴቶች በዝሙት ሲዘፈቁ ይወሯቸዋል:: እነዚህ መናፍስቶች በብልቶቻቸው በኩል ነው የሚገቡባቸው:: አጋንንቶች በመንጋ ህብረት ማድረግንና መዋደድን ይወዳሉ:: ሚሊዮኖችን የገደሉት እንደ ኤችአይቪ ያሉና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ወደ ሴቶችና ወደ ሰው ዘር የገቡት በሴት ብልት በኩል ነው:: አጋንንቶች መንጋና ቡድን መፍጠር ይወዳሉ:: የሚያዛቡ፣ የክፋት፣ የበሽታና የሞት መናፍስቶች ያለማቋረጥ ጥምረት በመፍጠር ሴቶችን በብልቶቻቸው በኩል ይወሯቸዋል::

የአጋንንቶች ማደሪያ እንዳትሆኚ ብልትሽን አጠብቀሽ ጠብቂ! የትኛውን ብልት እያሰስክ እንደሆነ ልብበል! የአጋንንቶች መንጋን ከአጋሪህ ልትጋራ ትችላለህ! ብዙ እየኖርክ ስትሄድ ሰዎች ከዝሙት ጸጸት እንዴት ማገገም እንደሚከብዳቸው ታያለህ:: በህጋዊነት ገብቶ እነርሱ ውስጥ በመኖር የሚያስጨንቃቸው የእርኩሳን መናፍስት ኃይል ነው::

## 6. የፊንጢጣ በር

**ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።**

**እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤**

**ሮሜ 1፥26-28 (አመት)**

ፊንጢጣ ሌላኛው የአካል ቀዳዳ ነው። ሰዎች የሴት ልጅ ብልትን በመተካት በፊንጢጣ በኩል እርስ በእርስ ነውር ያደርጋሉ። ይህ በላይ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ በግልጽ ሰፍሯል። ፊንጢጣ የሚያገለግለው ለሰገራ ማስወገጃነት ነው። ይሁን እንጅ ወደ ግብረስጋ ግንኙነት የመግቢያ አካልነት ተቀይሯል። አንዳንድ ሰዎች ፊንጢጣቸው ስለላላ ሰጋራቸውን ለመቆጣጠር ዳይፐር ያስፈልጋቸዋል።

የግበረሰዶማዊነት መንፈስ እና ኢ-ተፍጥሮአዊ የሆነ ነገር ወደ ሰዎች የሚገባው የወንድ የአካል ብልትን ፊንጢጣ ውስጥ በመጨመር ነው። ግብረሰዶማዊነት ኃጢአት ነው ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚናገር። ብዙ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የህክምና ማህበራት በዚህ ዝንባሌ የሰው ልጅ እንዳልተወለደ በግልጽ እየተናገሩ ነው። ይህ ከውልደት በኂላ የዳበረ ነው።

የግብረሰዶማዊነት ኃጢአት እርኩሳን መናፍስቶች እንዲገቡ መንገድ ይከፍታል። በግብረሰዶማዊነት ውስጥ ያሉት ሰዎች በዚያ ውስጥ ከሌሉት ሰዎች በላቀ ሁኔታ በሚያሳዩት ከፍተኛ ፍላጎት የግብረሰዶማዊነት መንፈስ መልክ ይታያል። ግብረሰዶማዊነት ወደ ወንድ ልጅ ህይወት ሊገባ ከሚችለው ኃይል ሁሉ በላቀ የሚያበላሽ እና የሚያቁነጠንጥ ነው። ዝሙት የመፈጸም ግፊትና ፍላጎት በግብረሰዶማዊነት ለመቀጠል ካለው ፍላጎት ያነሰ ነው። በዚህ ህይወት በሚቀይር ሁኔታ ውስጥ ላለ ሰው ርህራሄን የማሳየት አስፈላጊነት የላቀ መሆን ያስፈልጋል።

ራስን ለመቆጣጠር እንኳን የሚከብደው የዚህ ከፍተኛ ጉጉት ባህሪይ በህግ እንኳን ሳይቀር እውቅና አግኝቷል። አንድ

ታዳጊ ወጣት ልጅ በአዋቂ ሰው ወሲባዊ ጥቃት ከተፈጸመበት ህይወቱ ለዘላለም ሊቀየር እንደሚችል ህግ እውቅና ይሰጣል። አንድ ሰው ግብረሰዶማዊ ከሆነ ሰው ጋር ግንኙነት ካደረገ በኋላ ህይወቱ ፈጽሞ ጠንካራ እና በማይነቃነቅ ኃይል ሊለወጥ ይችላል። የግብረሰዶማዊያን ከፍተኛ ፍላጎታቸውን በልጅነታቸው ከደረሰባቸው ወሲባዊ በደል ጋር የሚያይዙ ሰዎች አሉ። የልጆችን ፊንጢጣ ጥሶ በመግባት የልጆችን ህይወት የሚያበላሹ አዋቂ ሰዎች እንደ ወንጀለኞች ይቆጠራሉ። በፊንጢጣቸው በኩል ለአጋንንቶች የተጋለጡትን ሰዎች ለመርዳት ከፍተኛ የሆነ ጸጋና ርህራሄ ይፈልጋል።

የግብረሰዶም ፍላጎት መንፈስ ብቻ አይደለም በፊንጢጣ በኩል የሚገባው። እንደ ተለመደው የአጋንንቶች መንጋ ህብረት ለማድረግ ወደ አንተ ይገባሉ። ብዙ ሰዎችን ያረደው የኤችአይቪ ወራሪ በሽታ ወደ ዓለም የገባው ቫይረሱን ባሰራጨው ግብረሰዶማዊ በኩል ነው። በእርግጥ ፊንጢጣ ለሞት መንፈስ፣ ለሊቅና ኢ-ተፍጥሮአዊ ለሆኑት ዋና የመግቢያ በር ነው።

# ምዕራፍ 24

# በእግዚአብሔር የእቃ ጦር ደህንነትህን እንዴት ታጣናክራለህ?

**ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ።**

**1ኛ ጴጥሮስ 3፥4**

**በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥**

**ኤፌሶን 3፥16-17**

**በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥**

**ሮሜ 7፥22**

በመንፈስ የሰው መልክ ይዘህ እንደ ሰው ትታያለህ:: የሰው አምሳያ አለህ ማለት ነው:: ዲያብሎስና መላዕክቶች በመንፈስ እንደ ወንድና ሴት ያዩሃል:: ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የውስጥ ሰውን የውስጥ ሰውነት ወይም የተሰወረ ሰው ብሎ የሚገልጸው:: የተሰወረ ሰው፣ የውስጥ ሰው፣ ወይም ደግሞ እንደ ፍላጎትህ የውስጥ ሰውነት አለህ::

ኢየሱስ በአልዓዛርና የሀብታሙ ሰውዬ ምሳሌ ላይ እንደተናገረው ከሞት በኋላ በህይወት መኖር የሚቀጥለው ይህ ሰውነታችን ነው:: ሀብታ ሰውዬና አልዓዛር ከሞቱ በኋላ በህይወት የሚኖሩና በደንብ መግባባት ችለው ነበር:: ከሞቱ

በኋላ እንኳን ሀብታሙ ሰውዬ፣ አልዓዛርና አብርሃምም ሳይቀር የሚኖሩና ተለይተው እንደ ሰው የሚታወቁ ነበሩ። እኔና አንተም በመንፈስ ውስጥ በእርግጥ እንደ እውነተኛ ሰዎች ስንሆን በዲያብሎስ፣ በመላዕክቶች እና በእግዚአብሔርም ጭምር የምንታየው በዚህ መልኩ ነው።

የዲያብሎስ ዒላማ የሚሆነውም ይሄው የውስጥ ሰው፣ የተሰወረ ሰው ወይም የውስጥ ሰውነታችን ነው። የአጋንንት ጉባዔም በናፍቆት እየሰለሉህ በአንተ ውስጥ ገብተው በደስታ ለመኖር በመከላካያህ ላይ ክፍተቶችን ይፈልጋሉ።

እንደ ሰው ለብሰህ ወይም ራቁትህን ልትሆነ ትችላለህ። ሎዶቃዊያን ራቁታቸውን እንዳሉ ክርስቲያኖች ነበር የተጠቀሱት። ይህ አካላዊ ራቁትነት እንዳለሆነ ግልጽ ነው ምክንያቱም እነርሱ ራሳቸው ራቁታቸውን መሆናቸውን አያውቁም ነበርና። ራቁትናታቸው ተነግሮአቸው ነው።

**ሁብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስከማታውቅ።**

**ራእ** 3፥17

በመንፈስ ከመልበስ ሌላ በጦር እቃም ትጠበቃለህ። ይህ የጦር እቃ የምድርን ከባቢ ከሞሉት የሚበሩ ወራሪ አጋንንቶች ጥበቃ ይሰጥሃል። በእርግጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ሁሉም ክርስቲያኖች አንዳንድ የጦር እቃን እንዲለብሱ ተናግሮአል። ይህ ያስፈለገው በከባቢው ውሰጥ እንደ አዕዋፋት መንጋ የሚበሩ አጋንንቶች ስላሉ ነው። እንደ ዝንቦችና በራሪ ነፍሳት መንጋ ወዲህና ወደዚያ የምንቀሳቀሱ አጋንንቶች አሉ። እነዚህ አጋንንቶች በሰው ልጅ ውስጥ ለማረፍ የሚሹ ናቸው። ራስህን ዘና ካደረግክ እነዚህ አጋንንቶች አንተን ወይም ጓደኛህን ይወራሉ። በመንፈሳዊ ዓለም እውነታ የምትቀልድ ከሆነ

ከፍተኛ የሆነ ዋጋ ያስከፍልሃል።

እብድ ሰው ስታይ ሁኔታው እንዴት እንደዚህ ሊሆን እንደቻለ ጥያቄ ይፈጥርብሃል። ይህ የዘመናት ጥያቄ ነው። ሰዎች ለአጋንንት እንዴት ይጋለጣሉ? ሁሉም ሊባል በሚችል ሁኔታ ሰዎች በአስፈሪ ሁኔታ በአጋንንት የተያዘ ሰው ያውቃሉ ወይም ጓደኛ አላቸው። ይህ እውነታ ሁላችንም ለአጋንንቶች እንዳንጋለጥ ራሳችንን እንድንጠብቅ የሚያደርገን ነው።

የወራሪውን አጋንንት መንጋ ጥቃትን መመከት እንድንችል መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ደህንነታችንን ማጥበቅ እንዳለብን በግልጽ ይነግረናል። የነፍስህ፣ የመንፈስህ እና የስጋህ ደህንነት ሊጠብቅ የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለጠው መሰረት ብቻ ነው። ራስህን መከላከል ትችላለህ!

ጊዜው ለአጋንንቶች እና ወራሪ ዲያብሎስ ተጋላጭ የምትሆንበትን መንገድ ሁሉ የምትቀንስበት ነው። ለአጋንንቶች መንጋ ተጋላጭነትህን የምትጨምርበት ስድስት ግልጽ መንገዶች አሉ። ደህንነትህን ለማሳደግ መፍጨርጨር አለብህ። ማንኛውንም ዓይነት ወረራ መክተህ መመለስ አለብህ! ራስህን መከላከል አለብህ!

## ደህንነትህን በእግዚአብሔር የጦር ዕቃ አጥብቅ

1. **እውነትን መከተል እና ሽንገላን መቃወም አጋንንቶች የመንፈስህን ሰው እንዳያጠቁ ጥበቃውን ያጠነክራል።** ውሸትና ሽንገላ የመንፈስህን ቀበቶ ያላላና በመንፈሳዊው ዓለም ተጋላጭ ያደርግሃል።

   ማንኛውም ዓይነት ውሸት ለአጋንንታዊ ወረራ ያጋልጥሃል። ማንኛውም ዓይነት ሽንገላ ለአጋንንታዊ

ወረራ ያጋልጥሃል። ማንኛውም ዓይነት ራስን ማታለል ለአጋንንታዊ ወረራ ያጋልጥሃል።

**እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥** የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ።

ኤፌሶን 6፥14

2. **ጽድቅን መፈጸምና ከኃጢአት መራቅ አጋንንቶች የመንፈስህን ሰው እንዳያጠቁ ጥበቃውን ያጠነክራል።** የትኛውም ዓይነት ዓመጸኝነት የመንፈስህን ደረት ለአጋንንቶች መንጋ ያጋልጣል። የትኛውም ዓይነት ኃጢአት ለአጋንንታዊ ወረራ ያጋልጥሃል። ይህ ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት የሚበሩት አጋጋንንቶቸ ወደ አንተ ወርደው አንተን እንዲወሩህ ያደርጋቸዋል። ዕድለቢሳም ብትሆንን በአንተ አካባቢ ብዙ ዓይነት የወፎች እና በራሪ አካላት መንጋ ቢኖር መጥፎ ወረራ ሊያጋጥምህ ይችላል።

እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ **የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥** በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ።

ኤፌሶን 6፥14

3. **ስለ ድነትህ አጥብቆ መናገር አጋንንቶች የመንፈስህን ሰው እንዳያጠቁ ጥበቃውን ያጠነክራል።** መዳንህን ቸል ማለት የመንፈስህን ራስ ለአጋጋንንቶች ወረራ ያጋልጣል። ስለ መዳን መስበክና ማስተማር የቤተክስቲያንን ድህንነት ያጠብቃል። ስለ መዳንህ መስበክ እና ስላለው ዋጋ አታሳንሰው ምክንያቱም ያ ራስህን ለአጋንንቶች ያጋልጣልና።

**የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።**

ኤፌሶን 6፥17

4. **ለወንጌል ዋጋ መስጠት እና ወንጌልን መስበክ አጋንንቶች የመንፈስህን ሰው እንዳያጠቁ ጥበቃውን ያጠነክራል።** ወንጌልን አለመስበክ የመንፈስህን እግር ለአጋንንቶች ወረራ ያጋልጣል።

**በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤**

ኤፌሶን 6፥16

5. **እምነትህ እና እምነትን መለማመድ አጋንንቶች የመንፈስህን ሰው እንዳያጠቁ ጥበቃውን ያጠነክራል።** አለማመን ሙሉ በሙሉ ለአጋንንቶች ያጋልጥሃል። የጥሪ እምነት! ስለማይታዩት እምነት! የፈውስ እምነት! የብልጽግና እምነት!

**በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤**

ኤፌሶን 6፥16

6. **የእግዚአብሔርን ቃል የሁሉም ነገሮች መሰረት አድርጎ መጠቀም የመንፈስህን ደህንነት ያጠነክራል።** የእግዚአብሔርን ቃል በተናገርክ/በተጠቀምክ ቁጥር የመንፈስን ሰይፍ እያወዛወዝክ ስለሆነ ዲያብሎስ አይወደውም። ለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃልን አለመጠቀም ለአጋንንቶች የሚያጋልጥህ። የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ፣ ማስታዋስ፣ ማጥናትና እንደ ቃሉ በህይወትህ ዘመን ሁሉ መኖር አስፈላጊ ነው። ይህን ስታደርግ የመንፈስ ሰይፍ በእንቅስቃሴ ላይ የሚሆን ሲሆን ደህንነትህም ጠንካራ ይሆናል።

**የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።**

**ኤፌሶን** 6፣17

7. **ጸሎት አጋንንቶች የመንፈስህን ሰው እንዳያጠቁ ጥበቃውን** ያጠነክራል። አለመጸለይ ሁሉ ነገርህን ለዲያብሎስ ያጋልጣል። ለዚህ ነው ጳውሎስ የመንፈሳችንን ደህንነት እንድናጠናክር ጸሎትን እንደ መጨረሻና አጠቃላይ የምንፈልገው ነገር አድርጎ የሰጠን።

**በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤**

**ኤፌሶን** 6፣18

# ምዕራፍ 25

# በእግዚአብሔር የጦር እቃ ጥቃትን እንዴት ማገድ ትችላለህ

**የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።**

**ኤፌሶን** 6፥11

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አንድ እርምጃ ወደፊት መሄድ አለብህ። ደህንነትህን ከማጠናከር ያለፈ ነገር ማድረግ አለብህ። ሰይጣን የሚከፍትብህን ጥቃት በሙሉ ማገድ አለብህ።

የዲያብሎስ ማታላያዎች በዚህ ዓለም ላይ ከሁሉም የላቀ የክፉ ፍጡር ጥቃት ናቸው። ሰይጣን በጣም ተንኮለኛ ስለሆነ እያደረገ ያለውን ነገር ማየት ቀላል ላይሆን ይችላል። ክፋቱ በአንተ ላይ በጣም ትልቅ ቢሆንም የምታገኘው ግን መጨረሻ ላይ ብቻ ነው።

ምንም ሳታውቅ አልጋ ላይ በአንሶላ ውስጥ ቀስ ብሎ ከሚሄድ ኮብራ እባብ ጋር መተኛትን አስብ። ይህ ገዳይ አደጋ ሲተሻሽህ ማሳጅ ሊመስልህ እንኳን ይችላል። አልጋ ውስጥ ተደብቆ የገባውን የዚህን ክፉ እባብ ጀርባ በስሱ እየዳሰስክ ስለ ፓስታና ስለ ስጎው ሁላ ልታልም ትችላለህ።

ይሁን እንጂ የጠላት ተንኮል፣ ወጥመድና ደፈጣ እንዳይሰራ የሚያደርግ ዋና መገለጥ ደግሞ እግዚአብሔር ሰጥቶናል።

# የእውነት ማሰሪያ የዲያብሎስን ጥቃት ያግደዋል

1. በህይወትህ ስለ የእግዚአብሔር ፈቃድን በተመለከተ ሽንገላን አታስተናግድ እንዲያ ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃት፣ ብልሃትና ተንኮልን ፊፅመህ ታግደዋለህ። ውሸትን፣ አታላይነትንና እውነት ያልሆነውን በማገድ የዲያብሎስን ብልሃት ማገድ ትችላለህ።

**እግዚአብሔርም፦ ወጥቶ በሬማት ዘገለዓድ ይወድቅ ዘንድ አክዓብን የሚያሳስት ማን ነው? አለ። አንዱም እንዲህ ያለ ነገር፥ ሌላውም እንዲያ የለ ነገር ተናገረ። መንፈስም ወጣ በእግዚአብሔርም ፊት ቆሞ፦ እኔ አሳስተዋለሁ አለ። እግዚአብሔርም፦ በምን? አለው እርሱም፦ ወጥቼ በነቢያቶቹ ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ እሆናለሁ አለ። እግዚአብሔርም፦ ማሳሳትስ ታሳስተዋለህ፥ ይሆንልሃልም ውጣ፥ እንዲሁም አድርግ አለ። አሁንም፦ እነሆ፥ እግዚአብሔር በእነዚህ በነቢያትህ ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ አድርጎአል፤ እግዚአብሔርም በላይህ ክፉ ተናግሮብሃል።**

1ኛ ነገስታት 22፥20-23

2. ምን ያህል ቆንጆ እንደሆንክና ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆንክ ማጭበርበሪያዎችን አታስተናገድ ያ ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃት ታስወግደዋለህ።

**የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፦ የሰው ልጅ ሆይ፥ ለኢየሩሳሌም ርኵሰትዋን አስታውቃት፥ እንዲህም በል፦ ጌታ እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም እንዲህ ይላል፦ ዘርሽና ትውልድሽ ከከነዓን ምድር ነው፤ አባትሽ አሞራዊ ነበረ እናትሽም ኬጢያዊት ነበረች። በተወለድሽ ጊዜ በዚያው ቀን እትብትሽ አልተቈረጠም ንጹሕም ትሆኚ ዘንድ በውኃ አልታጠብሽም፥ በጨውም አልተቀባሽም በጨርቅም አልተጠቀለልሽም። በተወለድሽበት ቀን ከሰውነትሽ ጕስቍልና የተነሣ በሜዳ ላይ ተጣልሽ እንጂ ከዚህ አንዳች ይደረግልሽ ዘንድ ዓይን አልራራልሽም፥ ማንም አላዘነልሽም።**

በአንቺም ዘንድ ባለፍሁ ጊዜ በደምሽም ውስጥ ተለውሰሽ ባየሁሽ ጊዜ፦ በደምሽ እንዳለሽ በሕይወት ኑሪ አልሁሽ፤ አዎን፦ በደምሽ እንዳለሽ በሕይወት ኑሪ አልሁሽ። በእርሻ ላይ እንዳለ ቡቃያ አበዛሁሽ፥ አንቺም አደግሽ ታላቅም ሆንሽ፥ በእጅጉም አጌጥሽ፤ ጡቶችሽም አጐጠጐጡ ጠጕርሽም አደገ፥ ነገር ግን ዕርቃንሽን ሆንሽ፥ ተራቍተሽም ነበርሽ። በአንቺ ዘንድ ባለፍሁና ባየሁሽ ጊዜ፥ እነሆ፥ ጊዜሽ የፍቅር ጊዜ ነበረ፤ እኔም መጐናጸፊያዬን በላይሽ ዘረጋሁ ኀፍረተ ሥጋሽንም ከደንሁ፤ ማልሁልሽም ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፥ አንቺም ለእኔ ሆንሽ።

በውኃም አጠብሁሽ ከደምሽም አጠራሁሽ በዘይትም ቀባሁሽ። ወርቀ ዘቦም አለበስሁሽ በአቆስጣ ቁርበትም ጫማ አደረግሁልሽ፤ በጥሩ በፍታ አስታጠቅሁሽ በሐርም ከደንሁሽ። በጌጥም አስጌጥሁሽ በእጅሽም ላይ አንባር በአንገትሽም ላይ ድሪ አደረግሁልሽ። በአፍንጫሽም ቀለበት በጆሮሽም ጕትቻ በራስሽም ላይ የክብር አክሊል አደረግሁ። በወርቅና በብር አጌጥሽ፥ ልብስሽም ጥሩ በፍታና ሐር ወርቀ ዘቦም ነበረ፤ አንቺም መልካምን ዱቄትና ማርን ዘይትንም በላሽ፤ እጅግ በጣም ውብ ሆንሽ ለመንግሥትም ደረስሽ።

ባንቺ ላይ ካኖርኋት ከክብሬ የተነሣ ውበትሽ ፍጹም ነበረና ዝናሽ በአሕዛብ መካከል ወጣ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ነገር ግን በውበትሽ ታምነሻል ስለ ዝናሽም አመንዝረሻል ምንዝርናሽንም ከመንገድ አላፊ ሁሉ ጋር አበዛሽ።

ሕዝቅኤል 16፡1-15

3. የቤተክርስቲያንህን ሁኔታ በተመለከተ ማጭበርበሪያ ሃሰቦች አታስተናግድ ያ ሲሆን የዲያብሎስን የተንኮል ጥቃት ማስቆም ትችላለህ። ሰይጣን ቤተክርስቲያንህን በማውደም ምንም እንድትሆን ሊያደርግህ ይፈልጋል።

የበጎችህን መልክ አስተውለህ እወቅ፥ በከብቶችህም ላይ ልብህን አኑር፤

ምሳሌ 27፡23

4. በህይወትህ አጭበርባሪ ሃሳቦችን አታስተናግድ ወይም እንዴት በመንፈሳዊ ህይትህ ጠንካራ እንደሆንህ በማሰብ አትታለል፣ ያ ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃት ማገድ ትችላለህ።

ስለዚህ እንድ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።

1ኛ ቆሮንቶስ 10፥12

5. ከተቃራኒ ጾታ ጋር ስላለህ ግንኙነት ማጭበርበሪያዎችን አታስተናግድ ያ ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃትና ብልሃት ታግዳለህ።

ከዚህም በኋላ በሶሬቅ ሸለቆ የነበረች ደሊላ የተባለች አንዲት ሴትን ወደደ። የፍልስጥኤማውያንም መኳንንት ወደ እርስዋ ወጥተው፦ እርሱን ሸንግለሽ በእርሱ ያለ ታላቅ ኃይል በምን እንደ ሆነ፥ እኛስ እርሱን ለማዋረድ እናስረው ዘንድ የምናሸንፈው በምን እንደ ሆነ እወቂ፤ እኛም እያንዳንዳችን ሺህ አንድ መቶ ብር ሺህ አንድ መቶ ብር እንሰጥሻለን አሉአት።

ደሊላም ሶምሶንን፦ ታላቅ ኃይልህ በምን እንደ ሆነ፥ እንድትዋረድስ የምትታሰርበት ምን እንደ ሆነ፥ እባክህ፥ ንገረኝ አለችው። ሶምሶንም፦ በሰባት ባልደረቀ በእርጥብ ጠፍር ቢያስሩኝ፥ እደክማለሁ እንደ ሌላም ሰው እሆናለሁ አላት። የፍልስጥኤማውያንም መኳንንት ሰባት ያልደረቀ እርጥብ ጠፍር አመጡላት፥ በእርሱም አሰረችው።

በጓዳዋም ውስጥ ሰዎች ተደብቀው ነበር። እርስዋም፦ ሶምሶን ሆይ፥ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ አለችው። እርሱም የተልባ እግር ፈትል እሳት በሸተተው ጊዜ እንዲበጠስ ጠፍሩን በጣጠሰው ኃይሉም በምን እንደ ሆነ አልታወቀም።ደሊላም ሶምሶንን፦ እነሆ፥ አታለልኸኝ፥ የነገርኸኝም ሀሰት ነው፤ አሁንም የምትታሰርበት ምን እንደ ሆነ፥ እባክህ፥ ንገረኝ አለችው።

መሳፍንት 16፥4-10

እርስዋም፦ አንተ፦ እወድድሻለሁ እንዴት ትለኛለህ፥ ልብህ ከእኔ ጋር አይደለም? ስታታልለኝ ይህ ሦስተኛ ጊዜህ ነው፥ ታላቅ ኃይልህም በምን እንደ ሆነ አልነገርኸኝም አለችው። ዕለት ዕለትም በቃልዋ

ነዘነዘችው አስቸገረችውም፥ ነፍሱም እስከ ሞት ድረስ ተጨነቀች። እርሱም፦ ከእናቴ ማኅፀን ጀምሬ ለእግዚአብሔር የተለየሁ ነኝና በራሴ ላይ ምላጭ አልደረሰም፤ የራሴንም ጠጕር ብላጭ ኃይሌ ከእኔ ይሄዳል፥ እደክማለሁም፥ እንደ ሌላም ሰው እሆናለሁ ብሎ የልቡን ሁሉ ገለጠላት። ደሊላም የልቡን ሁሉ እንደ ገለጠላት ባየች ጊዜ፦ የልቡን ሁሉ ገልጦልኛልና ይህን ጊዜ ደግሞ ኑ ብላ ላከችና የፍልስጥኤማውያንን መኳንንት ጠራች። የፍልስጥኤማውያን መኳንንትም ብሩን በእጃቸው ይዘው ወደ እርስዋ መጡ።

እርስዋም በጕልበትዋ ላይ አስተኛችው፤ አንድ ሰውም ጠራች፥ እርሱም ሰባቱን የራሱን ጕንጕን ላጨው። ልታዋርደውም ጀመረች፥ ኃይሉም ከእርሱ ሄደ። እርስዋም፦ ሶምሶን ሆይ፥ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ አለችው። ከእንቅልፉም ነቅቶ፦ እወጣለሁ እንደ ወትሮውም ጊዜ አደርጋለሁ አለ። ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ እንደ ተለየው አላወቀም። ፍልስጥኤማውያንም ይዘው ዓይኖቹን አወጡት፤ ወደ ጋዛም አምጥተው በናስ ሰንሰለት አሰሩት፤ በግዞትም ሆኖ እህል ይፈጭ ነበር።

መሳፍንት 16፥15-21

6. ያንተ ህይወትህ እንዴት ለትጉህ ስራ እና ለጠንካራ ስራ አስፈላጊ ነው ብለህ ማጭበርበሪያ ሃሳቦችን አታስተናግድ ያ ሲሆን የዲያሎስንት ጥቃት ታግዳለዋህ::

አንተ ታካች፥ እስከ መቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ? ጥቂት ትተኛለህ፥ ጥቂት ታንቀላፋለህ፥ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ፤ እንግዲህ ድህነትህ እንደ ወንበዴ፥ ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል።

ምሳሌ 6፥9-11 (አመት)

# የጽድቅ ጥሩር የዲያብሎስን ተንኮል ያግደዋል

1. ዝሙት አታድርግ እንዲያ ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃት ትከላከላለህ:: ዝሙት መፈጸም ጥሩርህን በመስበር አጋንንቶች ወደ አንተ እንዲገቡ ክፍተት ይፈጥራል::

ኃጢአትንና ጽድቅ ያልሆነውን በለማድረግ የዲያብሎስን ተንኮል ታግደዋለህ፡፡

ከዚህ በኋላ ታላቅ ስልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች። በብርቱም ድምፅ፦ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤ አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቍጣ ወይን ጠጅ የተነሳ ወድቀዋልና፥ የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ የምድርም ነጋዴዎች ከቅምጥልነትዋ ኃይል የተነሳ ባለ ጠጋዎች ሆኑ ብሎ ጮኸ።

ራእይ 18፥1-3

2. ጣዖትን አታምልክ እንዲያ ስታደርግ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ፡፡ የጣዖት አምልኮ ጥሩርን ሰብሮ የጥፋት አጋንንቶች ወደ አንተ እንዲገቡ በር ይከፍታል፡፡

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፦ የሰው ልጅ ሆይ፥ እነዚህ ሰዎች ጣዖቶቻቸውን በልባቸው አኑረዋል የበደላቸውንም መቅሠፍት በፊታቸው አቁመዋል፤ እኔስ ከእነርሱ ልጠየቅን? ስለዚህ፦ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሁሉም በጣዖቶቻቸው ከእኔ ተለይተዋልና የእስራኤልን ቤት በልባቸው እይዝ ዘንድ ከእስራኤል ቤት ጣዖቶቹን በልቡ የሚያኖር፥ የበደሉንም መቅሠፍት በፊቱ የሚያቆም ሰው ሁሉ ወደ ነቢዩ በመጣ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር እንደ ጣዖታቱ ብዛት እመልስለታለሁ ብለህ ንገራቸው።

ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፦ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ንስሐ ግቡ ከጣዖቶቻችሁም ተመለሱ፥ ፊታችሁንም ከርኵሰታችሁ ሁሉ መልሱ።

ከእስራኤልም ቤት፥ በእስራኤልም ዘንድ ከሚቀመጡ መጻተኞች የሚሆን፥ ከእኔ ተለይቶ ጣዖቶቹን በልቡ የሚያኖር፥ የበደሉንም መቅሠፍት በፊቱ የሚያቆም ሰው ሁሉ፥ ስለ እኔ ይጠይቅ ዘንድ ወደ ነቢዩ በመጣ ጊዜ፥ እኔ እግዚአብሔር በራሴ እመልስለታለሁ፤

ፊቴንም በዚያ ሰው ላይ አደርጋለሁ ምልክትና ምሳሌም አደርገዋለሁ ከሕዝቤም መካከል አጠፋዋለሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። ነቢዩም ቢታለል ቃልንም ቢናገር፥ ያንን ነቢይ ያታለልሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ እጄንም በእርሱ ላይ እዘረጋለሁ ከሕዝቤም ከእስራኤል መካከል አጠፋዋለሁ።

ሕዝቅኤል 14፥2-9

3. በጥንቆላና አስማት አትሳተፍ እንዲያ ሲሆን የዲብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: ጥንቆላ ጥሩርን በመስበር የጥፋት አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ በር ይከፍታል::

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፦ አንተም የሰው ልጅ ሆይ፥ የባቢሎን ንጉሥ ሰይፍ ይመጣ ዘንድ ሁለት መንገዶችን አድርግ፤ ሁለቱም ከአንዲት ምድር ይውጡ፤ ምልክትም አድርግ፥ በከተማይቱ መንገድ ራስ ላይ አድርገው። ሰይፍ ወደ አሞን ልጆች አገር ወደ ረባት ወደ ይሁዳም ወደ ተመሸገች ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣ ዘንድ መንገድን አድርግ።

የባቢሎን ንጉሥ ምዋርቱን ያምዋርት ዘንድ በመንታ መንገድ ላይ በሁለቱ መንገዶች ራስ ላይ ቆሞ ነበር፤ ፍላጾችን ወዘወዘ፥ ከተራፊምም ጠየቀ፥ ጉበትም ተመለከተ። የቅጥሩን ማፍረሻ ያደርግ ዘንድ፥ አፍንም በጩኸት ይከፍት ዘንድ፥ በውካታም ድምፅን ከፍ ያደርግ ዘንድ፥ የቅጥሩን ማፍረሻ በበሮች ላይ ያደርግ ዘንድ፥ አፈርን ይደለድል ዘንድ፥ ምሽግም ይሠራ ዘንድ የኢየሩሳሌም ዕጣ በቀኝ እጁ ውስጥ ነበረ። መሐላውንም በማሉ በዓይናቸው ዘንድ የሐሰት ምዋርት ይመስላል፥ ነገር ግን እነርሱ ይያዙ ዘንድ እርሱ ኃጢአትን ያሳስባል።

ሕዝቅኤል 21፥18-23

4. ግብረሰደሞዊነትን አትፈጽም እንዲሁም ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃት ግደዋለህ:: ግብረሰደሞዋዊነት ጥሩርን በመስበር አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ በር ይከፍታል::

ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ

የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።

ሮሜ 1፡24-27

5. ትዕቢተኛ አትሁን እንዲያ ስሆን የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: የትዕቢት ኃጢአት ጥሩርን በመስበር አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ክፍተት ይፈጥራል::

ትዕቢት ጥፋትን፥ ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል።

ምሳሌ 16፡18

6. ይቅር የማታደርግ ሰው ሆነህ አትኑር ያን ስታደርግ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: ይቅር ያለማለት ኃጢአት ጥሩርን በመስበር አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ክፍተት ይፈጥራል::

ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቈጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች። መቈጣጠርም በጀመረ ጊዜ፥ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። የሚከፍለውም ቢያጣ፥ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ።

ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና፦ ጌታ ሆይ፥ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ አለው። የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፥ ዕዳውንም ተወለት። ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘና፦ ዕዳህን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው። ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ፦ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው።

እርሱም አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው። ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ። ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ፦ አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤ እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው። ጌታውም ተቈጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚሣቀዩት አሳልፎ ሰጠው። ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።

ማቴዎስ 18፥23-35

7. ክፉ ሰው አትሁን እንዲያ ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: የክፋት ኃጢአት ጥሩርን በመስበር አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ክፍተት ይፈጥራል::

እጅግ ክፉ አትሁን፥ አልከኛም አትሁን፥ ጊዜህ ሳይደርስ እንዳትሞት።

መክብብ 7፥17

8. ስለራስህ ጽደቅ እና ተከበርኩ አልተከበርኩ ስለሚለው አትጨነቅ ያ ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃትና ተንኮል ታግደዋለህ:: የጽድቅ ያልሆነ ፍርድ አትስጥ:: በጽድቅ ላይ ኃጢአት መስራት፣ የጽድቅ ያልሆነ ፍርድ፣ ራስን ማክበር፣ ራስን ማወደስ እና ከልክ በላይ ራስን ከፍ ማድረግ ጥሩርን በመስበር አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ክፍተት ይፈጥራል::

እጅግ ጻድቅ አትሁን፥ እጅግ ጠቢብም አትሁን፥ እንዳትጠፋ።

መክብብ 7፥16

ምሕረትና እውነት ከአንተ አይራቁ፤ በአንገትህ እሰራቸው፤ በልብህ ጽላት ጻፋቸው። በእግዚአብሔርና በሰው ፊትም ሞገስንና መልካም ዝናን ታገኛለህ።

ምሳሌ 3፥3-4

9. ዓመጸኛ አትሁን እንዲያ ሲሆን የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: የአለመታዘዝ ኃጢአት ጥሩሩን በመስበር አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ክፍተት ይፈጥራል::

ነገር ግን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰማ፥ ዛሬም ያዘዝሁህን ሥርዓቱንና ትእዛዙን ሁሉ ባትጠብቅ ባታደርግም፥ እነዚህ መርገሞች ሁሉ ይመጡብሃል ያገኙህማል። በከተማ ርጉም ትሆናለህ፥ በእርሻም ርጉም ትሆናለህ። እንቅብህና ቡሃቃህ ርጉም ይሆናል።

የሆድህ ፍሬ፥ የምድርህም ፍሬ፥ የላምህም ርቢ፥ የበግህም ርቢ ርጉም ይሆናል። አንተ በመግባትህ ርጉም ትሆናለህ፥ በመውጣትህም ርጉም ትሆናለህ። እኔን ስለ ተውኸኝ፥ ስለ ሥራህ ክፋት፥ እስክትጠፋ ፈጥነህም እስክታልቅ ድረስ በምትሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር መርገምን፥ ሽሽትን፥ ተግሣጽን ይሰድድብሃል።

ዘዳግም 28፥15-20

# የወንጌል ስብከት የዲያብሎስን ሽንገላ ያግደዋል

1. ወንጌል መስበክን አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት እና ማታላያዎችን ታግደዋለህ:: ወንጌልን አለመስበክና በወንጌል አለመዘጋጀት በጦር እቃችን ላይ ክፍተት በመፍጠር የእጦትና የፍላጎት አጋንንቶች እንዲወሩህ ያደርጋል::

ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።

ማቴዎስ 6፥33

2. ወንጌል መስበክን አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: ወንጌልን አለመስበክና በወንጌል አለመዘጋጀት በጦር እቃህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የግድየለሽነት አጋንንቶች ወደ ህይወትህ ያስገባል::

**በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ *ሥራህን* አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር። እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።**

**ራእይ 3፡15-16**

3. ***ወንጌል መስበክን አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: ወንጌልን አለመስበክና በወንጌል አለመዘጋጀት በጦር እቃ ላይ ክፍተት በመፍጠር የዋይታ እና የችግር አጋንንቶችን ወደ ህይወትህ ያስገባል::***

**ወንጌልን ብሰብክ እንኳ የምመካበት የለኝም፤ ግድ ደርሶብኛ ነውና፤ ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ!**

**1ኛ ቆሮንቶስ 9፡16**

4. ***ወንጌል መስበክን አለማቆም የዲያብሎስን ጥቃት እና ማታላያዎችን ታግደዋለህ:: ወንጌልን አለመስበክና በወንጌል አለመዘጋጀት በጦር እቃው ላይ ክፍተት በመፍጠር የቤተክርስቲያን እድገትን በሚከለክሉ አጋንንቶች እንድትወረር ያደርጋል::*** *ቀጥሎ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ወንጌልን መስበክ ምን ያህል ለቤተክርስቲያን እድገት በር እንደሚከፍት ያሳያል:: ብዙ ቤተክርስቲያኖች እየታገሉ ያሉት ለበር ላይ ከተቀመጡት የቤተክስቲያንን ከሚያመነምኑ አጋንንቶች ጋር ነው:: ቤተክርሰቲያኖቻቸው በየቀኑ እያነሱ እና ትንሽ እየሆኑ ይሄዳሉ:: ሰይጣን ብዙ ሰዎችን ወስዶባቸው በትንሽ ሰዎች ለምን እንዳስቀራቸው አይጋባቸውም::*

**በብዙ ሌላ ቃልም መሰከረና፦ ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ ብሎ መከራቸው። ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤ በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።**

**የሐዋርያት *ሥራ* 2፡40-42**

ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፥ የወንዶችም ቍጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ።

የሐዋርያት ሥራ 4፥4

ሕዝቡ ግን ያከብሩአቸው ነበር፤ የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ **ይጨመሩለት** ነበር፤ ወንዶችና ሴቶችም ብዙ ነበሩ።

የሐዋርያት ሥራ 5፥14

ጉባኤውም ከተፈታ በኋላ ከአይሁድና ወደ ይሁዲነት ገብተው ከሚያመልኩ ብዙዎች ጳውሎስንና በርናባስን ተከተሉአቸው፥ እነርሱም ሲነግሩአቸው በእግዚአብሔር ጸጋ ጸንተው እንዲኖሩ አስረዱአቸው።

በሁለተኛውም ሰንበት ከጥቂቶቹ በቀር የከተማው ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰሙ ዘንድ ተሰበሰቡ።

የሐዋርያት ሥራ 13፥43-44

# የእምነት ጋሻ የዲያብሎስን ማታለያዎች ያግደዋል

1. ማመንህን አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ። እምነት ማጣት በጦር እቃህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የድህነት አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል። እምነትን መለማመድ ብልጽግናን በማስለቀቅ ድህነትን ያግዳል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የብልጽግና ቃሎችን ማመን አስፈላጊ ነው።

ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።

3ኛ ዮሐንስ 2

2. ማመንህን አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ። እምነት ማጣት በጦር እቃህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የችግርና ስቃይ አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ

ያደርጋል:: እምነትን መለማመድ ብልጽግናን እና ተድላን በህይወትህ ይለቅቃል::

**ቢሰሙ ቢያገለግሉትም፥ ዕድሜአቸውን በልማት፥**

ኢዮብ 36፥11

3. ማመንህን አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: እምነት ማጣት በጦር እቃህ ላይ ክፍተት በመፍጠር ህመም አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል:: እምነትን መለማመድ በህይወትህ ውስጥ ጤንነትን በመልቀቅ እና ህመምን ያግዳል::

**ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።**

3ኛ ዮሐንስ 2

4. ማመንህን አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: እምነት ማጣት በጦር እቃህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የችግር አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል:: እምነትን መለማመድ ለምኞትህ መሟለት በር ይከፍታል::

**ስለዚህ እላችኋለሁ፥ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል።**

ማርቆስ 11፥24

5. ማመንህን አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህ:: እምነት ማጣት በጦር እቃህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የትላልቅ ችግር እና የተራራ አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡና እንዲቆዩ ያደርጋል:: እምነትን መለማመድ ተራራችን የሚያንቀሳቅስና የማይገፉ ችግሮችን የሚያመጡ አጋንቶችን ያግዳል::

**እውነት እላችኋለሁ፥ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን ተራራ፦ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢል ይሆንለታል።**

**ማርቆስ 11፥23**

6. ***ማመንህን አታቁም የዲያብሎስን ጥቃት ታግዳለህና::*** *እምነት ማጣት በጦር እቃህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የሚያሰጥሙህ አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል:: እምነትን መለማመድ ምኞቶችን በመልቀቅ ፍጹም ጥፋቶችን ከህይወትህ ያግዳል:: ሰይጣን ሊያጠፋህ ነው የሚወደው:: አጥፊ የሚያወራው ስለጥፋት ነው::*

**እምነትና በጎ ሕሊና ይኑርህ፥ አንዳንዶች ሕሊናን ጥለው፥ መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ፥ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና፤**

**1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥19**

# የመዳን ራስ ቁር የዲያብሎስን ጥቃት ያግደዋል

***የድነትን መሰረት ገሸሽ ማድረግ በእቃ ጦርህ ላይ ክፍተት በመፍጠር አጋንንቶችን ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል::*** *አጋንንቶን በመዳን ራስ ቁር ማገድ ትችላለህ:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለመዳን ባለመስበክ እና የመዳንን ጽንሰ ሀሳብ በማሳነስ ለአጋንንቶች በር ትከፍታለህ:: የመዳን መሰረቶች ላይ ማተኮር ለክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ኃይል የሚሰጥ እና እርኩሳን መናፍስቶች ወደ ህይወታችን እንዳይገቡ የሚያግድ ነው:: ድነት የክርስትና ህይወታችን መሰረት ነው::*

**አንተ የሠራኸውን እነሆ እነርሱ አፍርሰዋልና፤ ጻድቅ ግን ምን አደረገ?**

**መዝሙር 11፥3**

1. ስለድነት መናገር አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህና። የድነን መሰረት ገሸሽ ማድረግ በእቃ ጦርህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የቁሳዊያን እና የምድራዊ አዕምሮ አጋንንቶች ወደ ህይወታችን እንዲገቡ ያደርጋል። እምነትህን በተግባር ላይ ማዋል ፍላጎትህ እንዲጨምር ያደርጋል እንዲሁም አሉታዊ ነገሮች ወደ ህይወትህ እንዳይገቡ ያግዳል።

በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም። ሞታችኋልና፥ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና፤

ቆላስይስ 3፥2 - 3

2. ስለድነት መናገር አታቁም፣ የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህና። የድነትን መሰረት ገሸሽ ማድረግ በእቃ ጦርህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የከንቱ ንግግር አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል። ድነትህ ላይ ማተኮር እንደ ክርስቲያን ኃይል የሚሰጥህና እርኩሳን መናፍስቶች ወደ ህይወትህ እንዳይገቡ ያግዳል።

የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው፤ ከእነዚህም አንዳንዶች ስተው፥ የሚሉትን ወይም ስለ እነርሱ አስረግጠው የሚናገሩትን ሳያስተውሉ፥ የሕግ አስተማሪዎች ሊሆኑ እየወደዱ፥ ወደ ከንቱ ንግግር ፈቀቅ ብለዋል።

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥5 - 7

3. ስለመዳንህ መናገር አታቁም የዲያብሎስን ጥቃት ታግዳለህና። የድነትን መሰረት ገሸሽ ማድረግ በእቃ ጦርህ ላይ ክፍተት በመፍጠር የአለማመን እና የአለመታመን አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል። ድነትህ ላይ ማተኮር እንደ ክርስቲያን ኃይል የሚሰጥህና እርኩሳን መናፍስቶች ወደ ህይወትህ እንዳይገቡ ያግዳል።

... የብሩክ እግዚአብሔርንም ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ እንደ ተሰጠኝ ወንጌል የሆነውን ደኅና ትምህርት ለሚቃወም ለሌላ ነገር ሁሉ ሕግ እንደ ተሰራ እንጂ ለጻድቅ እንዳልተሰራ ሲያውቅ ነው። ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለ ቈጠረኝ፥ ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ፤

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡11-12

# የመንፈስ ሰይፍ የዲያብሎስን ጥቃት ያግደዋል

1. የእግዚአብሔርን ቃል የሁሉም ነገር መሰረት አድርገህ መጠቀምህን አታቁም፣ የዲያብሎስንም ጥቃት ታግደዋለህና:: የመንፈስን ሰይፍ አለመጠቀም የጦር እቃህ ላይ ክፍተት ይፈጥርና *አታላይ ስጋዊ ፈታኝ አጋንንቶች* ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል:: አጋንንቶችን በመንፈስ ሰይፍ ማገድ ትችላለህ:: የእግዚአብሔርን ቃል ገሸሽ በማድረግ ለአጋንንቶች በርን ትከፍታለህ::

ዲያብሎስም፦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ ይህን ድንጋይ፦ እንጀራ ሁን ብለህ እዘዝ አለው። ኢየሱስም፦ ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል ብሎ መለሰለት።

ሉቃስ 4፡3-4

2. የእግዚአብሔርን ቃል የሁሉም ነገር መሰረት አድርገህ መጠቀምህን አታቁም፣ የዲያብሎስንም ጥቃት ታግደዋለህና:: የመንፈስን ሰይፍ አለመጠቀም የጦር እቃህ ላይ ክፍተት ይፈጥርና *አታላይና ገዳይ የአቋራጭ መንገድ* አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል::

ዲያብሎስም ረጅም ወደ ሆነ ተራራ አውጥቶ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየው። ዲያብሎስም፦ ይህ ሥልጣን ሁሉ ክብራቸውም ለእኔ ተሰጥቶአል ለምወደውም ለማንም እሰጠዋለሁና ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ ስለዚህ አንተ በእኔ ፊት ብትሰግድ፥ ሁሉ

ከአንተ ይሆናል አለው። ኢየሱስም መልሶ፦ ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል አለው።

ሉቃስ 4፥5 - 8

3. *የእግዚአብሔርን ቃል የሁሉም ነገር መሰረት አድርገህ መጠቀምህን አታቁም፣ የዲያብሎስንም ጥቃት ታግደዋለህና:: የመንፈስን ሰይፍን አለመጠቀም የጦር እቃህ ላይ ክፍተት ይፈጥርና አታላይ ስልጣን ያለአግባብ የመጠቀም አጋንንቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል::*

ወደ ኢየሩሳሌም ደግሞ ወሰደው፤ በመቅደስም ጫፍ ላይ አቁሞ፦ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል፥ እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፥ ከዚህ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው። ኢየሱስም መልሶ፦ ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎአል አለው።

ሉቃስ 4፥9 - 12

## *"ሁሌም መጸለይ" የዲያብሎስን ጥቃት ያግደዋል*

1 *"ሁሌም መጸለይ"ን አታቁም የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህና:: ሁሌም አለመጸለይ በጦር እቃህ ላይ ክፍተት ይፈጥርና በሰማያዊ ስፍራ ያሉት የክፋት መናፍስቶች በአንተ ላይ እንዲሰሩ እና ተልዕኮህን እንዲቃወሙ ያደርጋል:: አጋንንቶችን በጸሎት ማገድ ትችላለህ:: ባለመጸለይ ለአጋንንቶች በርን ትከፍታለህ::*

እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ፥ እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬአለሁና የምነግርህን ቃል አስተውል፥ ቀጥ ብለህም ቁም አለኝ። ይህንም ቃል ባለኝ ጊዜ እየተንቀጠቀጥሁ ቆምሁ። እርሱም እንዲህ አለኝ፦ ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት

**ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል፤** እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ።

**የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤** እነሆም፥ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት። ራእዩም ገና ለብዙ ዘመን ነውና በኋለኛው ዘመን ለሕዝብህ የሚሆነውን አስታውቅህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ። ይህንም ቃል በተናገረኝ ጊዜ ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርሁ፥ ዲዳም ሆንሁ። እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከንፈሬን ዳሰሰኝ፤ የዚያን ጊዜም አፌን ከፍቼ ተናገርሁ በፊቴም ቆሞ የነበረውን፦ ጌታዬ ሆይ፥ ከራእዩ የተነሣ ሕመሜ መጣብኝ፥ ኃይልም አጣሁ። ይህ የጌታዬ ባሪያ ከዚህ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ እንዴት ይችላል? አሁንም ኃይል አጣሁ፥ እስትንፋስም አልቀረልኝም አልሁት። ደግሞ ሰው የሚመስል ዳሰሰኝ፥ አበረታኝም። እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ሆይ፥ አትፍራ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን፤ በርታ፥ ጽና አለኝ። በተናገረኝም ጊዜ በረታሁና፦ አበርትተኸኛልና ጌታዬ ይናገር አልሁ።

ዳንኤል 10፥11-19

2 "ሁሌም መጸለይ"ን አታቋም የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህና:: ሁሌም አለመጸለይ በጦር እቃህ ላይ ክፍተት ይፈጥርና በሰማያዊ ስፍራ ያሉት የክፋት መናፍስቶች መረዳትህን እንዲሰርቁ ያደርጋል::

እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ፥ እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬአለሁና የምነግርህን ቃል አስተውል፥ ቀጥ ብለህም ቁም አለኝ። ይህንም ቃል ባለኝ ጊዜ እየተንቀጠቀጥሁ ቆምሁ። እርሱም እንዲህ አለኝ፦ ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት **ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል፤ እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ።**

የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ እነሆም፥ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት።

ራእዩም ገና ለብዙ ዘመን ነውና በኋለኛው ዘመን ለሕዝብህ **የሚሆነውን አስታውቅህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ።**

ይህንም ቃል በተናገረኝ ጊዜ ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርሁ፥ ዲዳም ሆንሁ። እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከንፈሬን ዳሰሰኝ፤ የዚያን ጊዜም አፌን ከፍቼ ተናገርሁ በፊቴም ቆሞ የነበረውን፦ ጌታዬ ሆይ፥ ከራእዩ የተነሣ ሕመሜ መጣብኝ፥ ኃይልም አጣሁ።

ይህ የጌታዬ ባሪያ ከዚህ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ እንዴት ይችላል? አሁንም ኃይል አጣሁ፥ እስትንፋስም አልቀረልኝም አልሁት።

ደግሞ ሰው የሚመስል ዳሰሰኝ፥ አበረታኝም። እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ሆይ፥ አትፍራ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን፤ በርታ፥ ጽና አለኝ። በተናገረኝም ጊዜ በረታሁና፦ አበርትተኸኛልና ጌታዬ ይናገር አልሁ። እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ፥ እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬአለሁና የምነግርህን ቃል አስተውል፥ ቀጥ ብለህም ቁም አለኝ። ይህንም ቃል ባለኝ ጊዜ እየተንቀጠቀጥሁ ቆምሁ።

እርሱም እንዲህ አለኝ፦ ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል፤ እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ። የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ እነሆም፥ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት። ራእዩም ገና ለብዙ ዘመን ነውና በኋለኛው ዘመን ለሕዝብህ የሚሆነውን አስታውቅህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ። ይህንም ቃል በተናገረኝ ጊዜ ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርሁ፥ ዲዳም ሆንሁ። እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከንፈሬን ዳሰሰኝ፤ የዚያን ጊዜም አፌን ከፍቼ ተናገርሁ በፊቴም ቆሞ የነበረውን፦ ጌታዬ ሆይ፥ ከራእዩ የተነሣ ሕመሜ መጣብኝ፥ ኃይልም አጣሁ። ይህ የጌታዬ ባሪያ ከዚህ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ እንዴት ይችላል? አሁንም ኃይል አጣሁ፥ እስትንፋስም አልቀረልኝም አልሁት። ደግሞ ሰው የሚመስል ዳሰሰኝ፥ አበረታኝም። እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ሆይ፥ አትፍራ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን፤ በርታ፥ ጽና አለኝ። በተናገረኝም ጊዜ በረታሁና፦ አበርትተኸኛልና ጌታዬ ይናገር አልሁ።

ዳንኤል 10፥11-19

3. “ሁሌም መጸለይ”ን አታቋም የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህና:: ሁሌም አለመጸለይ በጦር እቃህ ላይ

ክፍተት ይፈጥርና በሰማያዊ ስፍራ ያሉት የክፋት መናፍስቶች በአገልግሎት ላይ ያለህን ብርታት እንዲሰርቁ ያደርጋል።

እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ፥ እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬአለሁና የምነግርህን ቃል አስተውል፥ ቀጥ ብለህም ቁም አለኝ። ይህንም ቃል ባለኝ ጊዜ እየተንቀጠቀጥሁ ቆምሁ። እርሱም እንዲህ አለኝ፦ ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል፤ እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ።

የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ እነሆም፥ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት። ራእዩም ገና ለብዙ ዘመን ነውና በኋለኛው ዘመን ለሕዝብህ የሚሆነውን አስታውቅህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ። ይህንም ቃል በተናገረኝ ጊዜ ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርሁ፥ ዲዳም ሆንሁ። እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከንፈሬን ዳሰሰኝ፤ የዚያን ጊዜም አፌን ከፍቼ ተናገርሁ በፊቴም ቆሞ የነበረውን፦ ጌታዬ ሆይ፥ ከራእዩ የተነሣ ሕመሜ መጣብኝ፥ ኃይልም አጣሁ። ይህ የጌታዬ ባሪያ ከዚህ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ እንዴት ይችላል? አሁንም ኃይል አጣሁ፥ እስትንፋስም አልቀረልኝም አልሁት።

ደግሞ ሰው የሚመስል ዳሰሰኝ፥ አበረታኝም። እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ሆይ፥ አትፍራ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን፤ በርታ፥ ጽና አለኝ። በተናገረኝም ጊዜ በረታሁና፦ አበርትተኸኛልና ጌታዬ ይናገር አልሁ።

ዳንኤል 10፥11-19

4. “ሁሌም መጸለይ”ን አታቁም የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህና። ሁሌም አለመጸለይ በጦር እቃህ ላይ ክፍተት ይፈጥርና በሰማያዊ ስፍራ ያሉት የክፋት መናፍስቶች በአገልግሎት ውስጥ ያለውን ሰላምህን እንዲሰርቁ ያደርጋል።

እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ፥ እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬአለሁና የምነግርህን ቃል አስተውል፥ ቀጥ ብለህም ቁም አለኝ። ይህንም ቃል ባለኝ ጊዜ እየተንቀጠቀጥሁ ቆምሁ። እርሱም እንዲህ አለኝ፦ ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአልና፤ እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ። የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ እነሆም፥ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት።

ራእዩም ገና ለብዙ ዘመን ነውና በኋለኛው ዘመን ለሕዝብህ የሚሆነውን አስታውቅህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ። ይህንም ቃል በተናገረኝ ጊዜ ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርሁ፥ ዲዳም ሆንሁ።

እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከንፈሬን ዳሰሰኝ፤ የዚያን ጊዜም አፌን ከፍቼ ተናገርሁ በፊቴም ቆሞ የነበረውን፦ ጌታዬ ሆይ፥ ከራእዩ የተነሣ ሕመሜ መጣብኝ፥ ኃይልም አጣሁ። ይህ የጌታዬ ባሪያ ከዚህ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ እንዴት ይችላል? አሁንም ኃይል አጣሁ፥ እስትንፋስም አልቀረልኝም አልሁት። ደግሞ ሰው የሚመስል ዳሰሰኝ፥ አበረታኝም። እርሱም፦ እጅግ የተወደድህ ሰው ሆይ፥ አትፍራ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን፤ በርታ፥ ጽና አለኝ። በተናገረኝም ጊዜ በረታሁና፦ አበርትተኸኛልና ጌታዬ ይናገር አልሁ።

ዳንኤል 10፡11-19

5. “ሁሌም መጸለይ”ን አታቁም የዲያብሎስን ጥቃት ታግደዋለህና:: ሁሌም አለመጸለይ በጦር እቃህ ላይ ክፍተት ይፈጥርና የግራ መጋባት፣ የሰላም ማጣት፣ የአምልኮ ማጣት እና የአለመታመን እርኩሳን መናፍስቶች ወደ ህይወትህ እንዲገቡ ያደርጋል::

እንግዲህ፥ ልጄ ሆይ፥ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።

1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-2

# ምዕራፍ 26

# የዲያብሎስ መኖሪያ ከመሆን እንዴት እንጠበቅ

**በብርቱም ድምፅ፦ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኵሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤**

**ራእይ 18፡2**

የእርኩሳን መናፍስቶ እና የዲቃላ ፍጡራን ዋነኛ ዓላማ አንተን መያዝ ነው። አንዴ አንተ ውስጥ ከገቡ፣ ወድቋል ትባላለህ። ባቢሎን የወደቀች የተባለችው የእነዚህ እርኩሳን መናፍስቶች መኖሪያ፣ መጠጊያና መያዣ ስለሆነች ነበር። አንዴ የእነዚህ እርኩሳን መናፍስቶ መጠጊያ፣ መያዣና መኖሪያ ከሆንክ የወደቅክ ትበላለህ። እንደ ክርስቲያን ያንተ ትግል እነዚህ ፍጡራን ወደ አንተ እንዳይገቡ መግቢያ በሮችህን መጠበቅ ነው።

እርኩሳን መናፍስቶች ፈጽመው የማይወዱአቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህ ነገሮች አንዱን ባደርግክ ቁጥር እርኩሳን መናፍስቶችን ታሸብራለህ፣ ታስፈራራለህ፣ ግራ ታጋባቸውና ታስወጣቸዋለህ። የእነዚህን እያንዳንዱን ስራ አስተውል። ከተለማምድካቸው፣ ሊያጠፉህ የተላኩብህን እርኩስ ፍጥረቶችን በማስፈራራት ትበታትናቸዋለህ። እነዚህን ነገሮች የምታደርጋቸው ከሆነ እርኩሳን መናፍስቶች ከአንተ ጋር መሆን አይፈልጉም። እነዚህን ነገር ካደርግካቸው እርኩሳን ማናፍስቶ አንተን ሰለማጥቃት የሚያስቡት ሁለቴ ነው።

## 1. በመልካም ነገር በመሞላት የዲያብሎስ መኖሪያ ከመሆን ራስህን ጠብቅ።

እርኩሳን መናፍስቶች አንተን የእነርሱ ቋሚ ቤት እና አድራሻ አድርገው መግለጽ ይመኛሉ። ባቢሎን ሙሉ በሙሉ የጠፋችው የእርኩሳን ማፍስቶች መጠጊያ ስትሆን ነው። እንደ ራእይ 18፡2 መውደቅ ማለት የእርኩሳን መናፍስቶች መኖሪያ መሆን ማለት ነው።

የአንተ ኃላፊነት ህይወትህን መልካም በሆነው ቃል፣ መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ኃይል መሙላት ነው። ተፍጥሮ ወና የሆነ ነገርን ይጠላል። እርኩሳን መናፍስቶች ተመልሰው መጥተው ቤቱ ባዶ መሆኑን ባዩ ጊዜ ወዲያው ተጣድፈው ገቡበት። ለዚህም ነው ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እንድትሰማው የማይፈልገው። ስለዚህ ሰይጣን መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች የክርስቲያን መጽሐፎችን እንድታነብ አይፈልግም። ለዚህ ነው ሰይጣን በልሳን እንድትጸልይና በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞላ የማይፈልገው። ሊወርርህና ሊሞሃህ ፈልጎ ሰይጣን ባዶ አዕምሮና ባዶ ቤት እንዲኖርህ ይፈልጋል።

በዶ ቤት ለእርኩሳን መናፍስቶችና እርኩሳን ፍጥረቶች ተመራጭ ቦታ ነው። ብዙ ሰዎች በውስጣቸው የተጠሉ እና እርኩስ ወፎችን ይዘው ይዞራሉ። የባቢሎን ውድቀት የመጣው እርኩሳን መናፍስቶችና የተጠሉ ወፎች ስኬታማ በሆነ ሁኔታ ሲወሯት ነው።

መውደቅ ትፈልጋለህ? በእርኩን መናፍስቶች መያዝ ትፈልጋለህ? አትፈልግም! መቼም በአጋንንቶች አትያዝም! መቼም ብሆን የተያዘው የጨለማው መንግስት ግዛት ተብለህ አትጠራም!

ለምን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ እንደሚፈልግ እንደሚገባህ እርግጠኛ ነኝ።

**ሙሴም የእስራኤልን ልጆች አላቸው፦ እዩ፥ እግዚአብሔር ከይሁዳ ነገድ የሆነውን የሆር የልጅ ልጅ፥ የኡሪ ልጅ ባስልኤልን በስሙ ጠራው። በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም በማስተዋልም በእውቀትም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላበት፤**

**ዘጸአት** 35፥30-31

**ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።**

**የሐዋርያት ሥራ** 4፥31

ለምን እግዚአብሔር በቃሉ እንድንሞላ እንደሚፈልግ እንደሚገባህ እርግጠኛ ነኝ።

**የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤**

**ቆላስይስ** 3፥16

ለምን እግዚአብሔር በእግዚአብሔር እውቀት እንድንሞላ እንደሚፈልግ እንደሚገባህ እርግጠኛ ነኝ።።

**ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለችና።**

**ዕንባቆም** 2፥14

ለምን እግዚአብሔር በፍቃዱ እውቀት እንድንሞላ እንደሚፈልግ እንደሚገባህ እርግጠኛ ነኝ።።

**ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም፤**

**ቆላስይስ 1፥9**

ለምን እግዚአብሔር በእርሱ ፍጹም ሙላት እንድንሞላ እንደሚፈልግ እንደሚገባህ እርግጠኛ ነኝ::

**ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።**

**ኤፌሶን 3፥18-19**

የአጋንንቶች መኖሪያ እንዳትሆን የሚጠብቁህ ነገሮች እነዚህ ናቸው::

2. **አጋንንቶችን በሚያስወግድ የቃሉ ስብከት ራስህን በማጠር የአጋንንቶች መኖሪያ ከመሆን ራስህን ትጠብቃለህ:: አጋንንቶች የቃሉን ስብከት አይወዱም::**

**ወደ ቅፍርናሆምም ገቡ፤ ወዲያውም በሰንበት ወደ ምኩራብ ገብቶ አስተማረ። እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበር እንጂ እንደ ጻፎች አይደለምና በትምህርቱ ተገረሙ። በዚያን ጊዜም በምኩራባቸው ርኩስ መንፈስ ያለው ሰው ነበረ፤**

**እርሱም፦ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ፥ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ። ኢየሱስም፦ ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው። ርኩሱም መንፈስ አንፈራገጠውና በታላቅ ድምፅ ጮኾ ከእርሱ ወጣ።**

**ማርቆስ 1፥21-26**

በሰውየው ውስጥ የነበሩት ርስኩሳን መናፈስትም "ከአንተ ጋር ምን አለን?" ብለው እንደ ጮሁ ልበ በል:: ኢየሱስ

አልገሰጸውምም ውጣም አላለውም። ኢየሱስ ቃሉን ብቻ ያስተምር ነበር። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ውስጥ የተሳለ ሰይፍ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በወጣ ቁጥር ምሽጎችን የሚቆራረጥና የሚያፍርስ ሰይፍ በአየር ላይ ይለቀቃል። ለዚህ ነው የቃሉን ትምህርትና ስብከት የሚሰሙ ክስርስቲያኖች በጊዜ ሂደት ከአጋንንቶ ነጻ የሚሆኑት። አንድም ቀን ላይጸለይላቸው ይችላል። አጋንንት ተገስጾላቸውም ላይሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እርኩሳን መናፍስቶቹ ያለማቋረጥ በሚወረወርባቸው በሁለቱም በኩል ስለታም የሆነ ሰይፍ ለመውጣት ተገደው ነው። ሰይፎች ሁሌም በሚበሩበት አካባቢ መኖር ትፈልጋለህ? በእርግጠኝነት አትፈልገውም! የመንፈስ ሰይፍ በእርሱ ውስጥ ቀንም ሆነ ማታ እንዲበሩ በሚፈቅድ ሰው ውስጥ አጋንንቶች መኖር አይፈልጉም።

ለዚህ ነው ቃል የሚሰሙ ሰዎች በሚገርም ሁኔታ የሚለወጡት። እርኩሳን መናፍስቶ በእግዚአብሔር ቃል ከእነርሱ ይወጣሉ። የእግዚአብሔር ቃል የጨለመውን ህይወታችንን የሚያበራ ነው። በጨለማ ስፍራ የሚቀመጡት ርኩስ ፍጡራን ብርሃን እነርሱና ስራቸው ላይ እንዲበራባቸው አይፈልጉም።

የአርነት ጊዜና በመንፈስ የመቀጣጠል ጊዜ በሌላቸው ቤተክርስቲያኖች ላይ ልታላግጥ ትችላለህ። አጋንንት የማስወጣት ፕሮግራም በሌላቸው ቤተክስቲያኖች ላይ ልታላግጥ ትችላለህ። "እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች ኃይል የላቸውም ቃል ብቻ ነው የሚያስተምሩት ልትል ትችላለህ።" ያ ግን ያንተ ስህተት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር እርኩሳን መናፍስቶችን ለማስፈራራት፣ ለማሸበር፣ ለማሰቃየትና ለማስወጣት ኃይለኛ መሳሪያ ነው። የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል ቃሉን አስተምር። በየቀኑ ቃሉ በተነገረ ቁጥር በቤተክርስቲያንህ አባላት ውስጥ ያለው የርኩስ ኃይል

እየተሰበረ ይሄዳል።

3. **አጋንንቶችን የሚያስወጣ ትንቢታዊ መልዕክቶችን እየተቀበልክ የአጋንንቶች መኖሪያ ከመሆን ራስህን ጠበቅ። አጋንንቶች ትንቢታዊ የእምነት መልዕክቶችን አይወዱም።**

**በሰንበትም በአንድ ምኩራብ ያስተምር ነበር። እነሆም፥ ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች፥ እርስዋም ጐባጣ ነበረች ቀንታም ልትቆም ከቶ አልተቻላትም። ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና። አንቺ ሴት፥ ከድካምሽ ተፈትተሻል አላት፥ እጁንም ጫነባት፤ ያን ጊዜም ቀጥ አለች፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነች።**

**ሉቃስ** 13፥10-13

ኢየሱስ ይህቺን ለአስራ ስምንት ዓመት በድካም መንፈስ የታሰረችውን ሴት አገለገላት። ግን እንዴት ነው ያገለገላት? ቃል ተናገራት። ይህ የኃይል፣ የእምነትና የትንቢት ቃል ነበር። ያንን ቃል ሊናገር የቻለው በመንፈስ ቅዱስ ተነሳስቶ ነበር። የእምነት ቃል ሲነገር የመፍጠር ኃይል አለው። ኢየሱስ እንዲህ አለ "ማንም ይህን ተራራ 'ተነቅለህ ወደ ባህር ተወርወር' ቢልና በልቡ ባይጠራጠር ያለውን ያገኛል።"

በሌላ አባባል፣ በእምነት የተነገረ ቃል በእምነት ከተቀበሉ የሚደንቅ ኃይል አለው።

አጋንንቶች እንዲህ ዓይነት መልዕክት አይወዱም።

አጋንንቶች "ፈውስ ይሁንል/ሽ! ተባረክ/ኪ! ነጻ ውጣ! ተባርከሃል! ተዓምራትህን ተቀበል! ተነስና ዳን! በሚቀጥለው ዓመት በተመሳሳይ ስፍራ አትገኝም!" የሚሉትን ቃላቶች መስማት በፍጹም አይወዱም።

እነዚህ ኃይለኛ የእምነት አዋጆች ናቸው። እያንዳንዱ እነዚህ

አዋጆች ለአስራ ስምንት ዓመት ጎባጣ የነበረችውን ሴት ነጻ እንዳስወጣት እርኩሳን መናፍስቶች እንዲወጡ ሊያደርግ ይችላል። መጋቢ ከሆንክ ኃይለኛ እምነት የተሞላ በረከቶችን ሰዎችህ ላይ መናገርን ልመድ። ቃልህ ይፈጸማል አጋንንቶችም አባላቶችህ ላይ ያላቸው ስልጣን ይበጠሳል።

4. **አጋንንቶችን የሚያሰወግድ የተመረጡ እጆች በአንተ ላይ እንዲጫኑ በማድረግ የአጋንንቶች መኖሪያ ከመሆን ራስህን መጠበቅ ትችላለህ። አጋንንቶች ሰዎች ላይ እጅ ሲጫን አይወዱም።**

> **በሰንበትም በአንድ ምኵራብ ያስተምር ነበር። እነሆም፥ ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች፥ እርስዋም ጐባጣ ነበረች ቀንታም ልትቆም ከቶ አልተቻላትም። ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና። አንቺ ሴት፥ ከድካምሽ ተፈትተሻል አላት፥ እጁንም ጫነባት፤ ያን ጊዜም ቀጥ አለች፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነች።**
>
> **ሉቃስ** 13፥10-13

ኢየሱስ በሴትየዋ ላይ እጁን ሲጭን እርኩሳን መናፍስቶች በእርስዋ ውስጥ ለመቆየት ምቾት አላገኙም። ሰዎች ላይ እጅ ሲጫን እርኩሳን መናፍስቶች አይፈልጉም ምክንያቱም እጅ መጫን የእግዚአብሔርን ኃይል ያስተላልፋል። እጅ መጫን ኃይልን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነው። ለዚህ ነው እጃቸውን ሰዎች ላይ የሚጭኑትን አጋልጋዮች ዲያብሎስ የማይወዳቸው። እጅ በተጫነብህ ቁጥር ኃይል እየተላለፈ እንደሆነ እና አጋንንቶች እንደሚወጡ አስታውስ።

5. **አጋንንቶችን በሚያሰወግደው በማይቋረጥ ጸሎት በመጸለይ የአጋንንት ማደሪያ ከመሆን ራስህን ጠበቅ። አጋንንቶች ጸሎት አይወዱም።**

**ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ ኢየሱስ ቀረቡና፦ እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው? አሉት። ኢየሱስም፦ ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ፦ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም። ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው።**

**ማቴዎስ 17፥19-21**

ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ክፍል አጋንንቶች እንዴት በጾምና በጸሎት እንደሚጎዱ በጣም ግልጽ አድርጓል። ጸሎት በአጋንንቶች ውጊያ ላይ በጣም አስላጊ ነው። የጸሎት ህይወት የሌለው ክርስቲያን ለሚዞሩ እርኩሳን መናፍስቶች እንደ ሳቢ ሆቴል ነው። አጋንንቶች ብዙ የሚያወራ እና የማይጸልይ ክርስቲያን ሲያገኙ እርሱ ጋር ማረፍያ ለመከራየት ባለው ምቹ ሀኔታ በጣም ይደሰታሉ። በክፍልህ ውስጥ እየዞረክ ስትጸልይ በአከባቢህ ላይ የሚያንዣብቡትን ርኩስ ፍጥረቶች አቅጣጫ እያሳትካቸውና እያስፈረራሃቸው ነው። ክፍልህ አጠገብ ባለው ዛፍ ላይ ያሉት እርኩሳን መናፍስቶች ሌላ ክፍል አጠገብ ወዳለውና በልሳን የሚጸልይ ወደሌለበት ክፍል ይሄዳሉ። እርኩሳን መናፍስቶች ሁሌም የሚያርፉበት፣ የሚኖሩበትና የሚቆጣጠሩትን ቦታ ፍላጋ ሁሌም እንደሚዞሩ አስታውስ።

እርኩሳን መናፍስቶች ልክ እንደ እንስሶች በድንበር የተገደቡ ናቸው። ለዚህ ነው አለቆች የተባሉት። አከባቢን ይቆጣጠራሉ። ለዚህ ነው የተለያየ ቦታ የለያየ ባህሪይና እርኩሰት የሚኖራቸው። ከአስፈሪ የጸሎት ዞን ጋባዥ ወደሆነው ጸሎት አልባ ዞን ይሄዳሉ።

6. **አጋንንቶችን በሚያሰወግድ ባልተቋረጠ ጾም የአጋንንቶች መኖሪያ ከመሆን ራስህን ጠብቅ። አጋንንቶች ጾምን አይወዱም።**

**ኢየሱስም ገሠጸው ጋኔኑም ከእርሱ ወጣ፥ ብላቴናውም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ። ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ ኢየሱስ ቀረቡና፦ እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው? አሉት።**

**ኢየሱስም፦ ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ፦ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም።**

**ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው።**

**ማቴዎስ 17፥18-21**

*ጾም ስጋን ያስገዛል። እርኩሳን መናፍስቶች የሚመገቡት ከስጋ በመሆኑ የክርስቲየኖችን ስጋ መኮርኮር ይወዳሉ። ክርስቲያኖች በጾሙ ቁጥር ስጋቸውን በማስገዛት ለእርኩሳን መናፍስቶች መመገቢያ የማያስደስቱ ያደርጓቸዋል። የአጋንንት ስራ በከፍተኛ ሁኔታ በጾም ይቀንሳል። ሁሉም የስጋ ሥራ ጾሙ እስኪያልቅ ድረስ ይቆማል። አንድ አንዴ ክርስቲያኖች የበለጠ ውጊያ የሚደርስባቸው ጾሙ ካበቃ በኋላ ነው። ይህ ሁሌም ራሳቸውን በቦታቸው መልሰው ማቋቋም የሚፈልጉ የተራቡ እርኩሳን መናፍስቶች የምልሰት ጥቃት ነው።*

*ከማንኛውም የአጋንንታዊ ኃይልና ተጽዕኖ ነጻ ነህ! በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና በኢየሱሰ ደም ኃይል በመተተኞች ላይ፣ በአጋንንቶች ላይ፣ በጠንቋዮችና በአስማተኞች ሁሉ ላይ ኃያል አለቃ በአዋጅ ተደርገሃል።*